
# የእግዚአብሔር ትዕግሥት



6ኛ እትም

በዲያቆን አሸናፊ መኰንን

www.ethiopianorthodox.org

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው!
የመጀመሪያ እትም መስከረም 2002 ዓ.ም
ሁለተኛ እትም ታኅሣሥ 2002 ዓ.ም
ሦስተኛ እትም ጥቅምት 2003 ዓ.ም
አራተኛ እትም ኅዳር 2004 ዓ.ም
አምስተኛ እትም ነሐሴ 2005 ዓ.ም
ስድስተኛ እትም ሚያዝያ 2006 ዓ.ም

አድራሻ:- መ.ሳ.ቁ. 62552
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ይህን መጽሐፍ ለማከፋፈል ለምትፈልጉ:-
<u>በአሳታሚው አድራሻ</u>
የስልክ ቁጥር 0911-393521
መጠየቅ ትችላላችሁ::

*«ሳትደክም ሁሉን ትሸከማለህ፣
ሳታጎድል ለሁሉ ትመግባለህ፣
ዝም ሳትል ለሁሉ ታስባለህ::
ሳታጕድል ለሁሉ ትሰጣለህ፣
ሳትነጥፍ ለሁሉ ታረካለህ፣
ሳትዘነጋ ሁሉን ታስባለህ::
ሳትተኛ ሁሉን ትጠብቃለህ፣
ቸል ሳትል ሁሉን ትሰማለህ
ሳትቀበል ለሁሉ ትተዋለህ::»*

/ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ/::

www.ethiopinorthodox.org

## ስጦታ

ለተወዳጅ ____________________

ከወዳጅ ____________________

የትዕግሥቱን ምሥጢር አውቀን ከእግዚአብሔር ጋር በፍቅር እንድንኖር ይህን መጽሐፍ በአክብሮት አበረክታለሁ::

ቀን ____________

ፊርማ ____________

## ምስጋና

ከሁሉ በላይ እንዳውቅህና እንዳመልክህ የፈጠርከኝን አንተ ጌታዬ እግዚአብሔርን አመሰግንሃለሁ:: የማልፋቸው ያልመሰሉኝን ቀኖች አሳልፈህ፣ ከሚያልፈው ችግር የማያልፍ ትምህርትን ሰጥተህ፣ ይህንን መጽሐፍ ለወገኖቼ እንዳበረክት ስለረዳኸኝ አመሰግንሃለሁ:: ሰዎችም አንተን ባለ ድምፁን ትተው ድምፅ ማጉያውን እኔን እንዳያዩ ስለምትረዳቸው አመሰግንሃለሁ::

ጌታዬ አንተን ያወቅሁባትን ቤተ ክርስቲያኔን በታላቅ በረከትህ አስባት:: ዘመን የሚሻገሩ መጻሕፍትን እንድጽፍ በብርቱ ያሳሰቡኝን ሻለቃ ካሣዬ አራጋውን ፀንታ በምትኖር ማዳንህ አስብልኝ:: በፍቅራቸው የማረኩኝን የልብ ወዳጆቼን ዶ/ር ታዬንና ቄስ ኃይሉን ከማይቆመው የቸርነት ጠልህ አረስርስልኝ:: እስከዚህች ቀን ድረስ ወዳጅነቱን የጠበቀልኝን ወንድምም ወዳጅም ያደረክልኝን ኃይሉ ኪዳኔን እጁን ይዘህ ምራልኝ:: ይህ መጽሐፍ እንዲወጣ በጸሎትና በምክር የረዱኝን ልጠቅሳቸው የማይበዙትን ቅንነታቸውን ጠብቅልኝ:: ጊዜያቸውን በመስጠት በዕድሜ አሥራት የዚህን መጽሐፍ ፊደል በጥንቃቄ የለቀሙልኝንና ለሕትመት እስኪበቃ ያልተቆጠበ ድጋፍ ያደረጉልኝን እህቶቼን ገነት ታደሠን፣ ፍጥረት ገረመውን፣ ወንድሜን ብንያም ስዩምን፣ እንዲሁም ለባናዊ ማተሚያ ቤት ባለቤትና ሠራተኞች በሙሉ አእምሮአቸውን አንተ ባርክልኝ:: ለእኔ የተደረገውን የምትከፍልልኝ አቅሜ አንተ ነህና ደግሞም ለስምህ የተከፈለውን ዋጋ የማትረሳ አንተ ነህና ለዘላለሙ አሜን!

## መታሰቢያነቱ

በብዙ አሳብና በቅንነት ምክሩ ለብዙ ዘመናት አጠገቤ ለቆመው ለወዳጄና ለወንድሜ ለብሥራት ያሬድ ይሁንልኝ!

www.ethiopinorthodox.org

የመከራው ግፊት ውስጤን እያዛለኝ
ሰዎች ፊት ነስተውኝ መጠጊያ ሲጠፋኝ
የሮጥኩለት ነገር አልሳካ ሲለኝ
የጨበጥኩት ነገር በኖ ሲጠፋብኝ
ሁሉም ባዶ ሆኖ ተስፋ ሲያሳጣኝ
አንተን ማየት ትቼ ከሰው እጅ ስጠብቅ
እርካታን ለማግኘት ዓለምን ስናፍቅ
የማይዘገንን ለመዝገን ስዳክር
የተሻለን ተስፋ ካንተ ውጭ ስሞክር
ተስፋ ሣትቆርጥብኝ ጌታ ጠብቀኸኝ
ችለህ ተሸክመህ አዝለኸኝ መርተኸኝ
በትዕግሥትህ ምሥጢር እረፍትን ሰጠኸኝ
በመቻልህ አቅም ተስፋን አደስክልኝ
ልቤ ባንተ ብቻ እንዲያርፍ ረዳኸኝ

# ማውጫ

ገጽ


የአሳታሚው ማስታወሻ .................... 9
ቀዳሚ ቃል .................... 11
መግቢያ .................... 16
ምዕራፍ አንድ
ፈቃደኞች ነን? .................... 19
ምዕራፍ ሁለት
ለፍቶብናል .................... 25
ምዕራፍ ሦስት
የትዕግሥቱ ምሥጢር .................... 33
ምዕራፍ አራት
ባሕርዩ ነው .................... 41
ምዕራፍ አምስት
ይችለናል .................... 49
ምዕራፍ ስድስት
እንደ እኛ አይደለም .................... 56
ምዕራፍ ሰባት
አንከብደውም .................... 64
ምዕራፍ ስምንት
ይቅር ባይ እንሁን .................... 74
ምዕራፍ ዘጠኝ
ዕድል ነው .................... 81
ምዕራፍ ዐሥር
ይጠብቀናል .................... 91
ምዕራፍ ዐሥራ አንድ
ለአንድ አዳር . . . . . . . . . . . . . . . 100


www.ethiopinorthodox.org

ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት
የተዘረጋው መረብ......................................109
ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት
አይቻኩልም..........................................122
ምዕራፍ ዐሥራ አራት
የማዳን ኃይል........................................131
ምዕራፍ ዐሥራ አምስት
ያልታገሥነው ዕድል..................................143
ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት
በጊዜው ይሠራል......................................151
ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት
አንቀድመውም.......................................162
ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት
ትዕግሥተኛ እንሁን...................................173
ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ
አንሸበር ...........................................183
ምዕራፍ ሃያ
የማይበርድ ተስፋ....................................192
ምዕራፍ ሃያ አንድ
ተጨማሪ ሙከራ......................................204
ምዕራፍ ሃያ ሁለት
የሚመጣውን እንጠብቅ ...............................216
ማጠቃለያ...............................................228



# የአሳታሚው ማስታወሻ

በአንድ መጽሐፍ ምረቃ ላይ የሰማሁት ነገር ትዝ አለኝ:: መጽሐፉ ከተጻፈ ስድስት መቶ ዓመታት ያለፉት ሲሆን ከስድስት መቶ ዓመታት በኋላ እንደ አዲስ ተፈለገና ተተረጎመ:: በዚህ ጥንታዊ መጽሐፍ ምረቃ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ከተጋበዙት ሰዎች መካከል የመጀመሪያው አስተያየት ሰጪ ወደ መድረኩ ወጥተው ሰላምታ ከሰጡ በኋላ:- «ሁለት ነገሮችን ለማለት እፈልጋለሁ» አሉ:: ለስድስት መቶ ዓመት የቆየን መጽሐፍ በሁለት ነገር ለመግለጽ መሞከራቸው በራሱ የሚገርም ይመስላል:: ጥሩ አሳብ ያለው ሰው ብዙ ንግግሮች አያስፈልጉትም:: «ሁለት ነገሮች ለማለት እፈልጋለሁ» ካሉ በኋላ:- «ከስድስት መቶ ዓመታት በኋላ በታላቅ አድናቆት የተቀበልነውን መጽሐፍ ስናስብ እኛም ብንጽፍ ለስድስት መቶ ዓመታት ያህል ተቀባይ ባናገኝ እንኳ ከስድስት መቶ ዓመታት በኋላ ግን አንባቢ እንደምናገኝ፣ መጽሐፋችንም እንደ አዲስ እንደሚነበብ ይህ መጽሐፍ ይመሰክርልናል» አሉ::

ወደ ሁለተኛው አሳባቸው ሲሸጋገሩ ለታዳሚዎቹ ሁሉ ቍራጭ ወረቀት አከፋፈሉ:: «በዚህ ወረቀት ላይ ሕይወቴን ለውጠውታል የምትሏቸውን የሁለት መጻሕፍት ርእስ ጻፉ» አሉ:: በእነዚያ ቍራጭ ወረቀቶች ላይ ለመጻፍ ሁሉም ጎንበስ አለ:: እኔም ሁለት መጻሕፍትን ለመጻፍ ሞከርኩ:: ወረቀቱ ይሰበሰባል ብዬ ስጠብቅ:- «ወረቀቱ እናንተ ጋ ይቀመጥ» አሉ ተናጋሪው:: «ወረቀቱ እናንተ ጋ ይቀመጥ:: እናንተም ብትጽፉ ሰዎች ሕይወታችሁን የለወጠ መጽሐፍ ጥቀሱ ሲባሉ የእናንተን መጽሐፍ ይጠቅሳሉ» ብለው ንግግራቸውን ፈጸሙ:: የእኚህ አስተያየት ሰጪ ምክር ለፀሐፊዎች ጉልበት የሚሰጥ የጀግንነት ንግግር ነበር::

የንባብ ባሕል ባልዳበረበትና የሚጽፉ ሳይሆን የሚነቅፉ በበዙበት ማኅበረሰብ ውስጥ መጽሐፍ መጻፍ ብዙ ዋጋ ያስከፍላል:: ብዙ ፀሐፍያን ተቺ እንጂ መካሪ ባለማግኘታቸው ብዕራቸውን አስቀምጠዋል:: ብዙዎች በብድር አሳትመው መክፈል ባለመቻላቸው ሲሸማቀቁ አይተናል:: መጻፍ ወንጀል አይደለም፣ ግን ምላሽ በማጣት እነዚህ ከዋክብት ብዙ ዘመን ጨልመዋል:: ለ80 ሚሊየን ሕዝብ ሦስት ሺህ ኮፒዎች በሚታተሙበት አገር ላይ በመሆናችን ልናፍር ይገባናል:: በውጭ አገር በሱቆች ላይ ሰልፍ ካያችሁ አዲስ መጽሐፍ ወጥቷል ማለት ነው:: አንድ መጽሐፍም በሚሊየን ቅጂዎች ይሰራጫል:: በአገራችን ግን ሰልፍ የሚታየው አዲስ ምግብ ቤት ከተከፈተ በመሆኑ ያሳፍራል:: አዲሱ ትውልዳችንም ሥነ



www.ethiopinorthodox.org

ልቡናው ስለተሰረቀ የፈረንጅ ሥዕል ያለበት የነውር መጻሕፍትን ያነባል እንጂ የሚጽፉ ወገኖቹን አያበረታታም:: ባጠቃላይ ራሱን ከሚያሳዩት መጻሕፍት ጋር ጠብ የፈጠረ ይመስላል::

ሌሎችም ላለመጻፍ እርስ በርስ የሚጠባበቁ ይመስል ፀሐፍያን ብቅ ሲሉ የብረት ዱላቸውን ያሳርፉባቸዋል:: «በቅሎ አትወልድም፣ የሚወልድም አትወድም» እንዲሉ:: ግን ይህን ሁሉ ተግዳሮት ተቋቁመው የሚጽፉ ፀሐፍት ዋጋቸው እስከ ረጅም ዘመን ይኖራል:: አሳብ ያላችሁ እባካችሁ ጻፉ! ሀብት ያላችሁ እባካችሁ ፀሐፍያንን አበርቱ! ቤት ያላችሁ መጻሕፍትን ከወር ቀለባችሁ ጋር ገዝታችሁ ግቡ!

«የእግዚአብሔር ትዕግሥት» የሚለው መጽሐፍ ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በዲያቆን አሸናፊ መኰንን ሲጻፍ እኔም አሳብ ሰጥቻለሁ:: በወቅቱ ሲጻፍ በአነስተኛ ገጾች የተጻፈ አነስተኛ መጽሐፍ እንደ ነበር ይታወቃል:: በመጀመሪያው ሥራ አሳቦች ያልተዘረዘሩት የማሳተም አቅም ስላልነበረ ነው:: መጽሐፉ ርእሶች ብቻ የተደረደሩበት አሳቦች ሳይፍታቱ የተጨቆኑበት እንደ ነበር አሁን ላይ ቆመን ስናየው ግልጽ ነው:: ፀሐፊው በውስጡ ያለውን አሳብ ለመብጣትና ለማስተንፈስ ግን መጽሐፉ አገልግሏል:: የመጀመሪያው እትም ከገበያ ላይ ከጠፋ አራት ዓመታት ሆነውታል:: ብዙ አንባብያንም በእነዚህ ዓመታት ጥያቄ ቢያቀርቡም እስከዚህ ዓመት ድረስ ሊታተም አልቻለም:: የእግዚአብሔርን ጊዜ የሰው ድካም አይሽረውምና ፀሐፊውን አበርትቶ ዳግም ለመታተም በቅቷል:: የቀደመው እትም 34 ገጽ ሲሆን በአራት ምዕራፎችም የተከፋፈለ ነበር:: በዚህ እትም ግን በ22 ምዕራፎች በ232 ገጽ መጽሐፉ ተስፋፍቶ ለአንባብያን ቀርቧል::

አንድ ፀሐፊ ሲጽፍ የተጎዳ ሰው አግኝቶ ከመከረበት፣ ከራሱም ጉዳት ከተማረበት እንዲሁም መጻሕፍትን ሲያነብ ከተገነዘበው ነውና ተግተው የሚያነቡ ባለማወቅ ራሳቸውንና ሌላውን ከሚጎዱበት ስህተት ይድናሉ:: ስለዚህ ይህን መጽሐፍ በትሕትና ሆናችሁ ብታነቡት ሕይወታችሁ እንደሚረሰርስ እርግጠኛ ነኝ:: በመጽሐፉ ከእግዚአብሔር አንጻር ሕይወትን ስለምታዩ የከበዳችሁ ቀሎ፣ ያሳዘናችሁ ተኖ ታገኙታላችሁ:: መጽሐፉ ለእግዚአብሔር ክብር ለአገራችን ሕዝቦች በረከት እንዲሆን ጸሎታችን ነው:: እግዚአብሔር አእምሮአችሁን ይባርክ!

አሳታሚው



# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

## ቀዳሚ ቃል

ጊዜው ቢርቅም፣ ከመራቅ የተነሣ ብዙ ነገሮች ቢረሱኝም የማልረሳው አንድ ነገር አለ:: እርሱም:- የእግዚአብሔርን ቃል የመገቡኝ እነዚያ የእውቀት አባቶቼ ናቸው:: የመጣሁበትን የሕይወት መንገድ ወደ ኋላ ዞር ብዬ ሳየው እንደ ጉብታ ከፍ ብለው ከሚታዩኝ ሁኔታዎችና ሰዎች የመጀመሪያው እነዚህ አባቶች ናቸው:: ምክራቸው ዛሬም ይደግፈኛል:: የሰጡኝ የእውቀት ሀብት ለብዙዎች ብሰጠውም ሲበዛ እንጂ ሲጐድል አላየሁም:: በቃል ያስተማሩኝን በኑሮዬና በሕይወቴ ሆኖ ሳገኘው ረቂቁ ቃል ገዝፎ፣ አካል ነሥቶ አግኝቼዋለሁ:: እንደ ገናም በብረት ሰሌዳ ላይ እንደ ተቀረፀ ፊደል በውስጤ ላይ ታትሞልኛል:: ትምህርት ቤቶች የእውቀትን ረሀብ ለመቀስቀስ የተቋቋሙ እንጂ የሊቅነት መድረኮች አይደሉም:: «ሊቅ ለመሆን ሁሉን ሳትንቅ፣ ሞኝና እብድን ሳይቀር አዳምጥ» የሚለውን የአባቶችን ምክር እጅግ አከብረዋለሁ:: እኔም አስተማሪዎቼን ብቻ ሳይሆን ሁሉን ሳልንቅ ለመስማት ሞክሬአለሁ:: ቢሆንም እኔን ለመመገብ ቆመው የሚያገለግሉኝን መምህራን መርሳት እንደምን ይሆንልኛል? ሳያስቡ ከሚወልዱ አስበው የሚወልዱ አባቶች እንዴት የተባረኩ ናቸው! ለልጃቸው ያዩት ግብ ወይም ዳር አለና:: የእውቀት አባቶችን ከሥጋ አባቶች የሚለያቸው ይህ ፲ውነት ነው:: የሥጋ አባቶች እንደሚናገሩት ተሳስተው ይወልዳሉ:: የእውቀት አባቶች ግን በራእይ ይወልዳሉ::

ሙያን ካስጠኑኝ ይልቅ ሕይወትን የነገሩኝ፣ የኑሮ ዘዴን ካሳዩኝ ይልቅ የዘላለምን ሕይወት የሰበኩኝ እነዚያ አስተማሪዎቼ እግዚአብሔር ለእኔ ያለው የፍቅር መገለጫዎችና ስጦታዎቼ ነበሩ:: አንዳንዶቹ እንደ ሙሴ ፍርድን እየነገሩ ከግብፅ ያወጡኝ፣ ሌሎቹም እንደ ኢያሱ ምድረ ርስትን ያሳዩኝ ቢሆኑም ሁሉንም አከብራለሁ:: የመጣኹበትን መንገድ ረስቼ አሁን ያለሁበትን ብቻ ማሰብ ሕይወትን መካድ ሆኖ ይሰማኛል:: ያለ ትላንት ዛሬ አላልኩምና::

በሕይወት እግረ መንገድ መማር ደስ ይላል:: ለፈተና ብሎ ከሚያጠና ተማሪ ይልቅ በሕይወት እግረ መንገድ የሚማር ሰው ትምህርት ይገባዋል:: ትምህርት ሕይወት የሚሰጠውም መንገድነቱን ሲጠብቅ ነው:: ስለ ቤት ሥራ እንጂ ስለ ተማሪው ስሜት የማይጠይቅ አስተማሪ መንፈሳዊ አስተማሪ ሊሆን አይችልም::



www.ethiopinorthodox.org

በሕይወት እግረ መንገድ ካስተማሩኝ፣ በቃልና በኑሮአቸው ከመከሩኝ፣ በጌትነት መንፈስ ሳይሆን በወዳጅነት መንፈስ ካገለገሉኝ አስተማሪዎቼ መካከል አንዱን አባት አስታውሳለሁ:: እኚህ መምህር ዓላማቸው ከእውቀት ያለፈ እምነት፣ የክርስትና ማዕከለ ባሕርን (ጥልቀትን) ማሳየት ነበረ:: አቋማቸው የተሟላ ነው:: ሰው በቂ ነው የሚለው መንፈሳዊና ዘመናዊ እውቀት አላቸው:: የሰውን ተፈጥሮ ከሕክምና ሙያቸው ጋር እያያያዙ ሲገልጡት እግዚአብሔርን ለማመስገን ሳይንስም ይረዳል ያሰኛል::

እግዚአብሔር የሰጣቸውን አካለ ሥጋ በጥሩ ንጽሕና የሚጠብቁ ባለ አደራነታቸውን ለመወጣት ሥጋቸውን ከሕመም የሚጠብቁ ይመስላሉ:: ብዙ ሰዎች ለመቆሸሽ ይነጻሉ:: ቀኑን በሙሉ ሲታጠቡ የሚውሉት የዝሙት ፕሮግራም ካላቸው ነው:: እነዚህ ሰዎች ለመቆሸሽ ይነጻሉ:: እኚህ መምህር ግን ለመንጻት ይነጻሉ:: ቢያንስ የሰባ ዓመት የኑሮ ልምድ አላቸው:: ሽምግልናን የሚያለመልመው ባለ ዘይቱ ጌታ ግን በእርግጥም ቀብቷቸዋል:: በጸሎት ጀምረው በጸሎት የሚፈጽሙት ስለ ነበር ትምህርታቸው በጸጋ ነበር:: ስሜትን ይነካል፣ የዕንባን ጋን ይመታል፣ የቆሸሸ ኅሊናን ያነጻል::

ሲያስተምሩ ቶሎ ቶሎ እጽፋለሁ:: አየር ላይ ሳይነጥቡ ቃላትን ለመያዝ እፋጠናለሁ:: አጠገቤ የሰማንያ ዓመቱ ቄስ የሰባ ዓመቱ መሪጌታ ለመጻፍ በጣም ይዘገያሉ:: የቁም ጽሕፈት እንደሚጽፍ በውበት ፊደሉን ይቀርጻሉ:: ማራኪውን ቃል በልዩ ቀለም ያሰምሩበታል:: መምህሩ ግን በፍቅር እያዩ ይጠብቃሉ:: የእኔ ችኩልነቴና አንደኛነትን የሚወደው ወጣትነቴ ቶሎ ጽፎ ሌላስ በማለት ቀና ይላል:: የእውቀት ረሀቤ የሕይወት ረሀብም ነበረበት:: ተበልቶ በቃኝ የማይባለውን ቃል ይጽፍና ቀጥሉ የማለት ድጋፍ ይሰጣል:: መምህሩ ግን በእኔ ፍጥነት እነዚያን አረጋውያንን ጥለው መሄድ አይፈልጉም:: ይጠብቃሉ፣ ቀጣዩ ምን ይሆን? እያልኩ ውስጤ ሲቆጣ መምህሩ በመንፈስ ቅዱስ ያወቁ መሰለኝ:-

«አየህ ልጄ እነዚህ አባቶቼን ኢየሱስ ክርስቶስ በእነርሱ ፍጥነት እያስተማረ ከአሳቡ ያደርሳቸዋል:: እዚህ ጋ የቆመው እርሱ ቢሆን ፈጣኑን እየተከተለ የሚያዘግሙትን ጥሎ አይሄድም:: ሁሉንም በትዕግሥቱ ያደርሳቸዋል» አሉኝ:: ይህን ቃል ስሰማ ለእኔ ብቻ የሚለው ራስ ወዳድነቴ ተቀርፎ ወደቀልኝ:: በሕይወት ላይም ለሚያዘግሙት ልጆቹ እግዚአብሔር ድንቅ ትዕግሥት እንዳለው ማሰብ ጀመርኩኝ::





የቀደመ አንደኛ ተብሎ በሚሸለምበት ዓለም ላይ ጥሎ መሄድ ክብር አለው:: የመንፈሳዊው ዓለም ክብር ግን የበረታው የደከመውን ማገዝ ነው:: ያደገ ልጅ አድጌአለሁ ብሎ የሚናገርበት የተግባር ቋንቋው ታናሹን መሸከሙ ነው:: የማኅበረሰቡን ሙገሳ ለመስማት የማደግ ምልክት የሆነውን ታናሹን ይሸከማል:: የስምንት ዓመት ልጅ የአራት ዓመት ትንሽ ወንድሙን ይሸከማል:: ቢከብደውም የማደግ ልክ ነውና ይሸከማል:: በመንፈሳዊው ዓለምም ደካማውን መሸከም የማደግ ምልክት ነው:: ተጣጥሎ መሄድ፣ ተራርቆ መካሰስ ላጠቃው የዘመናችን ክርስትና ይህ አሳብ ሩቅ እንደሆነ ይሰማኛል:: በቤተ ክርስቲያን ሰዎችን የምንሸከመው ለጥምቀት ሲመጡ በ40ና በ80 ቀን እንደ ገናም ሲሞቱ ለመቀበር ነው:: ሸክም ላይ የዋለው ያ ሰው በሁለቱም ጊዜዎች የተሸከሙትን ሰዎች ፍቅር መረዳት አይችልም:: መለያየታችን አንዱ አንዱን መሸከም ባለመፈለግ ነው:: እንዲሸከሙን እንጂ እንድንሸከም አንፈልግም::

በመንፈሳዊ ዓለም የአንዳንዶች ለውጥ ፈጣን ነው:: አንዳንዶች ደግሞ ይዘገያሉ:: ፈጣኖቹ ተምረው ወዲያው አገልጋይ ሲሆኑ አብረዋቸው የጀመሩት ግን ገና የክርስትናን የጅማሬ ትምህርት ያጠናሉ:: ሁሉንም ለመንፈሳዊ አካለ መጠን እስኪደርሱ የሚታገሣቸው እግዚአብሔር ነው:: በልጅነቴ ወደ ቤተ ክርስቲያን ያመጡኝን ወገኖቼን አስተምሬአለሁ:: እነዚህ ሰዎች ዕድገታቸው ብዙ አይደለም:: ዛሬም ግን በቤቱ ናቸው:: መራቀቅ አይችሉ ይሆናል፣ ምንም ቢሆን ግን ከቤቱ መራቅ እንደሌለባቸው ያምናሉ:: እነዚህን ወገኖቼን እግዚአብሔር በትዕግሥት እንደሚያሳድጋቸው አምናለሁ::

ለዐሥር ዓመታት ያህል ያገለገልኳቸውን ወጣቶች ዛሬም አስታውሳለሁ:: እነዚህ ወጣቶች ግልጽ በሆኑ ጥፋቶች ውስጥ በማለፋቸው እኔም ተወቅሻለሁ:: መከራ መከራ እንዳልለያቸው ግን ይዞኝ የነበረው ነገር እኔንም እግዚአብሔር እንደ ቻለኝ ማሰብ ነበር:: ከእግዚአብሔር ጋር የኖርኩት በጠባዩ መልካምነት ሳይሆን በቸርነቱ ነው:: እነዚህን ወጣቶች ከዐሥር ዓመት በኋላ በቊርጥ ተናግሬ ስለያቸው ልቤ ፀና:: ከዚያ በኋላ የቅጣትና የመለወጥ ዘመን ጀመረ:: አንዳንዶች ተቀጡ አንዳንዶች ተለወጡ:: በጌታ ቀኝና ግራ የተሰቀሉ ሁለት ወንበዴዎች አብረው ኖረው በመጨረሻይቱ ሰዓት ተለያዩ:: ልዩነታቸው ግን ኃጢአተኛ አለመሆን ሳይሆን ክርስቶስን ማግኘትና አለማግኘት ነበር:: እኛም ከጠፋው ዓለም የምንለየው በፍጹምነታችን ሳይሆን በክርስቶስ ምሕረትን በመቀበላችን ብቻ ነው::



www.ethiopinorthodox.org

ከብዙ አስቸጋሪ ሰዎች ጋር ኖሬአለሁ። እግዚአብሔር በፈጣን ቅጣቱ እንዲያስደነግጣቸውም ጠይቄዋለሁ። አሁንም የሚገርመኝ ለእኔ ኃጢአት ምሕረትን የምለምነው እየደጋገምኩ «ኪርያላይሶን» እያልኩ ነው። ሰዎች ግን ለኃጢአታቸው ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ እጸልያለሁ። ይህ ድካሜ ነው። ሌሎችን እንደ ራስ አለመውደድ ትልቅ ኃጢአት ነው። እግዚአብሔር ግን ከቅጣት ይልቅ በፍቅር ያምናል። እኛ የፍቅርም የቅጣትም ኃይል ባይኖረንም እንዲኖረን የምንመኘው ግን የቅጣት ኃይል ነው። እግዚአብሔር የቅጣቱን ኃይል የሚጠቀመው ፍቅሩን ሲገፉ ነው።

እናት አጥፊ ልጇን በብዙ ተቃውሞ ውስጥ ትወደዋለች። የሚቃወሟት ለዚያ ልጅ ቅርብ የሆኑት አባት፣ እህትና ወንድሞች ቢሆኑም እናት ግን ደጋፊ በሌለበትም አጥፊውን ልጅ ትወደዋለች። ለምን? ስንል ከእኔ በቀር ቢሳሳት ተመለስ፣ ቢወድቅ ተነሣ የሚለው የለም ብላ በሯን ከፍታ ትጠብቀዋለች። እግዚአብሔርም ዓመፀኛ ሰዎችን የሚወዳቸው ከእርሱ በቀር ምንም ተስፋ ስለሌላቸው የመመለስ ዕድልን እየሰጣቸው ነው። እነዚህን አስቸጋሪ ሰዎች ላለመቅጣቱ ምክንያት አድርጎ የሚያሳየን የእነርሱን የተሰወረ መልካምነት ሳይሆን የእኛን የተሰወረ ኃጢአት ነው። ይህን በተረዳሁበት ዘመን ሁሉ፦ «ጌታ ሆይ÷ በቍጣህ ና አልልህም። በቍጣህ ከመጣህ እኔም አላመልጥም» ብዬ ጸልያለሁ። ክፉ ገዢዎችን፣ ክፉኛ የበደሉኝንም ሳይቀር ይቅር ካላልኩኝ ወደ ታሰበልኝ በረከት መግባት እንደማልችል ተረድቻለሁ። አዎ እግዚአብሔር ሁሉንም በትዕግሥቱ የማስተማር ዕቅድ አለው።

ዛሬ የምንከሳቸውና የምንወቅሳቸው ሰዎች ብዙዎቹ በምንወቅሳቸውና በምንከሳቸው ኃጢአት ንስሐ ገብተውበት ከሆነ አሳፋሪ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ይቅር ያለውን ሰው ሰይጣን እንኳ አይከሰውምና ከሰይጣን መባሳችን ነው። በጌታ ቀኝ የተሰቀለውንም ወንበዴ ስናየው በሕይወት ያለ ሰው ተስፋ እንዳለው እንረዳለን። ወንበዴው የነበረው ጊዜ ከ6-9 ሰዓት የሦስት ሰዓት ጊዜ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ግማሹን ሰዓት ጌታን ሲቃወምበት ጨርሶታል። በቀረው ሰዓት ግን አምኖ ድኗል (ሉቃ. 23:40-43)። ስለዚህ ዘመኔ አለፈ ንስሐ ለመግባት አልችልም የሚል ካለ ከወንበዴው ያነሰ ጊዜ አለህ ወይ? ብለን ልንጠይቀው ይገባናል። ዛሬ ጊዜ የለኝም የሚለው ሰው ቢያንስ በተለያየ አጋጣሚ በሰማው ቃል ስለ ክርስቶስ ያውቃል። ያ ወንበዴ ግን ክርስቶስን ለማወቅ፣ ለማመን፣ ለንስሐ፣ ለምሕረት የነበረችው ሰዓት ያችው ሦስቷ ሰዓት ናት። ለእውቀት፣ ለእምነት፣ ለንስሐና ለምሕረት ሦስት ሰዓት በቂ





ከሆነ የእኛማ ጊዜ ይልቁን እንዴት? ተስፋ የቆረጥንባቸውንም ሰዎች ወንበዴውን ያዳነ ጌታ እንደሚያድናቸው ልናምን ይገባናል።

የኮምፒዩተር ጽሑፍ የምትጽፍልኝ እህት ተሳስተሻል ስላት ተመልሳ የምታስተካክልበትን undo ትነካለች። ለብዙ ስህተቷ ይህ «አንዶ /undo/» ፍጹም ሲያፀዳላት፦ «ለሕይወትም ምነው አንዶ /undo/ በኖራት?» አለችኝ። ነገር ግን ለሕይወትም አንዶ (ማስተካከያ) አላት። እርሱም ንስሓ ነው። ንስሓ የእግዚአብሔር የትዕግሥቱ ስጦታ ነው።



www.ethiopinorthodox.org

## መግቢያ

አንድ ሰው በጣም የሚወደውን ትዳሩን በሁለት ምክንያቶች ሊተው ይችላል:: የመጀመሪያው ዝሙት ሲሆን ሁለተኛው ሞት ነው:: በእነዚህ ምክንያቶች ሰው ትዳሩን ቢፈታ ትክክል ነው:: ማንም አይወቅሰውም:: በምእመናንና በክርስቶስ መካከል ያለው ግንኙነት የባልና የሚስት ግንኙነትን እንደሚመስል መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ኤፌ. 5÷21-23):: አንድ ሰው:- *«ጌታዬ ሆይ÷ እኔን ለመተው በቂ ምክንያት፣ ሕጋዊ አመክንዮ አለህ:: ካንተ ውጭ ያመነዘርኩ ጣዖታዊ፣ በኃጢአት የወደቅሁ ሙት ነኝ:: አንተ ግን አልተውከኝም»* እያለ በዕንባ ይጸልይ ነበር:: እግዚአብሔር እኛን ለመተው በቂ ምክንያት እያለው ያልተወን ባሕርዩ ፍቅር ስለሆነ ነው:: በሕግ የተፈረደብንን በጸጋ ወደደን:: ርቀን ስንሄድ ተከተለን፣ በሞታችንም ተስፋ አልቆረጠብንም:: የሆንነውን ሳይሆን የምንሆነውን አየ::

መውደቅ መነሣት የሚፈራረቅበት አንድ አገልጋይ ክፉኛ ሲያለቅስ ሰማሁ:: ይህ ሰው እርሱና እግዚአብሔር በሚያውቁት የሕይወት ስብራት ውስጥ እያለፈ ነው:: አንዲት እህት ስለ ሁኔታው ባታውቅም ያየችውን ሕልም ትነግረዋለች:: የሕልሙ ይዘት ዛሬም እወድሃለሁ:: የትም ብትሄድ እከተልሃለሁ፣ ከእኔ የሚርቅ የምድር ጥግ የለም የሚል ነበር:: ደንድኖ ቍጣን የሚጠብቀው ያ ሰው በፍቅር እሳት ቀለጠ:: ያለ ይሉኝታ ሁሉንም ሰባኪዎች እየዞረ «ጠይቁልኝ ከእኔ ሌላ ሰው አጥቷል ወይ? እኔ አልረባውም ሌላ ሰው ይፈልግ» አለ:: ሁላችንም አለቀስን:: ለሰውዬውም ለእግዚአብሔርም:: እግዚአብሔርም ይህን ቃሉን እንደ ታላቅ ንስሓ ይቆጥረዋል:: እግዚአብሔር አልችልም ስንለው ከእኛ ጋር ለመሥራት ይመቸዋል:: አዎ የመኖራችን ትልቁ ምሥጢር እግዚአብሔር በእኛ ተስፋ አለመቍረጡ ነው::

የታጋሾች ትዕግሥት፣ የደጎች ደግነት፣ የአፍቃሪዎች ፍቅር፣ የቸሮች ቸርነት፣ የወዳጆች ወዳጅነት ያልቃል:: እግዚአብሔር ግን ምሕረቱ ለዘላለም ነው:: መሥሪያ ቤቱ አልችልህ ያለውን ጓደኞቹ ይችሉታል፣ ጓደኞቹ አልችልህ ያሉትን ትዳሩ ይችለዋል፣ ትዳሩ አልችልህ ያለውን እናቱ ትችለዋለች፤ እናቱ አልችልህ ያለችውን መንግሥት ይችለዋል:: መንግሥት አልችልህ ያለውን ሞት ይችለዋል:: እግዚአብሔር ግን የእኔ ጉዳይ ብሎ ይሸከመዋል:: እርሱ ብዙ ሺህ የምሕረት ዕድሎችን ይሰጣል:: ያ ሰው ካልገባው ግን ይቀጣዋል:: ነገሥታት እንኳ መቅጣት



የሚችሉት ሥጋን ነው:: እግዚአብሔር ግን በነፍስም የመቅጣት ሥልጣን አለውና የመቻሉን ምሥጢር ካልተረዳን ውጤቱ ያስፈራል::

ብዙ ሰዎችን መክረን መክረን፣ ብለን ብለን ትተናቸዋል:: ቢመለሱ እንኳ የሚቀበል ልብ የለንም:: ሰዓቱ አልፏል እንላለን:: ስለዚህ ከቤታችን እናባርራቸዋለን፣ በአንድ መንገድ ላይ አብረን ላለመሄድ በሩቅ ስናያቸው መንገድ እናሳብራለን:: የእነርሱ እጅ ያለበት የመሰለንን መልካም ነገር ላለመቀበል እንወስናለን:: በእነርሱ ምክንያት የሥራ ቦታችንን ቀይረናል:: እነርሱን ብቻ ሳይሆን ዘራቸውን ጠልተናል:: ጾታቸውንም ላለመቀበል ምለናል:: እኛ አንድ ሰው መሸከም አቅቶናል:: እግዚአብሔር ግን ስድስት ቢሊየን ሕዝብ ተሸክሟል:: እኛ ኃጢአተኞች ሆነን ስኅጥኡ መራራት አልሆነልንም:: እግዚአብሔር ግን ንጹሕ ሆኖ እኛን ተቀብሏል:: ዛሬም የምንካፈለው የክርስቶስ መከራ ለአስቸጋሪ ሰዎች ወንጌልን ለማድረስ ስንሄድ የሚሰጠን ክፉ ምላሽ ነው::

እግዚአብሔር ያንተ ነገር በቃኝ ቢል ከእኛ ጋር ማን ይጀምራል? እግዚአብሔር አልችልም ቢለን ማን ይሸከመናል? እግዚአብሔር ርቄሃለሁ ካለን ማን ይቀርበናል? የዛሬና የዘላለም ተስፋችን እግዚአብሔር ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ርቆኛል ጠላት አስጨንቆኛል እያለ ለሚያለቅሰው ንጉሥ ሳኦል ሳሙኤል ሲመልስ:- *«እግዚአብሔር ከራቀህ ጠላትም ከሆነህ ለምን ትጠይቀኛለህ?»* (1ሳሙ. 28:16) ብሎታል::

የእግዚአብሔር ተግሳጹና ቅጣቱ ሳይቀር የፍቅሩ መገለጫ ነው:: *«እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል»* (ዕብ. 12:10):: የሚቀጣ አባት ነው:: አባት ልጁን ሲቀጣ በልጁ ላይ ያለውን መብት ያሳያል:: ማንም አይቀጣምና:: አባት ልጁን ሲቀጣ ስላናደደው እንጂ ልጁ ስለተበላሸ አዝኖ ላይሆን ይችላል:: እግዚአብሔር ግን የሚቀጣን ስላናደድነው ሳይሆን እንድንለወጥ ነው:: ይህም ለእኛ ያለውን ፍቅር ያስረዳል:: የምክሩ፣ የቅጣቱ ዓላማ ከገባን መልካምና ሕይወት ነው:: ካልገባን ግን ውጤቱ አስፈሪ ነው::

ከምን ጊዜውም ይልቅ እግዚአብሔር ታግሦናል:: ዓለም አቀፍ የሆኑት ርኩሰቶቻችን ለዓለም አቀፋዊ መከራ እያዘጋጁን ነው:: በቀደሙት ዘመናት በአደባባይ እግዚአብሔርን ካድን፣ በቆሸሸው ሰውነታችን ላይ ሽቱ ተቀብተን እግዚአብሔር እግዚአብሔር አልን:: እግዚአብሔር የለም ማለት ዘመናዊነት



www.ethiopinorthodox.org

አይደለም:: በተግባር መካድ ግን ዘመናዊነት ነው አልን:: የክህደት ዙፋኖች ካደባባይ ተነቅለው በልባችን ላይ ተተክለዋል:: እግዚአብሔር የለም እያልን በአደባባይ መካድ ትግል ነው ብለን በብልሃት ቤተ ክርስቲያንን ብንመራት ይሻላል በሚል ስውር ሴራ ተሰማርተናል:: ዛሬ ከኢአማንያን ስለ ክርስቶስ መከራ አንቀበልም:: ክርስቲያን ነን የሚሉት ግን ያሳድዱናል:: ነገሥታት የእምነት ነጻነትን አልነፈጉንም:: ቤተ ክርስቲያን ግን ወንጌል ሰባኪዎችን ታፍናለች:: ብልሃቱ ሠርቷል:: ግዙፉ ረቋል:: እግዚአብሔር አሁንም ታግሦናል:: ከብዙ ትዕግሥት በኋላ የሚመጣው ብዙ መከራ ነው::

ችኩሉ ትውልዳችን በሃያ አራት ሰዓት ስኬታማ የሚያደርጉ መጻሕፍትን፣ በሃያ ቀናት ሀብታም የሚያደርጉ ንቃተ ኅሊና ቀስቃሽ ትምህርቶችን፣ ተደማጭ የሚያደርጉ የንግግር ችሎታ አስጠኚ መምህራኖችን ይፈልጋል:: «ሕይወት ልምምድ ናት:: የጥሩ ኑሮ መነሻው መንፈሳዊነት ነው:: መፍትሔው ራስን መርሳት ሳይሆን ራስን በወንጌል ማንሣት ነው:: የልብ ደስታን በመንፈስ ቅዱስ ካላገኘ ን የሳቅ ኮከቴሎች ወደ በለጠ ሀዘን ይከታሉ ...» የሚሉትን ድምፆች የዛሬው ትውልድ መስማት አይፈልግም:: ለኑሮው እንጂ ለአኗኗሩ የማይጨነቀው፣ ለቆዳው እንጂ ለቅንነቱ የማያስበው፣ መነሻ የሌለው መድረሻ የሚሻው ትውልዳችን በዝሙት እንስሳ፣ በአደንዛዥ ዕፅ ፍርስራሽ እየሆነ ነው ያለው:: አንድ ሰው በታላቅ ሀዘን:- «የጀመርኩትን ሕንጻ ስጨርስ ልጆቼ ፈርሰው አለቁ» ብሏል::

ይህንን ጨለማ ብዙ መንፈሳውያን ሰዎች ረግመዋል:: ትውልዱንም ተጠይፈዋል:: ነገር ግን ጨለማን ከመርገም አንድ ሻማ መለኮስ መፍትሔ መሆኑን አላስተዋሉም:: ለትውልዱ ያልሰጡትን ከትውልዱ መጠበቃቸውም ገንዘብ ካላስቀመጡበት ባንክ ቤት ገንዘብ እንደ መጠየቅ ያስቆጥርባቸዋል:: በርግማናችን የወደቁትን ከመርገጥ እጃችንን ብንዘረጋ ብዙዎች ይነሣሉ:: «የወደቁ ሰዎች የተዘረጉ እጆችን ይፈልጋሉ::»

የእግዚአብሔር ትዕግሥት የቻለው እነዚህን ወገኖች ብቻ አይደለም:: እኛንም ነው:: ትዕግሥቱ ያላስፈለገው ትውልድ ማንም የለም:: ይህ መጽሐፍም የትዕግሥቱን ውዳሴ ለማቅረብና የትዕግሥቱን ምሥጢር በመግለጥ ለንስሓ ለማዘጋጀት ተጽፎአል:: እኔንም በምናገረው እንዳልፈተን እግዚአብሔር ይርዳኝ:: ለእናንተም ሰላሙን ያብዛላችሁ!



# ምዕራፍ አንድ

## ፈቃደኞች ነን?

ልጅቷ እናቷን ለመጠየቅ ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ ትመጣለች:: እናቷንም ልታለብስ፣ ልታስጌጥና ልታንቆጠቊጥ ወደ ልብስ መሸጫ ሱቅ ይዛቸው ትወጣለች:: እናቲቱም ከዚህ በፊት መስታወት አይተው አያውቁም ነበርና በቁም መስተዋቱ ፊት ሲቆሙ:- «ይህች አስቀያሚ ሴትዮ ደሞ ማን ናት?» ይላሉ:: ልጅቱም ስቃ:- «እማዬ አንቺ እኮ ነሽ?» አለቻቸውም:: እርሳቸው በትካዜ ቆዩና:- «ለአባትሽ አዘንኩለት» አሉ:: «ለምን?» ብትላቸው «እኔን ወዶ መኖሩ» አሉ ይባላል::

የሌሎች የመሰለን ጉድለት ለፍርድና ለስድብ ያስቸኩለናል:: ጉድለቱ የእኛ መሆኑን ስናወቅ ግን ዝምታን እንመርጣለን:: ለራሳችን ኃጢአት ኪርያላይሶን፣ ለሌሎች ኃጢአት ቶሎ ፍረድ እንላለን:: እኛ የምንራራው ለእኛ ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ግን ለሁላችን ይራራል:: እግዚአብሔር የታገሠው ጨካኝ ነገሥታትን፣ ዓለማዊ ጳጳሳትን ይመስለናል:: እግዚአብሔር ግን ሁላችንንም የሚያኖረን በሰፊው ትዕግሥቱ እንደሆነ እርሱ ያውቀዋል:: የሚገባንን ቢሰጠን ኖሮ አንኖርም ነበር:: የሚገባን ሞት ነውና:: የመኖራችን ምሥጢሩ የማይገባንን መቀበላችን ነው::

እኒያ እናት መልካቸውን ባዩ ጊዜ ራሳቸውን ጠሉትና ፈረዱበት:: በዝግታ ሲያስቡ ደግሞ ራሳቸው የገፉትን ማንነት የተቀበለውን የባላቸውን ፍቅር አሰቡት:: ሁላችንም ብንሆን ራሳችንን ለብዙ ዘመን አልተቀበልነውም:: ራሳችንን ተፀይፈነዋል:: ራሳችን ለራሳችን የጠላነውን ማንነት ግን እግዚአብሔር እንደ ተቀበለው ስናስብ ፍቅሩ ደንቆናል:: እኒያ እናት:- «ባሌ ስለ እሴቴ ሳይሆን ስለ ማንነቴ የወደደኝ ወዳጄ ነው» ብለው የባላቸውን ፍቅር እንደገና አተሙት:: ራሳችንን በቅጡ ስናየውና ቀና ብለን የእግዚአብሔርን ፍቅር ስንመለከት ልባችን በቅዱስ ሐዘን መነካት፣ ዓይኖቻችንም በጸጋ ዕንባ መርጠብ ይጀምራሉ::

በእውነት ስናስበው እግዚአብሔር ያሳዝናል:: ሀዘናችንን ከእርሱ ጋር፣ ደስታችንን ከዓለም ጋር የምናሳልፈውን እኛን መውደዱ ያሳዝናል:: ልባችን በክፋት፣ አንደበታችን በርግማን፣ ተግባራችን በርኩሰት የተሞላውን እኛን መፈለጉ በእውነት



www.ethiopinorthodox.org

ያሳዝናል:: ነቢዩ ለአምላኩ አዝኖ:- *«እናንተ የዳዊት ቤት ሆይ፥ ስሙ፤ በውኑ ሰውን ማድከማችሁ ቀላል ነውን? አምላኬን ደግሞ የምታደክሙ»* (ኢሳ. 7:13) ማለቱ እውነት ነው:: ይህን ስናስብ እንዲህ ብለን እንጸልያለን:-

> *«እግዚአብሔር ሆይ፥ በፍርድ ና አልልህም በፍርድ ከመጣህ እኔም አላመልጥም:: ያኛውን ወገኔን ብትፈርድበት ይቀጣል፣ ይጠፋል:: በፍቅርህ ብትማርከው ግን ከጎዳኝ በላይ የሚጠቅመኝ፣ ከከዳኝ በላይ የሚታመንልኝ ይሆንልኛል:: እባክህ በመልካም አስበን! አሜን::»*

እኛ ሁላችን እንደሚታየን ፍርድ እንሰጣለን:: ፍርዳችንም የሐቅ መሠረት የሌለው በመሆኑ ራሳችንንና የምንፈርድበትን ወገን የሚጎዳ ነው:: እግዚአብሔር እንደሚታየው መጠን ይታገሠናል:: ሰዎች ከእኛ ጋር የሚጣሉት በምንናገረው ክፉ ነገር ነው:: የምንናገረው ግን ጥቂት ሲሆን በኅሊና መጋረጃ የተጋረደው አሳባችን ግን እጅግ ክፉ ነው:: እግዚአብሔር ግን የአሳባችንንና የተግባራችንን ኃጢአት እያየ ለንስሓ ይጋብዘናል::

በድሮ ዘመን አንድ ሰው ወደ ከተማ ለሥራ ጉዳይ ይመጣል:: በከተማው እንደ ድንቅ ይታይ የነበረው መስተዋት ነበርና ያንን ፊት ማሳያ መስተዋት ለሚስቱ ለመስጠት በታላቅ ፍቅር ይገዛል:: ወስዶም ለሚስቱ ይሰጣታል:: ሚስቲቱም ከዚህ በፊት መስተዋት አይታ አታውቅም ነበርና ገልጣ ብትመለከተው መልኳን አየች:: ሶርሷ ግን ባሏ በከተማ ውስጥ የወደዳት አንዲት ልጃገረድ መስላት በብስጭት ታስቀምጠዋለች:: ነገሩንም ታግሣ መቆየት አልሆንልሽ ሲላት ያሳደጓት አያቷ ዘንድ ሄዳ:- «እማማ ባሌ ከተማ ሄዶ ከእኔ ሌላ ሴት ወደደ:: ይባስ ብሎ ዕድሜዬ በብስጭት እንዲያጥርና እርስዋን አስገብቶ ለመኖር ስዕሏን ይዞልኝ መጣ:: ከዚህ በኋላ እኔና እርሱ አንድ ቤት አንኖርም» ብላ እያለቀሰች ትነግራቸዋለች:: አያቷም:- «የታለች እስቲ ልያት?» ብለው ቢያዩአት የራሳቸውን መልክ፣ የተሸበሸበውን ፊት አዩና:- «ይህችማ የተሰባበረች አሮጊት ናት:: ነገ ትሞትልሻለች፡ ባልሽም ወደ ቤቱ ይመለሳል:: ለዚህችስ አታልቅሺ» አሏት ይባላል::

ለመልካም የተደረገው ነገር ባለ ማወቅ እንዴት ክፉ ትርጉም እንዳገኘ ይህ ታሪክ ያስረዳናል:: ዛሬም በስጦታቸው ጦር የተመለሰላቸው ብዙ ሰዎች በዙሪያችን አሉ:: መልካሙን መልካም የሚል እግዚአብሔር ብቻ ነው:: የሰው ጥርጣሬ ግን መልካሙን ያከፋል:: ሁላችንም እንደ ታየን እንፈርዳለን:: ሁላችንም በራሳችን



www.ethiopinorthodox.org



እንፈርዳለን:: እግዚአብሔር ግን በእውቀቱና በትዕግሥቱ ያስተምረናል:: ስለ ክርስቶስ በተነገረው ትንቢት:- *«ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል»* የሚል ይገኝበታል (ኢሳ. 53:11):: እኛ ባለማወቅ ብዙዎችን እንኮንናለን:: እንደ እኛ የነገሩን ወራጅ ሳይሆን ምንጩን የሚያየው ጌታ፣ በእውቀቱ መልካሞችን ነጻ አእምሮ ይሰጣቸዋል::

እኛ *ሥራውን* እንፈርዳለን:: እግዚአብሔር ግን *ሥራው* የተሠራበትን አሳብ ይፈርዳል:: እንደ ሳኦል አሳቡ ክፉ ሆኖ የሚሠራውን መልካም ነገር የሚቀጣ (1ሳሙ.15:21-23)፣ እንደ ጳውሎስ አሳቡ ቅን ሆኖ የሚሠራውን ክፉ ነገር የሚያርም የሕሊና መርማሪ እግዚአብሔር ነው::

ይህ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲታተም መጽሐፉን ለማከፋፈል በመጀመሪያ የሄድንበት የመጻሕፍት መደብር ውስጥ የነበረች ተረካቢ ሴት እስከ አሁን ትዝ ትለኛለች:: መጽሐፉን አውጥተን ገና ስናሳያት «የእግዚአብሔር ትዕግሥት» ብላ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች:: ዕንባዋ ጉንጯን እየተረፈ በልብስዋ ላይ መፍሰስ ጀመረ:: ዛሬ ሌሊቱን በሙሉ የእግዚአብሔርን ትዕግሥት እያሰብኩኝ እንቅልፍ አልተኛሁም ስለዚህ የእኔ መልእክት ነውና ለማንኛውም እኔ ልግዛ ብላ መጽሐፉን ገዛች:: የእግዚአብሔር ትዕግሥት ስናስበው እንቅልፍ ነሥቶ፣ በዕንባ የሚያርሰን ነው:: እግዚአብሔር ስድስት ቢሊየን ሕዝብን ከነ አመሉና ቀለቡ ችሎ አልተመረረም:: እኛ ግን አንድ ሰው መሸከም አቅቶን ኡኡ እንላለን:: በየዕለቱ ሣንቲም የምንሰጠውን ያንን ለማኝ እንጠየፋለን:: ቦታ የሚለዋውጥ ጌታ ግን እኛን ተቀባይ፣ እርሱን ሰጪ ማድረግ እንደሚችል እንዘነጋለን::

የእግዚአብሔር ትዕግሥት ያስለቅሳል፣ የእግዚአብሔር ትዕግሥት የጨካኞች ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዳችን የንስሓ ዕድላችን ነው:: የእግዚአብሔር ትዕግሥት የሚለው ቃል በራሱ ብርቱና አመራማሪ አስደናቂም ነው:: እኛ ኃጢአተኞች ሆነን ኃጢአተኞችን እንገፋለን:: ንጹሑ እግዚአብሔር ግን ወደ ራሱ ይጠራናል:: የጋራ ግብር ያለን የጋራ ርኅራኄ የለንም:: እግዚአብሔር ግን ከሥራችን የተለየ ቢሆንም በምሕረቱ ግን ከእኛ ጋር ነው:: ቃሉ እንደሚል:- *«ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤም ከአሳባችሁ ከፍ ያለ ነው»* (ኢሳ. 55:9) ይላል:: እግዚአብሔር ከእኛ ለመራቅ በቂ ምክንያት አለው:: በምክንያቱ ሳይሆን እንዲሁ ግን ወደናል:: እኛ የሚመስሉንን ለደጋፊነት እንፈልጋቸዋለን:: እግዚአብሔር ግን የማይመስሉትን ሊለውጣቸው

ይፈልጋቸዋል:: እኛ የሰዎችን በደል ደብቆ የመያዝ አቅም የለንም:: ቀላል ሰዎች ነን:: እስክናወራው ይጨንቀናል:: የራሳችንን በደል ደግሞ እንኳን ልናወራው ልናስበው አንፈልግም:: «በቃ አልፏል፣ ሆኗል» እንላለን:: እግዚአብሔር ግን በትዕግሥቱ ሁላችንን ሸፍኗል:: የምናመልከው ጌታ በደላችንን ተሸክሞ በመስቀል ላይ ሞቷል:: ሰው የራሱን በደል ተሸክሞ መጠየቅ በማይፈልግበት ዓለም ክርስቶስ ግን የሁላችንን በደል ተሸክሞ መሞቱ ይገርማል::

ውቅያኖስን በልብስ መክደን አይታሰብም:: የእግዚአብሔር ትዕግሥት ግን ከውቅያኖስ የሚሰፋውን በደላችንን ሸፍኗል:: ማንም የማይችለውን ምሥጢራችንን እርሱ ደብቋል:: እኛ ለሰዎች በሕይወት ዘመናችን የምንሰጣቸው ዕድል አንድ ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ግን በየዕለቱ ሁለተኛ ዕድል ይሰጠናል:: እኛ ይቅር የምንላቸው፣ መልሰን የምንቀርባቸው የሥጋ ቤተሰቦቻችንን ነው:: መንፈሳውያን ሆነን እንኳ ለመንፈሳውያን ቤተሰቦቻችን ያለን ፍቅር ከሥጋ ቤተሰቦቻችን ያነሰ ነው:: ስንጋጭ እናቆማለን:: እግዚአብሔር ግን ያለ ልዩነት ሁላችንን ችሎናል:: ዛሬ እግዚአብሔር፡- «አንድ ሰው ተሸከሙልኝና መከራዬን አግዙኝ» ይለናል:: ፈቃደኞች ነን?

ባልና ሚስት ከሁለት ወንዝ ለአንድ ትዳር ይቀዱ ይሆናል እንጂ ባልና ሚስት ከአንድ ወንዝ መቀዳታቸው አጠራጣሪ ነው:: ታዲያ ባልና ሚስት ብዙ ጊዜ ተቃራኒዎች ናቸው:: አንዱ ዝምተኛ አንዱ ተናጋሪ፣ አንዱ ስስታም አንዱ ሰጪ፣ አንድ ገለልተኛ አንዱ ማኅበራዊ ... ናቸው:: እግዚአብሔር ደግና ደጉን ቢያጣምር ክፉውን ማን ይችልለታል? የዓለምን ክፋት ለማርከስ፣ አንዱን በአንዱ ለማነጽ እግዚአብሔር ተቃራኒዎችን ያስተባብራቸዋል:: አንዲት ደግ ሚስት እጅግ ዓመፀኛ ስለነበረው ባሏ በጻፈችው ማስታወሻ፡- «እግዚአብሔር እጅግ ለሚወደኝ ልጁ ይህንን ባል የሰጠኝ ካንቺ ይልቅ የሚሸከምልኝ የለም ብሎ ነው» ብላለች::

አስቸጋሪ የትዳር ጓደኞች፣ አስቸጋሪ የሥራ ባልደረቦች፣ አስቸጋሪ ጎረቤቶችና ልጆች እግዚአብሔር የእኛን ትዕግሥት ለመገንባትና የእርሱን ትዕግሥት ሊያሳየን አጠገባችን የሚያስቀምጣቸው ናቸው:: አንዳችን ለአንዳችን ጥያቄ ነን:: ክፋትን በእነርሱ ላየነው እንዲህ ካስጠላን እኛ ብናደርገው ምን እንደምንመስል የምናይባቸው መስተዋቶች ናቸው:: እግዚአብሔር ፍጥረተ ዓለሙን ተሸክሟል:: እኛ ግን የአንድን ሰው አመል መሸከም አቅቶናል:: አንድን ሰው ስንችል የእግዚአብሔርን ሸክም ተጋርተናል ማለት ነው:: ለዚህ ግን ፈቃደኝነታችን ያስፈልጋል::





ፈቃደኞች ነን? ስንፈቅድ ኃይል አለን:: *«በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነውና»* (ምሳ. 23:7)

## <u>እናስተውል!</u>

አይሁድ አንድ ጊዜ ስለሰቀሉት ሁልጊዜ እናዝናለን:: እኛ ግን በየዕለቱ በኃጢአታችን ስንሰቅለው አናዝንም:: አይሁድን እንጠላለን:: የሞተልንን ግን አንወደውም:: መስቀሉን በሥጋ እንጂ በመንፈስ ማየት አልሆነልንም:: የሌሎች መጥፋት ይገርመናል:: ከሌሎች መጥፋት በላይ የሚገርመው የእኛ መዳን ግን አይገርመንም:: በጉባዔ ቃሉን ስንሰማ ምነው እነ እገሌ በኖሩ እንላለን:: ቃሉ ለእኔ የተነገረ ነው ብለን ግን አንጸጸትም:: በእውነት እግዚአብሔር እኛን ወደ መኖሩ አይደንቅም ወይ? በእርግጥም እግዚአብሔር ያሳዝናል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የታመመው በዕለተ ዓርብ ብቻ ሳይሆን ዘመኑን በሙሉ «የሕማም ሰው» ነበረ:: ሌሎችን የሚወድ ታማሚ ነው:: ሕመሙ የሚወዳቸው ፍቅሩን ስለማይረዱለት ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ሰዎች ፍቅሩን አያውቁለትምና ስለዚህም አይድኑምና «የሕማም ሰው» ነበረ::

አዲስ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ጸጋ ያመነ መሆኑን ስለሚረሳ ባላመኑት ላይ መፍረድ ይቀናዋል:: ስንበስል ከፍርድ እንታቀባለን:: ፍርድ ስንፈርድ በተዘዋዋሪ በነገው ምርጫችን ላይ እየፈረድን መሆኑን ማስተዋል ይገባናል:: በማናውቀው ከመፍረድ፣ በጎውን ነገር በክፉ ከመተርጎም እንዲጠብቀን መጸለይ ያስፈልገናል:: ፍረድ ባንለውም እግዚአብሔር ጻድቅ ነውና ይፈርዳል:: ማረን ብንለው ግን ይሻላል:: ሰውን ከቅጣት በላይ «የሚሠራው ምን መሆኑን» ሲያውቅ ራሱን በጸጸት ይቀጣል (ሉቃ. 23:34):: ለመለወጥም ይዘጋጃል:: በማናውቀው እንፈርዳለን:: ባወቀ የሚምረን ጌታ ግን ድንቅ ነው!

የእግዚአብሔር ትዕግሥቱ ይቆጨናል እንጂ እንድናመሰግን አላደረገንም:: ትዕግሥቱ ቢገባን ግን የክረምት ዝናብ ነጠብጣብን ያህል እናመሰግን ነበር:: ትዕግሥቱ ሲገባን እንታገሣለን:: ስንታገሥ ሌሎችን ለመሸከም ፈቃደኞች እንሆናለን::

## <u>ጸሎት</u>

በዘመናት ሁሉ ታላቅ፣ በሚወዱህ ዘንድ ድንቅ፣
በሚያምኑህ ዘንድ ተአምረኛ የሆንከው ጌታዬ ሆይ



www.ethiopinorthodox.org

አመሰግንሃለሁ:: እኔን መውደድህ ይገርመኛል:: እንደ ሞተ ውሻ የምቆጠረውን እኔን ከንጉሣዊ ማዕድህ ማስቀመጥህ ይደንቀኛል:: ብዙ ዘመን አለቀ ስል አስጀመርከኝ:: ሞቷል ስባል ሕያው አደረከኝ:: ንጉሤ ሆይ! ምኔን አይተህ ነው የወደድከኝ? ራሴን በጽሞና ሳየው ራሴን እንኳ መውደድ አቃተኝ:: አንተ ግን ንጹሕ ሳለህ እንደ ወንጀለኛ ተከሰስክልኝ:: የማይገባኝን ሕይወት ልትሰጠኝ የማይገባህን መከራ ተቀበልክልኝ:: የምለው ባጣ እንዲሁ ተመስገን እልሃለሁ:: ኃጢአቴን አሳይተህ ልትድን ትወዳለህን? ያልከኝ ራሴንና ወዳጆቼን ካታከተው ኃጢአቴ አንተ አድነኸኝ:: በማላውቀው እፈርዳለሁ አንተ ግን ባወቅህ ትምራለህ:: ጌታ ሆይ በማላውቃቸውና በፍርድ ቀን በማልከሰስባቸው ሰዎች ስከራከር እውላለሁና ይቅር በለኝ:: እገሌ በደለ እንጂ እኔ በደልኩ የማልለውን እኔን ፈውስ:: የሰው መልካም ዕድሉ እንጂ ውድቀቱ እንዳያስደስተኝ ልቤን ጠብቅልኝ:: የሰውን ስህተቱን ሳይሆን መልካምነቱን የሚያይ የፍቅር ዓይን ስጠኝ:: ከወዳጅ ጋር ማርጀት ናፍቆኛልና እባክህን የሚዘልቀውን ፍቅር አድለኝ:: ምን አደረጉልኝ? ሳይሆን ምን አደረኩላቸው? እንድል እርዳኝ:: ልጅ ያጠፋውን የሰው ንብረት ወላጆች ይክሳሉና እኔ የሰበርኳቸውን ወዳጆቼን እባክህ ጠግንልኝ:: የእንደገና አምላክ ነህና ከተለየኋቸው ወገኖቼ ጋር እንደገና ዕድል ስጠኝ:: ዘመኔን በፍቅር እንድፈጽመው እርዳኝ:: ፍጻሜን የምታሳምር የፍጻሜ አምላክ አንተ ነህና ፍጻሜዬን አሳምርልኝ:: አጥር ቅጥሬ በሆነው ስምህ ለዘላለሙ አሜን!





# ምዕራፍ ሁለት

## ለፍቶብናል

አንድ ታዋቂ ሳይሆኑ አዋቂ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን አባት በአንድ ወቅት እግዚአብሔር በአገራችንና በቤተ ክርስቲያን ላይ ሊያመጣ ያለውን ቅጣት እንዳሳያቸው ያንንም ለሚመለከታቸው ለመግለጥ እንደሞከሩ አጫወቱኝና ወደ ጥልቅ ሀዘን ውስጥ ገብተው:- «እኔ ይመጣል ብዬ የተናገርኩት ውሸት ተብሎ እኔም ነቢየ ሐሰት ተብዬ ይህ ክፉ ነገር በተመለሰ» አሉኝ:: የእኝህን ሰው አስተሳሰብ ሳስብ ዛሬም ድረስ ይደንቀኛል:: እኛ የተናገርነው ትንቢት ከሚነጥፍ ሕዝብ ቢያልቅ እንመርጣለን:: ሕዝቡ ወይም እግዚአብሔር ተመልሶ ገፀ ምሕረት ቢታይ እንከፋለን:: በዚህ ምክንያት የምሕረት ሳይሆን የሞት አገልጋዮች እንሆናለን:: ከሰው ሕይወት የእኛ እውነተኛነት ካስጨነቀን ከባድ ነው:: እግዚአብሔር መዓቱም ምሕረቱም በእጁ ነው:: እኛ ግን ያለን ፍርድ ብቻ ነው:: ስለዚህ ምሕረትም ካለው እግዚአብሔር ጋር ብዙ ጊዜ እንጋጫለን:: እግዚአብሔር እኛን ያስደፈረን፣ ራሱንም ያስደፈረ ይመስለናል:: «እነ እገሌ ካልተቀጡ እኔ ክርስቲያን አይደለሁም» ብለን ራሳችንን እንረግማለን:: እግዚአብሔር የሚፈርደው እኛ ይቅር ስንል መሆኑን አናውቅም:: ተበዳይ ራሱ ማጥቃት ከጀመረ የበዳዩን በደል ዳኛ ማየት አይችልም:: ዳኛ የሚፈርደው ፍርድን ሁሉ ሙሉ በሙሉ ስንተውለት ነው:: ዳኛ ባለበት አገር ተበዳይ እንደ ፈራጅ ቢቀጣ ራሱ ወንጀለኛ ይሆናል:: እግዚአብሔርም ፍርድን ሁሉ ለእርሱ ስንተውለት ብቻ ይፈርዳል!

ነቢዩ ዮናስ እግዚአብሔር ወደ ነነዌ አገር ሄዶ የሚመጣውን ፍርድ እንዲናገር በላከው ጊዜ ኮበለለ:: እግዚአብሔር ግን መንገዱን በተአምራት አስቀይሮ ነነዌ አደረሰው:: የመዓቱንም ማስጠንቀቂያ በተናገረ ጊዜ ከትልቅ እስከ ትንሹ ከሰው እስከ እንስሳ ሁሉም በእግዚአብሔር ፊት ተዋረዱ:: እግዚአብሔርም ይቅር አላቸው:: ዮናስ ግን ተበሳጨ:- *«አቤቱ፥ እለምንሃለሁ፤ በአገሬ ሳለሁ የተናገርሁት ይህ አልነበረምን? አንተ ቸርና ይቅር ባይ፥ ታጋሽም፥ ምሕረትህም የበዛ፥ ከክፉው ነገርም የተነሣ የምትጸጸት አምላክ እንደ ሆንህ አውቄ ነበርና ስለዚህ ወደ ተርሴስ ለመኰብለል ፈጥኜ ነበር:: አሁንም፥ አቤቱ፥ ከሕይወት ሞት ይሻለኛልና እባክህ፥ ነፍሴን ከእኔ ውሰድ አለው»* (ዮና. 4:1-4)::



www.ethiopinorthodox.org

ዮናስ ማለት የስሙ ትርጉም ርግብ (የዋህ) ማለት ነው:: ዮናስ እንደ ስሙ ነበር:: እግዚአብሔርን በምሕረቱ በጣም ያውቀዋል:: ስለዚህ ይፈርዳል ብሎ አያምንም ነበር:: እግዚአብሔር ግን ፈራጅም አምላክ ነው:: ዛሬ የእግዚአብሔርን ምሕረት እያዩ ኃጢአት የሚሠሩ አሉ ይባላል:: ነገር ግን የእግዚአብሔር ምሕረት የኃጢአት ድፍረት በፍጹም አይሆንም:: ከፍርዱ በላይ ምሕረቱ ደንዳናውን ልብ ያለዝባል:: አንድ አባት:- «የእግዚአብሔር ቸርነቱና ፍቅሩ ቢነገር ሰው በደልን ይደፋፈራል እያሉ የአገሬ ቀሳውስት ወዮታን ይሰብካሉ:: ነገር ግን ሰው የእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር ቢገባው እንኳን ኖሮ ሊበድል መኖር አይፈልግም:: የእግዚአብሔር ፍቅሩ ልሂድ ልሂድ ያሰኛል:: ዓለምንም ያስመንናል» ብለዋል:: ዮናስ ግን አንተ ይቅር ማለትህ አይቀርምና እኔን መዓት አውሪ አታድርገኝ ብሎ ቀድሞ ኮበለለ:: አገሪቱ ይቅር በተባለች ጊዜ ደግሞ ተቆጣ:: እግዚአብሔር ግን ይቅርታ ያደረገው ለይቅርታው ምክንያት የሚሆነውን ንስሓን ስላየ እንጂ ባሕርዩ ተቆጥቶ የሚበርድ ስለሆነ አይደለም:: እቀጣቸዋለሁ ሲል ልክ ነበረ:: ሲምራቸውም ልክ ነበር::

ዮናስ ግን ይበልጥ ተቆጥቶ ከከተማ ውጭ ዳስ ሠርቶ በኩርፊያ ተቀመጠ:: እግዚአብሔር ግን ጥላውን አደረቀበት:: ዮናስም በፀሐይ ትኩሳት መኖርን እስኪጠላ ተመረረ:: ዮናስ ላልተከላት ዛፍ መድረቅ ተቆጨ:: እግዚአብሔርም ለፈጠረው ሰው ቢራራ ምን ይደንቃል? ዮናስ በፀሐይ ትኩሳት እንዲህ ተማረረ:: ለነነዌ ሰዎች ግን እሳት ካልዘነበ አለ:: እግዚአብሔርም እንዲህ አለው:- *«በውኑ ስለዚች ቅል ትቈጣ ዘንድ ይገባሃልን? አለው:: እርሱም:- እስከ ሞት ድረስ እቈጣ ዘንድ ይገባኛል አለ:: እግዚአብሔርም:- አንተ ትበቅል ዘንድ ላልደከምህባት ላላሳደግሃትም፥ በአንድ ሌሊት ለበቀለች በአንድ ሌሊትም ለደረቀች ቅል አዝነሃል:: እኔስ ቀኛቸውንና ግራቸውን የማይለዩ ከመቶ ሀያ ሺህ የሚበልጡ ሰዎችና ብዙ እንስሶች ላሉባት ለታላቂቱ ከተማ ለነነዌ አላዝንምን? አለው»* (ዮና. 4:9-11)::

ዮናስ ዋሾ ላለመሆን ወይም እውነተኛ ለመባል ሲጨነቅ ለሚጠፋው ሕዝብ ግን አልተጨነቀም:: እኛን የሚያስጨንቀንና እግዚአብሔርን የሚያስጨንቀው ለየራስ ነው:: እኛ ለእግዚአብሔር እውነት ሳይሆን ለራሳችን ሐቅ ስንታገል የምናሳየው ጭካኔ ወደር የለውም:: የእግዚአብሔር እውነት ከርኅራኄ ጋር ነው:: የእግዚአብሔር እውነት የሚያግዝም ኃይል አለው:: የእኛ እውነት ግን ፍርድ ሰጪ ብቻ ነው:: ከእኛ እውነት የእግዚአብሔር እውነት ይሻላል::





ጌታችን ዐሥራ ስምንት ዓመት በድካም መንፈስ ተይዛ ጎብጣ የነበረችይቱን ሴት በፈወሰ ጊዜ የምኵራቡ አለቃ ተበሳጭቶ ተናግሯል:: ካቀረበው ምክንያት ይልቅ የእርሷ በሽታ ትልቅ ምክንያትና ፈውሷም አስደሳች ነበር (ሉቃ. 13:10-17):: ጌታችን ደስ የሚያሰኘው የሰው መዳን ነው:: በሰው በሽታ አማካይነት መላምት እየተናገሩ መክበር የሚፈልጉ ግን ደስተኞች አይደሉም:: የኤድስ በሽታ ቢጠፋ የሚከፉቸው እንደማይጠፉ ሁሉ በሰውም ድካም የሚነግዱ በእግዚአብሔር ቤት አሉ:: በጨለማ የሚነግዱ የሐሰት አስተማሪዎች የእውነት ወንጌል ሲገለጥ እንጀራቸው የሚቆም ስለሚመስላቸው ወንጌሉንና ወንጌላውያንን ከቤተ ክርስቲያን ያሳድዳሉ:: የምኵራቡም አለቃ የዚያች ሴት መፈወስና የክርስቶስ መክበር የእርሱ ህልውና ማብቂያ ሲመስለው በእግዚአብሔር ስም ሥጋዊ ቅንዓቱን ቀባብቶ ተቆጣ:: የተቆጣው ግን ለራሱ እንጂ ለእግዚአብሔር አልነበረም:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ፈውሶ ከሳሽን ማሳፈር ልማዱ ነውና ተከራከረላት:: መዳን ከሳሽ አለውና!

የምናመልከው የፈጠርነውን ጣኦት ቢሆን ኖሮ እንሸከመው ነበር:: የፈጠረን ጌታ ግን ይሸከመናል:: እናት ባለጌ ልጇን በጣም የምትወደው ከእርሷ በቀር የሚወደው ስለሌለ ነው:: እግዚአብሔርም ኃጢአተኞችንና ደካሞችን ከእርሱ በቀር የሚቀርባቸውና የሚዳስሳቸው ስለሌለ ይወዳቸዋል:: እርሱ እንደ እኛ ቢሆን ኖሮ ዓለም ያለ ጊዜዋ ታልፍ ነበር::

ጌታችን ወደ ሳምራውያን መንደር በገባ ጊዜ አልተቀበሉትም:: ከደቀ መዛሙርቱም ያዕቆብና ዮሐንስ ተቆጥተው:- *«ጌታ ሆይ፥ ኤልያስ ደግሞ እንዳደረገ እሳት ከሰማይ ወርዶ ያጥፋቸው እንል ዘንድ ትወዳለህን? አሉት:: እርሱ ግን ዘወር ብሎ ገሠጻቸውና:- ምን ዓይነት መንፈስ እንደ ሆነላችሁ አታውቁም፤ የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም አለ:: ወደ ሌላ መንደርም ሄዱ* (ሉቃ. 9:54-56)::

የፍጡር ችኮላና የፈጣሪ ትዕግሥት የተለያየ ነው:: ደቀ መዛመርቱ ሰው እንደ መሆናቸው የእሳትን ኃይል ለመኑ:: ጌታ ግን የትዕግሥትን ኃይል ተጠቀመ:: የዛሬ አለመስማታቸው የዘላለም እምቢታ አይደለም ብሎ ለነገ ተስፋ አደረጋቸው:: ዛሬ በማይሰሙት ከማዘን ዛሬ ወደሚሰሙት ሄደ:: ሰው በቃል ብቻ ሳይሆን በሕይወትም ይማራልና ለሕይወት ጊዜ ሰጠ:: እርሱ ኃጢአተኞችንና ዓመፀኞችን ይመለከታቸው የነበረው እንደ በሽተኞች ስለነበር ሊረዳቸው ዝግጁ ነበር:: (ማቴ. 9:12):: የጨጓራ በሽተኛን፣ የሳንባ በሽተኛን ማንም አይቀየመውም:: ከዚያ ይልቅ ይረዳዋል:: ጌታችን



www.ethiopinorthodox.org

ኢየሱስ ኃጢአተኞችን እንደ በሽተኞች አያቸው:: በቃሉም:- *«ምሕረትን እወዳለሁ»* (ማቴ. 9:13) አለ::

የእኛ ድካም ከቅዱሳንም ትዕግሥት በላይ ነው:: ወደ ተፈጠርንበት ዓላማና ወደ ዳንንበት ምሥጢር የሚያደርሰን የእርሱ ትዕግሥት ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ከበዱኝ ብሎ ለማንም አሳልፎ ስለማይሰጠን በዚህ ደስ ይለናል:: የእኛ ነገር የእርሱ ዕዳ እንደሆነ ቆጥሮታልና:: ጳውሎስ:- *«አንተ በሌላው ሎሌ የምትፈርድ ማን ነህ? እርሱ ቢቆም ወይም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሲያቆመው ይችላልና ይቆማል»* (ሮሜ. 14:4) ይላል::

በጠፋው ልጅ ታሪክ ውስጥ የአባትን ፍቅር የወንድምን ጭካኔ እናያለን:: ያ ልጅ የአባቱን ጸጋ የትም አባከነ:: ረሀብ ሲጸናበት የእርያ ጠባቂ ሆነ:: እሪያዎች ከሚበሉት አሠር ለመጥገብ ይመኝ ነበር:: ወደ ልቡ ተመልሶ የአባቱን ፍቅርና የአባቱን ቤት ክብር ሲያስብ በልጅነት ሳይሆን በባርነት እንኳ መኖርን መረጠ:: ወደ አባቱ ጉዞ ሲጀምር አባቱ ከሩቅ አይቶ አዘነለት:: መንገድ አጋምሶ ተቀበለው:: ስለ እርሱም መገኘት ታላቅ ግብዣ አደረገ:: ወንድሙ ግን ቅጣት ለሚገባው ምሕረት በመደረጉ ተበሳጨ (ሉቃ. 15:11-32)::

የሁለቱ ልጆች አባት እግዚአብሔር ነው:: አንዱ ልጅ በቤት አንዱ ልጁ በደጅ ነበሩ:: አንደኛው የሰው ወገን በስሙ አምኖ በቤቱ ይኖራል፣ ሌላኛው የሰው ወገን ደግሞ ከእግዚአብሔር ኮብልሎ በኃጢአት ይኖራል:: እግዚአብሔር ለሰው ዘር ሁሉ በፍጥረት አባት ነው:: ኮብላዩ ልጅ ድርሻውን ወስዶ እንደ ኮበለለ የሚያልቅ ጸጋ ይዘው ከእግዚአብሔር ብዙዎች ይኮበልላሉ:: ጤና ሲያገኙ፣ ሀብት ሲያገኙ፣ አዋቂ ሲሆኑ ይኮበልላሉ:: ያ የጠፋው ልጅ ሁሉን ከስሮ ራሱንም እንደ ከሰረ ከእግዚአብሔር የኮበለሉም ያላቸውን ብቻ ሳይሆን ራሳቸውንም ይከስራሉ:: ያ ልጅ ከረሀቡ የተነሣ ከእርያ አሠር ለመጥገብ ተመኘ:: የእሪያ አሠር ለእሪያ ያጠግባል፣ ለሰው ግን ጥጋብ አይሆንም:: ከእግዚአብሔር የኮበለሉ ሰዎችም ጠጥቶ ሁሉን ለመርሳት፣ አመንዝሮ ለመደሰት ይፈልጋሉ:: ነገር ግን ኃጢአተኞችን የሚያረካውን ጊዜያዊ ደስታ በማጣት ምነው እንደ እነርሱ በሆንኩ ይላሉ:: የእግዚአብሔርን ደስታ ላየ የዓለም ደስታ በአሻንጉሊት ለመርካት እንደሚሞክር ጎልማሳ ነው:: አሻንጉሊት ሕጻናትን ለማታለልና ለማስረሳት በቂ ነው:: ለጎልማሳ ግን ከመደገፊያነት ያለፈ ደስታ አይሰጠውም:: በክርስቶስ መርካት የተለማመደና የኮበለለ ምእመንም ምንም ነገር ሲያረካው አይችልም:: እውነቱን ሳወቀ ሐሰት አያስተኛውም:: ለማያውቁ ግን



ሐሰት ይደልላቸዋል:: ቃሉም:- *«ለክፉዎች ሰላም የላቸውም»* (ኢሳ. 48:22) በማለት በግልጽ ይናገራል::

የጠፋው ልጅ ወደ አባቱ ሲመለስ አባቱ መንገድ አጋምሶ እንደተቀበለው እግዚአብሔርም ወደ እርሱ አንድ እርምጃ ስንመጣ ወደ እኛ ሁለት እርምጃ ይመጣል:: ያዝንልናል፣ ዳግመኛም ያቅፈናል፣ ጸጋን ይሰጠናል:: ለጠፋው ልጅ በተደረገው ቸርነት ታላቅ ወንድሙ እንደ ተከፋ ከልጅነታችን ጀምሮ ከቤቱ አልተለየንም የሚሉ አገልጋዮችም ከዓለም በመጡት ይከፋሉ:: ይጨክናሉ:: እግዚአብሔር ግን ይራራል:: «ከራሴ ጸጋ ለወደድኩት ብሰጥ የእናንተን አልነጠቅኋችሁ ስለምን ትከፋላችሁ?» ይላቸዋል::

እግዚአብሔር ምሕረትን ለማድረግ ምክንያት ይፈልጋል:: መመለሳችንን ብቻ በመፈለግ ያለ ወቀሳ ይቀበለናል:: እርሱ ከተቀበለን ዓለም ሁሉ ቢቃወመን የእርሱ ይቅርታ ብቻ ይጸናል:: አንድ አባት ስለ እግዚአብሔር ይቅርታ ጽኑነት ሲናገሩ:- «እግዚአብሔር ምሮኛል፣ ወደ መንግሥቱ በመግባቴ አያደርጉትም እንጂ መላእክት እንኳ ቢከፉቸው እናንተ ውጡ እንጂ እኔ ይቅር ያልኩት አይወጣም ብሎ እግዚአብሔር ስለ እኔ ይሟገታል» ብለዋል:: ለእርሱ ቅጣት የመጨረሻው አማራጭ እንጂ የመጀመሪያ መንገዱ አይደለም:: እርሱ ኃይሉን ለማሳየት ማንንም አይቀጣም:: ለገዛ ጥቅማችን እንድንመለስ ግን ይቀጣናል:: እኛ ሕፃናትን የምንቀጣቸው ስላናደዱን ይሆናል እንጂ ስለመለወጣቸው አስበን ላይሆን ይችላል:: እግዚአብሔር ግን የሚቀጣን ስላናደድነው ሳይሆን እንድንለወጥ ነው::

መሐል ውቅያኖስ ላይ የተለቀቀ ወዴት እንደሚሄድ ግራ እንደሚገባው የእግዚአብሔርን ትዕግሥት ለመናገርም ከየት እንደምንጀምር ግራ እስኪገባን ሰፊና ጥልቅ ነው:: ብቻ እርሱ ለፍቶብናል፣ ተስፋ ጥሎብናል:: ስለዚህ መርሳትን ምክንያት በማድረግ ሊረሳን አይችልም:: ሁላችንም ብንሆን የምንተወውን ነገር አንለፋበትም:: ለነገም በምንፈልገው ነገር ግን ብዙ እንለፋለን:: እግዚአብሔርም ከማኅፀን ጀምሮ እስከዚህች ቀን ደክሞብናል:: የደከመብን ሊጥለን አይደለም:: በቃሉ:- *«አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና»* (ዕብ. 13:5)::

ዐጼ ሚኒልክ ከሠራዊታቸው ስመ ጥር የሆኑ የጦር ሰው እርሳቸውን የሚያሳዝን ጥፋት በመሥራታቸው መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው:- «በድሎኛልና ይህን ሰው አንድ በሉልኝ» አሉ:: መኳንንቶቹም በየተራ እየተነሡ «እምዬ ሚኒልክን ከበደለማ ሞት



www.ethiopinorthodox.org

ይገባዋል» እያሉ የፍርድ አሳብ አቀረቡ:: እርሳቸው ግን ከዛሬ ጥፋቱ የትላንት ወዳጅነቱን፣ ከዛሬ ወንጀሉ የትላንት መልካምነቱን ከሁሉ በላይ በእርሱ ላይ የነበራቸውን ተስፋ አሰቡና:- «እናንተ የዋሆች እፊታችሁ ያቀረብኩት እንድትወቅሱልኝ እንጂ ግደለው እንድትሉኝ ነውን? እርሱን እዚህ ደረጃ ለማድረስ ሃያ ዓመት ፈጅቶብኛል» ብለው ይቅርታ አደረጉለት ይባላል:: እኒያ ራስም ከቀድሞ ይልቅ ታመኗቸው:: /ዘነበ ፈለቀ «ነበር ቊጥር ሁለት ገጽ 156»/::

ሐዋርያው ጳውሎስ *«እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን»* (2ቆሮ. 5:20) ብሏል:: ሰው የበዳይ አኩራፊ ሆኖ ስለተቀመጠ እግዚአብሔር በመልእክተኞቹ አማካኝነት መጪውን ዘላለማዊ ቅጣት እንዲያመልጥ ሰውን ይለምናል:: ወንጌል የእርቅ አሳብ ነው:: በመናገሻ ከተማ የነገሠው ንጉሥ ለሸፈቱት ሁሉ ምሕረት አድርጌላችኋለሁና ወደ ወገናችሁ ግቡ እንደሚል እግዚአብሔርም ያለድርድር በልጁ ሞት ምሕረትን አውጆልናልና በእርቁ አሳብ ልንመለስ በወንጌል አምነን ልንድን ይገባናል:: አዎ ሚኒልክ የሃያ ዓመት ልፋታቸውን እንደ ቀላል ሊተዉት አልወደዱም:: ከእርሳቸው ይልቅ እግዚአብሔር ሰውን ከማኅፀን ጀምሮ ለፍቶበታልና እንደ ቀላል ሊተወው አይፈልግም!!

## እናስተውል

በግለሰብም ሆነ በአገር ትልቅ ጥፋት የሚከሰተው «ካፈርኩ አይመልሰኝ» በሚለው መንገዳችን ምክንያት ነው:: ክፉ ነገርን አለመጀመር፣ ከጀመርን አለመጨረስ ክብር ነው:: ክፉ ነገርን ካሰብን እንናገረው፣ ከተናገርነው አናድርገው፣ ካደረግነው አንድገመው:: ሲጨርሱት ደስ የሚለው በጎ ነገር ብቻ ነው:: ክፉ አሳብን፣ ክፉ ንግግርን፣ ክፉ ተግባርን የሚፈጽሙት ሳይሆኑ የሚያቋርጡት ጀግኖች ናቸው:: በደለኛን አለመገሰጽ፣ ጨለማ ሥራውን ብርሃን ነው ብሎ ማጽደቅ ከበደለኛው በላይ የሚያስጠይቅ ኃጢአት ነው:: የምንናገረው ለሰዎቹ መመለስ ብቻ አይደለም ራሳችንን ከተጠያቂነት ነጻ ለማድረግም ነው:: የአገልግሎት ዋጋ ያለው ምን ያህል ሰው ቃላችሁን ተቀበላችሁ ተብሎ ሳይሆን አደራችሁን ምን ያህል ተወጣችሁ? ተብሎ ነው:: በጎ ሲናገሩ በጎ ይመጣል ብለን ንስሐ ለሚያስፈልገው ሕዝብ ተስፋን መስጠት ነቢያተ ሐሰት መሆን ነው:: በጎ የሚመጣው በጎ ሲሠሩ እንጂ በጎ ሲናገሩ አይደለም::



የምናገለግላቸውን ምእመናን በእግዚአብሔር ፍቅር እንጂ በእኛ ፍቅር አናድናቸውም:: የእኛና የእግዚአብሔር ፍቅር ልዩነቱ የእርሱ ፍቅር የሚያድን ፍቅር መሆኑ ነው:: እኛን አይተው እግዚአብሔርን የማያዩ፣ እኛን ወደው እግዚአብሔርን የማይወዱ፣ እኛን ፈርተው እግዚአብሔርን የማይፈሩ ምእመናንን እያተረፍን ነውና ያስፈራል! እግዚአብሔር የፍቅር ብቻ ሳይሆን የፍርድም ባሕርይ አለውና ፍቅሩንና ፍርዱን በሚዛናዊነት ማስተማር አለብን:: ለስማችን ከኖርን የእውነት ወገንተኛ መሆን አንችልም:: እውነት የሌለበት ፍቅርና ክብር በራሱ ሐሰተኛ ነው ብለን መናቅ ይገባናል:: ከዮናስ የምንማረው ይህን ነው::

ሰዎች እንዴት አልተቀጡም? ሳይሆን እኔ እንዴት ዳንኩኝ? ሰዎች እንዴት ሞቱ ሳይሆን እኔ እንዴት ኖርኩኝ? ማለት ይገባናል:: ከሰዎቹ መቀጣት የእኛ መዳን፣ ከሌሎች መሞት ይልቅ የእኛ ህልውና ይደንቃልና! የምንወደው ሰው ቅጣትና ስደት በሚገባው መንገድ ላይ ሆኖ የምንታገሠው በሥራው ተስማምተን ወይም ሳናዝን ቀርተን ሳይሆን በእርሱ ላይ የነበረን የገዛ ምኞታችንም ቆጭቶን ለገዛ ምኞታችንም አዝነንለት ነው:: እግዚአብሔርም ሰውን የማይተወው በሰው ላይ የነበረውን ትልቅ እቅዱን እያሰበ ነው::

## ጸሎት

ሺህ ምዕራፍ ስርቅህ ሺህ ምዕራፍ የተከተልከኝ፣ ወደ ሞት የሚሄደውን ልጇን ጨክና እንደማትሸኝ እናት ከፊቴ ቀድመህ የለመንከኝ፣ ጀርባዬን ስሰጥህ ፊትህን ያሳየኸኝ፣ ልቀድምህ ስፋጠን ጫፉ ላይ የጠበቅኸኝ፣ አፍሬ በኃጢአት ላይ ኃጢአት ለመጨመር ስሻ እቀበልሃለሁ በእሳት አትጫወት ያልከኝ፣ ከእኔ በጎነት ካንተ ክፉ ያጣሁብህ፣ እንደ እኔ ያልሆንከው ጌታዬ ክርስቶስ ተመስገን:: ከሰው ኀሊና የተረሳኹትን፣ ፍጹም ተስፋ የተቆረጠብኝን ተስፋ ያደረግኸኝ ጌታዬ ሆይ አመሰግንሃለሁ:: በእኔ ብጨርስም ባንተ ያኖርከኝ፣ ያንተ እንጂ የእኔ ታማኝነት ገና ነው ብለህ በአዲስ ኪዳን ያዳንከኝ አምላኬ ተመስገን:: ቢሞት ይሻለዋል ለተባልኩት ሞት ሳይሆን የሚሻለው ሕይወት ነው ብለህ ሕይወትን ሰጠኸኝ፣ የበደልኩህ አንተ እየወደድከኝ ያልበደልኳቸው ሰዎች ጠሉኝ፣ አንተ ሳትሰለቸኝ ሁሉ ሰለቸኝ፣ ከርኩሰት ለመርካት ስመኝ፣ ሞትን በፈለኩባት ቀን አዳንከኝ:: በብዙ የሕይወት ጎዳና ውስጥ ሳልፍ፣



www.ethiopinorthodox.org

ጉልበት የማይሻገረውን፣ ዘመድ ገንዘብ የማያሻግረውን ቀን አልፌ ሳይ እንዳልተውከኝ አወቅሁ። እሺ ስልህ ሁሉም ሺህ ሆነልኝ። እባክህ ጌታዬ እንደ ትላንቱ ዘመኔ በከንቱ አይለቅ። በሕይወቴና በሞቴ አንተ ብቻህን ክበር። ወሰን በሌለው ትዕግሥትህ አሜን!



# <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## <u>የትዕግሥቱ ምሥጢር</u>

የእግዚአብሔር ትዕግሥት የሚለው ቃል የተወሰደው በ1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 3 ቍጥር 20 ላይ ካለው ዓውደ ንባብ ተነቅሶ ነው። የመልእክቱ ሙሉ ቃል እንዲህ ይላል፡- *«ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ፥ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቈየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም።»*

የሰው ዘር ጉዞ እንደገና የቀጠለው በኖኅና በቤተሰቡ (በስምንት ነፍስ) ነው። ስምንት ነፍስ እስኪቀሩ መላው ዓለም በእግዚአብሔር ላይ ዐምፆ ነበር። ዛሬ በመንግሥት ላይ ዓምፀው ጫካ እንደሚገቡ ሽፍቶች ያ ትውልድ በእግዚአብሔር ላይ ዐመፆ ነበር። በአንድ አገር ላይ ትልቁ ወንጀል አገርን (መንግሥትን) መክዳት ነው። ይህ ወንጀል የሚከፈለው በሞት ነው። መንግሥት ግን ሕዝብን ሳይፈጥረው መክዳቱን በሞት ከቀጣ እግዚአብሔር ፈጣሪማ የከዱትን ቢቀጣ ተገቢ ነው። ያ ትውልድ እግዚአብሔርን ከዳ። እግዚአብሔር ግን ሕዝቡን አልከዳም ነበር። አየሩን ያነፍሳል፣ ፀሐዩን ያወጣል፣ ክረምትና በጋውን ያፈራርቃል። አስገኚ ፈጣሪ፣ ሰጪ ጌታ ቢያፈገፍግ ይገባ ነበር። ፍጡርና ለማኝ የሆነው ሰው ግን በፈጣሪው ላይ ሲከዳ በጣም ያሳፍራል። አባ ጳውሎስ ፓትርያርክ በአንድ ወቅት፡- «የሰው ልጅ ከ፡ዛሬ ብዙ ሺህ ዓመት ጀምሮ በታሪክ እንደምንረዳው ከእግዚአብሔር ጥገኝነት ተለይቶ የኖረበት ዘመን የለም። ያለ እርሱ ምንም ማድረግ ምንም መሆን እንደማይቻል እናስታውስ። እኛም ጥገኛ ላለመሆን ከእግዚአብሔር እጅ ለመውጣት በከንቱ አንድከም። ይልቅስ በእርሱ እንመን፣ በእርሱ እንደገፍ» ብለዋል።

እግዚአብሔር አለማወቅን የሚያግዝ አምላክ ነው። መንግሥት ወንጀለኛን ይቀጣል። ያለ ቅድመ ማስጠንቀቂያም በሕግ ይጠይቃል። «ሕግን አለማወቅም ከወንጀል አያነጻም» ይላል። እግዚአብሔር ግን አስቀድሞ በቃሉ ይመክራል። የንስሓ ጊዜም ይሰጣል። በዚህ አሠራሩ በኖኅ ዘመን ለነበሩት ወገኖች 120 ዓመት የንስሓ ጊዜ ሰጣቸው። እነርሱ ግን ኃጢአትን ሊጠግቧት አልቻሉም። አሁን እንዳላረካቸው ቢያውቁም ቀጥሎ እረካ ይሆናል እያሉ ኃጢአትን በተስፋ ይሠሩ ነበር። በዓመፀኛው ዓለም ግን አንድ ታዛዥ ሰው ተገኘ። ያ ሰው ኖኅ ነው። ቤተሰቡን አስመልጦ



www.ethiopinorthodox.org

ኀረቤቶቹንና ያንን ትውልድ ለማስመለጥ ንስሓን ቢሰብክም እነርሱ ግን አልሰሙትም (2ጴጥ. 2:5)። ኖኅም ለራሱ የመዳኛ መርከብ እየሠራ ንስሓን ያውጅ ነበር። የዛሬ ሰባክያን ንስሓ ሳይገቡ ንስሓ ግቡ የሚሉ፣ ንስሓ እያለባቸው ንስሓን የሚቀበሉ ናቸው። ኖኅ ግን ተሰብኮ የሚሰብክ ነበር።

ያለሁበት አካባቢና አገር እግዚአብሔርን ለማምለክ ምቹ አይደለም እንላለን። ኖኅ ግን መላው ዓለም ጠፍቶ ለእግዚአብሔር የተገኘ ሰው ነበር። እግዚአብሔር ክፉዎች በዙብኝ ብሎ በአንዱ ኖኅ አላፈረበትም። ሰው በጠፋበት ዘመን «ሰው የለም» ከማለት ሰው ሆኖ መገኘት ምንኛ መታደል ደግሞም ዘርን ማትረፍ ነው። ኖኅ በማያምኑ መካከል ሲኖር ዘወትር የጥላቻና የስድብ ድምፅ ይሰማ ነበር። ያመነውን ስለሚያውቅ አልታወከም። አንድ ቀን ይህ አገር ባሕር ይሆናል እያለ መርከብን ሲሠራ እነዚያ ዐመፀኞች አብዷል እያሉ ሳያፌዙበት አይቀሩም። ኖኅ ግን እግዚአብሔር የነገረውን አምኖ በእምነት መርከብ ሠራ። ኖኅ የሚኖረው በባሕር ዳርቻ ቢሆን መርከብን ለመሥራት ምክንያታዊ በሆነ ነበር። በደረቅ ምድር ላይ ከባሕር በብዙ ርቀት ላይ ሆኖ መርከብን መሥራትና አንድ ቀን ይህ ስፍራ ባሕር ይሆናል ብሎ መዘጋጀት እምነትን ይጠይቃል።

እግዚአብሔር ለዚያ ትውልድ የሰጠው የንስሓ ዘመን ረጅም ነበር። የመታገሡ ምሥጢር ግን አልገባቸውም። ስለዚህ ጠፉ። የእግዚአብሔር ትዕግሥት የሚጠቅመን ምሥጢሩ ሲገባን ነው። እግዚአብሔር በቅዱስነቱ ኃጢአትን አያይም፣ በጻድቅነቱም ኃጢአትን ያለ ቅጣት አይተውም። ነገር ግን ሰይፍ በሰገባ ውስጥ እንደሚጨበጥ እግዚአብሔር የቁጣውን ሰይፍ በምሕረቱ ሰገባ እየያዘ ይታገሠናል። የሚታገሠን መቅጣት ስለፈራ፣ ወይም ስለማይችል አይደለም። የሚታገሠን ኃጢአታችን ስለተስማማው ወይም የበደል ጽዋችን ሞልቶ ለፍርድ እንዲመቸው አይደለም። የሚታገሠን ንስሓ እንድንገባ ነው። ዳግም ምጽአቱን እንኳ የሚያዘገየው ለብዙዎች የንስሓ ዕድልን ለመስጠት መሆኑን መጽሐፍ ይናገራል፡- *«ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሓ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል»* (2ጴጥ. 3:9)።

ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ በአዲስ አበባ ውስጥ ብዙ ቤት ሠርተው ያከራዩ ነበር። በአንድ ክረምት ላይ የኪራይ ገንዘብ ለመሰብሰብ በአንድ የተከራየ ቤታቸው ደጃፍ ላይ እንደ ቆሙ ዝናብ መዝነብ ጀመረ። ቢያንኳኩ ቢያንኳኩ የሚሰማቸው አጡ። ምንም





መጠለያ ስላልነበረ ዝናቡ በላያቸው ላይ ካባራ በኋላ ሲያንኳኩ «ማነው?» ብለው ከውስጥ ወጡ። ተሰማ እሸቴም፡-

*«እኔ ነኝ ተሰማ እሸቴ፣*
*እደጅ ቆሜአለሁ በገዛ ቤቴ።»*

አሉ ይባላል። እንኳን የእኛ የሆነው ይቅርና እኛ ራሳችን የእግዚአብሔር ነን። ይህ ሰውነታችን የእርሱ ቤት ነው። እኛ ግን በገዛ ቤቱ እደጅ አቁመነው፡- *«እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ...»* ይለናል (ራእ. 3:20)። ደጃፋችን ላይ ቆሞ የሚያንኳኳ ወዳጅ ብዙውን ዋጋ እርሱ ከፍሎታል። ፀሐይ መትቶታል፣ ዝናቡ ወርዶበታል፣ የሠረገላ ወጪ አውጥቷል። ከእኛ የሚጠይቀን ትንሽ ድርሻ ነው። ተነሥቶ መክፈት! የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት ከጀመርን ስንት ዓመት ሆነን? በዚህ ሁሉ ዓመታት ውስጥ ንስሓ ገብተን ካልተመለስን በደጅ አቁመነዋል ማለት ነው። ንጉሥን በደጃፋችን አቁመን እንዴት ያስችለናል? ሁሉም ሃይማኖት ስለ አንድ አምላክ ኃያልነትና መልካም ስለማድረግ ሲናገር በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠው ሃይማኖት ግን ያ ኃያል አምላክ ኃይሉን ሰዎችን ለማዳን እንደሚጠቀምበት፣ ፈላጊና የሚያንኳኳ አምላክ መሆኑን፣ ሕይወት ሰጪም መሆኑን ያስረዳል (ራእይ. 3:20፣ ዮሐ. 14:23)። *«እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ»* ካለ በኋላ *«ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር እራት ይበላል»* (ራእ. 3:20) ይላል። እራት ትልቅ ግብዣ ሲሆን እጅግ ቅርብ የሆኑ ሰዎችን የምንጋብዝበት የግብዣ ዓይነት ነው። እነዚያ ሰዎች ግን አመሻሽተው ሲሄዱ የደመቀው ቤት ወደ ፀጥታው ይመለሳል። እራቱን እሺ እንዳሉ አዳሩን ብንጠይቃቸው እሺ አይሉም። አብሮ የሚያድረው፣ አስፈሪውን ጨለማ የማይለየው የወዳጅ ወዳጅ ነው። እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የመጨረሻው ቀን በእራት ግብዣ ተመስሏል። ዛሬ ድምፁን ሰምተው የልባቸውን እሺታ ለሚያቀርቡለት በዚያን ቀን ከእርሱ ጋር ይከብራሉ።

እግዚአብሔር ይገስፀናል። በቃሉ ይዘልፈናል። ብንሰማው ሕይወትና መታደስ ይሆንልናል። ካልሰማነው ግን ይቀጣናል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፈርዖን ሲናገር፡- *«ኃይሌን በአንተ አሳይ ዘንድ ስሜም በምድር ሁሉ ይነገር ዘንድ ለዚህ አስነሣሁህ ይላልና። እንግዲህ የሚወደውን ይምረዋል፥ የሚወደውንም እልኸኛ ያደርገዋል»* (ሮሜ. 9:17-18) ይላል።



www.ethiopinorthodox.org

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ያለውን ምሥጢር እንዳንረዳ ጥቅሱ የክርክር ርዕስ ሆኗል:: ስለዚህ በጥቅሱ ውስጥ ያለውን የእኛን መልእክት ሳንይዝ መቅረታችን ያሳዝናል:: ስለቅድመ ውሳኔ የሚያስተምሩ ወገኖች እግዚአብሔር የሚድኑትን አስቀድሞ ወስኗል ለማለት ይህን ጥቅስ ይጠቅሳሉ:: እግዚአብሔር ግን ራሱ ወስኖ ራሱ እንዴት ይፈርዳል? ይልቁንም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ሁሉ አድኖ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ብሎ ለአንዳንዶች እንዳይድኑ ወስኗል ማለት ተገቢ አይደለም (ዮሐ. 3:16)::

እግዚአብሔር ሕዝቡን ይለቅቅ ዘንድ ፈርዖንን ብዙ ጊዜ አስጠንቅቆታል:: ፈርዖን ግን ድምፁን ናቀ:: ቅጣቱ ሲያስጨንቀው ደግሞ እሺ ይልና ቅጣቱ ሲርቅ እምቢ ይላል:: በመጨረሻ እግዚአብሔር ልቡን አፀናና ለቅጣት አመቻቸው:: ፍጻሜውንም በኤርትራ ባሕር ውስጥ አደረገው:: ፈርዖን በመጀመሪያ ልቡን አፀና በመጨረሻ እግዚአብሔር ልቡን አጽንቶ ቀጣው:: *«እንግዲህ የሚወደውን ይምረዋል ፥ የሚወደውንም እልኸኛ ያደርገዋል»* (ሮሜ. 9:18) የሚለው ይህን ነው::

የእግዚአብሔር ትእዛዝ ወደ እኛ ሲመጣ ከኃይል ጋር ይመጣል:: ፈጥነን ስንታዘዝ ኃይሉ ይረዳናል:: ፈጥነን ካልታዘዝን ግን ኃይሉ ሄዶ ትእዛዙ ይቀራል:: ብንፈልግ እንኳ ኃይል ልናጣ እንችላለን:: ትእዛዙንም ደጋግመን ስንሰማ ልባችን እየደነደነ ይመጣል:: በመጨረሻ እግዚአብሔር ይቀጣን ዘንድ ልባችንን አጽንቶ ይጥለናል:: እግዚአብሔርን ፈጥነን መታዘዝ ያለብን ለዚህ ነው::

በኖኅ ዘመን የነበሩ ትውልዶችንም ድምፁን ሰምተው መመለስን ስላልፈለጉ እግዚአብሔር አጠፋቸው:: ከመቼውም ጊዜ ይልቅ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በዛሬው ዘመን ሰፍቷል:: ይህ ትዕግሥቱ ግን እንድንመለስ ስላላደረገን ቀጥሎ የሚሆነው ነገር አስፈሪ ነው:: በዓለም ላይ ግፍ በዝቷል:: ሰዎች ያልፈጸምነው ኃጢአት ምንድነው? እያሉ እየረከሱ ነው ያሉት:: የእግዚአብሔርን ቅጣት ከመልመዳችንም የተነሣ አሁን የመጣው መከራ አይሰማንም:: ቀጥሎ የሚሆነውን ክፉ ነገር ለመስማት እንጓጓለን:: ቤተ ክርስቲያንም ከዘመኑ ጋር ለመራመድ ስትል የዓለሙ የችግር መፍትሔ ሳይሆን የችግሩ አካል ሆናለች:: በዚህ ሁሉ ውስጥ በዋና የማናቋርጠው የእግዚአብሔር ትዕግሥት እንደ ውቅያኖስ ሰፍቷል:: የመታገሡ ምሥጢር ግን ለንስሓ እንድንበቃ ነው:: እግዚአብሔር ከእኛ በደላችንን ከማመን የበለጠ ነገር አልፈለገብንም:: *«ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሓ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን? ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሓ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቍጣ ቀን ቍጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ»* (ሮሜ. 2፥4-5):: «ጸሎት» በሚለው መጽሐፍ ላይ ይህንን ጥቅስ የሚተረጉም ገለጻ ተቀምጧል::

> «የሮሜ. 2:4 ያለውን ንባብ ብዙ ጊዜ ሳንረዳው እናልፋለን:: ቃሉ:- *«የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን?»* ይላል:: በራሳችን በኩል ልክ ኃጢአት እንደሠራን የምንጠብቀው ውጤት አለ:: የምንሄድበት መኪና አደጋ የሚደርስበት፣ የምንወጣበት ሊፍት መሐል ላይ የሚቆም፣ የጀመርነው ሥራ የሚበላሽ፣ ሰው ሁሉ አውቆብን የሚያሳድደን፣ ስብከት የሚጠፋን. . . ይመስለናል:: ነገር ግን በተቃራኒው መንገዳችን የተሳካ፣ ሥራው የሰመረ፣ ስብከቱም ብዙ ምሥጢር የፈለቀበት ይሆናል:: የዚህ ነገር ምሥጢሩ ምንድነው? ስንል እግዚአብሔር ከክፉ ሥራችን ጋር መተባበሩ ሳይሆን ስጦታውን ወይም ቸርነቱን በማብዛት ልባችንን ለንስሐ ማለዘቡ ነው:: እኛ ያጠፉ ሰዎችን ማስተማር የምንፈልገው የምናደርግላቸውን ቸርነት በመቀነስ ነው:: እግዚአብሔር ግን ቸርነቱን በማብዛት የኃጢአተኞችን ልብ ለንስሐ ያለዝባል:: ይህ ገብቶት ፈጥኖ የተመለሰ ምሕረቱ ይበዛለታል:: ይህ ሳይገባው ግን በኃጢአቱ የገፋበት ሰው ፍርዱ ታላቅ ነው:: ስለዚህ ኃጢአት ሠርተን ቸርነት ሲበዛልን ፈጥነን ንስሐ ካልገባን መፍራት አለብን:: ለዚህ ነው:- *«ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን?»* (ሮሜ. 2:4) የሚለው:: /«ጸሎት» ገጽ 126/::

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የማይቆጠሩ የመመለስ ዕድሎችን ይሰጣል:: በዕድሜአችን ላይ እያንዳንዱ ቀን ሲታደስልን እግዚአብሔር ገና በእኛ ላይ ተስፋ አለመቍረጡን ያስረዳል:: ከብዙ አደጋዎች አምልጠን፣ ከሞት ተርፈን መኖራችን፣ ችግርና በሽታችን ሳያሳልፈን አልፎልን መቆማችን፣ ከሳሾቻችንንና አሳዳጆቻችንን በዝተው በፈንጂ ወረዳ ውስጥ በሰላም ማለፋችን አስደናቂ ነገር ነው:: ይህ የጥንካሬአችን ወይም የብልሃታችን ውጤት ሳይሆን የትዕግሥቱ ፍሬ ነው:: ዕድሜያችን ስላስደሰትነው እግዚአብሔር የሸለመን ሳይሆን ተጨማሪ ዕድል ነው:: ከዕድሎች ሁሉ ዕድሜን የሚያህል ዕድል የለም::


www.ethiopinorthodox.org

በዓለም ላይ ብዙ ዕድሎች አሉ:: ዕድሎቹ ግን የፈለገ ሁሉ የሚያገኛቸው ሳይሆኑ ፈልገው ጥቂቶችን የሚጠቅሙ ናቸው:: ዕድል ሆኖ የፈለገ ሁሉ የሚያገኘው የእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ ነው:: ዕድል የጊዜ ወሰን፣ የመስፈርት ዝርዝር ያለውና ካለፈ የማይገኝ ነው:: ዕድሚያችን ወደ መንግሥቱ ለመግባት የተከፈተልን በር ነው:: የዚህ ዓለም ኑሮአችንን ፈጽመን በሞት ከተጠራን ዕድሉ ያበቃል:: መስፈርቱ ፍጹም ኃጢአተኛ መሆናችንንና ክርስቶስ ፍጹም አዳኝ እንደሆነ ማመን ብቻ ነው:: ታዲያ ሞትን የሚያህል በመንገድ የሚያስቀር ነገር ይዘን ያለ ዋስትና መንቀሳቀሳችን ትልቅ ድፍረት ነው:: እግዚአብሔር ከመንግሥቱ አልለየንም:: ስለዚህ ሁላችንንም ጠርቶናል:: ከመንግሥቱ ራሳችንን የለየን ግን እኛ ነን:: ዕድል የሚፈልገን ሳይሆን እውነተኛ ዕድል የምንመርጠው ነው:: ጌታችን:- *«ማርያምም መልካም ዕድልን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም»* እንዳለ (ሉቃ. 10:42)::

በሌላ ስፍራ ላይ ጌታችን:- *«ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል፤ ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች»* (ዮሐ. 9:4) ብሏል:: ጌታችን «ቀን» ያለው ዕድልን ነው:: ምቹ በሆነ ጊዜ ሳንሠራ በማይመች ጊዜ መሥራት እንዴት እንችላለን? ዛሬ ዕድል ናት:: ዛሬ በእጃችን ናት:: እግዚአብሔር በሰው ልጅ ላይ በሩን አልዘጋም፣ እስክንገባ እየጠበቀን ነው:: እናት ልጇ ካልገባ በሯን አጠንክራ መዝጋት፣ ተረጋግቶ መተኛት እንደማይሆንላት ዘላለማዊ አባታችን እግዚአብሔርም ሕይወት እያለን አማራጭ እንደሌለው መሞታችን እያሳዘነው ይጠብቀናል:: የትዕግሥቱ ምሥጢር ይህ ነው:: የግጉያ ዕቅድ ይዘን ስንጓዝ በሰላም ደርሰን የምንመጣው፣ ለዝሙት ሺህ ኪሎ ሜትር ስንጓዝ እንቅፋት የማይነካን ... እግዚአብሔር ለመዳን ቀን አስቦን ነው:: ግን የትዕግሥቱ ምሥጢር ገብቶናል?

## እናስተውል

አንድ አባት:- «ሰው እየደጋገመ የሚሠራውና የሚያደርገው ስህተት እየቆየና እያደረ ልማድና ሕግ ይሆናል:: ሌላው ቀርቶ ሐሰትም ቢሆን ስርቆት እያደር ለሰው ልጅ ልማድ ይሆንበታል:: ስለዚህ ክፉ ለመናገር ክፉ ለማድረግ ክፋትንም ለማሰብ ልማድ ሳይሆንብን ተጠንቅቀን እናሸንፈው፤ ደግሞ ክፉ ልማድ እንደ ተክል ያለ ነው፤ እየቆየ ረጅም ሥር ሲሰድ አይነቀልም:: በነፍሳችንና በሐሳባችን ወይም በሰውነታችን ሥር እየሰደደ የበረታ እንደሆነ አይነቀልም:: አስቀድሞ ሥር ሳይሰድ በጎ ልማድ በሆነው ምሳር ቆርጦ መጣል ይሻላል» ብለዋል::



ባለጌ እግዚአብሔር ሲታገሠው ኃጢአቱን ያጸደቀለት ይመስለዋል:: «ኃጢአት ሲለመድ ጽድቅ ይመስላል» እንዲሉ:: የኃጢአት ትልቁ ድንዛዜ ቅጣት ካልመጣ የሚሰማን የትክክለኛነት ስሜት ነው:: ኅሊና ዝም አይልም ይባላል:: እውነት ነው:: ነገር ግን ኃጢአት ሲበዛ ኅሊናም ይሞታል:: ስለዚህ ጸጸት አይኖርም:: አካሉ የበደነበት ሰው ቢደበድቡት አይሰማም:: ሲመታ ሕመም ከተሰማው ወደ መዳን እየመጣ መሆኑ ይታወቃል:: ድሮ በኃጢአቱ የማይጸጸት ሰው አሁን ማዘን ሲጀምር ወደ መዳን ክልል እየገባ መሆኑን እንረዳለን:: እግዚአብሔር ዝም የሚለን በሥራችን ተስማምቶ አይደለም:: ጠንቋይ እየቀለብን በምንሠራለት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንም ተደልሎ፣ እያመነዘርን ቀሳውስትን በመቀለባችን «ይቅር በቃ» ብሎ አይደለም:: የምንሠራውን አውቀን ንስሐ እስክንገባ ነው:: ቃሉ:- *«አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም:: ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤ በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና»* (ገላ. 6:7) ይላል:: መልካም ሥራም ሆነ ክፉ ሥራ ዘር ነው:: ዘር በአንድ ዘመን ይዘራል፣ በአንድ ዘመን ይታጨዳል:: ዘር በግድ የአጨዳ ወቅት አለው::

እግዚአብሔርን ለመከተል ብዙ ምክንያት እያለን ላለመከተላችን ብዙ ምክንያት እንጠቅሳለንና እናሳዝናለን:: ምክንያትን የሚወልድ የቅጣት ፍርሃት ነው:: እግዚአብሔር ግን የጠራን ሊምረን ነውና ምክንያት ማብዛት ተገቢ አይደለም:: ከምክንያታችን አንዱ ያለሁበት አካባቢ ለአምልኮት ምቹ አይደለም የሚል ነው:: በማያምኑ መካከል ግን ኖኅ አማኒ ሆኖ ተገኝቷልና ምክንያታችን ከንቱ ነው:: ያለሁበት አካባቢ ጥሩ አይደለምና እግዚአብሔርን መከተል አልችልም እንላለን:: ዳዊት ግን በሲኦልም አንተ አለህ (መዝ. 138/139/:7-8) በማለት ለእግዚአብሔር ተናግሯል:: እግዚአብሔርን ለመከተል ግድ ገዳም መግባት አያስፈልግም:: ለሚያምን ልብ ሁሉ ምቹ ነው:: ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ ይጸልይ ነበር፣ በዚህም ዳነ (ዮና. 2:2):: ኖኅ በማያምኑ መካከል የእምነት ሰው ነበረ፣ ሎጥም በኃጢአተኞች መካከል ጻድቅ ነበረ (ዕብ. 11:7፣ 2ጴጥ. 2:7):: ከአካባቢው በላይ የሰው ፈታኙ ወላዋይነቱ ነው:: ጌታችን ስለ ደቀ መዛሙርቱ:- *«ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም»* (ዮሐ. 17:15) ብሏል:: እውነተኛው ምናኔ ከዓለም መውጣት ሳይሆን ዓለምን ከልብ ውስጥ ማስወጣት ነውና:: ምናኔ የልብ እንጂ የመልክአ ምድር አይደለም:: ገዳሙም በዓለም ክልል በመንግሥት አስተዳደር ሥር ያለ እንጂ የተለየ አፈር አይደለም:: ለዚህ ነው አባቶች:- «ትልቁ ምናኔ በዓለም ሆኖ ዓለምን መመነን ነው» የሚሉት:: ከክፋት ሳይወጡ ከዓለም ወጣን የሚሉትን የጌታችን



www.ethiopinorthodox.org

*ጸሎት ያስፈልጋቸዋል፡- «ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም።»*

የበሽታ መድኃኒት የያዙ (ያውም ብዙ ጊዜ ፈውስ የሌለው) ሄደን ቢረዱን እንኳ ደስታችን ታላቅ ነው። የሞት መድኃኒት የሆነው ክርስቶስ ግን በደጃፋችን ቆሞ ሲያንኳኳ አለመክፈታችን ያሳዝናል። እርሱ ቤቴ ነው ብሎ ጥሶ አይገባም። አስፈቅዶ የሚያድን የነጻነት አምላክ ነውና ያስፈቅደናል። ልባችንን ለብዙ ነገር ስንከፍት የኖርን ብዙ ክፉ ገገር የተጫወተብን ሳለን አክብሮ ለሚገዛው ጌታ ዛሬም ዝግ መሆናችን ያሳዝናል። እንመለስ! ፀሐይ ዕድሜአችን ሳትጠልቅ ንስሐ እንግባ። ከሞት በኋላ ክፉም ሆነ ደግ የመሥራት ዕድል የለምና። ከሞት በኋላ ያለው የሥራችን ፍሬ ነው። ዋና ከተማዋን ወይም መናገሻ ከተማዋን የተቆጣጠረ ንጉሥ ዳሩ ቢሸፍትበት ቀስ እያለ ያስገብረዋል። ልባችን መናገሻ ከተማ፣ የአካል ክፍሎቻችን የአውራጃ ከተሞች ናቸው። በዋናው ከተማ በልባችን ላይ ክርስቶስን ካነገሥን ሌሎቹ የአካል ክፍሎቻችን በግድ ለንጉሡ ይገብራሉ። ስለዚህ በልባችን ላይ ንጉሣችንን እንሹመው (መዝ. 2:6)። ባልቻልንበት ነገር አልቻልንም እንበለው። የክርስትናችን መሥራች ክርስቶስ እርቃኑን መሰቀሉ ክርስትና ግልጽነት መሆኑን ያስረዳናል። የትዕግሥቱ ምሥጢር ይህ ነው።

## ጸሎት

የማለዳው ድምቀት፣ የቀኑ ውበት፣ ብርሃን ክርስቶስ አመሰግንሃለሁ። እኔን ፍለጋ ከገነት ጫካ እስከ ከብቶች በረት፣ ከከብቶች በረት እስከ ግብፅ በረሃ፣ ከግብፅ በረሃ እስከ ገዳመ ቆሮንቶስ፣ ከገዳመ ቆሮንቶስ እስከ ባሕረ ዮርዳኖስ፣ ከባሕረ ዮርዳኖስ እስከ ሊቶስጥራ፣ ከሊቶስጥራ እስከ ቀራንዮ፣ ከቀራንዮ እስከ ተዘጋው ደጃፌ፣ ከልጅነት እስከ እውቀት፣ ከማኅፀን እስከ ዛሬ የተንከራተትክ ፈላጊ ጌታዬ አሁን እጄን ሰጠሁህ በፍቅርህ ማርከኝ። ዓለም ከምታከብረኝ በቤትህ ተጥዬ ልኑር። ያላንተ ወርቅ ከምደርብ ከመስቀልህ ሥር እርቃኔን ልቀመጥ። የንስሐን መንፈስ አድለኝ። ያላንተ እንደማይሆንልኝ፣ እንኳን መራራው ጣፋጩ እንደማይጥመኝ ታውቃለህ። ወዳጅ ቢኖረኝ አንተ ሰጥተኸኝ፣ ገንዘብ ቢኖረኝ አንተ ባርከኸኝ ነው። ሁሉ ስላንተ ይወደዳሉ፤ አንተ ግን ስለራስህ ትወደዳለህ። አሁንም በፍቅርህ ስበህ ያንተ አድርገኝ። ለኃጢአት አቅመ-ቢስ ለጽድቅ ጠንካራ አድርገኝ። በሚለውጠው ፍቅርህ ለዘላለሙ አሜን!





# ምዕራፍ አራት

## ባሕርዩ ነው

እግር የሌለው አንድ ሰው እጅግ ያማረ ለምለም መስክ አይቶ ቍጭ አለና፡- «አይ ይሄ መስክ በእግር ቢያቋርጡት እንዴት መልካም ነበር?» አለ። እግረኛው ደግሞ መጣና፡- «አይ ይሄ መስክ በፈረስ ቢያቋርጡት እንዴት መልካም ነበር?» አለ። ይህን ያዳመጠው አካለ ጎዶሎ፡- «አይ አንተ እግዚአብሔር ማን ነው? የሚያመሰግንህ» አለ ይባላል።

ዛሬ እግዚአብሔር የተደነቀ ምስጋና እያገኘ ያለው ከጤነኞች ሳይሆን ከበሽተኞች ነው። ጤነኞች ሲያማርሩት የሚያልፋቸው በትዕግሥቱ ነው። በሕይወቴ ሁለት በሽተኛ የነበሩ እናቶችን አልረሳቸውም። አንደኛዋ እናት የአእምሮ በሽተኛ ናቸው። ሲያማቸው ቤታቸውንና የሚኖሩበትን ከተማ ለቀው የት እንደሚሄዱ ሳያውቁ ይባዝናሉ። ጤነኛ ሲሆኑ ደግሞ እንደ እርሳቸው መልካም ሰው የለም። ታዲያ ተሽሎአቸው አንድ ቀን ተገናኘንና «እንደምን አሉ? ጤናዎ ደህና ነው ወይ?» ስላቸው፡- «ሰማህ ልጄ አልጋ የሚችለው በሽታ ጸጋ ነው። የእኔን በሽታ አልጋ አይችለውም። ግን እስካሁን የጠበቀኝ ጌታ የተመሰገነ ይሁን!» አሉኝ። ሌላኛዋ እናት ደግሞ መላ አካላቸው መንቀሳቀስ የማይችል ሆኖ በአልጋ ቀርተዋል። «ለጤናዎ እንደምን አሉ?» ብላቸው፡- «እግዚአብሔር ይመስገን ለእኔ የሰጠውን ለማን ሰጥቶ! ሰው የሚሸሸው በሽታ አልሰጠኝም። ይኸው ቀርበህ ሳምከኝ። ምን ጐደለብኝ? አመስግኑልኝ» አሉኝ።

በእነዚህ እናቶች ቃል ዘወትር መነካት ብቻ ሳይሆን ራሴን እየመዘንኩ ቀላልነቴን አይበታለሁ። እነዚህ እናቶች እግዚአብሔር ከሰጣቸው መልካም ሳይሆን ክፉ ከሚባለው እንኳ መልካም እየፈለጉ የሚያመሰግኑ ናቸው። መልካሙንማ እንዴት ይገልጹት ይሆን? አስተውለን ስናየው ከመከራም መከራ ይመረጣል። እኛ ግን ሙሉ ጤንነት ሰጥቶን ገንዘብ አጣሁ ብለን እናማርራለን። ጤንነት ገንዘብን ሊያመጣ ይችላል። ገንዘብ ግን ጤንነትን ማምጣት እንደማይችል አልተገነዘብንም። አንድ ሰው፡- «ሰዎች ገንዘብ ለማግኘት ያለ ዕረፍት ይሮጣሉ። በብዙ ድካም ውስጥ ገንዘብ ሲያገኙ ጤንነታቸውን ያጣሉ። በገንዘባቸው ግን ጤንነታቸውን መመለስ ይቸገራሉ» ብሏል። አዎ ገንዘብ ጤናን አይገዛም። ጤናን የሚያህል ሹመት



www.ethiopinorthodox.org

የለምና ሥልጣን አጣሁ ብለን ስናለቅስ መታመማችንን እንወቀው! አንድ ወንድሜ «እንደምን አለህ?» ብለው፡- «ዕድሜን ያህል ጸጋ፣ ጤናን ያህል ሸማ ያለበሰኝ ጌታ ይመስገን» ብሎኛል፡፡ እነዚህ እናቶችም የእግዚአብሔርን ሥራውን እየቆጠሩ ያመሰግኑታል፡፡ ለምስጋና ከሚረዱን ነገሮች አንዱ ሥራውን መቍጠር ነው፡፡ እግዚአብሔርን ስለዚህ ቀን አየር እንኳ ማመስገን ይገባናል፡፡ የሚያጣጥሩ በሽተኞች አየር ተገጥሞላቸው ሲተነፍሱ አይተናል፡፡ ለእያንዳንዱ ትንፋሽ ይከፈላል፡፡ በነጻ የምንስበውን አየር ግን አናመሰግንበትም፡፡ ቢያንስ ዛሬ የአየር ወጪ የለብንም፡፡ ስናጣው ግን ሁሉም ነገር ዋጋ ያስከፍላል፡፡ ያውም ያለ ምቾት! ያውም ተመልሶ እንደ ጥንቱ ላይሆን!

«ከዚህ የባሰ ምን ይመጣል?» እንላለን፡፡ ብዙ ያላየ ሰው ንግግር ያበዛልና፡፡ አባቶች፡- «ኢታንክር ዘንተ ዘይብእስ ሀሎ - የባሰ አለና አታድንቅ» ይላሉ፡፡ ተጣብቀው የተወለዱ ሁለት ሰዎች ነበሩ ይባላል፡፡ እየተጓተቱ ሲኖሩ አንደኛው፡- «ተመስገን ጌታዬ! ከዚህ የባሰ አታምጣ» እያለ ያመሰግናል፡፡ ሁለተኛው ግን፡- «ከዚህ የባሰ ምን ይመጣል?» እያለ ያማርራል፡፡ ቆይቶ አመስጋኙ ሞተ፡፡ የሚያማርረው ግን የሞተውን አካል ተሸክሞ መዳከር ሲጀምር፡- «ለካ ይባስ አያልቅም ተመስገን ጌታዬ!» አለ ይባላል፡፡ የአገራችን ገጣሚም፡-

*ተመስገን ይለዋል ሰው ባያሌው ታም፣*
*ያማረሩት እንደሁ ይጨምራል ደም፤*

ያለው ለዚህ ነው፡፡ ያደረገልንን ሳይሆን አደረገብኝ የምንለውን መናገር እንወዳለን፡፡ ስላደረገልን ምስጋና ብንጀምር ግን ቀኑ ይመሻል፡፡ ከቍጥር ብዙ ነውና፡-

*«ውለታው ብዙ የእግዚአብሔር፣*
*አመስጋኝማ ቢኖር፤»*

እንደ ተባለ፡፡

ጤና ያላቸው ጤና ከሌላቸው እኩል ሲያማርሩ እግዚአብሔር ይታገሣቸዋል፡፡ ዛሬ ባለጠጎች የድሆችን ያህል ይማረራሉ፡፡ ይበሳጫሉ፡፡ ይህ እግዚአብሔርን ያሳዝነዋል፡፡ «ደሃ ምን አለበት?» ይላሉ፡፡ በድሆች ይቀናሉ፡፡ ድህነት ግን ገና በአሳባቸው ሲመጣ ሞትን ይመርጣሉ፡፡ ያ አካለ ጎዶሎ፡- «አይ አንተ እግዚአብሔር ማን ነው? የሚያመሰግንህ?» ያለው እውነት ነው፡፡



ይህን ጹሑፍ ስጽፍ መቆምና መቀመጥ እያቃተኝ ተንቆራጥጫለሁ፡፡ የእግዚአብሔር ትዕግሥት ዓለምን ሳይሆን እኔን እንዴት እንደ ቻለኝ ሳስብ መደነቅ ሞልቶብኛል፡፡ ትዕግሥቱ ልምምድ ቢሆን በጠፋን ነበር፡፡ ትዕግሥቱ ባሕርዩ ስለሆነ ግን ይኸው አለን፡፡ በዓለም ላይ ያለውን ኃጢአት በአካል ባንሠራው በአሳብ ያልሠራነው ምን አለ? የሌላው መገለጡ የእኛ መሠወሩ ካልሆነ በቀር ንጹሕ ማን አለ?

እንደ እውነቱ ከሆነ ይቅርታ ሰጪ ተለማኝ፣ ይቅርታ ጠያቂ ያውም ድንጋይ ተሸክሞ ለማኝ ነበር መሆን የነበረበት፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ግን የሚታየው በተቃራኒው ነው፡፡ በደለኛው የሰው ልጅ «የበዳይ አኩራፊ» ሆኖ ይለመናል፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ይለምናል፡፡ ሰው የጣለውን እግዚአብሔር ያነሣል፡፡ ዋጋ የለውም ለተባለው ዋጋ ይሆነዋል፡፡ ተስፋ የተቆረጠበትን ተስፋ ያለው ያደርገዋል፡፡ ይህን ሁሉ የሚያደርገው በትዕግሥቱ ነው፡፡ በሽተኛ ምግብ ለመብላት ይነጫነጫል፣ ብላ ያለውንም ሰው ይጣላል፡፡ አስታማሚውም እንደ ሕፃን ያባብለዋል፡፡ የበሽተኛው ምላሽ ግን ቀና አይደለም፡፡ የእኛ የመንፈስ በሽተኞች አስታማሚ የሆነው እግዚአብሔር ያባብለናል፡፡ ሲገባን እንደምንለምነው አውቆ ዛሬ ይለምነናል፡፡ እርሱ እንደ ሰው ቢሆን ኖሮ ምን ውስጥ እንገባ ነበር? እግዚአብሔር ግን እግዚአብሔር ነው፡፡ ትዕግሥቱም ሰፊ ነው፡፡

በአንድ ወቅት የማስተምራቸው የነበሩ ወገኖቼ በአንዳንድ በመካከላቸው በነበሩ ጥቂት ሰዎች ክፉ ስሜት ማስተማር እንደማልችል ነገሩኝ፡፡ እኔም ሌሎች አገልግሎቶች ይዘውኝ ስለነበር ለጊዜው አዝኜ ተውኳቸው፡፡ ኋላ ግን ተጸጸቱ፡፡ እኔም መርሳቴን እንደ ይቅርታ ቆጥሬ ተውኳቸው፡፡ የረሳሁት ግን ቂሙን ሳይሆን ህልውናቸውን ነበር፡፡ ይህ ደግሞ አደገኛ ነገር ነበር፡፡ ታዲያ በጉዳዩ አንድ አባት ገብተው ስለ ሁኔታው ጠየቁኝ፡፡ እኔም «እምቢ አሉ እኔም ትቻለሁ» አልኩኝ፡፡ እኝህ አባት ግን፡- «ልጅህ ምግብ ቢያስጠላው ትተወዋለህ ወይስ ሐኪም ቤት ትወስደዋለህ?» ካሉኝ በኋላ፡- «ልጅህ ምግብ ቢያስጠላው ሐኪም ቤት ይዘኸው ትሄዳለህ እንጂ እምቢ ብሏል ብለህ አትተወውም፡፡ እነዚህም ልጆች ትምህርት ቢያስጠላቸው ሐኪሙ እግዚአብሐር ዘንድ በጸሎት ታቀርባቸዋለህ እንጂ እንዴት ዝም ብለህ ትተዋቸዋለህ?» አሉኝ፡፡ ክርስትና እስከዚህ መሆኑን አስተማሩኝ፡፡ እግዚአብሔርም ቃሉን ገሸሽ ስንል፣ ከጸጋው ስንርቅ የሚከተለን እንደ መንፈስ በሽተኛ ስለራራልን ነው፡፡



www.ethiopinorthodox.org

የእግዚአብሔርን ትዕግሥት ስናነሣ ሁለት ነገሮችን እናያለን:- የመጀመሪያው:- ትዕግሥት ባሕርዩ መሆኑን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከኃይል ባሕርዩ አንዱ ትዕግሥቱ መሆኑን ነው::

## ባሕርዩ ነው

ባሕርይ የሚለውን ቃል ለሰው ጠባይ መግለጫ ስለምንጠቀምበት አመል የሚል ትርጉም ይሰጠናል:: ባሕርይ ግን ለመለኮት የሚነገር ተለዋዋጭ ጠባይን ሳይሆን ቋሚ መገለጫን የሚያሳይ ነው:: ባሕርይ መሠረት፣ የማይለወጥ መገለጫም ነው:: ለምሳሌ:- የድንጋይ ባሕርይ ጠጣር፣ የውኃ ባሕርይ ፈሳሽ ነው:: ድንጋይ ያለ ጠጣርነቱ ድንጋይ የተባለበት፣ ያለ ጠጣርነቱም ድንጋይ ተብሎ የኖረበት ዘመን የለውም:: የእግዚአብሔርንም ባሕርይ ስናነሣ ባሕርዩ ከአካሉ ጋር በዘላለማዊነት የነበረና የሚኖር ነው:: ባሕርዩ ልምምድ ሳይሆን ባሕርዩ የእግዚአብሔርነቱ መገለጫ ከመለኮታዊ አካላቱ ጋር እንደ ስሙ አብሮ የኖረ፣ የሚኖርም ነው::

እግዚአብሔር ዘላለማውያን የሚሆኑ ባሕርያት አሉት:: ከእነዚህ ባሕርያቱ አንዱ ትዕግሥቱ ነው:: የእግዚአብሔር ትዕግሥት ከፍቅሩ ውስጥ የሚወጣ ነው:: *«ፍቅር ይታገሣልና»* (1ቆሮ. 13:4)::

ዓለሙ በረሃ ነው:: የሚታይ ለምለም፣ የሚሰማ በጎ ነገር የለውም:: የመርዶ ዓለም፣ የትላንት ጉድ በዛሬ ጉድ የሚረሳበት ዓለም ነው:: በረሃነቱ ያቃጥላል:: ስለዚህ ያስመርራል:: ያስጠማል ስለዚህ ያቅበዘብዛል:: ያስጨንቃል ስለዚህ ዕረፍት ይነሣል:: ያባዝናል ስለዚህ መድረሻ ያሳጣል:: እንደ በረሃ በሚያቃጥለው ዓለም ግን የሰው ልጅ የኑሮ ጥላ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ ቸርነት፣ ምሕረት፣ ይቅርታና ትዕግሥት ናቸው:: እነዚህ ባሕርያት የእርሱ መገለጫ ብቻ ሳይሆኑ የእኛም ጸጋ ናቸው:: በጠራራ ፀሐይ ስንሄድ ሁላችንም የራሳችን ጥላ አለን:: ነገር ግን ጥላ ፍለጋ እንሮጣለን:: ለምን በራሳችን ጥላ አናርፍም? ስንል የራስ ጥላ ስለማያሳርፍ ነው:: እንዲሁም የራሳችን መልካምነት ሳይሆን የሚያሳርፈን የእግዚአብሔር መልካነት ነው:: ከመልካምነቱ አንዱ ትዕግሥቱ ነው::

ስለ እግዚአብሔር ትዕግሥት ቅዱስ መጽሐፍ:- *«እግዚአብሔር፥ እግዚአብሔር መሐሪ፥ ሞገስ ያለው፥ ታጋሽም፥ ባለብዙ ቸርነትና እውነት፥ እስከ ሺህ ትውልድም ቸርነትን*



www.ethiopinorthodox.org



*የሚጠብቅ፥ አበሳንና መተላለፍን ኃጢአትንም ይቅር የሚል፥ በደለኛውንም ከቶ የማያነጻ፥ የአባቶችንም ኃጢአት በልጆች እስከ ሦስትና እስከ አራት ትውልድም በልጅ ልጆች የሚያመጣ አምላክ ነው»* በማለት ይገልጸዋል (ዘፀ. 34:6-7):: ይህ ራሱ እግዚአብሔር ያወጀው አዋጅ ነው:: ወደ ዘጠኝ የሚጠጉ የእግዚአብሔር ባሕርያት ተጠቅሰዋል:: ባሕርያቱ:-

1. መሐሪ (በደልን የሚተው)፣
2. ሞገስ ያለው (ተወዳጅ)፣
3. ታጋሽ (በፍጥረቱ ተስፋ የማይቆርጥ)፣
4. ባለብዙ ቸርነት (ሰጥቶ የማያልቅበት)፣
5. ባለብዙ እውነት (የሕይወት መምህር)፣
6. ቃል ኪዳን አክባሪ (ታማኝ)፣
7. ይቅር ባይ (የእንደገና አምላክ)፣
8. በደለኛውን ንጹሕ ነህ የማይል (የቅን ፈራጅ)፣
9. እስከ ሦስትና እስከ አራት ትውልድ የሚቀጣ (መዓቱ የራቀ፤ ምሕረቱ የበዛ፤ ምክንያቱም በረከቱ እስከ ሺህ ትውልድ ነውና) በመባል ተጠቅሰዋል::

ባሕርያቱ ከንስሐ ለሚዘገዩ ታጋሽነት፣ ለሚመለሱ ምሕረት፣ ለሚያምፁ ቅጣትን እንደሚሰጥ ያመለክታሉ:: ዳግመኛም ነቢዩ ዳዊት:- *«አቤቱ፥ አንተ ግን መሐሪና ርኅሩኅ አምላክ ነህ፤ መዓትህ የራቀ ምሕረትህም እውነትህም የበዛ፤»* በማለት ያወድሰዋል (መዝ. 85(86):15):: እግዚአብሔር ባለጠጋ የተባለው በመዓቱ ሳይሆን በምሕረቱ ነው:: በነቢዩ በናሆምም:- *«እግዚአብሔር ትዕግሥተኛ፥ ኃይሉም ታላቅ ነው፥ በደለኛውንም ንጹሕ ነህ አይልም፤ እግዚአብሔር በወጀብና በዐውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው፥ ደመናም የእግሩ ትቢያ ነው»* (ናሆም. 1:3) ተብሎለታል:: ብዙ ኃያላን ይቸግራቸው የነበረው ትዕግሥት ነው:: ከመጣል በላይ መታገሥ ኃይል ይጠይቃል:: ብዙዎችን የገዙ ኃያላን በትዕግሥት ማጣት ግን ራሳቸውን መግዛት እንዳቃታቸው በታሪክ መስተዋት ይታያል:: የእግዚአብሔር ትዕግሥቱ ግን ከኃይሉ ውስጥ ይመደባል:: እውነተኛ ታላቅነትም ትዕግሥት በመሆኑ በትዕግሥቱ ታላቅነቱ ሲተረክ ይኖራል:: ነገሥታት ሁሉ በጦርነት ቀጠና ውስጥ ለቱሪስቶች ዋስትና መስጠት አይችሉም:: እግዚአብሔር ግን *«በወጀብና በዐውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው»* እኛንም ለመርዳት ሲመጣ የእግር ፈለግን አይከተልም:: ባሕር ተራምዶ ደመናን ጠቅሶ ይመጣል:: ለእርሱ ሁሉ መንገዱ ነው:: *«ደመናም የእግሩ ትቢያ ነው»* (ናሆም. 1:3)::

በትዕግሥቱ ውስጥ ያለው ምሥጢር አለመቻል፣ እያረሩ መቀመጥ፣ ቸልተኝነት ወይም ስንፍና አይደለም። በትዕግሥቱ ውስጥ ያለው ምሥጢር ደካሞችን ይነሣሉ ብሎ ተስፋ ማድረግ፣ እንዲለወጡም ጊዜ መስጠት ነው። የእግዚአብሔር ትዕግሥት የመኖራችን ምሥጢር፣ የማይጠቀመው ሰው ለጥቅም የሚሠራበት ሰፊ ዕድል ነው። ሁሉን በጊዜው ውብ አድርጎ የሚሠራበት ዕቅዱ ነው። ሰነፍ ሰው ግን እግዚአብሔር ሲታገሠው ኃጢአቱን ያጸደቀለት ይመስለዋል። ሲራክ፡- *«እግዚአብሔር ብዙ ዘመን ይታገሣልና ኃጢአት ሠርቼ ፍዳ አልተቀበልሁም አትበል። ስለ ኃጢአትህ ንስሓ መግባትን አትፍራ የእግዚአብሔር ቸርነቱ ብዙ ነው እያልክ በኃጢአት ላይ ኃጢአት አትሥራ»* ብሏል።

ልመናው ስለዘገየበት በእምነት የዛለው ምእመንም እግዚአብሔር ረስቶኛል በማለት ቅያሜውን ይገልፃል። አንድ አባት፡- «ለእግዚአብሔር የዘመናት ርዝማኔ ጸሎታችንን አያስረሳውም። አዳምና ሔዋንን ከ5500 ዘመን በኋላ አስታወሰ። መፃጉን ከ38 ዓመት በኋላ አስታወሰው። ስለዚህ እኛም እግዚአብሔር ረስቶናል፣ ጸሎታችንን አይሰማም አንበል። በተስፋ እንጠብቅ» ብለዋል። የትዕግሥትን ምሥጢር ዘንግቶ በዚህ ዓለም ላይ በኃይሉ ለመኖር የሚያስበው ወገንም ሲደክመው መታገሥ ይጀምራል። አንድ ደራሲ፡- «ታላላቅ ተግባራት የሚከናወኑት በጉልበት ሳይሆን በትዕግሥት ብቻ ነው» ብሏል።

## <u>የኃይሉ ባሕርይ</u>

እግዚአብሔር ባለጸጋ የተባለው በምሕረቱ እንጂ በመዓቱ አይደለም ብለናል። ይልቁንም በአዲስ ኪዳን ዘመን ሲታወቅበት የፈለገው ባሕርዩ ፍቅር ነው። ዘመኑም ዓመተ ምሕረት የተባለው በክርስቶስ በኩል ከገለጠው ትልቅ ፍቅር የተነሣ ጸጋ ስለበዛልን ነው (ሉቃ. 4:17-19)። የእግዚአብሔር ባሕርያት፡- የኃይል ባሕርያት፣ የጥበብና የጽድቅ ባሕርያት በመባል በሦስት ይከፈላሉ። የኃይል ባሕርያት የሚባሉት፡- ፍቅር፣ መንፈስነት፣ ሁሉን ቻይነት ... ናቸው። በፍቅር ባሕርያት ውስጥ፡- ራሱ ፍቅር፣ ይቅርታ፣ ቸርነት፣ ምሕረት፣ ትዕግሥት ይዘረዘራሉ። የእግዚአብሔር ትዕግሥት ከፍቅር ይመነጫል። የእግዚአብሔር ትዕግሥት የኃይሉ መገለጫ ነው። ትልቁ ኃይል ማጥፋት ሳይሆን መቻል ነውና።

አካል ያላቸው እያማረሩ አካለ ጎደሎዎች ሲያመሰግኑ፣ ድሆች እየዘመሩ ባለጠጎች ሲያዝኑ የእግዚአብሔር ትዕግሥት





ወይም መቻል ሰፊ እንደሆነ ይገባናል። በሽምግልና ዕድሜያቸው ንስሓ ለመግባት አምፀው የሚኖሩትን ሰዎች ስናይ ይህን ሁሉ ዘመን ለሰጣቸው ለእግዚአብሐር ይሉኝታ እንኳ የሌላቸው መሆናቸውን ስናይ ከእነርሱ ዓመጽ በላይ የእርሱ ትዕግሥት ይደንቃል። በደዌ ዳኛ በአልጋ ቊራኛ የተያዙ ሰዎች ለንስሓ ሲጋበዙ ያመነታሉ። የማመንታታቸው ምሥጢር ከበሽታቸው ቢድኑ ዳግም ኃጢአት መሥራት የማይችሉ መሆናቸውን ማሰባቸው ነው። ገና ተነሥተውም የሚያስቡት ለመበደል መሆኑን ስናይ ጌታ ከምድረ ገጽ የሰውን ልጅ አለማጥፋቱ ትዕግሥቱ ይደንቃል። እኛም ቢኖረኝ ይህን አደርጋለሁ እያልን የክፋትና የግፍ ዝርዝር እንናገራለን። ገና ባልኖርንበት ነገ በሚባለው ቀንና በሌለን ነገር በምኞት እንበድላለን። በእውነት እግዚአብሔር ታግሦናል።

የእግዚአብሔር የመታገሥ ምሥጢር ገብቶናል? መታገሡስ ለሕይወታችን ያለው ጥቅም ምንድነው? በእውነት እግዚአብሔርን ስለ ትዕግሥቱ ልናመሰግነው ይገባናል። የምናመሰግነው በገባን ነገር ላይ ነውና ስለ እግዚአብሔር ትዕግሥት መማር ያስፈለገን ለዚህ ነው። የእግዚአብሔር ትዕግሥት ለኑሮአችንና ለሕይወታችን ዋስትና የሆነው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ይታገሣል ስንል በመጀመሪያ ይችለናል ማለት ነው። ዳግመኛም ይጠብቀናል፣ ቀጥሎም አይቸኲልም በመጨረሻም በጊዜው ይሠራል ማለት ነው። ቀጣዮቹ ምዕራፎች እነዚህን ይዘረዝራሉ። የተፈጠርነው ባሕርያቱን እንድንካፈልና ለዓለም እንድናንጸባርቅ ነውና እኛም መሆን የሚገባንን በሰፊው እንማራለን። የእግዚአብሔር ትዕግሥቱ አድራጎቱ ሳይሆን ባሕርዩ ነው። እኛም እንድናደርግ ሳይሆን እንድንሆን መንፈስ ቅዱስ ይረዳናልና ወደ መሆን እንድንመጣ መሻት አለብን።

## <u>እናስተውል</u>

ሰውዬው እግዚአብሐር የኤርትራን ባሕር ከፍሎ ሕዝቡን እንዳሻገረና ፈርዖንንና ሠራዊቱን በኤርትራ ባሕር እንዳሰጠመ ሲሰማ በመደነቅ ታላቅ ምስጋና ጀመረ። እየዘለለ ሲያመሰግን፣ በሚቀጣጠል እልልታ ለእግዚአብሐር ሲቀኝ የሰሙት እምነት የለሾች «የምታመሰግነውና የምትዘለው ዝም ብለህ ነው፣ የኤርትራ ባሕር የሚባለው በዚያን ጊዜ የቦይ ውሃ የሚያህል ነበር። ስለዚህ ዝም ብለህ አትዝለል» አሉት። እርሱ ግን ይህን ሲሰማ ከፊት ይልቅ ምስጋና ጀመረ። እነዚያም ከሃድያን «የነገርንህ አልገባህም ወይ?» አሉት። እርሱም «ገብቶኛል» አላቸው። ታዲያ ለምን ዝም



www.ethiopinorthodox.org

አትልም? ሲሉት በደስታ እየዘለለ:- «በቦይ ውሃ ፈርያንንና ሠራዊቱን ማስጠመ ገርሞኝ ነው» አላቸው ይባላል:: አመስጋኝ ምስጋናው አይቋረጥም:: የሚሰማው ሰውን ሳይሆን መንፈስ ቅዱስን፣ የሚታየው የምድሩ ሳይሆን የሰማዩ ነውና::

ምስጋና ስለፈለግን የምናደርገው ቀላል ነገር ሳይሆን ምስጋና ትግል አለው:: እንዳናመሰግን ጠላት እግዚአብሔርን እንደማይችል፣ ራሱን እንደ ኃይለኛ አድርጎ ያሳየናል:: ታመሃል፣ ተቸግረሃል፣ ሩጎሩጎ ከሚባለው ጌታ ይህን እንዴት ትቀበላለህ? ይለናል:: አንድ መንፈሳዊ አባት:- «ጠላቴ እግዚአብሔር ይህን ይህን ከለከለህ እያለ በችግሮቼ ዝርዝር በአካል የመዋጋት ያህል ተዋጋኝ:: እኔም ይህን ይህን እግዚአብሔር ከልክሎኛልን? ብዬ ዳግም ጠየቅሁት አዎ ብሎ መለሰልኝ:: እንግዲያው እርሱ ከከለከለኝ አንተ አዝነህ ለምን አትሰጠኝም? ስለው በነነ:: ሰይጣን አዝኖ መስጠት አያውቅም እግዚአብሔር ከለከለህ ብሎ ማማት ግን ያውቃል» በማለት ተናግረዋል::

ምስጋና እግዚአብሔር ውለታ ሲውልልን ብቻ ሳይሆን ምስጋና የእግዚአብሔር ስለሆነ ልናመሰግን ይገባናል:: ስላልሆኑ ነገሮች አብዝተን ማመስገን ይገባናል:: በምስጋና ድል አለ:: በምስጋና የተዘጋው ደጅ ይከፈታል:: በምስጋና ደስታና ኃይል ይበዛልናል:: ይልቁንም እግዚአብሔርን ስለ ትዕግሥቱ ልናመሰግነው ይገባናል::

## ጸሎት

ጌታ ሆይ፣ በተራራ ሳመሰግንህ፣ በሸለቆ ሳማርርህ የምኖረውን ልጅህን እጅግ ስለታገሥከኝ አመሰግንሃለሁ:: ዘወትር አንተ ለእኔ መልካም ነህ:: እኔ ግን በክፉ ሥራዬ ዳግም የምቸነክርህ፣ ዳግም የምሰቅልህ ሆኛለሁና ከደፈረሰው ማንነቴ አንተ አድነኝ:: ሰዎች የእኔን ኑሮ እያዩ አንተን ይነቅፋሉ:: እኔ ባንተ እለካለሁ እንጂ አንተ በእኔ መቼ ትለካለህ? ቢሆንም ጌታ ሆይ ለኑሮዬ ሰላም ጽድቅህ ይሻለኛልና ሕይወቴን ለውጥ:: ከአፌ ምሬትን ቆርጠህ ምስጋናን ጨምር:: ውለታህን እንድቆጥር እባክህ እርዳኝ:: ብዙዎችን ወስደህ እኔን ግን እስከ ዛሬ ያቆምከኝ ትዕግሥትህን አስፍተህልኝ ነውና ስምህ ይባረክ:: ከተድላህም ፈሳሽ አጠጣኝ:: ህልውናህ ዘወትር ይሰማኝ:: ከፍታን ዝቅታ፣ ዝቅታን ከፍታ ማድረግ በሚቻለው ሥልጣንህ ለዘላለሙ አሜን!



# ምዕራፍ አምስት

## ይችለናል

በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘመን በሸዋ የተፈጸመ አንድ ታሪክ አለ:: አንድ ባለጠጋ ወሰንተኛው ከሚሆን ደሃ ጎረቤቱ ጋር በመሬት ይጣሉና በጨለማ አድብቶ ይገድለዋል:: ያ ደሃ ሚች ግን ማን እንደ ገደለው ሳይታወቅ ዘመናት አለፉ:: ቤተሰቡም ባለቤቱ እግዚአብሔር ይመራመረው ብለው ለእግዚአብሔር ሰጥተው መኖር ጀመሩ:: ያ ገዳይ ባለጸጋም ሲኖር ሲኖር ይታመማል:: በጠና ታሞ ከወተት በቀር እህል ውሃ አይቀምስም ነበር:: ሕመሙም እየጠና ሲሄድ የንስሓ አባቱን ይጠራና ይናዘዛል:: «ያንን ደሃ ጎረቤቴን በጨለማ አድብቼ የገደልኩ እኔ ነኝ:: እርሱ ዐረፈ እኔ ግን የማይድን የኅሊና ሕመም ገጠመኝ:: አባቴ ይናዙኝ» ብሎ ለቄሱ ይናገራል:: በመቀጠልም «ስሞት ወተት የሚያጠጡኝ እነዚህ ሁለት ላሞች የእርሶ ናቸው» ብሎ ቃል ይሰጣቸዋል:: እርሳቸውም ላሞቹ በቃል ስለተሰጧቸው በጣም ደስ አላቸው::

ሰውዬው ግን ከንስሓው በኋላ ከበሽታው እያገገመ፣ አልጋውን እየለቀቀ፣ ጉልበቱ እየታደሰ፣ ከሥራ ላይ እየዋለ መጣ:: ቄሱም ላሞቹን መቼ ይሰጠኛል? እያሉ ሁልጊዜ ስለ ላሞቹ ቢያስቡ ነገሩ እየተረሳ መጣ:: ባለመሞቱ ተናደው ይህን ሰው ማጋለጥ ኦለብኝ ብለው ተነሡ:: ለሚች ቤተሰብም ሄደው:- «ወንድማችሁን የገደለባችሁን ሰው አግኝቼዋለሁ እንዲሁ ለምን ይቀራል? ተፋረዱ» ይላሉ:: ቤተሰቡም:- «የገደለውን በምን እናውቃለን? ማንን ብለን እንፋረዳለን?» ይሏቸዋል:: ቄሱም:- «የገደለው እገሌ ነው:: እኔ ምስክር እሆናለሁ፣ በእኔ ይሁንባችሁ ክሰሱ» ይላሉ:: «በምን አወቁ?» ቢሏቸው:- «እንዴትና መቼ እንደ ገደለው ለእኔ ተናዞልኛል» ይላሉ:: እነዚያም የሚች ቤተሰቦች እንደ አዲስ አዝነው አልቅሰው፣ ደሙ አይቅር ብለው ክስ ጀመሩ:: ተከሳሽም ቀረበ:: ቄሱም መሰከሩ:: በዚህ ጊዜ ዳኞች በተከሳሽ ላይ የሞት ፍርድ ፈረዱበት::

የሞት ፍርደኛው ግን «ይግባኝ» ጠይቆ ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘንድ ይቀርባል:: ንጉሡም መዝገቡን ሲመረምሩ መስካሪው ቄስ ሆኖ አገኙት:: ቄሱ ደግሞ በዓይኑ እንዳየ አይገልጽም:: ንጉሡም ሁሉንም አስቀርበው ቄሱን ጠየቁ:- «እንዲህ ልትመሰክር የቻልከው እንዴት ነው?» አሉት:: ቄሱም:- «የሠራውን ኃጢአት



www.ethiopinorthodox.org

በሙሉ ለእኔ ተናዞልኛል» አላቸው:: ንጉሡም:- አምኖ የነገረውን ምሥጢሩን ያውም እንዲፈረድበት በሸንጎ በማውጣቱ በቁሱ አዝነው:- «መሬት አፍ አውጥታ መናገር ጀመረች? ቁስ እንዴት የተነገረውን ምሥጢር ይናገራል?» በማለት ከተናገሩ በኋላ ወደ ሟች ቤተሰቦች ዞረው:- «እናንተ ረስታችሁ በእግዚአብሔር ተጽናንታችሁ ኑሮአችሁን መኖር ጀምራችሁ ነበር:: ትኩስ ሀዘን ውስጥ የከተታችሁ ይህ ቁስ ነው:: ስለዚህ የወንድማችሁ ገዳይ እርሱ ነውና ገዳዩ በመፀፀቱ በነጻ ይለቀቃል:: ለእርሱ የተፈረደው የሞት ፍርድ ግን በቁሱ ላይ ይጸናል» ብለው ቁሱን በሞት ቀጡ::

ቀላል ሰው የሰማውን እስኪናገር ምጥ ይይዘዋል:: የእግዚአብሔር ሰው ግን የእግዚአብሔርን ባሕርይ ስለሚካፈል ያየውን ክፉ የማያሳይ፣ የሰማውን ክፉ የማያሰማ፣ መልካሙን እንጂ ክፉውን የማያውጅ፣ የበደለውን ወንድሙን በር ዘግቶ የሚወቅስ፣ ጥቅሙን ሳይሆን ፍቅርን የሚያስብ፣ ጭካኔን ድል ነሥቶ ርኅራኄን ገንዘብ ያደረገ ነው:: ይህን መስፈርት የሚያሟላ የእግዚአብሔር ሰው ያለ ባይመስለን እንኳ እግዚአብሔር ግን አለ:: ዛሬ ለክፋት የጨከኑ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ ለበጎ ነገርም የጨከኑ የእግዚአብሔር ሰዎች አሉ:: ምናልባት በአደባባይ ሳይሆን በእልፍኝ፣ በገዳም ሳይሆን በከተማ ስላሉ እነዚህን ሰዎች ማየት እንቸገር ይሆናል:: የእግዚአብሔር አሳብ ግን መልካም ሰዎችን እንድንፈልግ ብቻ ሳይሆን መልካም ሰው እንድንሆንም ነው::

ንጉሡ ነገርን እየሸፈኑ፣ ነገርን መሸፈን የሚገባቸው ቁሱ ግን ሲያጋልጡ እናያለን:: ሰዎች በሰብእና የሚያደርጉትን እኛ በመንፈሳዊነት ማድረግ ካልቻልን ቆም ብለን ራሳችንን መመርመር ያስፈልገናል:: እግዚአብሔር ግን የሰማውን የማያሰማብን፣ የነገርነውን ምሥጢር የማይዘራብን እውነተኛ አባት ነው:: ዛሬ የሰው ነውር ዜና ተብሎ ብዙ ሺህ ብር ከሚሸጥበት ዘመን ላይ ደርሰናል:: የሚደብቅልን ሰው የምንደብቅለትም ወዳጅ የሌለበት የመካሰስ ዘመን ላይ ነን:: ፍርድ ቤቶችን ያጣበበው የአብያተ ክርስቲያናት ክስ ነው:: በዓለም የሌለ ነውር በእነርሱ መታየቱ በክርስትናው ውስጥ አውሬ እንደ ገባ ምልክት ነው:: በፕሮቴስታንቱ አብያተ ክርስቲያናትም የመገለጥ ጸጋ አለን የሚሉ ሰዎች በአደባባይ ቆመው:- «እንዲህ ያለ ኃጢአት ሠርታችሁ የመጣችሁ ተነሡ» እያሉ የመገለጥ ሳይሆን የማጋለጥ ሥራ ይሠራሉ:: በአደባባይ በመገለጥ ስም የሚነገረው አስከፊ ነውር ምንም የማያውቁ ሕጻናትና የዋሃንን ኃጢአት የሚያለማምድ፣ ልምዱ ያላቸውን ደግሞ ለካ ብቻዬን አይደለሁም ብለው የሚደፍሩበት መሆኑን እነዚህ ነቢያት ነን ባዮች አላስተዋሉትም:: ክፉ ነገር በተወራ ቍጥር





መቀነስ ብቻ ሳይሆን እንደሚበዛ የተረዱ አይመስሉም:: በሰው ኃጢአት ቀሳውስት ከባላጋራ ጋር ይወዳኟሉ፤ ፕሮቴስታንቱ ደግሞ ነቢያት ነን ይላሉ:: እግዚአብሔር ግን ሁላችንን ሸፍኖናል::

ጠቢቡ ሰሎሞን:- *«የእግዚአብሔር ክብር ነገርን መሰወር ነው፤ የነገሥታት ክብር ግን ነገርን መመርመር ነው»* (ምሳ. 25:2) ያለውን ስናስብ ልብ ይነካል:: ነገሥታት ዳኞችም ናቸው:: አዋቂነታቸው የሚለካው ወንጀልንና የወንጀለኛን አካሄድ አውቀው ብይን መስጠት ሲችሉ ነው:: ጠቢቡ ሰሎሞን እስከ ዛሬ ድረስ የሚወደስበት ጥበቡ ነገርን መርምሮ ፍርድ መስጠት መቻሉ ነው (1ነገሥ. 3:16-28):: ነገሥታት ነገርን በመግለጥ ይከበራሉ:: እግዚአብሔር ግን ነገርን በመሰወር ይከብራል:: ኖኅ ሰክሮ በተራቆተ ጊዜ ካም የተባለው ልጁ ወጥቶ አወራ፣ ወንድሞቹ ግን ፊታቸውን ወደ ኋላ አዙረው አባታቸውን ሸፈኑ:: በዚህ ምክንያት እነርሱ ሲባረኩ የአባቱን ሐፍረት መሳቂያ ያደረገው ካም ግን ተረገሚል (ዘፍ. 9:20-27):: የምንባረከው በመሸፋፈን እንጂ በመገላለጥ አይደለም:: ቅዱስ መጽሐፍ:- *«ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና ከሁሉ በፊት እርስ በርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ»* (1ጴጥ. 4:8፣ ምሳ. 10:12፣ ያዕ. 5:20) ይላል:: አንድ ሰው ይህን ሲተረጕም:- «ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናል ማለት ቆሻሻ ጠርጎ እምንጣፉ ሥር ይደብቃል ማለት ሳይሆን ያጸዳል ማለት ነው» ብሏል:: የወዳጃችንን ሐፍረት ከሌሎች እየሰወርን ለመለወጡ ግን ተግተን መምከር አለብን:: ከላይ የተጠቀሰው የቁሱ ታሪክ የዘማሪውን ምስጋና ያስታውሰናል:-

*«አይተህ እንዳላየ ታልፈዋለህ ሁሉን፣*
*መዓቱም ምሕረቱም ሁሉም ያንተ ሲሆን፤*

እኛ ያየነውንም ያላየነውንም እናወራለን:: እግዚአብሔር ግን ከመነሻ እስከ ፍጻሜ ያለውን ታሪክ እያወቀ ዝም ይላል:: አንዳንዴም ሰውዬው ንስሐ የገባበትን በደል ሳይቀር እናወራለን:: ሰይጣን እንኳ በደልን በመመዝገብ ትጋቱ ንስሐ የተገባበትን ኃጢአት ሲጽፍ አይውልም:: እኛ ግን እንዲህ ስናደርግ ከሰይጣን መባሳችንን አንረዳም:: እኛ ምሕረት መስጠት፣ መዓት ማውረድ አንችልም:: ሁላችንም በታላቅ ችሎት ፊት አንድ ቀን እንቆማለን:: እግዚአብሔር ግን መዓቱም ምሕረቱም በእጁ ሆኖ ይታገሠናል:: ዛሬ አብረን እየበላንና እየጠጣን የወዳጃችንን ወንጀል ለአንድ ቀን እናጠራቅማለን:: ይልቁንም ሥልጣን ያላቸውን ሰዎች ለማዋረድ ስንት ፋይል ከፍተን እንሰበስባለን:: አላወቅነውም እንጂ የወንድማችን ውርደት የእኛ ውርደት ነው:: እግዚአብሔር ለሁሉም



www.ethiopinorthodox.org

እንደ ሥራው ይሰጠዋል:: እርሱ ሲፈርድ የእኛን ሰነድና ምስክርነት አይፈልግም:: የሁሉንም ጥፋት ከየግንባሩ ላይ ያነበዋል:: በክርስቶስ ፊት ስንቆም የራሳችን እንጂ የሌሎች በደል አይታየንም::

እግዚአብሔር ቢቀጣን ምክንያታዊ ነው:: ኃጢአተኞች ነንና:: ነገር ግን የመዳን ምክንያት እንዲሆነን ምሕረቱንና የልጁን ደም አቍሞልናል:: ሁላችንም «የአንድ ቀን ሥልጣን ቢኖረኝ» እንላለን:: በአንድ ቀን ሥልጣናችን ያንን ሁሉ ክፉ አሳባችንን ከፈጸምን በዘላለም ሥልጣኑ እኛን የሚያኖረን ጌታ ትዕግሥቱ እንዴት ሰፊ ነው! እግዚአብሔር በሕጉ ሳይሆን በጸጋው ስለሚያስተዳድረን ይኸው «አለን» ለማለት በቅተናል::

እግዚአብሔር ያየብንን ቢያሳይብን፣ የሰማብንን ቢያሰማብን ኖሮ እንደ ሰው እንኳ የማንቆጠር፣ አንድ ቀንም ለማደር የማይፈቀድልን ሰዎች በሆንን ነበር:: የኅሊናችንን ቍልፍ በራሱና በእኛ እጅ ስላደረገው እንኳ ልናመሰግነው ይገባናል:: የምናስበው ሁሉ ቢገለጥ ከማን ጋር እንኖር ነበር? የሚያስቡትን በቀጥታ የሚናገሩ መያዝና መቆጣጠር የማይችሉ በሽተኞች በዓለም ላይ በጥቂቱ አሉ:: እነዚህ ሰዎች ያሰቡትን መቆጣጠር ስለማይችሉ ወዲያው ይናገሩታል:: ሕመማቸው አሳዛኝ እንደሆነ ያያቸው ያውቀዋል:: በዚህ ሕመም ምክንያት ሰው በቀላሉ ስለማይረዳቸው ጠብ ያተርፋሉ:: እነርሱን ስናይ የምናስበውን በሸፈነና፣ ሸፍኖም በገሰጸን ጌታ ፍቅር እንማረካለን::

እግዚአብሔር ብቻ ይችለናል:: የእኛ ነገር የማይገርመው እርሱን ብቻ ነው:: በቅዳሴያችን:- «የሰውን ድካሙን አንተ ታውቀዋለህ» እንደ ተባለለት:: ለእርሱ የነገርነውን ምሥጢር ሌላ ጋ አናገኝበትም:: ራቁትነታችንን በንጹሕ ሸማው (በልጁ ጽድቅ) ሰውሮታል:: ከመቃብር ይልቅ ከባቴ አበሳ ሆኖልናል:: ሰውን ልብሱ፣ ቤቱ፣ ትዳሩ፣ ንስሓ አባቱ ገመናውን ይሸፍኑለት ይሆናል:: ልብስም፣ ትዳርም፣ ንስሓ አባትም የማይዘጉት በደል አለ:: ከእነዚህ በላይ የሚሸፍነው ግን የላይ ጌታ እግዚአብሔር ነው:: ሰዎች የምንናገረውን በማዳመጥ ይወዱናል:: የምናስበውን ግን አያውቁም:: ቢያውቁ ሊጠሉን ይችላሉ:: አውቆ የሚወደን ግን እግዚአብሔር ብቻ ነው:: የቀደሙት አባቶች እንደሚሉት «እርሱ ልብ ያመላለሰውን፣ ኵላሊት ያጤሰውን ያውቃል::» ይህ አምላክ አንድ ዓለማችን፣ አንድ ዓይናችን፣ አንድ ተስፋችን ነውና ተጠንቅቀን ልንይዘው ይገባል:: ከሰው የታጣ በእርሱ ይሞላል:: ከእርሱ የጎደለ ግን በማን ይሞላል? ሰው ቢሸሽን እግዚአብሔር ዘመድ ይሆነናል፤ እግዚአብሔር ቢርቀን ግን ማን ይቀርበናል?





ስለ ጌታችን ደገኛ ክህነት የዕብራውያን ፀሐፊ ሲናገር:- *«እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፥ ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ:: ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም»* (ዕብ. 4:14-15) ይላል:: ያ የብሉይ ኪዳን ካህን በምድራዊቷ መቅደስ በታላቁ መጋረጃ በዓመት አንድ ጊዜ የይቅርታ ደም ይዞ ያልፋል:: ነገር ግን ክህነቱ እርቅ፣ መሥዋዕቱም ደኅንነት ማምጣት አልተቻለውም:: ካህናት ነን ብለው በሚሰለፉት መካከል ትልቅ ሊቀ ካህን የሆነው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ የገዛ ደሙን ይዞ ያለፈው በሰማያዊቷ መቅደስ ነው:: የብሉይ ኪዳን ካህናት አገልግሎታቸው በድካም ወይም በሞት ያበቃል:: ትልቁ ካህናችን ክርስቶስ ግን ሕያው ነውና እርሱን ብቻ እያየን ሃይማኖታችንን መጠበቅ ይገባናል:: እርሱ ሰው ሆኖ የሰውን ድካም ያውቀዋል:: ስለዚህ ይቅርታን ስንለምነው ይራራልናል እንጂ አይጨክንብንም:: የብዙዎች ሽሽት እግዚአብሔር እኔን ይቅር አይልም የሚል ፍርሃት ነው:: እርሱ ግን ስለ ደካሞች ሞቷል:: ሁሉም ሰው ሲነገረው በትዕግሥት የሚሰማው እርሱን የማይነካውን በደል ነው:: በቀጥታ እርሱን የሚነካውን በደል ተቋቍሞ የሚሰማ ግን ማንም የለም:: እግዚአብሔር ግን ይሰማናል:: ይምረናል:: ያለ ቅድመ ሁኔታም ይቀበለናል:: አዎ እግዚአብሔር ይታገሣል ስንል ይችለናል ማለታችን ነው::

ሰዎች ፍቅራችንን ቢችሉት በደላችንን ግን መቻል አይሆንላቸውም:: መስጠታችንን ቢወዱትም ሁልጊዜ ተቀባይ መሆናችንን ግን አይፈልጉትም:: እግዚአብሔር በኃጢአታችንና በፍላጎታችን ይችለናል:: እርሱ እንዳየን ሰዎች ቢያዩን፣ እርሱ እንደ ሰማን ሰዎች ቢሰሙን እንደ እኛ ክፉ ፍጥረት ባልኖረ ነበር:: ኃጢአታችንን በየግንባራችን ላይ ቢጽፈው ኖሮ አንዱ በአንዱ ፊት ለመቆም ድፍረት ባላገኘ ነበር:: እርሱ ግን በደላችንን ከድኖታል:: የሕሊናችንን ቍልፍ በራሱና በእኛ እጅ ስላደረገው ምስጉን ነው:: ሕሊናችን ቢታይ ሰዎች እንደ ሰው የማይቆጥሩንና ከዓለም ላይ በፍርድ የሚያስወግዱን ነበርን:: እርሱ ግን ይወደናል:: ነቢዩ:- *«እንደ ኃጢአታችን አላደረገብንም እንደ በደላችንም አልከፈለንም»* (መዝ. 102:10) እንዳለ::

ከእርሱ ጋር ያለነው በአንድ ዕድል ቢሆን ኖሮ ሰው ለመሆን ባልበቃን ነበር:: «ከሎሌ ጥፋት፣ ከጌታ ምሕረት አይታጣም» እንዲሉ እኛ ከመበደል እግዚአብሔር ይቅር ከማለት ያረፍንበት ዘመን የለም:: እግዚአብሔር ለመጨረሻ ጊዜ ነው የምቀበላችሁ



www.ethiopinorthodox.org

ቢለን ምን እንደሆን ነበር? እርሱ ከእንግዲህ ወዲህ በቃኝ ቢለንስ ማን ይሸከመናል?

የማይለወጥ ፍቅሩ፣
የማይናወጥ ባሕርዩ፣
የማያልቅ ቸርነቱ፣
የማይሰለች ምሕረቱ፣
የማይወሰን ይቅርታው፣
የማይጠብ ትዕግሥቱ የተባረከ ይሁን!

## እናስተውል

የዝንጀሮ መንጋ ተሰባስበ አንዱ የአንዱን ቂጥ እያየ ይስቃል:: ጦጢት በዛፍ ላይ ተቀምጣ ታዘበችና:- «አትሳቅ ባታየው ነው እንጂ ሁልህም ሙሽልቅ ነህ» አለች ይባላል:: ዓይን ሁሉን ስታይ ራሷን ግን አይታ አታውቅም:: የገዛ ቅንድቧንም አይታ አታውቅም:: እኛም ሁልጊዜ የሚታየን የሌሎች ጉድለትና በደል ነው:: እነ እገሌ አጠፉ እንጂ እኔ አጠፋሁ የማይል አገርና ሕዝብ አይድንም:: የራሳችንን ደካማነት በደብተራ ቅኔ፣ በአሚና ዝማሬ፣ በአዝማሪ ውዳሴ እየሸፋፈንን፣ የሌሎችን ስህተት ግን ስንችል ራሳችን ሳንችል ሰዳቢ እየቀጠርን ስንሰዳደብ እንውላለን፣ ስንሰዳደብ እንኖራለን:: እግዚአብሔር አበሳን ሸፋኝ እንደሆነ እኛም የሰዎችን በደል ሸፋኝ መሆን ሲገባን አላደረግነውም:: የሰው ውድቀቱ እንጂ ትንሣኤው አያስደስተንም:: ግን የአገራችን ሰው እንደሚናገረው «ሰው ሆኖ የማይበድል፣ እንጨት ሆኖ የማይጤስ አይገኝም::»

ያለንበት ዘመን ለእውነት ተቆርቋሪ የሚመስለውም ሆነ በአቋም የሚዋሸው ሁሉም አንድ የሆነበት ዘመን ይመስላል:: የእግዚአብሔር ሰዎች ደግሞ በራቸውን ዘግተው የመጣው መዓት እስኪያልፍ አቤት አቤት እያሉ ነው:: በዛሬው ዘመን ያለው እውነተኝነት በእውነት ተከልሎ የጠሉትን ለማጥቃት እንጂ የጠፋውን ለመመለስ አለመሆኑ ያሳዝናል:: ለዚህ ድራማችን እግዚአብሔር በቅርብ ጊዜ ድንበር ይሰጠዋል:: ጥበብም፣ ሀብትም የማያልፈው ቍርጥ ቀን ቀርቧል:: ይህችን ቀን የምታልፍ ያለ ግብዝነት የምትቀርብ ጸሎትና እውነተኛ ንስሓ ብቻ ናት::

የአገራችን ሰው ዘመኑን ሲታዘበው እንዲህ እንዳለ እንሰማለን:-





የጅብ በሬ፣ የአንበሳ ገበሬ፣
የዝንጀሮ ጎልጓይ፣ የጦጣ ዘር አቀባይ፣
ሁሉም እንብላ ባይ፣ አንድ እንኳ የለ ገላጋይ፣
መገን ኑሮ መገን ኑሮ፣ ከጦጣ ጋር ከዝንጀሮ::

ወንጌል አይሰበክም ባዩ ቀጣፊ፣ ወንጌል አልተሰበከም ባዩ ቀጣፊ፣ እየሳቀ የሚፈርመው ቀጣፊ፣ እያለቀሰ የሚያስተዳድረው ቀጣፊ ቢሆንም ለእግዚአብሔር ግን አይሰወርም:: እግዚአብሔር ሲፈርድ የገዛ ልባችንን እየመረመረ ነውና:: ሰው ቃልን እግዚአብሔር ልብን ይመረምራል:: እናስተውል! ዘመኑን ሳይሆን የጠራንን ጌታ እንምሰል:: እርሱ ችሎ ችሎ የጣለን ቀን የትኛውም ኃይል አያነሣንም::

## ጸሎት

አቤቱ ጌታ ሆይ፣ አንተ ንጹሑ ችለኸናል:: እኛ ቆሻሾቹ ደግሞ መሸካከም አቅቶናል:: እባክህ ልቡና ስጠን:: እንዳንበድል የሚመልሰን ማስተዋል፣ ከበደልን በኋላ ለንስሓ የሚጋብዘን የንስሓ መንፈስ አድለን:: አንተ አበጃጀን:: በወንድሜ በደል ከመሳቅ እንድጸልይለት እርዳኝ:: እኔም የቆምኩት በጸጋህ መሆኑን እንዳውቅ ግለጽልኝ:: ማንም የማይሸፍንልኝን በደሌን አንተ ሰውረሃል:: አንተ ያየኸውን ሰው ቢያየው ምን ይለኝ ነበር? ጌታ ሆይ፣ ሸቱና ጌጥ ለሰው ነው:: ላንተ ግን እራቆታለሁና ይቅር በለኝ:: ሰው ሁሉ ደካማ ነው:: ከሰው ሁሉ ይልቅ ደካማ መሆኔን ላንተ እምናለሁ:: የሚፈረድበት ሳለ የሚፈርደውን ወገኔን አስተምረው:: ሁሉን በቻለው ትዕግሥትህ ለዘላለሙ አሜን::



www.ethiopinorthodox.org

# ምዕራፍ ስድስት
# እንደ እኛ አይደለም

በንጉሠ ነገሥት ዐፄ ዮሐንስ ሥር የነበሩት ንጉሠ ሸዋ ሚኒልክና ንጉሠ ጎጃም ተክለ ሃይማኖት በ1874 ዓ.ም ግንቦት 30 ቀን በእምባቦ ሜዳ ላይ ጦርነት እንዳደረጉ ይታወቃል:: የጦርነቱ መንስኤና በኋላም በትዕቢት የጦርነቱ ቀስቃሽ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ነበሩ:: ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከሚኒልክ ጋር የመዋጋት ፍላጎት ስላደረባቸው በብዙ ጉትጎታ ጦርነቱ እምባቦ ሜዳ ላይ ተደረገ:: በጦርነቱም የንጉሥ ሚኒልክ ኃይል ስላየለ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጦር ተፈታ:: ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ቆስለው ተማረኩ:: ምኒልክም ለተሸነፈው የጎጃም ሠራዊት ምሕረት አድርገው ዓባይን አሻግረው ሸኙት:: ከንጉሤ አልለይም ያለውን ሠራዊት ደግሞ ሚኒልክ ተከተለኝ ብለው ወደ መናገሻ ከተማቸው ወደ እንጦጦ ጉዞ ጀመሩ::

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን በአልጋ አሸክመው ቀስ እያሉ ጉዞአቸውን ሰኔ 5 ቀን 1874 ዓ.ም ጀምረው ሰኔ 19 ቀን 1874 ዓ.ም. እንጦጦ ደረሱ:: ሚኒልክም እንደ ወንድም እንጂ እንደ ባላጋራ ሳያዩአቸው በታላቅ ርኅራኄ ቍስላቸውን እያጠቡ፣ ሐኪም አምጥተው እያሳከሙ፣ ጠቦት አርደው እየመገቡ እንዲድኑ አደረጉ::

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከዳኑ በኋላ አንድ ቀን ንጉሥ ሚኒልክ ታላቅ ግብር አገቡ:: በግብገባው ላይ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሠራዊት፣ የሸዋ መኳንንት ባለበት ሚኒልክ አንድ ጥያቄ ለጎጃሙ ንጉሥ ለተክለ ሃይማኖት አቀረቡ:: ሚኒልክም ተክለ ሃይማኖትን:- «እኔ ማርኬ እንደዚህ አንቀባርሬ አስቀመጥኩህ:: ተሸንፌ አንተ ማርከኸኝ ቢሆን ኖሮ ምን ታደርገኝ ነበር?» ብለው ጠየቋቸው:: የጎጃሙ ንጉሥም:- «እኔማ ብሆን ቆራርጬ ነበር የምጥልዎ» ብለው ሲናገሩ ሳቅ ሆነ:: ሚኒልክም በመቀጠል «ታዲያ የሚሻለው ያንተ ነው ወይስ የእኔ?» ቢሏቸው «ሲያሸንፉ ለተሸነፈ መራራት አግባብ ነው» ብለው የሚኒልክን ተግባር አወድሰዋል::

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በሚኒልክ ተግባር ተነክተዋል:: እንደውም ቍስላቸውን ሲያጥቡላቸው «የወጋዎ እኔን ቍስሌን እንዴት ያጥቡልኛል? ምን ልበልዎ እንደው እምዬ ልበልዎ» ብለዋል ይባላል:: ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ራሳቸውን እኔ ብሆን ምን



www.ethiopinorthodox.org



አደርግ ነበር? እያሉ ሳይጠይቁት አይቀሩም:: እኔ ብሆን እንዲህ አላደርግም በሚል ስሜት ውስጥ ሆነው:- «እኔማ ብሆን ቆራርጬ ነበር የምጥልዎ» ብለው መለሱ:: በእጁ ለወደቀ ጠላቱ፣ ይልቁንም ሊገድል መጥቶ ለተማረከ ባላጋራ ቍስልን ማጠብ፣ በቀኝ ዙፋን አዘርግቶ ማስቀመጥ በሰው ዓለም አልተለመደም:: ሚኒልክ ግን እግዚአብሔር ረድቷቸው ይህን አድርገዋል::

ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ትልቁ ጠብ ትዕቢት ነው:: ስለዚህ ከእርሱ ጋር ዘወትር ጦርነት እንገጥማለን:: ግን እንሸነፋለን:: ታስረን፣ ታመን፣ ወድቀን፣ ተንኮታኩተን ሲያየን መልሶ ያጽናናል እንጂ «ይገባቸዋል» ብሎ እግዚአብሔር አይጨክንብንም:: በእውነት እኛ መሐሪ፣ እግዚአብሔር ጥፋተኛ ቢሆን ኖሮ ይህን ሁሉ አድርጎብን በእውነት ይቅር እንለው ይሆን? እግዚአብሔር ግን ይህን ሁሉ በደላችንን ይቅር ብሎናልና በእውነት ድንቅ ነው::

በኮሚኒዝም ርእዮተ ዓለም አንድ ሰው እግዚአብሔር የለም ብሎ ካደ:: ብዙዎችንም አስካደ:: እግዚአብሔር ከሌለ በጥፋቱ የሚጠይቀው የለምና የቻለውን በደል ሁሉ ፈጸመ:: ጭንቀቱ ግን እየበረታ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም:: በመጨረሻ የፈጠረውን የማይክድ ጌታ ደረሰለት:: ያ ሰው በወንጌል አምኖ ንስሓ ገባ:: ንስሓ በገባ ዕለት በዕንባ ጅረት እየታጠበ ሲጸልይ እንዲህ አለ:-

*«እግዚአብሔር ሆይ፣ እኔ አንተን ብሆን ኖሮ በደልህን ይቅር አልልህም ነበር፤ አንተ ግን በርግጥ መልካም አምላክ ነህ:: በፍጹም ልቤ እወድሃለሁ::»*

እኔም ብዕሬን አስቀመጥኩና እንዲህ ብዬ ማመስገን ቀጠልኩ:-

«አቤት ያንተ ምሕረት፣ አቤት ያንተ ሥራ፣ አቤት ያንተ ግብር፣ በቃላት የማይነገር:: ስንቱን ላውራ ስንቱን ልመስክር እግዚአብሔር የእኔ ክብር:: የማይደክም ልሳን፣ የመላእክት ቋንቋ ዛሬ ለእኔ በሆነልኝና ያደረክልኝን ያንተን ውለታ ምነው ላንተ በነገርኩህ:: ያደረክልኝ ምን አድርጌልህ ነው? ምንስ ያደርግልኛል ብለህ አባበልከኝ? እኔን ከኃጢአቴ ለይተህ አየኸኝ:: ስለ ሰጠኸኝ ጸጋ ለመክፈል አላስብም:: ደሃ ነኝና:: ፍጡር ሲያደርግ ብድር መላሽነትን አገናዝቦ ወይም ለተደረገለት መልካም ነገር ምላሽ እየሰጠ ነው:: አንተ ግን በነጻ ይቅር አልከኝ:: ራሴን በመስተዋት ባየሁ ቊጥር ራሴን ከምወቅስበት ሐፍረት ፈታኸኝ:: የእኔ የባዶው ወዳጅ፣

ባዶነቴን ሞልተህ እንደ ቃናው ውሃ ልትለውጠኝ የፈለግህ፣ በእኔ ጅምር የማትጨረስ፣ አዲስ ነገርን የምትጀምር የእኔ ጌታ አመሰግንሃለሁ። ሳታየኝ ሰጠኸኝ፣ ከሰጠኸኝ በኋላ የሰጠኸኝን ረሳኸው። ለዘላለም ፍቅር ነህ። ጌታዬ እንደ አንተ ያለ ማን ነው? አሜን።

ይልቁንም ወደ እግዚአብሔር የተመለስንበትን የመጨረሻውን ሰዓት ስንመለከት ከባድና ለሞት የተቃረብንበት ጊዜ እንደ ነበር እናስታውሳለን። ወደ ንስሐ ልንቀርብ ስንል እግዚአብሔር የለም እያልን በድፍረት የምንናገርበት፣ በኃጢአት (በፈንጅ) ኳስ የምንጫወትበት፣ ፍጹም ተስፋ የቆረጥንበት፣ እግዚአብሔር ካለ ያጥፋኝ ያልንበት ... ጊዜ ነበር። ታዲያ እኛን መቀበሉ እጅግ አይደንቅም ወይ? እጅግ ስንርቀው እጅግ ቀረበን። በእውነት እርሱ እንደ እኛ አይደለምና ክብር ምስጋና ይገባዋል።

ሌቦች ነፍስ ገዳዮችን እንዴት ይገድላሉ? ብለው ይጠሏቸዋል። ነፍስ ገዳዮችም ሌቦችን «ልክስክስ» ብለው ይጸየፉአቸዋል። አመንዝራዎች ሰዶማውያንን ሲያስቧቸው ይንገሸገሻሉ። እነዚያም እንዲሁ። ሁሉም ሰው ኃጢአት የሚለው እርሱ የማይሠራውን ኃጢአት ነው። ለራሱ ኃጢአት የዳቦ ስም ይሰጣል። ሁሉም ሰው ራሱን በቃሉ ሳይሆን ከእርሱ ይልቅ በደከመው ወንድሙ ስለሚመዝን የተሻለ ይመስለዋል። በኃጢአተኛ የሚፈርድ ኃጢአተኛ ነው። ንጹሕ ሰው ግን ይጸልያል። የአንዱ ኃጢአት የተሰወረ፣ የአንዱ ኃጢአት የተገለፀ ነው። የአንዱ ኃጢአት የተግባር፣ የአንዱ የአሳብ ነው። ግን ሁሉም አዳፋ ነው። በእኛና በዓለማውያን መካከል ያለው ልዩነት ኃጢአተኛ አለመሆን ሳይሆን ይቅርታ ማግኘት ነው። የእግዚአብሔር ይቅርታ ላለፈው ስርየት ብቻ ሳይሆን ለሚመጣው ንጹሕ ልቡናን ይሰጣል።

በራሳችን መቀደስ አይቻለንም። ወደ ጸጋው አብልጠን ስንቀርብ ግን ከኃጢአት እየራቅን፣ ኃጢአት ከሚያዝዝበት ክልል እየወጣን፣ ከነጻው ዓለም ከሰማያዊ ስፍራ በእምነት መቀመጥ እንጀምራለን። በዮሐ. 8. ላይ የተጠቀሰችው ሴት ከላይ ያነሣነውን አሳብ ታብራራልናለች።

ሴቲቱ ስታመነዝር ተገኝታ አይሁድ እያዳፉ ወደ ጌታ አመጧት። ኃጢአተኞቹ እኛ በኃጢአተኞች የምንፈርደውን ያህል ንጹሑ ጌታ በእኛ አለመፍረዱ ይገርማል። ይህችን ሴት ወደ ጌታ ያመጡአት በእርሱ መምህርነትና ዳኝነት አምነው ሳይሆን ሊፈትኑት ነው። ይህችን ሴት እንዲህ የሚያዳፉአት ለሕጉ ተቆርቍረው፣





የእግዚአብሔር ትእዛዝ እንዴት ተደፈረ? ብለው አይደለም። ለትእዛዙ ቢቆረቆሩ ኖሮ በኑሮአቸው ራሳቸው ባላፈረሱት ነበር። በዚህች ሴትና በእነርሱ መካከል ያለው ልዩነት እነርሱ ስለ ሕግ እያወሩ ሕግን ያፈርሳሉ። ሕጉን የሌላውን ኃጢአት ለማጋለጫ፣ የራሳቸውን ኃጢአት ደግሞ ለመሰወሪያ ይጠቀሙበታል። የሕጉ የመጀመሪያ ፍላጎት መቅጣት ሳይሆን ሰውን ከስህተት መመለስ ነው። እነርሱ ግን ሕጉን ለመካሰሻ አደረጉት።

የዓለም ሕግ አመንዝራነትን አይቀጣም። ተስማምተው ቢያመነዝሩ አይዳኝም። ምክንያቱም የዓለም ሕግ የማኅበረሰብን ሰላም በዋናነት የሚጠብቅ እንጂ ግላዊ ቅድስናን የሚያስጠብቅ አይደለም። የእግዚአብሔር ሕግ ግን ሰውነታችንን በዝሙት ስናፈርሰው ይጠይቀናል። ቃሉ ለግል ቅድስናችንም ይጨነቃልና። የእግዚአብሔር ቃል ስካርን፣ ዘፈንን... በመከልከል ለእኛ ያስባል።

ይህችን ሴት ስታመነዝር አግኝተዋት ወደ ሸንጎ ሳይሆን ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አመጡአት። እርሷ ሕግን በማፍረሷ ሳይሆን ኢየሱስን የሚፈትኑበት ርዕስ አገኘን ብለው ይዘዋት መጡ።

ሴቲቱ ብቻዋን አላመነዘረችም። ታዲያ ወንዱ የት አለ? ለመደፈር እንኳ የተጋለጠች ሴቷ ናት። ወንዱ ግን የለም። ሕጉ ደሃን ይገዛል፣ ባለጠጎችና ኃይለኞች ደግሞ ይገዙታል። ያ ማኅበረሰብ ለሴት የነበረው አመለካከት ምን ያህል የወረደ እንደ ነበር ይህ ታሪክ ያስገነዝበናል።

አይሁድም ወደ ጌታ ቀርበው፡- *«መምህር ሆይ፥ ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች። ሙሴም እንደነዚህ ያሉት እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን፤ አንተስ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ? አሉት»* (ዮሐ. 8:4-5)። በነጻ ቢለቃት ለእግዚአብሔር ሕግ የማይገደው ዓመፀኛ ሊሉት፣ ቢፈርድባት «ሳድን መጥቻለሁ» እያለ የሚጨክን ክፉ ሊሉት ይህን ጥያቄ አቀረቡ። *«ኢየሱስ ግን ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ፤ መላልሰው በጠየቁት ጊዜ ግን ቀና ብሎ፡- ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት አላቸው። ደግሞም ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ»* (ዮሐ. 8:6-8)።

ጌታ በሰይጣን የተፈተነው አንድ ጊዜ ነው። ዘመኑን በሙሉ ግን በሰው ተፈትኗል። ረቂቁ ሰይጣን በክፉ ሰዎች ገዝፎ ይታያል። በገሀነመ እሳት ደመወዝ ለሰይጣን የሚሠሩ ብዙዎች ናቸው። ዋነኛ ሥራቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስንና ተከታዮቹን መክሰስ ነው።



www.ethiopinorthodox.org

ጌታችን የእነዚያን ከሳሾች ኃጢአት ለየራሳቸው እንዲነበብ አድርጎ እየጻፈ ይሆናል:: በሕጉ ከሆነ ማን ያመልጣል? በሚፈርድብን ሕግ ከመመጻደቅ፣ በሚያድነን ጸጋ መማጸን አይሻልምን? ሕጉ በራሱ ለሾመው ጌታ የመጨረሻውን ሪፖርት ሲያቀርብ:- *«ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፣ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነትን የሚያደርግ የለም፥ አንድ ስንኳ የለም»* (ሮሜ. 3:11-12) ብሏል:: ዓለም ሕግን ያፈቅራል፣ ግን በሕግ አይኖርም:: ጸጋውን ትቶ በሚፈርድበት ሕግ ሲሟገት ይኖራል:: ሕግ የሚያሳልፈው አንድ ሙሉ /ፍጹም/ ሰው አይገኝም::

ጌታ ኃጢአት የሌለበት የመጀመሪያውን ድንጋይ በመወርወር ይጀምር አለ:: እነርሱ ሴቲቱን ሲያዩ ጌታ ራሳቸውን አሳያቸው:: ስለማናውቃቸው ሰዎች ስንከራከርና ስንሟገት ለምንውል፣ በፍርድ ቀን ስለምንጠየቅበት ስለ ገዛ ኑሮአችን ትተን በፍርድ ቀን ስለማንጠየቅባቸው ሰዎች ስንጨቃጨቅ ለምንውል ለእኛም ራሳችንን ያሳየን! ማንም ሰው በሰው ኃጢአት ይስቃል:: የራሱ ኃጢአት ሲገለጥ ግን ማዘን ይጀምራል:: አንድ ጣቱን ወደ ሰው ሲጠቁም ሦስቱ ወደ ራሱ እንደሚጠቊሙ አያውቅም:: ዓይን በታሪክ ከእርሷ ውጭ ያለውን እንጂ ተመልሳ ራሷን አይታ አታውቅም:: የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ራስን ያሳያል:: ማሳየት ብቻ ሳይሆን ይለውጣል::

*«እነርሱም ይህን ሲሰሙ ሕሊናቸው ወቀሳቸውና ከሽማግሌዎች ጀምረው እስከ ኋለኞች አንድ አንድ እያሉ ወጡ፤ ኢየሱስም ብቻውን ቀረ ሴቲቱም በመካከል ቆማ ነበረች:: ኢየሱስም ቀና ብሎ ከሴቲቱ በቀር ማንንም ባላየ ጊዜ:- አንቺ ሴት፥ እነዚያ ከሳሾችህ ወዴት አሉ? የፈረደብሽ የለምን? አላት:: እርስዋም:- ጌታ ሆይ፥ አንድ ስንኳ አለች:: ኢየሱስም:- እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ ከአሁን ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ አላት»* (ዮሐ. 8:9-11):: በጽድቅ በመፍረድ የታወቀ ሲሆን አልፈረደባትም:: ያለፈውን ዘመኗን ተወላት:: ከአሁን ጀምሮ ግን እንደሚጠብቃት ገለፀላት:: ቅጣት ሰውን የተሻለ አያደርገውም:: በጌታ ግራ የተሰቀለው ወንበዴ በታላቅ መከራ ውስጥ ሆኖ እንኳ ጌታችን ኢየሱስን ይሰድብ ነበር:: አብሮት የተሰቀለው ወንበዴ እንኳ:- *«አንተ እንደዚህ ባለ ፍርድ ሳለህ እግዚአብሔርን ከቶ አትፈራውምን?»* (ሉቃ. 23:40) ቢለውም ልቡ አልተመለሰም:: የጌታችን ኢየሱስን የይቅርታ ጸሎት ቢሰማም (ሉቃ. 23:34) ልቡ ገና ደንዳና ነበር:: ከዚህ በኋላ የመኖር ተስፋ እንደሌለው ቢያውቅም ለማመን ግን ፈቃደኛ አልነበረም:: አዎ ቅጣት ሰውን የተሻለ አያደርገውም:: ፍቅር ግን የመታዘዝ ጉልበት



www.ethiopinorthodox.org



ነው:: ከዚህ በኋላ መማገጥ እንኳ ቢፈልጉ ሁኔታቸው የማይፈቅድላቸው ደካማ ሽማግሌዎች አሁንም በክርስቶስ ማመን አይፈልጉም:: በበሽታ የሚያጣጥሩ ከሰይጣን ጋር ያላቸውን ቃል ኪዳን አንበጥስም ብለው እምቢ ሲሉ እናያለን:: የሚያሳዝኑ ሰዎች ናቸው:: በፍቅርም በቅጣትም ለመመለስ ፈቃደኛ አይደሉም::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ:- *«ሂጂ ከአሁን ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ አላት»* (ዮሐ. 8:11):: ባለፈው ይቅር ብዬሻለሁ አሁን ደግሞ እጠብቅሻለሁ ማለቱ ነው:: ሰዎች እንዲለወጡ የሚያደርጋቸው በእነርሱ ላይ ያለን ተስፋ ነው:: ወደፊት ምን እንደሚሆኑ የምንነግራቸውን ነገር ራእያቸው ያደርጉታል:: የመልካቸውን መጥቆር፣ የአፍንጫቸውን መጎረድ እያየን ገና በጨቅላነታቸው «ይህስ ተደባዳቢ ነው የሚሆነው» ያልናቸው በትክክል ሆነዋል:: ዓመፀኛ ናቸው ብለን የጻፍንላቸው አመፀኛ ሆነው አይተናል:: ሰዎች እንደጻፍንላቸው ናቸው:: መልካምን ስንጽፍላቸው መልካም ይሆናሉ:: ቀይ ሌባ ሰርቆት ጥቁር ደህነኛን «ሌባው እርሱ ነው» ብሎ የሚያሲዝ ስንቱ ነው? ሌባ በእኛ አመለካከት ጥቁር መልክ ያለው ብቻ ነው:: እነዚህን ወጣቶች ለምን እያሰናዳናቸው መሆኑን አናውቅምና እግዚአብሔር ያብራልን:: ጌታችን ግን ደካማ ሳለን ኀበዞች ብሎ ያበረታናል:: እንዲህ የሚያደርገው እየሸነገለን እውነትንም እየደበቀ ሳይሆን በእኛ ላይ ያለውን ተስፋ እየገለጠ ነው:: የሞተውን ቃሬዛ እየነካ:- *«አንተ ጎበዝ፥ እልሃለሁ፥ ተነሣ»* (ሉቃ. 7:14) ብሎታል:: የሞተውም ነቅቷል:: አንድ የኦሮምኛ ምሳሌ:- «እናት ዓይነ ሥውር ልጇን ብርሃኔ፣ ሽባ ልጇን መሰሎዬ ትለዋለች» ይላል:: እናትን እንዲህ ስትል ማን ዋሽተሻል ይላታል? ጌታም በእኛ ላይ ተስፋ አለውና እንዲህ ይለናል::

ንጹሕ ጌታ ቢከሰን ሁላችንም ወንጀለኞች ነን:: የዋሁ ጌታ ቢፈርድ ሁሉም ሟች ነው:: ቅጣት ወንጀለኛውን የተሻለ ሰው እንደማያደርገው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያውቃል:: እንደገና ዕድል ይሰጠዋል:: መቼም ለመፍረድ የምንደፍረው እኛ ባልወደቅንበት ኃጢአት ነው፣ በምንወድቅባት ኃጢአት ግን እንደ እኛ ሩኅሩኅ የለም:: ሁላችንም ለራሳችን ብናዝንም እግዚአብሔር ግን ለሁላችን ያዝናል:: እርሱ ድካማችንን ያውቀዋልና:: እንደ እኛ አይደለም::

## <u>እናስተውል</u>

መታበይ ከመውደቅ ያደርሳል:: ትዕቢተኛ እንደሚወድቅ ነቢይ መሆን አያስፈልግም:: እግዚአብሔር ትዕቢተኛን ሳይጥል

አይቀርምና:: ትዕቢተኛን መግፋት አያስፈልግም፣ ራሱ ይወድቃልና:: ትዕቢት የሚመጣው የሐሰትን ሸንገላ በማዳመጥ ነው:: ትዕቢተኛ ከሆነው በላይ ራሱን ስለሚመለከት ይታለላል:: ትዕቢት አወዳሾች አሏት:: ሰውዬው ሲወድቅም እነዚያ አወዳሾች መልሰው ይስቁበታል:: ትዕቢተኛ ዘመድ የለውም:: ዘመድ ብቻ ሳይሆን ምሥጢርም የለውም:: ማንነቱን ራሱ ያጋልጣል:: ትዕቢተኛ ከሰውና ከእግዚአብሔር ጋር ይዋጋል:: መጨረሻው ግን ውድቀት ነው:: በዓለም ላይ የወደቁ ሁሉ ይነሣሉ፤ ትዕቢተኞች ግን ላይነሡ ይወድቃሉ:: «ከፍ ከፍ ይበል፣ ላወዳደቁ እንዲመች» እንዲሉ:: ከፍ ባሉ ቊጥር ጥንቃቄ ከሌለ ገደልን ማርዘም ሬሳን ማራቅ ነው:: በገዛ ኃይሉ የገነነ ይወድቃል:: የሚያነሣው ግን የለም:: ከጥንት ጀምሮ ገናና የነበሩ ትዕቢተኛ ነገሥታት ዛሬ የልጆች መማሪያ ሆነው ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ተቀርጸዋል:: ፍጻሜአቸው ሞት ነው:: የትዕቢት ውርደት ግን እስከ ሞት አያደርስም:: ቀድሞ ይጀምራል:: የትሕትና ክብረት ግን እንደ ገነነ፣ ዋጋውም እንደ ከበረ ይኖራል:: ባለቅኔው የትዕቢታችንንና የምኞታችንን ከንቱነት ሲናገር እንዲህ ብሏል:-

«ምንትኑ መንግሥት ከመ ንትሜነይ መንግሥተ፣
ለብሂለ ነግሠ ፍጻሜሁ አኮኑ ብሂለ ሞተ፤»

ትርጓሜው:-

«ንጉሥ መሆንን ለምን ተመኘነው፣
የነገሠ መጨረሻው ሞተ ነው፤»

ኀሊናው የተናገረውን መውቀስ ተገቢ አይደለም:: ከኀሊና በላይ ማንም አይናገርምና:: ሰውን የምንናገረው ኀሊናው እንዲናገረው እንጂ ምክራችን ኀሊናውን ተክቶ እንዲሠራ አይደለም:: በእውነት ከውጭ ድምፅ የውስጥ ድምፅ ይሻላል:: ኀሊናው የሚወቅሰውን መውቀስ ደንዳና እንዲሆን ማድረግ ነው:: ዛሬ በእጃችን የወደቀውን የቀድሞውን ክፉ፣ እግዚአብሔርን በመፍራት ልናስተናግደው ይገባል:: እኛ በእርሱ እጅ በወደቅን ጊዜ ጨክኖብናል:: ስለዚህ ክፋቱን እስከ ዛሬ እናወራለን:: ዛሬ በእጃችን ወድቋልና እግዚአብሔር እንዳይታዘበን መልካም ማድረግ ይገባናል:: ይልቁንም የትላንት ባለጠጎች ዛሬ ሲደኸዩ፣ የትላንት ኃያላን ዛሬ ሲደክሙ መፍራት ይገባናል እንጂ መሳለቅ አይገባንም::

ለራሳችን ኃጢአት «ማረኝ» እያልን በሌሎች ኃጢአት ፍርድን መናፈቅ የለብንም:: ሰው ቢፈረድበት ዳግም የእኛ





አይሆንም:: ቢለወጥ ግን ከቀድሞ ይልቅ ያገለግለናል:: በእውነት እግዚአብሔር እንደ እኛ አይደለምና ልናመሰግነው ይገባናል:: ሰዎች የፈረዱብንን እርሱ ግን ይቅር አለን::

## ጸሎት

ሞት ለሚገባኝ ምሕረት የሰጠኸኝ፣ በከሳሾቼ ፊት ተሟግተህልኝ ለብቻዬ ለንስሐ የጋበዝከኝ፣ ልብሴ በአደባባይ ሲወልቅ ፈጥነህ የሸፈንከኝ ከባቴ አበሳ እግዚአብሔር አመሰግንሃለሁ:: በሕይወቴ ስንት አለፈ ተራራውን ደልድለህ፣ ሸለቆውን ሞልተህ መንገድ ያቀናህልኝ እግዚአብሔር አምላኬ ከልቤ አመሰግንሃለሁ:: ሰዎች ከስሰው ከስሰው ካንተ ፊት አቀረቡኝ:: በቅጡ ሳላውቅህ የእርሱ ነው ብለው አሳደዱኝ:: ስለፈለግኸኝ በደጅ አገኘኸኝ:: ከታሪኬ ጋር ሳይሆን ከዛሬ ጋር ጉዳይ እንዳለህ አወቅሁኝ:: ጌታዬ ክብሬ አመሰግንሃለሁ:: አንተ ከወደድከኝ ኀሊናዬም ሆነ ሕግ አያስፈራኝም:: አንተ ከእነዚህ ኃይላት በላይ ባለሥልጣን ነህና አመሰግንሃለሁ:: ሰዎች የትላንቱን፣ አንተ ግን የነገን አየህልኝ:: ምን እላለሁ ብቻህን ተመስገን!



www.ethiopinorthodox.org

# ምዕራፍ ሰባት

## እንከብደውም

አንድ የሥነ እጽዋት ተመራማሪ የሆነ ሰው በአንድ ጥልቅ ገደል ውስጥ ለምርምር የምትረዳውን ዕፅ ያያል:: እንዴት እንደሚያወጣት ሲያስብ ከማዶ ልጆች ሲጫወቱ አየ:: አንዱንም ልጅ ጠርቶ:- «ማሙሽ እዚያ ጥግ አንዲት ቅጠል ትታይሃለች? ገንዘብ እሰጥሃለሁ ወገብህን በገመድ አስሬ ልልቀቅህና ቅጠሏን አምጣልኝ» አለው:: ልጁም:- «እሺ አወጣልሃለሁ ገመዱን ግን አባቴ መያዝ ስላለበት ቆይ ጠርቼው ልምጣ» አለው:: ሰውዬውም:- «ለምን ትጠራዋለህ? እኔ እይዝሃለሁ» አለው:: ልጁ ግን መልሶ:- «አንተ አባቴ ስላልሆንህ ስከብድህ ትለቀኛለህ፤ አባቴ ግን ምንም ብከብደው አብሮኝ ይገባል እንጂ አይለቀኝም» አለው:: ሰውዬውም «አባት ምንም ቢከብደው ልጁን አይለቅም» እያለ መደነቅ ጀመረ::

እግዚአብሔር ከአባት ይልቅ አባት ነው:: ከምድራዊ አባት ይልቅም አሳቢ ነው:: በቃሉም:- *«አልለቅህም ከቶም አልተውህም»* ይላል (ዕብ. 13:5)::

ሁሉም ሰው የሚችለውን ይፈልጋል:: የሚችለውን መፈለግ ብቻ ሳይሆን የሚችለውንም ያውቃል:: ሁሉም ሰው የሚችለውን ይፈልጋል ብለናል:: ቍጠኛው ቍጠኛን አያገባም:: የሚፈልገው ትዕግሥተኛዋን ነው:: ቢጋቡም እንደማይቻቻሉ ያውቀዋል:: ለፍላፊው ዝምተኛዋን ይወዳል:: ሁለቱም ቢጮኹ ቤቱ አይፀናምና:: በትዳር ላይ ከመልክ፣ ከቀለምና ከቁመና ሳይቀር ተቃራኒውን መፈለግ የተለመደ ነው:: ሰው ድካም እንዳለው አውቆ የሚችለውን ይፈልጋል:: የሰው ልጅ ድብቅ ጠባዩ በትዳሩ ውስጥ ይታያል:: ሌላ ቦታ ሊጠነቀቅ ቢችልም ትዳሩ ላይ ግን መጠንቀቅ አይችልም:: ትዳር ከጸታና ከአስተዳደግ ጀምሮ ተቃራኒ የሆኑ ሰዎች የሚሳሳቡበትና የሚቀራረጹበት ትምህርት ቤት ነው:: በትዳር ውስጥ አንዱ የአንዱን ድብቅ ጠባይ ያያል:: ሰው ተጠንቶ የማይታወቅ ፍጡር መሆኑንም ያውቃል:: የራሱንም ድብቅ ጠባይ በትዳር ውስጥ ያገኘዋል:: ቀናተኛ መሆኑን ወይም የተጋገረ እንጀራ የሚቆጥር መሆኑን ከዚህ በፊት አያውቀውም ይሆናል:: አሁን ግን የተሰወረ ማንነቱን ያገኘዋል::



የብዙ ትዳሮች መፈራረስ አለመቻቻል ነው:: የብዙ የተቃኑ ትዳሮች ምሥጢርም ችግር አለመኖሩ ሳይሆን መሸካከም መቻል ነው:: ሰው የሚችለውን ይፈልጋል:: ሰው የሚችለውን መፈለግ ብቻ ሳይሆን የሚችለውንም ያውቃል:: እናቱ ላይ የሚቀማጠለው ልጅ እናቱ የሌለች ቀን ወንድሞቹና እህቶቹ ላይ እንኳን ሲቀማጠል አያስበውም:: እናቱ የሰጠችውን ምግብ የሚደፋው፣ እናቱን ያጣ ቀን ባይሰጡትም ዝም ብሎ ጠሙን ያድራል:: ሰው ማን እንደሚሸከመው ያውቃል::

«ውሎ ውሎ ከቤት፣ ኖሮ ኖሮ ከመሬት» እንዲሉ የውሎው ሰብሳቢ ቤት፣ የዕድሜ ሰብሳቢ ሞት ነው:: ከቤት በላይ ከመሬት በላይ እግዚአብሔር ሰብሳቢ ነው:: የሰው ሁሉ ፍጻሜ እግዚአብሔር ነው:: ለሽልማትም ሆነ ለፍርድ በመጨረሻ በእርሱ ፊት መቆማችን አይቀርም:: እግዚአብሔር የሰው ሁሉ ግብ ነው:: በወጣትነታቸው ሲባዝኑ የኖሩ በሽምግልናቸው እግዚአብሔር የት ነው? ድጋፍ እፈልጋለሁ ይላሉ:: ከሥልጣናቸው የተወገዱ አክብሮ የማያዋርደው ጌታ የት ነው? ይላሉ:: ሀብታቸውን የተቀሙ የማይነጥፈው ብልጽግና እግዚአብሔር የት ነው ይላሉ:: ሲዘፍኑ የኖሩ ዘምሬ በሞትኩኝ ይላሉ:: ለምን? ስንል የሰው ሁሉ ፍጻሜ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው:: ከነአቅም ወደ እግዚአብሔር መምጣት ግን መታደል ነው:: ቆስሎ ከመማረክ በሰላም እጅ መስጠት ጉዳት ይቀንሳል:: ዓለም ስትተፋን ሳይሆን ስትፈልገን ማምለጥ ከነጉልበት ማምለጥ ነው:: ቤቱ ሲቃጠል ጥቂት ንብረት ይዞ የሚወጣ አለ፣ አንድ ራሱን የሚያወጣ አለ፣ ራሱንም የሚያጣ አለ:: የእሳት ቀጠሮ ባለበት ዓለም ከነገንዘቡ፣ ከነሥልጣኑ፣ ከነጉልበቱ የሚያመልጥ አለ:: ሁሉን ከስሮ ራሱን ብቻ የሚያድን አለ:: የዘገየ ግን ራሱንም ያጣል:: ሕዝባችንን ስንመለከት የሚበዛው ቤተ ክርስቲያንን የሚረግጠው ሁለት ጊዜ ነው:: ሁለቱንም ሲመጣ እርሱ አያውቀውም:: ሁለቱንም ጊዜ የሚመጣው በሸክም ነው:: ሲጠመቅና ሲሞት::

ሰው በውድቀት ሰዓቱ ወደ እግዚአብሔር መምጣቱ የሚሸከመው እርሱ ብቻ መሆኑን በማወቁ ነው:: የካደውን እግዚአብሔር ተቀበለኝ ሲል የማይሳቀቀው እግዚአብሔር ስሜት ስለሌለው ሳይሆን የሚቀበል ፍቅር ስለሆነ ነው:: እርሱ ለምን በደላችሁ ሳይሆን ለምን አልተመለሳችሁም? የሚል አምላክ ነው:: ከእኛም በደላችንን ከማመን የበለጠ ነገር አልፈለገብንም:: አዎ ከበዱኝ ብሎ የማይተወን አምላክ ነው:: ባሕር ጠላቂዎች ዋና ባለመቻል የሰጠመውን ከውድቀቱ ሥር ገብተው እንደሚያወጡት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስም ወደ መቃብር ገብቶ ወደ ሰማያት ከፍ አድርጎናል::



www.ethiopinorthodox.org

ቀሳውስቱ ሲያስተምሩ ዐፄ ቴዎድሮስ ያዳምጣሉ:: ቄሱም:- «እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ» ሲሉ ዐፄ ቴዎድሮስ:- «ዛሬስ ምን እየሠራ ነው?» ብለው ጠየቁ:: ቀሳውስቱ ሁሉ ዝም አሉ:: ለጥያቄውም ራሳቸው ንጉሡ:- «የዛሬ ሥራው የእኛን ተፈጥሮ መሸከም ነው» በማለት አስደናቂ መልስ ሰጡ:: እግዚአብሔር ፍላጎታችንን ብቻ ሳይሆን አመላችንንም ተሸክሟል:: ይህ ትዕግሥቱ ነው::

የሰው ፊት ሲጠቍር እርሱ በፍቅር ይቀበለናል:: ፍጡር ደጁን ሲዘጋብን እርሱ እጁን ዘርግቶ ይጠብቀናል:: መሳቂያና መዘበቻ ስንሆን እርሱ ሸፍኖ ያድሰናል:: ወደ ገደል ስንወረወር ከውድቀታችን ሥር እርሱ ይነጠፍልናል:: የፍጡር ክንድ ሲዝል በዘላለማዊ ክንዱ ያንተርሰናል:: ስንገፈተር ያቅፈናል:: ከምኩራብ ሲያባርሩን በደጅ ያገኘናል (ዮሐ. 9):: በዚህ በረሃ ዓለም ላይ ያገኘነው የምድረ በዳው ጓደኛችን እርሱ ብቻ ነው:: ከማዘን ምክንያታችን የመደሰት ምክንያታችን የበለጠው በእግዚአብሔር ፍቅር ነው::

በራሱ በእግዚአብሔር ደስ ይለናል:: በሥራውም ደስ ይለናል:: በዚህ ፈታኝ ዓለም ላይ ሰው ተፈጥሮውን ያባክናል:: ጉልበታችን እንደ ጥንቱ አይሠራም፣ ዓይናችን እንደ ድሮው አያይም:: ጆሮም ያሳልፋል:: ልቤን፣ ኵላሊቴን ... የምንለው ተፈጥሮ እየባከነ ስለሆነ ነው:: ከማንም ይልቅ የሚቀርበን ይህ አካላችን የእኛ አይደለም:: የእኛ ቢሆንማ ለምን ሄደ? ያየናቸው ቦታዎችና ሰዎች ጠፍተውናል:: በጨለማ ያጠናነው ትምህርታችን ተኗል:: የማስታወስ አቅማችን ቀንሷል:: የደከመውን ተፈጥሮ የሚያግዙ ብዙ መድኃኒቶችንና ሥልጣኔዎችን እንጠቀማለን:: አካላችን፣ ጤናችን፣ የምግብ አምሮታችን፣ ፍቅራችን፣ እንቅልፋችን፣ ንቃታችን ... የእኛ አለመሆኑ የሚገባን ቆይቶ ነው:: የእኛ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ዘመን ተሻግሮ ያገኘነው እርሱን ብቻ ነው::

ልጁ አድጎ የእናቱን ውለታ ለመመለስ ሁሉን ማድረግ ጀመረ:: ትዝ ሲለው እናቱ ተሸክመው አሳድገውታል:: ስለዚህ «እናቴ ተሸክመሽ አሳድገሽኛል እኔም ልሸከምሽና ውለታሽን ልክፈል» አለ:: እምቢ ቢሉት አስቸገረ:: አንድ ቀን ተሸከማቸውና በማግስቱ አልደገመውም:: «በል እንጂ ዛሬም ተሸከመኝ እኔ እኮ አንተን አንድ ቀን ብቻ አይደለም የተሸከምኩህ?» ቢሉት ልጁ የሚችለው አልሆነም:: አዎ የእናት ውለታ እንኳ የማይመለስ ከሆነ የእግዚአብሔር ውለታማ እንዴት ይሆን? ዛሬ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንን አሳንፀው፣ አሥራት በኵራት ሰጥተው ዘላለም



ለመመካት ይፈልጋሉ:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሕይወቱን ሰጥቶን አልተመካም:: ከማኅፀን ጀምሮ እስከዚህች ቅጽበት ተሸክሞን ሳለ አልታከተም:: በእውነት እጅግ ጻድቅ ስንሆን እጅግ ኃጢአተኛ ነኝ ማለት ይገባናል:: ምክንያቱም እግዚአብሔር እኛን የወደደበትን ፍቅር ዓይነት መቼም እርሱን ልንወደው አንችልምና:: ምንም ብናገለግለው እርሱ ከሰማይ ወርዶ ያገለገለንን ያህል ልናገለግለው አንችልምና:: የእኛ ጽድቃችን የጽድቅ ያህል የሚቆጠር አይደለም:: እንደዚህ ባለ ባሕርዩ ግን ያስደንቀናልና በእግዚአብሔር ደስ ይለናል::

በዚህ በፈታኝ ዓለም ላይ የሰው ልጅ የጨበጠውን እየጣለ እንደ ገና ምኞትን ይከተላል:: አንድ ደራሲ:- *«ሀብት የሰውን ፍላጎት ጥም አያረካም፣ ክብርም አድካሚ ነው፣ ምድራዊ ደስታም ይሰለቻል፣ ጥበብም ወሰኗ ሰፊ በመሆኑ ሊደረስበት አይቻልምና ታበሳጫለች:: ስለዚህ የሰው ልጅ እውነተኛ ሰላምና ደስታ ሊያገኝ የሚችለው የደስታ ምንጭ ከእግዚአብሔር ስለሆነ ልቡን ወደ እግዚአብሔር አቅንቶ እውነትንና ፍቅርን መመሪያ ያደረገ እንደሆነ ነው»* ብሏል::

ብዙ ሥልጣን የነበራቸው ሰዎች ትክክል ብለው የሠሩትን ዛሬ ትክክል ስለማይሉት የማሻሻያ ዕድሜ ምነው በኖረን ይላሉ:: ብዙ ሀብት የነበራቸው ሁሉም ሲከዳቸው «እውነተኛ ዘመድ ድሆች ነበሩ» እያሉ ይቆጫሉ:: በዓለም ላይ ሕልም እውን መሆኑ ብቻ ሳይሆን እውንም ሕልም ይሆናል:: ብዙ ነገር ይዶለትባቸው የነበሩ ቪላዎች ዛሬ ጎዳና ሆነዋል:: ከቤታቸው ሰው ያስወጡ የነበሩ አከራዮች እነርሱም ተከራይ ናቸውና ለቀው መቃብር ሄደዋል:: አገር እየቆረሱ መስጠት የሚችሉ መቀበሪያ አጥተው ቀርተዋል:: በዚህ መልከ - ብዙ በሆነው ዓለም ላይ «ደስታ» በዘላለማዊ ውበቱ የሚኖረው እግዚአብሔር ብቻ ነው::

ታማኝነት በሌለበት በዚህ ጥላ ዓለም ላይ በእግዚአብሔር ደስ የሚለን:-

## 1. ሙሉ ሆኖ ስለሚቆም

እያንዳንዱ ቀን የመካብና የመናድ ቀን ነው:: ይልቁንም ዓለም የእንቧይ ካብ ነው:: የእንቧይ ካብ ሠርተን ሳንጨርሰው ተንዶ አልቋል:: ሁልጊዜ ለመፍረስ ይቸኵላል:: ዓለም የእንቧይ ካብ ናትና ሠርግ እየተደገሰ ኃብቻው ይሠረዛል:: የሹመት ጠጅ እየተጠመቀ ሹመቱ ለሌላ ይሠጣል:: በአደባባይ የወጣልን ዕጣ የምሥራቹ



www.ethiopinorthodox.org

ሳያልቅ በስህተት ነው ይባላል:: ለዓመት ያሰቡት ለዕለት የማይበቃበት ባዶ ዓለም ነው:: በዚህ ዓለም ላይ ያለ እግዚአብሔር ለመኖር ማቀድ ያለ አየር ለመኖር እንደማቀድ ነው::

አንዱ ወዳጅ በጓሮ ይወጣል፣ አንዱ በበር ይገባል:: ያበደርናቸው እየካዱን የማናውቃቸው አዲስ ሥራ ያመጡልናል:: የወዳጅ አጥር ሲፈርስ ጥሩውን ሰው ማመን ይከብዳል:: የገንዘብ አጥር ሲፈርስ የመኖር መብት የሌለን ይመስለናል:: የጤና አጥር ሲፈርስ ሞት የተፈረደብን ይመስለናል:: የዘመድ አጥር ሲፈርስ ቊጭቱ ያሳምማል:: ቅጥር ሲፈርስ ሐፍረቴ ይታያል፣ ብርድ ይገባኛል፣ ወንበዴ ይደፍረኛል የሚል ስጋት ይነሣብናል:: እግዚአብሔር ግን በፈረሰው አጥር በኩል ሙሉ ሆኖ ይቆማል:: የወዳጅ አጥር ሲፈርስ ወዳጅ ሆኖ፣ የእናት አጥር ሲፈርስ እናት ሆኖ፣ የገንዘብ አጥር ሲፈርስ ገንዘብ ሆኖ ... እግዚአብሔር ይቆምልናል:: በእውነት የመደሰት መብት አለንና በእግዚአብሔር ደስ ይበለን:: እርሱ ብቻውን ይበቃናል::

ሰውዬው ጎርፉ እያንከባለለው ሲወስደው ግንዱን ይዞ:- «ጌታ ሆይ አድነኝ» እያለ መጮህ ጀመረ:: ጌታም ተገለጠለትና:- «እንደማድንህ ታምናለህን?» ቢለው «አምናለሁ» አለ:: እግዚአብሔርም:- «እንዳድንህ ግንዱን ልቀቅ፣ ብቻዬን እበቃሃለሁ» አለው:: ሰውዬው ግን ከጎርፉ ጋር እየታገለ:- «ጌታ ሆይ ግንዱንም አልለቅም አንተንም አልክድም» አለ ይባላል:: ዛሬም ጠንቋይንም አልለቅም፣ እግዚአብሔርንም አልለቅም:: ሌብነትንም አልለቅም፣ ምጽዋትንም አልለቅም የሚሉ እግዚአብሔር እንደሚበቃ የማያምኑ ብዙዎች ናቸው:: እግዚአብሔር ግን ብቻውን ይበቃል:: በፈረሰብን ቅጥር በኩል ሙሉ ሆኖ ይቆማል:: አንድ ደብተራ «ለምን ይጠነቊላሉ፣ በእግዚአብሔር አይተማመኑም ወይ?» ብላቸው:- «እግዚአብሔርንማ አየነው ወዳጆቹን ሲያስበላ» ብለው መልሰውልኛል:: እኚህ ሰው ግን ራሳቸውን የሚያስቡት የእግዚአብሔር ጠበቃ አድርገው ነው:: ለእግዚአብሔር ሲሟገቱለት ይውላሉ፣ እንደሚጠብቃቸው ግን አይተማመኑበትም:: የሰይጣንን ከለላ የምንፈልገው ለምንድነው? የእግዚአብሔር ጥበቃ የሚያስፈልገን ለዚህ ምድር ብቻ ነው ወይ? ደግሞስ ከሰይጣን ለመዳን ሰይጣንን እንዴት እንጠጋለን? ክፉ ራሱ ለፈጠረው ችግር የራሱ መፍትሔ የለውም:: ሰይጣንም ችግር ማምጣት እንጂ መፍትሔ መስጠት አይችልም:: መፍትሔው በእግዚአብሔር እጅ ብቻ ነው ያለው:: በእውነት እግዚአብሔር ብቻውን በቂ ነው::





## 2. አይፈቅድም

ሞት እያለብን ውስጣችን ግን አይቀበለውም:: ለምን? ስንል ለሕይወት ስለ ተፈጠርን ሞትን መቀበል አይሆንልንም:: ኃጢአት ሠርተን አንተኛም:: ለምን? ስንል የተፈጠርነው ለጽድቅ ስለሆነ ኃጢአት ሰላም አይሰጠንም:: ማንም ሰው ጽድቅ ሠርቼ ታወኩኝ፣ ኃጢአት ሠርቼ ተደሰትኩኝ ብሎ ቢናገር ሐሰተኛ ነው:: ምክንያቱም እንደ ጽድቅ የሚያስተኛ፣ እንደ ኃጢአት የሚያውክ የለምና:: ኃጢአት አንዳንድ ጊዜ ምርጫችን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ውድቀታችን ነው:: እግዚአብሔር ግን ያጠቃን ኃጢአት እንዳጠቃን እንዲኖር አይፈቅድም:: ከኃጢአት ፈተና ነጻ የሆነ አዲስ የትንሣኤ አካል አዘጋጅቶልናል (ሮሜ. 8:23):: ባስጨነቀን ሱስና ዓመፅ ላይ ድል ይሰጠናል (ሮሜ. 1:16)::

ከደስታችን አንዱ ጠላታችን ዘላለማዊ አለመሆኑ ነው:: ትግላችን ሁሉ ያልፋል:: ዛሬ ውጊያ የበዛብን ከጠላት ጋር በጋራ ዓለም ስለተገናኘን ነው:: ከዚህ ዓለም ስንሄድና በጉ ክርስቶስ በሚያበራባት ከተማ ስንደርስ ፈተናና መከራው ያበቃል:: እኛ በተፈጥሮአችን አንድ ቦታ ስንቀመጥ እንረጋለን:: ደማችን ሳይቀር ይረጋል:: መላ ተፈጥሮአችን የመርጋት ጠባይ አለው:: እግዚአብሔር የመንግሥተ ሰማያትን ደስታ ትንሽ ትንሽ ቢያፈስልን ችግርንና በሽታን ቢያርቅልን «ጌታ ሆይ፥ መንግሥተ ሰማያት ያልከውን ተወው ትተነዋል:: በዚህ መኖር ይሻለናል» እንለው ነበር:: እግዚአብሔር ግን ወደ ታላቁ ግብ፣ ወደ ሰማዩ ወደብ በመከራ ጅራፍ እየገረፈ ያደርሰናል:: *«አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና»* (ራእ. 22:20) የምንለው መከራውና ፈተናው ሲያይል ነው::

አዎ እግዚአብሔር ያጠቃን ኃጢአትና መከራ ሁልጊዜ እንዳጠቃን እንዲኖር አይፈቅድምና በዚህ ደስ ይለናል::

## 3. ታማኝ ነው

መንገዳችንን የፍርሃት ያደረገው መተማመን በመጥፋቱ ነው:: በምትኩ ሽንገላና ሌብነት ነግሦአል:: ድሮ ኃጢአት ኃጢአት ይባል ነበር:: ዛሬ ግን ኃጢአት እንደ እውቀት ተቆጥሯል:: ሌቦችን «ሲሾም ያልበላ» እያልን እናወድሳለን:: ጥብቆ የሰረቀውን ሌባ ከበን እንደበድባለን:: ሚሊዮን ብር የሰረቀውን የአገር ጠላት ደግሞ «ወንድ» እንላለን:: አንዲት ባለ ንብረት ታማኝነት ስለመጥፋቱ



www.ethiopinorthodox.org

ስትናገር:- «የተማሩ የተባሉ ዶክተሮችንና ኢንጂነሮችን ቀጠርኩ ሰርቀውኝ ጠፉ:: መሰረቱ ካልቀረ ድሆቹና እንደ ሌባ የሚፈሩት የጎዳና ተዳዳሪዎች ይውሰዱት ብዬ ከጎዳና ላይ አንሥቼ ንብረቴን ጠብቁ አልኳቸው:: ከዚያ ቀን በኋላ መርፌ አልጠፋብኝም:: የሚጣለውን ዕቃ እንኳ ሳይቀር ይዘው ይጠብቁኝ ጀመረ» ስትል ሰምቻለሁ:: አዎ መተማመን እየጠፋ ባለበት ዘመን እግዚአብሔር ግን ታማኝ ስለሆነ ከማይጠበቁና ተስፋ ከተቆረጠባቸው ሰዎች ታማኞችን ያስነሣል::

እግዚአብሔር በቃሉ፣ በተስፋውና በሥራው ታማኝ ነው:: በእርሱ ያመነ አያፍርም (ሮሜ. 10:11-13):: የተጠጉትን አውጥቶ ለአራዊት አይሰጥም:: ቀን ሲከፋ አብሮ አይከፋም (ናሆ. 1:3):: ጊዜ ሲለወጥ አይለወጥም:: ሁልጊዜ በአድራሻው ነው:: ለተሰደዱት አገር ነው:: ስለዚህ በእርሱ ደስ ይለናል::

## 4. አንከብደውም

እግዚአብሔር አልችለውም የሚለው በሽታ፣ ከበደኝ የሚለው ጉዳይ የለውም:: ሁሉ ለእርሱ ቀላል ነው:: አንድ ሰው:- «እግዚአብሔር በሽታ ለመፈወስና ሙት ለማንሣት የሚጠቀመው ኃይል አንድ ነው:: አሁን ሙት ላስነሣ ነው ብሎ የበለጠ ኃይል አይጠቀምም:: በሽተኛ በሚያስነሣበት ኃይሉ ሙት ይቀሰቅሳል:: ኃይሉ ፍጹም ነው» ብሏል::

እግዚአብሔር ሁሉን ስለሚተካና በዓለም ያለውን ትልቅ ነገር ስለሚያስንቀን፣ ስምና ታሪክን ስለሚለውጥ፣ ሁልጊዜ በታማኝነት ስለሚገኝ ከዚህ ሁሉ በላይ ለእግዚአብሔር ስለማንከብደው በእግዚአብሔር ደስ ይለናል:: ለእግዚአብሔር ተአምር አንሠራለትም፣ የሚሠራውን ተአምር ለማየት ግን እንደተጠራን እየተሰማን ገና ለመኖር እንናፍቃለን::

እግዚአብሔር በማይጠገብ ፍቅር ስለወደደን ደስታችን ነዋሪ ነው:: የእርሱ ይቅር ባይነት ባይሆን ኖሮ የመላእክትና የደጋግ ሰዎች ይቅርታ ከሚችለው በላይ በደለኞች ነን (ዘፀ. 23:21):: የእርሱ ሰጪነት ባይሆን ኖሮ የፍጡር ሰጪነት በሰለቸን ነበር (ያዕ. 1:5):: እግዚአብሔር ግን ይችለናል:: ከበዱኝ ብሎም ለማንም አሳልፎ አይሰጠንም:: እርሱ ከበደኝ ቢለን ማን ይሸከመናል?





በአገራችን የሚነገር አንድ አፈ-ታሪክ አለ:- መልአኩ ገብርኤል:- እግዚአብሔር ይህችን ዓለም የሚያይበትን መነጽር አሳየኝ ቢለው እግዚአብሔርም:- «እኔ እንዳየሁ ብታይ እኔ እንዳለፍኩ ማለፍ አትችልም» አለው ይባላል:: አዎ የእርሱ ትዕግሥት ካልሆነ ማን ይችለናል? ይህንን ባሕርዩን ሲያወድስ ሊቁ እንዲህ ብሏል:-

«ሳትደክም ሁሉን ትሸከማለህ፣
ሳታጎድል ለሁሉ ትመግባለህ፣
ዝም ሳትል ለሁሉ ታስባለህ::
ሳታጉድል ለሁሉ ትሰጣለህ፣
ሳትነጥፍ ለሁሉ ታረካለህ፣
ሳትዘነጋ ሁሉን ታስባለህ::
ሳትተኛ ሁሉን ትጠብቃለህ፣
ቸል ሳትል ሁሉን ትሰማለህ
ሳትቀበል ለሁሉ ትተዋለህ::»

/ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ/::

## እናስተውል

ልጅ ሲድህ ደስ ይላል:: ሲኮላተፍ ይጣፍጣል:: ይህ ግን ጊዜያዊ ደስታ ነው:: ለዘለቄታው ቢድህ፣ ለዘለቄታው ቢኮላተፍ ከመደሰት ያሳስባል:: ዘላቂ ደስታ ያለው በማደግ ነው:: በመንፈሳዊ ኑሮም ሁልጊዜ በሽክም መኖር ሊስማማን አይገባም:: ማደግ አለብን:: ማደግ ብዙ መገለጫዎች ቢኖሩትም ከማደግ መገለጫዎች አንዱ ታናሽን መሸከም መቻል ነው:: አንድ ልጅ ታናሹን ሲሸከም አድጌአለሁ በሚል የተግባር ቋንቋ እየተናገረ ነው:: እንዲሁም እግዚአብሔር ማደጋችንን የሚለካው በእምነት የደከሙትን ስንሸከም ነው:: እግዚአብሔር እኛን መሸከሙን የምናዘክርበትና የምናደንቅበት ዋጋ ሌሎችን መሸከም ነው:: መሸከም ፍቅር ነው:: እግዚአብሔር በመሸከሙ ፍቅርን ይገልጥልናል:: በኑሮችን ለዘላለም ይሸከመናል:: በኃጢአታችን ግን እስከ ንስሐ ይታገሠናል:: «እጸድቅ ብዬ ባዝላት ተንጠለጠለች» እንደተባለው እንዳንሆን ማሰብ አለብን:: ሲሸከሙት የማያስብ ባለጌ ብቻ ነው::

እግዚአብሔር ስናጠፋ መቅጣቱ የፍቅሩ መግለጫ ነው ተብሏል:: የእግዚአብሔር ቀጥተኛ የፍቅሩ መገለጫ ግን ቅጣት አይደለም:: ሳይቀጡ የሚኖሩ ጨዋ ልጆችም አሉና ጨዋ ልጅ መሆን ይገባናል:: እርሱ ግን ዘላለማዊ የኑሮችን ዋስትና ነው::



www.ethiopinorthodox.org

ሲፈጥረንም ራሳችንን ማኖር የምንችልበትን አቅም አገናዝቦ ሳይሆን በብቃቱ ሊያኖረን ነው::

ዛሬ በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ፣ ለመጸለይ አሻፈረኝ እንላለን:: አንድ ቀን ግን በፊቱ በግድ እንቀርባለን:: ንጉሥን ካልለመዱት ፊቱ ያስፈራል:: ሲለምዱት ግን ይናፍቃል:: በእግዚአብሔር ፊትም ለመቆም እንዳንፈራ ዛሬ ፊቱን መለማመድ አለብን:: አንድ አባት በአደባባይ ሲናገሩ እንዲህ አሉ:- «እዚህ ዓውደ ምሕረት ላይ እየዘመርኩ እንድሞት ጸልዩልኝ:: በአምላኬ ዙፋን ፊት ስቀርብ ከየት መጣህ ስባል እየዘመርኩ ሳለ መጣሁ እንድል ፍጻሜዬን ከአደባባዩ ያርግልህ በሉኝ» ብለዋል:: ልገድል ስሄድ ተጠራሁ፣ ሳመነዝር ተጠራሁ፣ ሰክሬ ሳለሁ ተጠራሁ፣ ስዘፍን ሳለ ተጠራሁ፣ እገሌ ዘፋኝ ሞቶ ሳዳንቅ ሄጄ በግርግር ተረጋግጬ ከቤቴ ሳልገባ ሰማይ መጣሁ ከማለት ያድነን!!

የሰው ሁሉ ፍጻሜው እግዚአብሔር ነው:: ሀብታችን ሲያልቅ፣ ቁመናችን ሲበላሽ፣ ዝናችን ሲቀር እርሱን መፈለጋችን አይቀርምና ሳይመሽ እንጠጋው:: የእግዚአብሔር ፍቅር ሲያስደንቀን የት አግኝቼ ፍቅሬን ልግለጥለት ማለት አንችልም:: እርሱ ለሚወዳቸው የሰው ልጆች በጎነት ስናደርግ ለእርሱ ፍቅር ምላሽ መስጠታችን ነው:: ለሰማያዊው አባት ያለንን ፍቅር የምንገልጠው ለምድራዊ ልጆቹ መልካም ስናደርግ ነው:: ሰው የእግዚአብሔር ፎቶ ወይም መልክ ያለበት ነውና::

በእውነት እርሱ እግዚአብሔር በፈረሰው ቅጥራችን በኩል ሙሉ ሆኖ ስለሚቆም፣ ያስጨነቀን ነገር እንዳስጨነቀን እንዲኖር ስለማይፈቅድ፣ ታማኝነት በሌለበት ዓለምና ዘመን ታማኝ ሆኖ ስለሚገኝ፣ ከዚህ ሁሉ በላይ ስለማንከብደው ደስ ይለናል::

## ጸሎት

የማላጣህ ዕድሌ እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ:: ጉድለቴ ባያልቅም አንተ ግን አትታዘበኝም:: ነውሬን ሸፍነህ ድካሜን አግዝህ ትቆማለህና አመሰግንሃለሁ:: ዛሬማ ወግ ደርሶኝ የሰማያዊ ንጉሥ ባለሟል ሆኛለሁ:: መስፈርት ሳታወጣ የምትወድ አንተ ብቻ መሆንህን አውቄአለሁ:: የፍጡር ፍቅር ከእንካ ጋር ነው:: በባዶ አይጸናም:: እንዲሁ በባዶ ያፈቀርከኝ አንተ ነህና አመሰግንሃለሁ:: አንተ ቅደም ብሎ ሰው ለመንገድ ይግደረደራል:: እኔ ልሙት ብሎ ግን ማን ይግደረደራል!

አንተ ግን ለእኔ ሞተህልኛል:: ስቸነክርህም ትወደኛለህ ስሰቅልህም ትወደኛለህ:: አንተ ፍቅር ነህ አመሰግንሃለሁ:: እኔ መውደድም መጥላትም እችላለሁ:: አንተ ግን መጥላት የማትችል ፍቅር ብቻ ነህና አመሰግንሃለሁ:: ያንተ ነገር በቃኝ ብለውኝ ብዙዎች ጥለውኝ ሄደዋል:: ከሳሽ ሁሉ ሄዶ መሐሪው ቀርተሃል:: ሳትፈርድብኝ በሰላም ስለሸኘኸኝ በእውነት አመልክሃለሁ:: ሁሉም ያንተ ነው:: ለዘላለሙ አሜን!


www.ethiopinorthodox.org

# ምዕራፍ ስምንት

## ይቅር ባይ እንሁን

በአንድ ወቅት ሁለት ባልንጀሮች ታላቅ ምድረ በዳን እያቋረጡ ይጓዙ ነበር:: በመንገድም ሲሄዱ በአሳብ መግባባት አልቻሉም:: አንደኛውም ትዕግሥት ያጣና ባልንጀራውን በጥፊ ይመታዋል:: ያ የተመታው ግን የተቀበለውን የሚመስል ምላሽ አልሰጠውም:: ነገር ግን አንድ ነገር አደረገ:: ወደ መሬት ዝቅ ብሎ በበረሃው አሸዋ ላይ:- «ዛሬ ጓደኛዬ በጥፊ መታኝ» ብሎ በጣቱ ጻፈ:: ከጻፈ በኋላ እንደገና ጉዞአቸውን ቀጠሉ:: ሲሄዱ ሲሄዱ አንድ ትልቅ ባሕር ጋ ደረሱ:: በጥፊ የተመታውም ሳት ብሎ ከባሕር ውስጥ ጠለቀ:: በዚህ ጊዜ ባልንጀራው አብሮት ገብቶ አዳነው:: ሕይወቱ መትረፉን ያረጋገጠው ያ ሰው እንደገና ሲጽፍ ዓለት መፈለግ ጀመረ:: በዓለቱ ላይም ፊደሎቹን ቀረጸ:: «ዛሬ ጓደኛዬ ሕይወቴን አዳናት» ብሎ በዓለት ላይ ቀረፀ:: በዚህ ጊዜ ባልንጀራው ጥያቄ ተፈጠረበት:: ቅድም በጥፊ ስመታህ በአሸዋ ላይ የጻፍከው፣ አሁን ደግሞ ከባሕር ሳወጣህ በዓለት ላይ የቀረጽከው ለምንድነው? አለው:: ያም ሰው እንዲህ ብሎ መለሰ:- «የሰዎችን በደላቸውን ሲረገጥ በቀላሉ በሚጠፋው፣ ነፋስ በሚሸፍነው በአሸዋ ላይ መጻፍ ይገባናል:: መልካምነታቸውን ግን በማይጠፋው ዓለት በልባችን ላይ መቅረጽ ይገባናል» አለው ይባላል::

የአገራችን ሰው «ሁለት እግር እንኳ ሲሄድ ይጋጫል» «ዕቃና ዕቃ እንኳ ይጋጫል» ይላል:: አሳቡ አንድ አካል የሆኑ ሁለት እግሮች እንኳ በጉዞ ውስጥ መጋጨታቸው የግድ ነው፤ ግዑዛኑ ዕቃዎችም ሲጋጩ መጮኻቸው ያለ ነው:: የራሱ አስተሳሰብና ምኞት ያለው ሰውማ ቢጋጭ ምን ይደንቃል? ማለታቸው ነው:: በሁሉም የሕይወት ስፍራ ግጭት እንደ መጨረሻ ይታያል:: በቤተ ክርስቲያን፣ በትዳር፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች ... ግጭት እንደ መጨረሻ መታየቱ ያሳዝናል:: ግጭት የአንድ ትልቅ ምዕራፍ ዋዜማ ነው:: ሁሉም ሰው አሳቡን በመግለጡ ግጭት መጥቷል:: ከዝምታ ሰላም ይህ ግጭት ወደ እውነተኛ ሰላም ያደርሳል:: ዝምታ ሸንገላ ነው:: ግጭት ግን ወደ አንድነት የሚያደርስ ነው:: ግጭት የተለያየ አስተዳደግና አስተሳሰብ እንዳለን፣ መላእክት ሳይሆን ሰው እንደሆንን፣ በገነት ሳይሆን በምድር እንዳለን የሚገልጽ መሆኑን ካወቅን የምንሳሳልበት ነው:: ግጭትን በመፍራት የታመቁ አስተሳሰቦች ሲፈነዱ የእሳተ ጎሞራን ያህል ይጎዳሉ:: እሳተ



www.ethiopinorthodox.org



ጎሞራው በአግባቡ ሲተነፍስ ጠቃሚና ጤና ሰጪ፣ የተፈጥሮ ውበትም ነው:: ታምቆ ሲፈነዳ ግን የጥፋት መልእክተኛ ነው::

የግጭቱን አፈታት ካወቅንበት ጥብቅ ወደ ሆነ አንድነት እንደርሳለን:: ግጭት መፈራራትንና መተፋፈርን ያርቃል:: አንዱ በአንዱ ላይ ያለውን መንፈሳዊ ሥልጣን እያጎላው ይመጣል:: ነገር ግን ግጭትን እንደ ፍጻሜ መቁጠር አይገባንም::

በስሜንና በሸዋ የተወለዱ ሁለት ሰዎች ሲጋቡ ብዙ ጊዜ የሚገጥም ነገር አለ:: አንድ ባል የመጀመሪያውን በግ ለአዲሱ ቤቱ ሲያርድ ከፍ ያለ ክብርና ወግ ይሰማዋል:: በስሜን አካባቢ ሳንባ ከሌሎች የበጉ የአካል ክፍሎች ጋር እንደ ዱለት ተሠርቶ የሚበላ ጣፋጭ ምግብ ነው:: በሸዋ ደግሞ ሳንባ ለድመት ነው እንጂ ሰው አይበላውም:: ታዲያ በጉን ያረደው ባለ ወጉ አባወራ ሳንባውን ጥሩ አድርገሽ ሥሪው ሲል ተደጋግሞ እንደ ሰማሁት ሚስቶች ደንግጠው ወደ ጓዳ ይገባሉ:: ባልም ይደነግጣል:: እርሱ ሲያድግ ሳንባ ጣፋጭ ምግብ መሆኑን ያውቃል:: እርሷ ደግሞ ሳንባ የድመት ድርሻ መሆኑን ታውቃለች:: ባልም ልክ ነው:: ሚስትም ልክ ናት:: አንደኛው ልክ ግን ለአንደኛው ልክ መሸነፍ አለበት:: ይህ ነው የትዳር ምሥጢሩ!

ይህ ሁሉ የሚያሳየን ጥብቅ የትዳር ኅብረቶች እንኳ ሳይቀሩ ማንነት የሚቀረጽባቸውና የሚታረቅባቸው እንጂ ማንነት የሚጨፈለቅባቸው አለመሆናቸውን ነው:: ግጭቶቹ ግን በመልካም ሊወሰዱ ይገባል:: ግጭቶች የተነሡበትን መነሻ ስንፈልግ አስተዳደግ፣ ትምህርት ሊሆን ይችላል:: ግጭት ግን ሁለት ደንቦች ወይም ልማዶች እንኳ የሚሳሳሉበት ነው::

የአሳብ መለያየት ተፈጥሮ ነው:: ተፈጥሮን መሻር አይቻልም:: ተፈጥሮ ግን በመወያየት ይታረቃል:: ባልና ሚስት እኮ የሚያዋህዳቸው የተፈጥሮ ልዩነታቸው እንጂ አንድነታቸው አይደለም:: ጾታቸው የተለያየ ነው:: ልዩነቱ ግን የአንድነት ምክንያት ነው:: ልዩነት ወደ አንድነት ያመጣል:: ፍቅር ነው:: የአሳብ መለያየት እንደ ጠላት እያስተያየ ማጋደሉ ዛሬም ድረስ ዘልቋል:: ቀይ ሽብርና ነጭ ሽብር እየተባባሉ በጕዳና ሲቀላሉ የኖሩት የአንድ እናት ልጆች አመለካከትን ማስታረቅ አቅቷቸው ነው:: የአሳብ ልዩነት እንደ ጠላት ማስተያየቱ አሳዛኝና ኋላ ቀርነትም ነው::

በግጭቶች ውስጥ አንዱ ትዕግሥት ያጣና ክፉ ቃል ይናገራል፤ ክፉ ርምጃ ይወስዳል:: እርሱ ጀምሮታል ብለውም ሁለተኛውን ክፋት ብዙዎች ይቀጥላሉ:: አንተ ትዕግሥት የምታጣው ወገን አንድ ክፉ ስትናገር ሁለት ክፉ ትሰማለህ:: የዘራኸውን ስድብ አትረፍርፈህ ታመርታለህ:: አንተም ክፉ ምላሽ የምትሰጥ እርሱ በጀመረው ላይ ስለቀጠልክ የማትጠየቅ እንዳይመስልህ የሚያስጠይቀው ቅድም ተከተሉ ሳይሆን ክፉ ማድረጉ ነው:: ይልቁንም እርሱ ሲያደርገው የጠላኸውን እንዴት እንዲጠጋህና እንዲገዛህ ትፈቅዳለህ? ለክፉ ክፉ ስትመልስ የተንኰል ደቀ መዝሙር እየሆንህ ለክፋት ሠራዊት ተጨማሪ ወታደር እንደሆንህ ማሰብ አለብህ:: እርሱ በእጁ ያለውን ድንጋይ ይወርውር ባንተ እጅ ያለውን ብርቱካን ወርውርለት:: ድንጋዩ ሲያልቅበት ያንተን ብርቱካን መልሶ ይወረውርልሃል:: ክፉ ነገር ያልቃል፤ መልካም ነገር ግን አያልቅም:: ብዙ ኃይለኞች ዛሬ ደክሟቸው የትንንሽ ልጆች መጫወቻ ሆነዋል:: የእግዚአብሔር ሠራዊቶች ግን በዓመታት ውስጥ አይደክሙም:: አንድ ታዋቂ መሪጌታ ነበሩ:: እኚህ መሪጌታ ክፉ ነገር ከአፋቸው ተሰምቶ አይታወቅም:: ታዲያ አንድ ቀን ሰዎች:- «እርስዎ መቼ ነው ተሳስተው ክፉ የሚናገሩት?» ቢሏቸው:- «መልካሙ መቼ አልቆብኝ ነው ክፉ የምናገረው» አሉ ይባላል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ:- *«ክፉውን አትቃወሙ፤ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፤ ...»* (ማቴ. 5:39) ብሏል:: ትዕግሥት ማጣት፣ ክፉውን በክፉ መመለስ ደካማነት ነው:: ብርቱዎች ግን ይቅርታ የሚያደርጉና በመልካም የሚያሸንፉ ናቸው::

ለብዙዎቻችን ጠላታችንን ይቅር ከማለት ወዳጃችንን ይቅር ማለት ይከብደናል:: የመዋደዳችን ፍጻሜ መጠላላት ለምን ሆነ? ከመጀመሪያው ፍቅር የኋላው ይቅርታ ይሻላል:: አዎ «የሰዎችን በደላቸውን ሲረገጥ በቀላሉ በሚጠፋው፣ ነፋስ በሚሸፍነው አሸዋ ላይ መጻፍ ይገባናል:: መልካምነታቸውን ግን በማይጠፋው ዓለት በልባችን ላይ መቅረጽ ይገባናል::»

እኛ ግን የምናደርገው በተቃራኒው ነው:: መልካምነታቸውን በአሸዋ ላይ፣ ስህተታቸውን በዓለት ላይ እንጽፋለን:: አንገት የተሰጠን ለጌጥ አይደለም፣ ዞር ብለን ለማየትም ነው:: ስለዚህ ያለፈውን መልካም ጊዜ ዞር ብለን ማየት አለብን:: ለክፋት ሳይሆን ለመልካም ነገር ዋጋ መስጠት አለብን:: በእግዚአብሔር ዘንድ የሰናፍጭ ቅንጣት እምነት፣ የእሳት ፍንጣሪ የምታህል ምግባር ዋጋ





አላት (ማቴ. 17:20፤10:42):: በእግዚአብሔር ዘንድ የመልካም ነገር ዋጋው ብዙ ሲሆን በሰው ዘንድ ግን የክፉ ነገር ሚዛኑ ከፍ ያለ ነው::

የራሳችንን ደካማነት ስንረዳ የሌሎችን ደካማነት ለመረዳትና ይቅርታ ለማድረግ ዝግጁ እንሆናለን:: ሰው ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ካገኘን ይቅርታ የማይከብደን ሰዎች እንሆናለን:: እውነተኛ ፍቅርም በክፋት ተሸንፎ ቂመኛና በቀለኛ የሚሆን ሳይሆን በመልካም አሸንፎ በዳዩን ሰው ለንስሐ የሚጋብዝ ነው:: በዓለም ላይ ከሰዎች ጋር የማንነካካበት ኑሮ ስለሌለን አስተውለን ካየነው የብዙ ሁከታችን ምንጩ የይቅርታ ሕይወት ማጣት ነው:: ይቅርታ የጎደለው ልብ ሁሉም ነገር ይከብደዋል::

ሰዎችን ከማኩረፍና ከመሸሽ በላይ የምናስተምራቸው በይቅርታ ነው:: ይቅርታ ማድረግ የወደቀው እንዲነሣ ዕድል መስጠት ነው:: በዓለም ላይ ትልቅ ሥራ የሚሠራው ከተአምራት ይልቅ በይቅር ባይነት ነው:: በክፋት እየመረረች ያለችውን ዓለማችንን የሚያጣፍጡ ይቅር ባይና አፍቃሪ ሰዎች ከሌሉ የሰው ሕይወት ፈጽሞ ተስፋ የሌለው ይሆናል:: ስለዚህ ይቅር ባይ እንሁን! ይቅር ያልናቸው ሰዎች ከበደሉን በላይ ይክሱናል:: ይቅርታ ያበላሸው ሰው እንዲያስተካክል ዕድል መስጠት ነው:: ሕጻን ልጅ ወድቆ የሚነሣው ዙሪያውን አይቶ የሚጠብቁት ሰዎች ድጋፍ ከሰጡት በኋላ ነው:: ተስፋ የሚያደርገው ሰው ከሌለ ለመነሣት አያስብም:: እዚያው እንቅልፍ ይይዘዋል:: ሰዎችም ከስህተታቸው የሚመለሱት የውዳጆቻቸውን ይቅርታ ሲያገኙ ነው:: አሊያ እንደ ወደቁ ይቀራሉ:: ሌባ የሚባሉት የሚሰርቁትን ንብረት ጠብቁ ስንላቸው ከደህነኛው በላይ ይጠብቃሉ:: ፀጥታ ሲጠፋ የበጥባጮቹን አለቃ አደራው ላንተ ነው ሲባል ሌት ተቀን ተግቶ ሰላምን ያስከብራል:: ሰዎች ባመናቸው መጠን ይታመኑልናል:: ይቅርታ የወደቁ ሰዎች እንዲነሡ ዕድል መስጠት ነው::

ከአንድ ኮሚቴ ጋር መስማማት ያልቻልኩበት ዘመን ትዝ ይለኛል:: ስለ ኮሚቴ ካነሣሁ አንድ ወዳጄ:- «በኮሚቴ ቢሆን ኖሮ እስራኤል እስከ ዛሬ ከግብፅ አይወጡም ነበር:: ሙሴ ግን እግዚአብሔርን እያዳመጠ ሕዝቡን አሻገረ» ያለኝ የማልረሳው የሚያስቅ ግን ቁምነገር ያለበት ንግግር ነው:: ታዲያ አንድ አባት ስለ ጉዳዩ ሲያነጋግሩኝ:- «ልጄ በአንድ አፍ ውስጥ የሚኖሩትን ጥርስንና ምላስን አስታውስ:: እነዚህ አካላት ተፈጥሮአቸው የተለያየ ነው:: ጥርስ ነጭ ነው፣ ምላስ ቀይ ናት:: ጥርስ ጠንካራ ስለታም ነው፣ ምላስ በጣም ለስላሳ ናት:: አፍ ሲከፈትላት ምላስ ትወጣለች::



www.ethiopinorthodox.org

ሲከደን በገዛ ጎረቤቷ ላለመጎዳት ትሸሻለች:: ጥርስ ያደማውን እጅ ምላስ ትልሳለች:: ጥርስ ሲያኝክ ምላስ ታርስለታለች:: የፊት ጥርስ ማኘክ ሲከብደው ወደ መንጋጋው እህሉን በመውሰድ ትራዳዋለች:: ግን በአንድ ቤት ይኖራሉ:: እኛም መልካችን፣ አቅማችን፣ የሥራ ድርሻችን የተለያየ፣ አንዳችን ስለታም አንዳችን ለስላሳ ብንሆንም ተቻችለን መኖር ይገባናል» አሉኝ:: አዎ እሾህ ያላቸው ጃርቶች ተጠባብቀው ይሄዳሉ:: አንዱ ያንዱን ሙቀት ለማግኘትና ብርዱን ለመከላከል መወጋጋታቸውን ይችላሉ:: እኛም ገና ባልተለወጠ ማንነት ውስጥ እንደ መኖራችን ሁላችንም ያልተነቀለ እሾህ አለን:: ተገልለን ለመቀመጥ የዓለሙ ብርድ ይገድላል:: ከመሞት መቍሰል የተሻለ ነውና ልንጠጋጋ ይገባናል:: ድካማችንን እንደ አደጋ ከመቍጠር ተፈጥሮ መሆኑን ማሰብ ያበረታናል:: ክፉ ጠባይ ባለቤቱም እየጠላው አብሮት ይቆያል:: እግዚአብሔር ግን ይለውጣል:: ተሠርተን እስከምናልቅ መሸካከም ይገባናል:: አንድ ሰው:- «ማን ፈጠረህ?» ቢሉት «እግዚአብሔር» ካለ በኋላ «ግን ገና አላለቅሁኝም» አለ ይባላል::

ይቅርታ በነበረን ታሪክ ላይ ያልነበረንን አዲስ ታሪክ በሕይወታችን ላይ ይጨምርልናል:: የበደለንን ብናስፈርድበት ይህ ለዓለም አዲስ ነገር አይደለም:: ይቅር ብንለው ግን አዲስ ታሪክ ነው:: ይህ ብቻ አይደለም በይቅርታ ሊማሩ የማይፈልጉ ሰዎችን እናስተምርበታለን:: በእውነት የሚከብደን ይቅር ማለት ብቻ ሳይሆን ይቅርታ መቀበልም ይከብደናልና እግዚአብሔር ይጎብኘን::

አዎ እግዚአብሔር በኃጢአታችንና በድካማችን ተሸክሞናል:: ራርቶ ይቅር ብሎናል:: ይህ ትዕግሥቱ ከማረከን እኛም ይቅር ባዮች ልንሆን ይገባናል:: እግዚአብሔር በድካማችን ብቻ ሳይሆን በፍላጎታችንም ተሸክሞናል:: እኛም የሰዎችን በደላቸውን ብቻ ሳይሆን ፍላጎታቸውንም በትዕግሥት ልናሟላላቸው ይገባናል:: በእውነት ትዕግሥትን ገንዘብ በማድረግ ይቅር ባይ እንሁን!

## እናስተውል

አንድ ሰው:- «በዚህ ዓለም ላይ ያለኝ ወዳጅ ልብስ ሰፊዬ ነው:: እርሱ ብቻ በትላንቱ አይለካኝም» ብሏል:: ልብስ ሰፊ ትላንትና ለክቶ እንደ ሆነ ዛሬም ስንሄድ ይለካናል እንጂ በትላንቱ ልኪት ተረጋግቶ አይቀመጥም:: እውነተኛ ወዳጅም በትላንትናው ማንነት የማይለካ ዛሬም በመለወጣችን የሚያምንብን ነው:: የአገራችን ሰው:- «አንዴ ሌባ ካሏት ብትቆርብም አያምኗት» እንደሚል የአንድ ቀን ስህተት የሁልጊዜ ስህተት፣ የአንድ ቀን





ጥፋተኝነት የሁልጊዜ ጥፋተኝነት አድርገን መውሰድ በእውነት ኃጢአት ነው:: ሰው ይለወጣል:: ሰው እንደሚለወጥ ካላመንን ሰውነታችንን እያጣን ነው:: እኛም እንደ ቀድሞ አይደለንም:: ሰዎችም እንደ ቀድሞ አይሆኑም:: ይህ ዓለም በየዕለቱ ትምህርት አለውና::

የሰዎችን የቀደመ ስህተታቸውን ልንረሳላቸው አልቻልንም:: ንስሐ ገብተውበት ይሆናል:: እኛ ግን ይቅርታውን ሳይሆን ስህተቱን ስናወድስ እንኖራለን:: ታላላቅ ሰዎችም ቢሳሳቱ ሊገርመን አይገባም:: ታላቅነታቸው ሰው መሆናቸውን አያስቀረውምና:: ደካማ ሰዎች በታላላቆች ስህተት ሲሳለቁ ይኖራሉ:: ቃሉ:- *«እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ»* (1ቆሮ. 10:12) ይላል::

አንድ ወዳጄ የነገሩኝ ታሪክ ትዝ ይለኛል:- ሁለት መነኮሳት በመንገድ ሲሄዱ ወንዝ ዳር ይደርሳሉ:: አንዲት ሴትም ውሃ ሞልቶባት ለመሻገር ተጨንቃ ያገኟታል:: አንደኛው መነኩሴ ልቡ ራርቶ «ላሻግራት» ይለዋል:: ጓደኛው መነኩሴም:- «በገዳማችን ሕግ ከሴት ጋር መነጋገር አይፈቀድም፣ የገዳም ሕግ የመነኮሳትን ደንብ ታፈርሳለህ» ይለዋል:: ልቡ የራራው መነኩሴም እምቢ ብሎ ተሸክሞ አሻገራት:: በመንገድ ሲሄዱ እንዴት ያሻግራታል? እያለ አንደኛው መነኩሴ ማጉረምረም ይጀምራል:: የራራውም መነኩሴ «ምን ሆነህ ነው እንዲህ የምትበሳጨው?» ይለዋል:: ያም መነኩሴ «እንዴት ሴት ትሸከማለህ? የመነኮሳትን ደንብ አፍርሰሃል» ቢለው የራራው መነኩሴ መልሶ:- «እኔስ አንዴ ተሸክሜ አሻገርኳት፤ አንተ ግን እስከ አሁን ተሸክመሃታል» አለው ይባላል::

ሰዎች የጣሉትን ሸክም እኛ ተሸክመንላቸው እየተበሳጨን እንዳይሆን እግዚአብሔር ይግለጥልን:: ከዚህ ሁሉ በላይ ይቅር እንባባል:: እናቶቻችን የቂም ሙዳዮች፣ እንዳይበሰብስ የሚጠብቁት ናቸው:: እገሌን በዓይኔ አያሳየኝ የሚሉት ምክንያቱ ምንድነው? ብንላቸው በመንግሥቱ ንዋይ ግርግር ጊዜ እንዲህ አድርጋኝ ይላሉ:: እስከ ዛሬ በዚህ ክስተት ይበሳጫሉ:: በደሉ የተፈጸመው ግን በ1953 ዓ.ም. ነው:: ቂምን መንከባከብ አረም ስንዴ ላይሆን መልፋት ነው:: ይልቁንም በዛሬው ዘመን ክርስቲያኖችን ከማስታረቅ ዓለማውያንን ማስታረቅ እንኪቀል መራሮች ሆነናልና በእውነት ይቅር እንባባል::



www.ethiopinorthodox.org

## ጸሎት

አምላኬ ሆይ! ምሕረትህ ለዘላለም ነው። እኔ ግን ቂሜ ለዘላለም ነው። አንተ የጥንቱን ንጹሕ ተፈጥሮአችንን ታያለህ። እኔ ግን ከመጀመሪያው ፍቅር ለኋላው ጠብ ዋጋ እሰጣለሁ። ጌታ ሆይ ያንተን ይቅርታ ማስተላለፍ ያልሆነልኝ የልቤ መስተዋት የቆሸሸብኝ ሰው ነኝ። ይቅር ማለት እየተናነቀኝ መንገዴን የትካዜ አድርጌዋለሁ። ራሴን ብቻ ይቅር ብዬ ሰውን ሁሉ ተቀይሜአለሁ። እባክህን የይቅርታ ሰው አድርገኝ። ከተደረገልኝ መልካም ነገር ለተደረገብኝ ክፉ ነገር ዋጋ እሰጣለሁ። መልካሙን ቀን፣ ወዳጆቼ ያደረጉልኝን የማይቆጠረውን ውለታ እየረሳሁ ተቸግሬአለሁ፣ ፍቅሬ ነጻ ሳይሆን ሰጥቶ መቀበል የሚፈልግ የሰው ፍቅር ነውና ያንን ሲያጣ ልቤን ሸካራ አደረገው። እባክህን በመንፈስህ ዘይት ውስጤን አለስልሰው። የሚወዱኝን መውደድ ሳልጀምር ጠላቶቼን ለማፍቀር እታገላለሁ። ለበደሉኝ ይቅርታን ለሚወዱኝም ምላሽ የምሰጥ ሕያው ሰው አድርገኝ። ወትሮም በማላፍርበት ስምህ ለዘላለሙ አሜን!



## ምዕራፍ ዘጠኝ
## ዕድል ነው

ራሳቸውን ያልቻሉ ችግረኛ ቤተሰቦች ስላሉአቸው የሚያዝኑ የሚከፉ፡- «መቼ ነው የእኔን ኑሮ የምኖረው?» የሚሉ፣ «ወይ ከደሀና ተወለድ፣ ወይ ከደሀና ተጠጋ» እያሉ ድህነትን እንደ በሽታ ባለጠግነትን እንደ ጤንነት የሚቆጥሩ፣ ከገንዘብ ድህነት የምግባር ድህነት እንደሚያይል የማይረዱ ብዙ ወገኖች አሉ። የሕይወት ሙላቷ ለኃላፊነት መብቃት፣ ስለ ሌሎች ማሰብ መጀመር፣ ወዳየነው ራእይ መገስገስ ነው። ድሆችና ችግረኛ ቤተሰቦችን ለመደገፍ መኖርም ትልቅ ትዳር ነው። በአገራችን ቋንቋ አንድ ሰው ትዳር ያዘ የሚባለው ከሌላ ተቃራኒ ወገን ጋር ኅብረት ሲያደርግ ብቻ ሳይሆን የራሱን ቤትና ንብረት ማደራጀት፣ ለሌሎች መጠጊያ ማበጀት ሲጀምር ትዳሬን አበጀሁ ይላል፣ ትዳሩን አበጀ ይባላል። የተመሠረተው ቤተሰቡ እየፈረሰ ሌላ ቤተሰብ መመሥረት፣ የተወለዱት ልጆች ለሞት እየተቃረቡ ሌሎች ልጆችን ወደ ዓለም ለማምጣት ማሰብ አስፈላጊ አይደለም።

የሚረዱት ቤተሰብ ያላቸውና የሚረዳ ቤተሰብ የሌላቸው ወገኖች የሕይወታቸው ደስታ እኩል አይደለም። ቤተሰባቸውን የሚረዱት በሕይወታቸው በጣም ደስተኞች ናቸው። ለተቸገረው ቤተሰባቸው የሚሰጡት ሲያገኙ በእልልታ ይዘላሉ። የቤተሰባቸው የተከፈተ ጉሮሮ እየታያቸው በየመንገዱ ያለውን የመጠጥ፣ የዝሙትና የዘፈን ግብዣ እየጠቀጠቁ ያልፋሉ። እነዚህ ሰዎች ስለ ራሳቸው መኖር ቢጠሉ እንኳ ስለ ድሆች ቤተሰቦቻቸው መኖርን ይፈልጋሉ። ምክንያቱም እንኳን የሰው ፍቅር የውሻ ፍቅር እንኳ ዕድሜ ይጨምራልና። ድሆች ቤተሰቦቻቸው ደስታቸው፣ የቅድስና አጋሮቻቸው፣ የመኖር ምክንያታቸው ናቸው።

ራስን የማጥፋት ወንጀል የበረከተው በደሃዋ አፍሪካ ሳይሆን የተሟላ ኑሮ አለ በሚባልባቸው በስላማውያን እንደ እነ ስዊድን ባሉ አገሮች ላይ መሆኑ ይገርማል። እነዚህ አገሮች ዜጋቸው በሰላም ስላደረ የሚከፍሉ፣ ፍላጎትን ያሟሉ ቢሆኑም ተስፋን ግን ማሟላት አልቻሉም። ስለዚህ ብዙ ዜጎቻቸው ራሳቸውን በማጥፋት ያልቃሉ። ለልጄ ለእናቴ ብለው አያስቡም። ልጁ ከተወለደ ጀምሮ የመንግሥት ደሞዝተኛ ነው። ሁሉም የራሱ የሆነ የተሟላ ኑሮ አለውና ስለዚህ አይፈላለጉም። ድሆቹ ሕዝቦች ሀብትን ተስፋ ያደርጋሉ። እነዚህ ግን



www.ethiopinorthodox.org

ሀብት ባዶ ሆኖባቸዋል:: ድሆቹ ሕዝቦች በጠባብ ቤት ተደራርበው ይኖራሉ:: እነዚህ ግን ለአካለ መጠን ሲደርሱ ወደ ተሠራ ቤት ይገባሉ:: ድሆቹ ሕዝቦች ትዳራቸውን ለማቅናት ሲታገሉ እስከ ሞት አብረው ይኖራሉ:: እነዚህ ግን ትዳርን በኮንትራት ውል ይፈጽማሉ:: የማግኘት ትልቁ ፈተና እርካታ ማጣት ነውና እርካታ በማጣት ሲሰቃዩ ለምን እኖራለሁ? ብለው ይጠይቃሉ:: የሚኖሩለት ጌታና የሚኖሩላቸው ድሆች ስለሌሏቸው ራሳቸውን ያጠፋሉ:: እነዚህን ተስፋ ያጡና የምቾት መከራ የሚያሰቃያቸውን ሕዝቦች ለመርዳት ገንዘባቸውን እየተቀበሉ የአፍሪካ ሕፃናትን እንዲረዱ መደረግ ተጀመረ:: በገንዘባቸው የሚያሳድጉትን ሩቅ ያለውን ሕፃን ፎቶ በማምጣት:- «አንተ ለምን እኖራለሁ ትላለህ፣ መኖርህ ግን ይህን ሕፃን ያሳድጋል» ሲሏቸው ተስፋቸው መለምለም፣ ሕይወታቸው ማበብ ጀምሯል::

ደስታ በመልክአ ምድር፣ ደስታ በጊዜ ውስጥ አልተቀመጠችም:: ደስታን ለማግኘት በባሕር በአየር ብንሄድ ደስታ አይገኝም:: መጠጥና ዝሙትም እንኳን ደስታ ሊሰጡን የደስታ ተቀኂ ናቸው:: ሐሰተኛ ሳቅም ጉልበትን ይጨርሳል:: እግዚአብሔር ግን የእኛን ደስታ የደበቀው በሌሎች ጉድለት ውስጥ ነው:: የሌሎችን ጉድለት ስንሞላ የእኛም የልብ ክፍተት ይሞላል:: አንድ ደራሲ:- «የእኔ እምነት ይህ ነው:: ደስተኛ መሆን ብቻ ጥሩ ነው:: ደስተኛ ለመሆንም ቦታህ እዚህ፣ ጊዜውም አሁን፣ መንገዱም ሌሎችን መርዳት ነው» ብሏል::

ብዙ ባለጠጎች የኑሮ ቅሬታ አላቸው:: ዛሬ ማንም የሚበላውን ገንዘባቸውን ያቺ ደሃ እናታቸው ሳትበላ ትኩስ እንጀራ እንዳማራት መሞቷ ከቅሬታቸው ዋነኛው ነው:: ዛሬ እናታቸው ማግኘት ቢችሉ ወርቅ አልብሰው፣ እንደ እቴጌ ባከባበሯት ነበር:: ነገር ግን አልቻሉም:: አዎ መርዳት መቻልም ዕድል ነው:: ይህ ዕድል የማይገኝበት ጊዜ አለና:: ስለዚህ ድሆች ቤተሰቦቻችን መርዳት በመቻላችን ከፍ ያለ ደስታ ሊሰማን ይገባል::

ድሆች የምንላቸው መሠታዊ ፍላጎት የጎደለባቸው ሰዎች ነው:: የሰው ልጆች ቀን በሚሰጥና ቀን በማይሰጥ ችግሮች ውስጥ ይኖራሉ:: ድሆች ቀን በማይሰጥና መታገሥን በማያውቅ በሆድ ጥያቄ ተፋጠዋል:: ምናልባት የራሳችን የሕይወት ጥያቄ ስላስጨነቀን ስለ ማንም ግድ አይለን ይሆናል:: ግን ጥያቄያችን ቀን የማይሰጥ ነው? አንዳንዴ የእኛ ትርፍ ሳንቲም ለድሆች ዋና ነገ ሊሆን ይችላል:: የእኛ ተጨማሪ ምግብ ለእነርሱ ከሞት ማምለጫ ይሆናል::



የእስራኤል ልጆች ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲገቡ ከተሰጣቸው የቅድስና ሕግ አንዱ የሌሎችን ችግር እንደ ራሳቸው እንዲያዩና እግዚአብሔር ያሳያቸውን ፍቅር ለጎረቤታቸው እንዲያሳዩ ነበር:: *«በአገራችሁ ውስጥ ከእናንተ ጋር እንግዳ ቢቀመጥ ግፍ አታድርጉበት:: እናንተ በግብፅ ምድር እንግዶች ነበራችሁና ከእናንተ ጋር የሚቀመጥ እንግዳ እንደ አገር ልጅ ይሁንላችሁ፣ እርሱንም እንደ ራስህ ውደድ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ»* (ዘሌዋ. 19:33-34)::

ያደግንበትን ሁኔታ ያሳለፍነውን የሕይወት መሰናክል ብዙ ጊዜ እንረሳለን:: ሌሎች በስንፍናቸው የወደቁ እኛ ግን በጥረታችን ለዚህ የበቃን እየመሰለን እንስታለን:: አንዳንዴም በድፍረት እንናገራለን:: ስለዚህ ድህነትና ችግርን ካላዩ ሰዎች ይልቅ ያየነው እኛ እንጨክናለን:: እግዚአብሔር ግን:- *«እናንተ በግብፅ ስደተኞች ነበራችሁና ስለዚህ ስደተኛውን ውደዱ»* ይለናል (ዘዳ. 10:19): ወይም እኛ ሲደርስብን የማንፈልገው ክፉ ነገር በሌሎች ላይ ሲደርስ ያስችለናል:: ምን ዓይነት መንፈስ ነው!

*«የእርሻችሁን ድንበር ፈጽማችሁ አትጨዱ»* (ዘሌ. 19:9) ተብለናልና ገንዘባችንን ጨርሰን መብላት የለብንም:: ለድሆች ወገኖቻችን ማስቀረት አለብን:: በኦሪት ዘዳግም 15:7-11 የተገለጠው ቃል በእውነት ያራራል:-

*«አምላክህ እግዚአብሔር በሰጠህ በአገርህ ደጅ ውስጥ ከሚኖሩ ከወንድሞችህ አንዱ ቢደኸይ÷ ልብህን አታጽና÷ በድሀው ወንድምህ ላይ እጅህን አትጨብጥ:: ነገር ግን እጅህን ለእርሱ ክፈት÷ የለመነህንም አስፈላጊውን ነገር አበድረው:: ሰባተኛው ዓመት የዕዳ ምሕረት ዓመት ቀርቦአል ብለህ ክፉ አሳብ በልብህ እንዳታስብ÷ ለድሀውም ወንድምህ አንዳች የማትሰጥ እንዳትሆን÷ ዓይንህም በእርሱ ላይ ክፉ እንዳይሆን÷ እርሱም ወደ እግዚአብሔር በአንተ ላይ እንዳይጮኽ÷ ኃጢአትም እንዳይሆንብህ ተጠንቀቅ:: እጅህን በምትጥልበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ስለዚህ በሥራህ ሁሉ ይባርክሃልና ፈጽመህ ስጠው÷ በሰጠኸውም ጊዜ በልብህ አትጸጸት:: ድሆች ከምድሪቱ ላይ አያልቁምና ስለዚህ እኔ:- በአገርህ ውስጥ ላለው ድሀ ለተቸገረውም ወንድምህ እጅህን ትከፍታለህ ብዬ አዝዝሃለሁ»* (ዘዳ. 15:7-11)::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም:- *«ድሆችስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና»* (ዮሐ. 12:8) እንዳለ ድሆች ፍቅርና ልግስናችንን



www.ethiopinorthodox.org

የምንገልጥባቸው ናቸው:: እግዚአብሔር ሲፈጥረን ጠባያቱን ስላካፈለን በቸርነት ውስጥ ያለውን ደስታ ፈላጊዎች ነን:: በመስጠት ውስጥ ደስታ አለ (የሐዋ.ሥራ 20:35):: ይህንንም ደስታ የሚሰጡን ድሆች ናቸው:: ስለዚህ የመባ ስጦታ ፍቅርን፣ ፍቅርም ልግስናን፣ ልግስናም ደስታን ያስገኙልናል:: ጌታ ልዝብ ቀንበርና ቀላል ሸክም ሰጥቶናል (ማቴ. 11:30)፣ ይህም ስለ ሌሎች የሚሰማን ኃላፊነት ነው:: ድሆች አደራዎቻችን ናቸውና ልንጠነቀቅላቸው ይገባል::

## ድሆች በረከቶቻችን ናቸው

### 1. የእግዚአብሔርን በረከት እናይባቸዋለን

የአይሁዶች ምሳሌ:- «በዚህ ዓለም ባለጠጎች ድሆችን፣ በሚመጣው ዓለም ግን ድሆች ባለጠጎችን ይረዳሉ» ይላል:: አንድ ሰውም:- «የድሆች ጉያ፣ የመበለቶች ቤት፣ የልጆች አፍ ለዘላለም የሚኖሩ ጐተራዎች ናቸው» ብሏል:: በአጠቃላይ አነጋገር ድሆች በረከቶቻችን ናቸው::

እውነተኛ ስጦታ ብድር መመለስ ለማይችሉት የምናደርገው ቸርነት ነው:: እግዚአብሔርም የድሆች አባት፣ ክርስቶስም የምስኪኖች ወንድም (ማቴ. 25:40) ነውና ብድራቱን ይመልሳል:: የድሆች መባ በእግዚአብሔር ፊት የሚናገር መሥዋዕት ነው:: በድሆች መባ ስንታመን:-

- ሥራችን ይባረካል (ዘዳ. 14:29፤ ምሳሌ 22:9)፤
- ጸሎታችን ይሰማል (ምሳሌ. 21:13፣ የሐዋ. 10:4)፤
- ሀብታችን ይበዛል (ምሳ. 28:27)፤
- በደዌ ቀን እግዚአብሔር ይፈውሰናል (መዝ. 40(41):1-13፤ የሐዋ. ሥራ 9:36-42)::

### 2. ወደ ቸርነት ሙላት ያደርሱናል

ለችግረኞች ማዘን ብቻ አይበቃም፤ ምክንያቱም ማስተዛዘን እኔ ደግ ሰው ነኝ የሚለው አስደሳች ስሜት ብቻ ሊሆን ይችላል:: ከሀዘንም ጋር መልካም መሥራት ያስፈልጋል:: ቃሉም:- «*... ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው÷ ወንድሙም የሚያስፈልገውን ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን÷ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል? ልጆቼ ሆይ÷ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ*» ይለናል (1ዮሐ. 3:17)::





ከማዘን አልፈን ማድረግ ስንጀምር፣ ከትርፍ መስጠት አልፈን ማካፈል ስንጀምር ያን ጊዜ ወደ ቸርነት ሙላት እንደርሳለን:: በቸርነት ውስጥ ደግሞ የተገለጠ ፍቅር ይታያል:: ስለዚህ ድሆች የእግዚአብሔርን ጠባያት እንድናገለብት ያግዙናል::

ውድ አንባቢ ሆይ!
የቃሉን ጥያቄ ከአሉታዊ አንጻር ብቻ ነው እየታዘዝን ያለነው:: አዎንታዊ ምላሽ ከሌለን ግን መታዘዝ ሙሉ አልሆነም ማለት ነው:: ክፉ አለማድረግ አሉታዊ ርምጃ ነው:: በጎ ስናደርግ ብቻ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተናል:: ከክፉ ርቄአለሁ ነጻነትና ደስታ ግን አይሰማኝም? ብንል በጎ ማድረግ ገና ይቀረናል:: በእውነት ከሠራናቸው ኃጢአቶች ያላደረግናቸው መልካም ነገሮች ይበዛሉ::

የእግዚአብሔር ቃል የምንርቀውን ብቻ ሳይሆን ልናደርገው የሚገባን ነገር እንዳለ ይነግረናል «*ሕዝቡም:- ምን እናድርግ? ብለው ይጠይቁት ነበር:: መልሶም:- ሁለት ልብስ ያለው ለሌለው ያካፍል÷ ምግብም ያለው እንዲሁ ያድርግ ይል ነበር*» (ሉቃ. 3:10-11):: ክርስትናው ሲገባን «ምን እንተው?» ከማለት «ምን እናድርግ?» ወደ ማለት እናድጋለን (የሐዋ.ሥራ. 2:37):: በእውነት ወደ መልካም ነገር አንድ ርምጃ ስንሄድ ብቻ ከክፋት አንድ ርምጃ እንርቃለን::

የብዙ ሃይማኖቶች መመሥረቻ ቃል «ባንተ ሊደረግብህ የማትሻውን ክፉ ነገር በሌላው ላይ አታድርግ» የሚል ነው:: ኮንፊዩሼስ፣ ሙሴ፣ መሐመድ፣ ቡድሃ፣ በሃኢ ይህን መልእክት ይዘው ወደ ዓለም መጥተዋል:: የክርስትናችን መሥራች የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ግን «ሊያደርጉልህ የምትፈልገውን አንተ ደግሞ ለሌላው አድርግ» የሚል ለተጨነቀችው ዓለም የአዎንታዊና የሰላም ቃል ይዞ መጣ (ሉቃ. 6:31)::

ጌታችን ዳግመኛ ለፍርድ ሲመጣ የሚጠይቀን ስለሠራነው ኃጢአት ሳይሆን ስላላደረግነው መልካም ነገር መሆኑ ይገርማል:: እኛ ሰርቀን ስለሮጥነው ብቻ የሚጠይቀን ይመስለናል፣ የተራበውን ወንድም በጭካኔ ስላለፍነው ይጠይቀናል (ማቴ. 25:34-46):: በእውነት ከሠራናቸው ኃጢአቶች ያላደረግናቸው መልካም ነገሮች በጥፋት መንገድ



www.ethiopinorthodox.org

ላይ አቊመውናል። (ዳግመኛም «የሚለውጥ ፍቅር» የሚለውን መጽሐፍ ገጽ 25-28 ተመልከቱ)።

### 3. <u>እርካታን ይሰጡናል</u>

ብዙ የውጭ አገር ዜጎች በድሃ አገሮች ላይ ከምስኪኖችና ከአካል ጉዳተኞች ጋር ተፋቅረው የምናያቸው ለምን ይመስላችኋል? የአገራቸው ውብ ሕንጻዎች፣ የተሟላው አኗኗር ከሚሰጣቸው እርካታ በላይ እነዚህ ድሆች ስላረኳቸው ነው። አስተውሉ ማንም ለኪሣራ አይሠራም። በዓለም ላይ ያሉ ታላላቅ እቅዶች ሳይቀሩ ጊዜያዊ ናቸው። በሰዎች ላይ የሚኖረን እቅድ ግን ዘላለማዊ ነው። አንድ የቻይና ምሳሌ እንዲህ ይላል፡- «የአንድ ዓመት እቅድ ካለህ ሩዝ ዝራ፣ የአምስት ዓመት እቅድ ካለህ ዛፍ ትከል፣ የዘላለም እቅድ ካለህ ሰው ትከል።»

መቼም ለድሆች ከተሰጣቸው ጸጋ አንዱ በትንሹ መርካት ነው። የምድር ፍላጎቶች እየተሟሉ በመጡ ቊጥር እርካታ እየቀነሰ መምጣቱ ይገርማል። ድሆች ግን መርካት ቅርባቸው ነው። ታዲያ በትንሹ ስጦታችን ሲመርቁን፣ በደስታ ሲፈነጥዙ፣ የምርቃት ብዛት ሲያወርዱ፣ ጎንበስ ቀና እያሉ ፈጣሪያቸውን ሲያመሰግኑ ስናይ እኛም መርካት እንጀምራለን። ይህን ለእኩያችን ብናደርግ ግን ምን እንደሚመልስልን ይጨነቃል እንጂ አይረካም። እውነተኛ ድሆች ማለት እውነተኛ ተቀባዮች ናቸው።

በመንፈስ ጭንቀት ወይም ባለመርካት የሚሰቃዩ ሰዎችን ስንመክር ውሎአቸውን ከድሆች ጋር እንዲያደርጉ ብንመክር ውጤታማ እንሆናለን። ምክንያቱም እግዚአብሔር የእኛን ደስታ በሌላው ጎዶሎ ውስጥ አስቀምጦታልና። የቅድሙን ጥቅስ እንድገመው፡- «የእኔ እምነት ይህ ነው፡- ደስተኛ መሆን ብቻ ጥሩ ነው። ደስተኛ ለመሆንም ቦታው እዚህ፣ ጊዜውም አሁን፣ መንገዱም ሌሎችን መርዳት ነው።»

### 4. <u>ፍቅርን እንገልጥባቸዋለን</u>

እማሆይ ትሬሣ ድሆችን ስለ መርዳት በተናገሩበት ወቅት «እግዚአብሔር ማለት በድርጊት የሚገለጽ ፍቅር ነው» ብለዋል። ፍቅር ስሜት ሳይሆን ተግባር ነው። ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ከምንገልጥባቸው መንገዶች አንዱ ስለ ሌሎች ያለን አሳብ ነው። ጌታ ድሆችን ታናሽ ወንድሞቼ ብሏቸዋል። ለእነርሱ ያደረጋችሁትም





ለእኔ ያደረጋችሁት ነው፣ ለእነርሱ ያላደረጋችሁት ለእኔ ያላደረጋችሁት ነው ብሏል (ማቴ. 25:40-45)። የተገለጠ ፍቅር ሕይወት ነው። የክርስትናው ትልቁ መመሪያ «እግዚአብሔር ያሳየህን ፍቅር አንተም ለጎረቤትህ አሳይ» የሚል ነው።

በዓለም ላይ ሁሉም ሰው የሚሰማውና የሚረዳው ቋንቋ ፍቅር ነው። ብዙ እርዳታ ሰጪዎች ወደ አፍሪካ ድሆች ሲመጡ ያለ ቋንቋ ከሕዝቡ ጋር ተግባብተዋል። ፍቅር ከቋንቋ በላይ ነው።

ድሆች እውነተኛ ወዳጅ ናቸው። ይልቁንም በችግራችንና በሞታችን ሰዓት ጥልቅ ፍቅራቸውን ይገልጣሉ። የሚሰጡን ነገርም ዋጋው ከገንዘብ በላይ ነው። እኛ ጓደኛ የሚመስለን እኩያችን ብቻ ነው። በዚህች ሰዓት የእኛን እርዳታ የሚፈልግ ሁሉ ግን ጓደኛችን ነው።

### 5. <u>ለሕይወታችን ጣዕም ይሰጡናል</u>

ለራሳችን ብቻ የምንኖር ከሆነ እርካታ የለንም። ምክንያቱም ከተፈጠርንበት ዓላማ ውጭ እየኖርን ስለሆነ ነው። መኖር የሚለካው ምን ያህል ለራሴ ሰብስቤአለሁ? ተብሎ ሳይሆን ምን ያህል ለሌሎች መኖር ችያለሁ? በሚለው መስፈርት ነው። ብዙዎች በቅንጦታቸውና በራስ ወዳድነታቸው የማይረኩትን ያህል ለሌሎች መሥዋዕት የሚሆኑ ሰዎች ሲረኩ ይታያሉ።

የምንኖርለት ነገር በግድ ያስፈልገናል። የምንኖርለት ነገር ከሌለን መኖር ብዙም አይጥመንም። አንድ ቀን ሕይወት ከባድ ጥያቄ ትጠይቀናለች። «ለምን ትኖራለህ?» ይህን ጥያቄ መመለስ ያልቻሉ ብዙዎች ሁሉም ነገር ተሟልቶላቸው እንኳ ራሳቸውን አጥፍተዋል። ስለዚህ «ያንተ መኖር ለእነዚህ ይጠቅማል» የሚል ምላሽ ሲያገኙ ብቻ እንደገና መኖር ይፈልጋሉ። ቅዱስ ጳውሎስ ስለራሱ መኖር ባልፈለገበት ሰዓት ስለሚያገለግላቸው ሰዎች መኖርን ፈልጓል (ፊልጵ. 1:23-24)።

### 6. <u>ለኀላፊነት ያበቊናል</u>

ኀላፊነትና ተጠያቂነትን መሸሽ በራሳችን ላይ ያለንን ስጋት ያባብሰዋል። ኀላፊነት የማይሰማው ሰው የክፋት ሁሉ መሣሪያ ነው። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ፡- *«ሰው በታናሽነቱ ቀንበር ቢሸከም መልካም ነው»* የሚለው (ሰቆቃወ ኤር. 3:27)።



www.ethiopinorthodox.org

ብዙዎች በድህነት ማደጋቸውንና ገና በልጅነታቸው ለኃላፊነት መብቃታቸውን ይጠሉታል:: በዚያ ሕይወት ባያልፉ ግን የዛሬውን መልካም ይዞታ ባላገኙት ነበር:: ቀንበር የሌለው ሰው ብልግና ሁሉ የሚደፍረው አጥር የሌለውን ቤት የሚመስል ነው:: ሕይወት ጨካኝ በሆነብን መጠን እኛም ለመኖር በብዙ ነገሮች ላይ እንጨክናለን::

ድሆች ቤተሰቦች ያሉአቸው ገና በልጅነታቸው ብዙ ዝቅተኛ ሥራዎችን ሠርተዋል:: እንደ ሌሎቹ ለሱስና ለዝሙት የሚሆን ጊዜ አልነበራቸውም:: ቅንጦትና ኃጢአት ሲያምራቸው እቤታቸው የተከፈተ ጉሮሮ ይታያቸዋል:: ስለዚህ ቡና ቤቱንና የዝሙት ቤቱን እየጣሱ ድሆቻቸውን ለመታደግ ይፋጠናሉ:: ብዙ ወጣቶች ልጅነታቸው ቀርቶ አባት ሲሆኑ እናያለን:: እንደ ባለጠጋ ልጆች ለሲጋራ የሚጠይቁ ሳይሆኑ ላልወለዷቸው ልጆች ዳቦ ገዝተው የሚገቡ ደግ አባቶች ሆነዋል:: ታዲያ እነርሱ ለድሆቻቸው ያደረጉት ብዙ ቢመስላቸውም፣ ድሆች ቤተሰቦቻቸው ለእነርሱ ያደረጉት ይበልጣል:: በእውነት! ለድሆች ከሰጠናቸው ይልቅ እነርሱ የሰጡን ይበልጣል::

*መርዳት መቻል ዕድል ነው::* እግዚአብሔር እኛን ተቀባይ እነዚያን ሰጪ ማድረግ ይችላል:: ስለዚህ *መርዳት ዕድል* ነውና እንጠቀምበት! ያለዚያ ተቀባይ እንሆናለን:: እግዚአብሔር በፍላጎታችን ታግሦናል:: ሳይሰለች በጎ በረከቱን በየጊዜውና በየሰዓቱ ይልክልናል:: ወደ እኛ የመጣች ደግነት ወደ ሌሎች ካልሄደች ደስታ አይኖረንምና የተቀበልነውን ደግነት እኛም ለሌሎች እናሳይ:: ይልቁንም ከእኛ የሆነ ምንም ነገር የለምና ለእግዚአብሔር እጅ ሆነን እንደምንሰጥ ልናስብ ይገባናል:: እግዚአብሔር በትዕግሥቱ በፍላጎታችን ይችለናል ብለናል:: እኛም የእርሱን ባሕርይ ልንካፈል ይገባናልና ለመስጠት ካበቃን በደስታ መስጠት ይገባናል:: እንደውም እውነተኛ ስጦታ ከትርፍ ሳይሆን ከጉዳት ነውና ተጎድተን እስክንሰጥ ድረስ ገና እንዳልሰጠን ልንረዳ ይገባናል::

ብዙ ጊዜ መስጠት ላይ ትዕግሥት እናጣለን:: አንዳንድ ጊዜም የሰዎችን የሆድ ክፍተት እየሞላን የሰላማቸውን ሙላት ግን የሚነካ ንግግር እንናገራለን:: ትዕግሥት እየጎደለን ድሆችን ስንመረር እኛም ሳንቲም አጥተን ከቤት መውጣት ያፈርንበትን ዘመን ማስታወስ፣ ከሰው እጅ መቀበል የከበደንን ወራት ማሰብ ይገባናል:: እግዚአብሔር እንዳይታዘበን ለምንረዳቸው ሰዎች ታጋሽ እንሁን:: እኛም የምንሰጠው እርሱ ሲሰጠን ነውና ማቀባበል ታክቶን ከበረከቱ





እንዳንጎድል በእውነት ንስሐ እንግባ:: ሰጪነትም ተቀባይነትም ኃላፊ ነውና በሚያልፈው ነገር የማያልፍ ሥራ እንሥራበት:: ትዕግሥትን ገንዘብ በማድረግ ለሚለምኑን በደስታ እንስጥ:: በእጃችን ያለው ገንዘብም ሆነ የምንረዳቸው ወገኖቻችን ዕድሎቻችን ናቸውና እንጠቀምባቸው::

## <u>እናስተውል</u>

ወላጆቻችንንና ድሆች ቤተሰቦቻችንን በመርዳታችን እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባናል:: የረዳናቸው በሕይወት ኖረው ብናገኛቸው ነው:: እኛ የምንመኘው የሌለንን እንጂ ባለን ብናመሰግን ያለን ብዙ ነው:: ኑሮ ለኃላፊነት መብቃት ነውና ቤተሰቤን ስረዳ ዘመኔ አለፈ፣ ትዳሬ ታጎለ ብለን ማዘን ተገቢ አይደለም:: ይህም ረቂቅ ትዳር ነውና:: ወላጆቻችንን መርዳት የማንችልበት ዘመን አለ:: ሰው ባሻን ጊዜ ልናገኘው የምንችለው ቋሚ ፍጡር አይደለም:: ስለዚህ መርዳትም ዕድል ነውና አክብረን እንጠቀመው::

እኛን ሰጪ ሌላውን ተቀባይ ካደረገ ይህ የተሰጠን አገልግሎት ነውና በትጋት ልንፈጽመው ይገባናል:: እግዚአብሔር ቦታ ሊለዋውጥ ይችላልና:: *«እግዚአብሔር ድሀ ያደርጋል፥ ባለጠጋም ያደርጋል . . .»* (1ሳሙ. 2:6-8)::

መስጠት የምንችለውም በሕይወት ሳለን ነው:: ከሞት በኋላ ቸርነት ማድረግ አንችልም:: በገንዘባችን ማዘዝ የምንችለው ሳለን ብቻ ነው:: ካለፍን በኋላ የሚያዙበትን እኛም አናውቃቸውም:: ለዚህ ነው ለማኙ:-

«መስጠት በቁመና ሳሉ በውበት፣
እጅን እደረት ላይ ሳይነባብሩት፤» ያለው::

አንድ ድሀ ቄስ ታመው ተኝተው ሳለ አንድ ሰው ሊጠይቃቸው መጥቶ ስለ በሽታቸው ከተወያዩ በኋላ ጠያቂው ሰው:- «ለዚህ ሕመም መድኃኒቱ ወተትና ማር የሥጋ መረቅ እያደረጉ በየጊዜው ቢመገቡት ሕመሙ እንደሚለቅዎ የታወቀ ነው» አላቸው:: በዚህ ጊዜ ቄሱ በምግቡ ዓይነት ጎመዡና ከተኙበት ቀና ብለው:- «ያሉኝን ሁሉ ሳያመጡልኝ እንዳይቀሩ ገዝቼዎታለሁ» አሉ ይባላል:: የሚበሉት ለሌላቸው ስለ ምግብ ዓይነት፣ መታከሚያ ለሌላቸው ስለ መድኃኒት ዓይነት የምናወራ ስንቶች እንሆን? ዝናብ የሌላቸው ደመና የተባልነው እኛ እንሆን? ለድሆች የማያገኙትን



www.ethiopinorthodox.org

ከማውራት ያለንን መስጠት ይሻለናል:: በድህነታቸው ላይ መጎምጀትን ከምንዘራባቸው ብናካፍላቸው ይሻላል::

ብዙ መናገር መቻል ጥቂት ግን ማድረግ አለመቻል አለመታደል ነው:: አፋችን ድኖ ያልዳነ እጅ ከያዝን የምናሳዝን ፍጡራን ነን:: ያዕቆብ በመልእክቱ:- *«ወንድሞች ሆይ÷ እምነት አለኝ የሚል÷ ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር÷ ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን? ወንድም ወይም እኅት ራቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብንም ቢያጡ÷ ከእናንተ አንዱም:- በደኅና ሂዱ÷ እሳት መቁ÷ ጥገቡም ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጉትን ባትሰጡአቸው ምን ይጠቅማቸዋል? እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው»* (ያዕ. 2:14-18) ይላል::

## ጸሎት

ጌታ ሆይ! ስጦታህ አያልቅም:: ሀብትን ከችሮታ ጋር የያዘ እንዳንተ ያለ ባለጠጋ ከወዴት ይገኛል? ከሰፊው ቸርነትህ ያጠገብከኝ አንተ ነህና አመሰግንሃለሁ:: እጅን የፈጠርክልኝ እንድሠራበት፣ እንድበላበት ብቻ ሳይሆን እንዳጎርስበትም ነውና እባክህ እጄን ፍታው:: እጄን ያሠረው ሰይጣን ድሆች በረሀብ ሲሞቱ ማዶ ሆኖ ይስቃልና በቸርነት ድምፅህ ማሰሪያዬን በጥሰው:: ገንዘቤን ለአወዳሾች ሰጥቼ እየሳቅሁ ተዘረፍኩ:: እባክህ ለእውነተኛ ድሆች መዘርጋትን አድለኝ:: እኔም ረሀብን አይቼ በረሀብተኛ ጨክኛለሁ:: በሌለኝ ዘመን በምኞት ስቸር፣ ባገኝ እሰጣለሁ ብዬ ስሳል ኖሬ አሁን ረሀብተኛን ተጸይፌአለሁ:: እኔ እኔ አልሆንኩምና ለውጠኝ:: የድሆች መጠጊያ በሆነው ስምህ ለዘላለሙ አሜን!





# ምዕራፍ ዐሥር

## ይጠብቀናል

አንድ ልጅ እደጅ ሲያመሽ አባት ቀድሞ ከገባ ሁለት ሰዓት ላይ:- «ይሄ ልጅ እንዴት ጠግቧል? ለዚህ ያበቃሽው አንቺ ነሽ» በማለት ያጉረመርማል:: ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ሲል ልብሱን ቀይሮ ጋቢ የለበሰው አባት:- «እንግዲህ እኔ ወጥቼ እርሱ ይገባ እንደሆነ ነው እንጂ ሁለት አባወራ በአንድ ቤት ውስጥ አይኖርም» ብሎ በቊጣ ይናገራል:: እናትም ደጅ ደጁን እያዳመጠች ዝም ትላለች:: ከቊጣው በላይ የልጅዋ ደኅንነት እያሳሰባት:: ጋቢያቸውን ለብሰው ማዶና ማዶ የተቀመጡት ወላጆች ጆሮአቸውን ወደ ደጅ እንደቀሰሩ አራት ሰዓት ሲሆን «ግን በደህናው ነው?» ይላሉ:: አምስት ሰዓት ሲሆን «የዛሬን በደህና ይምጣ እንጂ መድኃኔዓለም ቃል ላንናገር» ይላሉ::

እነዚህ ወላጆች እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት በልጁ ጥፋት አዘኑ:: ከአራት ሰዓት በኋላ ግን ስለ ልጁ መጥፋት አዘኑ:: ልወቅሰው የቀጠርኩት አንድ ወንድሜ በንግግራችን መጨረሻ ላይ:- «ስለ ጥፋቴ ሳይሆን ስለ መጥፋቴ እዘንልኝ» አለኝ:: በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ልዩነት ይህ ነው:: እኛ የሰዎች ጥፋታቸው ያሳዝነናል:: እግዚአብሔር ግን መጥፋታቸው ያሳዝነዋል::

አዳምና ሔዋን ከውድቀታቸው በፊት እግዚአብሔር ኃያል፣ መጋቢ፣ ጥበበኛ፣ አስተዋይ ... መሆኑን ያውቁ ነበር:: በወደቁ ጊዜ ደግሞ ኃጢአተኛን የሚፈልገውን የቸርነት ባሕርዩን አውቀዋል:: ከእኔ ካልጎደለ ቢወድቁ ይውደቁ የማይል ለእኛ የሚቀናልን አባታችን ነው:: ትእዛዛቱንም የሰጠን ባለሥልጣንነቱን ሊያሳውቀን ሳይሆን እኛው እንዳንጎዳ ነው:: ጠፍተን እንዳንቀርም በሩን ከፍቶ ይጠብቀናል:: ያልጠፉ መቶ በጎች አሉኝ ብሎ በአንዲቱ መጥፋት ቸል የሚል አይደለም (ማቴ. 18:12-14):: ስለ አንድ ነፍስም የሚገደው አምላክ ነው:: ዛሬ ለስብከት ስንጠራ ምን ያህል ሰው አለ? እንላለን:: ሕዝብ ካልበዛ መስበክ አንፈልግም:: አንዲት በግን ለመፈለግ የመጣውን አምላክ የሚያመልክ ግን እንዲህ አያስብም:: እግዚአብሔር በገነት ጫካዎች የፈለገው ሁለት ሰዎችን ነው:: አዳምና ሔዋንን:: እግዚአብሔር የተሟገተው ስለ አንዱ ስለ አቤል ደም ነው:: መላውን ዓለም በውኃ ሲያጠፋ መርከብ እንዲሠራ



www.ethiopinorthodox.org

ያዘዘው ስለ ስምንት ነፍስ ነው። የሰዶምን ቅጣት ያዘገየው አራት ሰዎች እስኪወጡ ነው። እግዚአብሔር ስለ ጥቂቶች ግድ ይለዋል። የአንድን ሰው ዋጋ ያላወቀ አገልጋይ መሆን አይችልም።

«እግዚአብሔር ይታገሣል» ስንል ይችለናል ማለት እንደሆነ ተመልክተናል። እርሱ በደላችንን በይቅርታው፣ ፍላጎታችንን በበረከቱ ከቻለው እኛም ለበደሉን ይቅር ባዮች፣ ለሚለምኑን ቸሮች ልንሆን ይገባናል። ምክንያቱም ከተፈጠርንበት ዓላማ አንዱ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ለዓለም ለማንፀባረቅ ነውና። «እግዚአብሔር ይታገሣል» ማለት ይጠብቀናል ማለት ነው። የትዕግሥት ትርጉሙ መቻል፣ መጠበቅ፣ ተስፋ ማድረግ ነውና። ስለዚህ እግዚአብሔር ይታገሣል ማለት ይጠብቀናል ማለት ነው። ይጠብቀናል ስንል በመላእክት በረድኤት ይጠብቀናል ማለታችን ሳይሆን ለመመለስ ዕድል ይሰጠናል ማለታችን ነው።

የሰው ልጅ መውደቅ መጨረሻው ቢሆን ኖሮ ሰው ለመሆን ባልበቃ ነበር። እግዚአብሔርም ይቅርታው አንድ ጊዜ ብቻ ቢሆን እግዚአብሔር ባልሆነ ነበር። ነገር ግን ምሕረቱ ለዘላለም ነው።

እያንዳንዱ ሰዓትና ቀን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ የተሰጠን ዕድል ነው። ይህም ዕድል የሚቆየው የምድር ኑሮአችንን ጨርሰን የሞትን መንገድ እስክንጀምር ነው። ከሞት በኋላ ንስሓ የለምና። ከሞት በኋላ በጎ የማድረግም ሆነ ክፉ የማድረግ ዕድል የለም። ያለው የበጎና የክፉ ሥራችን ዋጋ ነው። ይህችን ዕድሜአችንን ካልተጠቀምንባት ጉዳታችን ዘላለማዊ ነው።

ሕዝባችን «ትድናለህ ወይ?» ብለን ብንጠይቀው «እኔ» ይልና «በፍጹም አልድንም» ይላል። የሚገርመው ግን አለመዳኑ አያስደነግጠውም። ነገር ግን ለዘላለም ከእግዚአብሔር ከመለየት የበለጠ ምን ጉዳት ይኖራል? ሕዝባችን የእግዚአብሔርን ፍቅርና ምሕረት መገንዘብ ስላልቻለ ከሞትና ከሲኦል ጋር ያለውን ኪዳን አፍርሶ በክርስቶስ ማመን ደግሞም ንስሓ መግባት አልሆነለትም። በዚህ ምክንያት በሥጋውም በነፍሱም ያልተመቸው ሆኖ ይኖራል። የነፍስ ሰላም ለሥጋ፣ የሥጋ ሰላም ለዓለም ሰላም መሆኑን አላወቀምና። የእግዚአብሔርን ትዕግሥት ተረድተን በማያሳፍረው ጌታ በክርስቶስ ስናምን እንዲህ የሚለው ቃል በሕይወታችን ይፈጸማል፡- *«ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እነሆ በጽዮን ድንጋይን ለመሠረት አስቀምጣለሁ፤ የተፈተነውን፥ የከበረውን፥ መሠረቱ የጸናውን የማዕዘን ድንጋይ የሚያምንም አያፍርም። ... ከሞትም ጋር ያደረጋችሁት ቃል ኪዳን ይፈርሳል*





*ከሲኦልም ጋር የተማማላችሁት መሐላ አይጸናም»* (ኢሳ. 28:16-18)።

ወደ እግዚአብሔር ልንመለስ ይገባናል። የእንቁላል አስኳል ጠቃሚ ነው። ያለው ግን ከመካከል ላይ ነው። የዕድሜም አስኳል ያለው በወጣትነት ዘመን ላይ ነውና በጉብዝናችን ወራት መመለስ ይገባናል። ልጅነታችን የዝግጅት ዕድሜ ሽምግልናችን ያሳለፍነውን የምንገመግምበት ዕድሜ ነው። ወጣትነታችን ግን የሥራ ዘመን ነው። ውድ አንባቢ ሆይ! ሁሉም ነገር ሳይጨልም በጉብዝናህ ወራት እግዚአብሔርን ፈልግ! ከነአካልህ ከነበረከትህ እጅህን ለእግዚአብሔር ስጥ! የተረታህ ቀን ወደ እርሱ መምጣትህ አይቀርምና።

ማፍቀርና መፈቀርን በሚፈልግ ተፈጥሮ ተፈጥረናል። ያለ ፍቅር ማሩ ሊጣፍጥ፣ መራራው ሊለወጥ በማይችልበት ሕይወት ውስጥ ከፍቅር ውጭ የሆነ ኑሮ መግፋት ከባድ ነው። ያለ ፍቅር ሲታሰብ ግዙፉ ፍጥረተ ዓለም አስፈሪና አስደንጋጭ ነው። የሰዎች ፍቅር ተለዋዋጭ በመሆኑ፣ የእኛም ፍቅር የሌሎችን የፍቅር ጥም ሊያረካ፣ የሌሎችም ፍቅር የእኛን የፍቅር ጥያቄ ሊመልስ በፍጹም አይችልም። ስለዚህ እግዚአብሔርን ማግኘት የእያንዳንዱ ነፍስ የጠበቀ ፍላጎት ነው። ችግሮቻችንን ለመግለጽ ቃላት የማይበቁን ጊዜ ጥቂት አይደለም፣ በሽታችንም ከሐኪም የሚሠወርበት ጊዜ ብዙ ነው። በመደጋገም የሚጥለንን ኃጢአት ለመንፈሳውያን ሰዎች እንኳ ለመንገር ያሳፍረናል። ስለዚህ ይህን ሁሉ ጉድለታችንን በርኅራኄ የሚያይልን አምላክ ፈላጊዎች ነን።

በማለዳ የፀሐይ ብርሃን መውጣቱ ብቻውን በድፍረት እንድንሠማራ አያደርገንም። ሌላ ብርሃን እንፈልጋለን። አምላካዊ የፍቅር ብርሃን! ይህ የፍቅር ብርሃን ካልተሰማን ቀኑን ለመዋል አቅም እናጣለን። በዚህ ቀን ላይ እንኳ ሥልጣን ያለውን ጌታ ተማፅነን መውጣት እንፈልጋለን። በተለያየ ጊዜ ከጠዋቱ 12 ሰዓት ገደማ የተደወሉልኝን ስልኮች አስታውሳለሁ። የስልኮቹ ድምፆች ተመሳሳይ ናቸው፡- «ዛሬን የሚያውል ቃል ንገረኝ» ቀኑን ገና ከጅምሩ ፈርተውታል። የሚፈጸም ቀን አልመሰላቸውም። የአንድ ሰዓት አቅም የላቸውም። እግዚአብሔር ግን ለቀኑ የሚሆን ቃል አለው። አዎ ያለ እግዚአብሔር ፍቅር ካሰብነው ዛሬ አስፈሪ ነው። የሰበሰብነው ንብረት እንደ ገጠጠ አውሬ አስደንጋጭ ነው።

እያንዳንዱ የእግር ኮቴ ሠራዊት የመጣብን ያህል ያስፈራን፣ እያንዳንዱ የስልክ ጥሪ የልባችንን ትርታ የጨመረብን፣ ደጅ ለመውጣት ድፍረት ያጣንበት፣ ወዳጆቻችንን ለማግኘት ምጥ



www.ethiopinorthodox.org

የተጋባንበት፣ ማንኛውንም ጥያቄ የፈራንበት፣ ምስጋናንንም እርግማንንም ለመቀበል አቅም ያጣንበት... ጊዜ ብዙ ነው:: በዚህ ሁሉ ውስጥ ከቤት የመውጣት ድፍረታችን እንኳ እግዚአብሔር መሆኑን ተረድተናል:: የእኛ የመሰሉን ነገሮች ሁሉ ሲሄዱ የእኛ አለመሆናቸውን፣ የእኛ ባዶነት ብቻ መሆኑን ተረድተናል:: አዎ የዚህ ሁሉ ውጊያ ድል መንሻው የእግዚአብሔርን ፍቅር ማሰብ ብቻ ነው:: እኛ እርሱን የወደድንበትን ሳይሆን እርሱ እኛን የወደደበትን ፍቅር፤ እኛ ለእርሱ የተገዛንበትን መታዘዝ ሳይሆን እርሱ የእኛን እግር ያጠበበትን ጽድቅ ማሰብ ዕረፍት ይሰጠናል:: የመኖር ኃይላችን የእርሱ ፍቅር ብቻ ነው:: ያለ እርሱ ፍቅር ሁሉም ነገር ባዶ ሆኖ ቢታየን፣ በአትክልትና በአበባ ያጌጠው ዓለም አስፈሪ ቢሆንብን፣ የከበቡን ወዳጆች ከብቸኝነት የማይሻሉ ቢመስሉን፣ እንዳልተገራ ፈረስ ሥጋችን ወደ ገደል ቢስበን ይህ አደጋ ሳይሆን ባሕርዩ ነው:: እርሱ በቃሉ:- *«ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና»* (ዮሐ. 15:5) ብሏል::

ጌታችን በቀኙ ለተሰቀለው ወንበዴ ለልመናው መልስ ሲሰጥ:- *«ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ»* ብሎታል (ሉቃ. 23:43):: ገነትን ገነት ያደረጋት የኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ መኖር ነው:: ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ ገነት ከሲኦል ትከፋለች:: የገነት መዓዛዋ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ገነት ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ ጨለማ ከሆነች ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሀብትና ዝና ጨለማ ቢሆን ምን ይደንቃል?

የአትክልት ሳይንስ እንደሚያስረዳን ማንኛውም አትክልት በቤት ውስጥ ብናስቀምጠው አትክልቱ የሚያዘነብለው የፀሐይ ብርሃን ወዳለበት አቅጣጫ ነው:: እንዲሁም የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር ሳያቀና መኖር በፍጹም አይችልም:: አንድ ታዋቂ የፈረንሣይ ፈላስፋ:- «በማንኛውም ሰው ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር ራሱ ብቻ ሊያረካው ወይንም ሊሞላው የሚችል አንድ ዓይነት ቀዳዳ ወይም የተተወ ባዶ ቦታ አለ» ብሏል::

ማንኛውም የዓለም ሀብትና ጥበብ ሊሞላው የማይችለው ክፍት ቦታ በሰው ሕይወት ውስጥ አለ:: ይህንን ክፍተት የሚሞላው እግዚአብሔርን ማግኘት ብቻ ነው:: *«ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?»* (ማቴ. 16:26):: *«እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ደስ ይበለው:: እግዚአብሔርን ፈልጉት፥ ትጸናላችሁም፤ ሁልጊዜ ፊቱን ፈልጉ»* (1ዜና. 16:10-11)::





ቅዱስ አውግስጢኖስ ወደ እግዚአብሔር ከመመለሱ በፊት ሕይወቱ እጅግ የባከነ፣ በኃጢአት የተጎሳቆለ ሰው ነበረ:: የጥበብ ፍለጋው መቆሚያ፣ የእውቀት ክምችቱ እርካታ ባጣ ጊዜ ተስፋው መነመነ:: በታላቅ የልብ መሰበር ውስጥ ሆኖ:- *«አምላኬና ፈጣሪዬ ሆይ እስከ መቼ ትዘገያለህ? እስከ መቼስ ነገ ዛሬ ትለኛለህ? ለምን አሁን አትታደገኝም፤ ለምንስ በዚህች ሰዓት ሐፍረቴ ፍጻሜ አያገኝም?»* በማለት ጸለየ:: እግዚአብሔርም እንኳን ፈልጎት ሳይፈልገውም ሲፈልገው ኖሯልና ልመናውን ሰማለት:: አውግስጢኖስም በክርስቶስ አምኖ ንስሐ ገባ:: በዚህ ጊዜ ያሳለፈውን ዘመን አስታውሶ:- *«ጌታ ሆይ፥ ለራስህ ስትል ስለ ፈጠርከን ልባችን በአንተ ላይ እስኪያርፍ ድረስ የትም ይባክናል»* በማለት አመሰገነ:: ይህ አውግስጢኖስ አሁን ያገኘውን የሕይወት መታደስ አሰበና:- *«አምላኬ ሆይ፥ ምነው በሕፃንነቴ ዐውቄህ በነበር»* አለ::

በሽምግልና ዘመናቸው ክርስቶስን ያገኙ ሁሉ የባከነው ዘመናቸውን ያስቡና ምነው በሕፃንነቴ አውቄህ በነበር ይላሉ:: በሽምግልና ከቊጭት ጋር ከማመን፣ ዛሬ አፍላውን ዕድሜ መጠቀም መታደል ነው:: ውብ የሆነውን ጌታ ሳያዩ መኖር ሞት ነው:: ይህን ጌታ ለማገልገል ሰማንያ ዓመትም ትንሽ ነው:: አዎ «ክርስቶስ የሁሉ አዳኝ፣ የውበት ሁሉ መደምደሚያ፣ የሰው ልጆች ሁሉ ናፍቆትና ግብ ነው::»

ቅዱስ አውግስጢኖስ:- ክርስቶስን ካገኘ በኋላ ሕይወቱ ፍጹም ተለወጠ:: ከክህደት ወደ እምነት፣ ከዝሙት ወደ ንጽሕና ሲፈልስ ሕያወቱ እንደ ሕፃን ሰውነት መለምለም ጀመረች:: ታዲያ አንድ ቀን በጎዳና ሲሄድ በድሮ ሕይወቱ አብሯት በዝሙት የሚወድቃት ሴት ገጠመችው:: እርሷም ውይ አውግስጢኖስ ብላ በፈገግታዋ ለመማረክ ወደ እርሱ ስትመጣ እርሱ መሮጥ ጀመረ:: ሴቲቱም ባያውቀኝ ነው ብላ አብሯው መሮጥ ጀመረች:: «አውግስጢኖስ አውግስጢኖስ እኔ ነኝ እኮ?» ብትለው እርሱ ግን ዘወር ብሎ:- «እኔ ግን እኔ አይደለሁም» ብሏት ሮጠ:: ሴቲቱም ተስፋ ቆርጣ ተመለሰች::

ክርስቶስን በእውነት ስናገኝ ሕይወታችን በምንም መንገድ እንደ ቀድሞው አይሆንም:: ክርስቶስ ይለውጣል:: አውግስጢኖስ የቅድስና ሕይወቱን ለመጠበቅ ሸሸ:: ቃሉ:- *«ከዝሙት ሽሹ»* (1ቆሮ. 6:18) ይላልና:: ዮሴፍም ልብሱን ጥሎ ሸሸ (ዘፍ. 39:12):: ወኅኒ ቢወርድም ከኃጢአት እስር ግን አምልጧል:: ዛሬ ብዙዎች በዝሙት የሚወድቁት ቆመው ስለሚደራደሩ ነው:: ካስፈለገን ለቅድስናችን



www.ethiopinorthodox.org

በአደባባይ መሮጥ ይገባናል:: የዓለም ብልጥ ከመሆን የእግዚአብሔር ሞኝ መሆን ይሻላል::

እግዚአብሔር የሚታገሠን ወይም የሚጠብቀን ይህ አዲስ ሕይወት እንዳያመልጠን ነው:: እኛ ጥሩ ምግብ ሲቀርብልን የምንወደው ሰው ቢመጣ እንደምንመኝ ጥሩ ሕይወት እንዳያመልጠን እግዚአብሔር ያስብልናል (ይቀናልናል):: ከሞት በኋላ የምሕረት ዕድል የለምና ሳለን በቁመና እንድንድን ይፈልጋል:: ነፍስ ይህን ጌታ ስታገኝ በፊደል ሳይሆን ነበልባላዊ በሆኑ የፍቅር አምላክ ቃሎች መነካት ትጀምራለች:: ዛሬ እርሱን ስላገኘች ብቻ አይደለም፣ ያለ እርሱ የኖረችበትን ወራት ሁሉ ከንቱ ትለዋለች:: ቅዱስ አውግስጢኖስ:- *«አምላኬ ሆይ! ምነው በሕፃንነቴ ዐውቄህ በነበር»* እንዳለ:: በእውነት እግዚአብሔርን መፈለግ ትልቅ ጥበብ፣ እርሱንም ማግኘት የመጨረሻው ድል ነው!

እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ደቂቃና ሴኮንድ እየጠበቀን ነውና ወደ እርሱ በንስሓና በእምነት እንመለስ! ኃጢአትን ወደን ካልተዉት ቆይቶ የሚገድል መርዝ ነው:: የኃጢአት ጠባዩም «ካለህበት ኑሮ የተሻለ ሕይወት የለም» እያለ ባሪያ ማድረግ ነው:: ግን የተሻለ ክርስቶስ አለ:: ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ሌላ ምቹ ጊዜ አንጠብቅ፤ ከዚህች ደቂቃ የተሻለ ምቹና የእኛ ጊዜ የለም:: *«የመዳን ቀን አሁን ነው»* (2ቆሮ. 6:2):: በዓለም ላይ ያሉት ፈላስፎችና ሊቃውንት ሁሉ ቢሰበሰቡ ሕይወትን ወደ ኋላ መልሰው እንድንኖራት አያደርጉንም:: የዓለምም ጠባይዋ ያባከነውን ጊዜ በማስታወስ ማንገብገብ ነው:: እግዚአብሔር ግን በእውነት ወደ እርሱ ስንመለስ ሠላሣ ዓመት ከዘራው ሰው እኩል በማሳጨድ ይክሰናል (የሚለውጥ ፍቅር የሚለውን መጽሐፍ ይመልከቱ)::

ብዙ ጊዜ የንስሓን ጥሪ ረግጠናል:: ንስሓን ለማካካስ ብዙ ሃይማኖታዊ ሥርዓትን ይዘናል:: ነገር ግን በዚያው መጠን ሕይወታችን ዕረፍት እንዳጣች ገብቶናል:: ወደ እግዚአብሔር መመለስን ግን ችላ ብለናል:: እግዚአብሔር የሚታገሠን በኃጢአታችን ተደስቶ አይደለም፣ ለንስሓ ጊዜ እየሰጠን ነው:: ካልተመለስን፣ የፍቅሩንም ምክር ከናቅን የኃይሉን ቃል በግድ እንሰማለን::

ቃሉም:- *«የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን? ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ*



*የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቍጣ ቀን ቍጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ»* (ሮሜ. 2:4-5)::

እናት ልጇ ካልገባ የመጨረሻውን መቀርቀሪያ አትቀረቅርም:: እግዚአብሔርም ደጁን ከፍቶ እየጠበቀን ነውና እንመለስ!

## እናስተውል

ዓለም:- «ስለ ብዙኃን ማሰብ ስንጀምር ስለ አንድ ሰው ማሰብ እንችላለን» ትላለች:: እግዚአብሔር ግን ስለ አንድ ሰው ስናስብ ስለ ብዙኃን ማሰብ እንደምንችል ይነግረናል:: አንድ የካርቶን ስዕል ሁለት ሰዎች ሲከራከሩ ያሳያል:: አንደኛው ኋደኛውን «አንተ ሐኪም መሆን አትችልም:: ምክንያቱም የሰውን ዘር አትወድም» ይለዋል:: ያኛውም ጮኾ ይመልሳል:- «የሰውን ዘር እወድዳለሁ፤ የማልወደው ግን ሰዎችን ነው» በማለት ይመልሳል:: የሰውን ዘር እወዳለሁ ማለት ቀላል ነው:: አንድን ሰው በእውነት ስለመውደዳችን ብንጠየቅ ግን መልሳችን ሙሉ አይደለም::

የአንድን ሰው ዋጋ ካላወቅን አገልጋይ መሆን አንችልም:: ሰዎች ከጥፋታቸው መጥፋታቸው ሊያሳዝነን ይገባል:: እኛን ከጎዱን በላይ ራሳቸውን የጎዱት ይበልጣል:: ከእኛ አንጻር ሳይሆን ከእነርሱ አንጻር ውድቀታቸውን ማየት ብንችል ስለ ምርጫቸው እናዝንላቸዋለን:: ብዙዎች ምንም ሳይጎድላቸው ነው ለእግዚአብሔርና ለሰው የማይመች ማቅ የሆኑት::

አንድ ታሪክ ሰማሁ:: ሰዎቹ እጅግ ባለጠጎች ናቸው:: ሚስቲቱ ግን እጅግ ኃይለኛ ነበረችና ሰላም አልነበራቸውም:: የባሏ እናት መልካምና እንደ ልጅ የሚያዩአት ቢሆኑም እርሷ ግን ፍጹም አትወዳቸውም ነበር:: እቤቷ አይደለም ማንኛውም የቤተሰብ ግብዣ ውስጥ እርሳቸውን ካየች ጥላ ትወጣለች:: እርሳቸው ግን ሰይጣን እኔን ክፉ አድርጎ ቢያሳያት ነው እኔ ልሂድ በማለት ያዝኑላታል:: ባለቤቷ ግን መቋቋም እያቃተው መጣ:: መፋታትን ፈለገ:: በዚህ ጊዜ እናቱ በእኔ ምክንያት አትፋቱም ብለው እግር ላይ ወድቀው ይለምናሉ:: ልጅም ስለ እናቱ ሲል ኑሮውን ቀጠለ:: ያች ሴት ግን ባልታሰበ ሕመም ሞተች:: ሀብት ሳያንሳቸው ሰላም አንሷቸው መኖራቸውን ባለቤቷ አሰበና ክፉኛ አዘነ:: «ለባለቤቴ የማዝነው ስለ መሞቷ አይደለም:: ሁሉ እያላት ፍቅር አጥታ መሞቷ ግን ያሳዝነኛል:: ከሞቱ ሰዎች ሁሉ ይልቅ የእኔ ባለቤት ታሳዝናለች» ብሎ



www.ethiopinorthodox.org

የመረረ ሀዘን አዘነ:: ከሞቷ በላይ ራሷን ከፍቅር ነጥላ የኖረችበት ዘመን፣ እርሱን ካሳዘነችው ይልቅ ያጣችውን ደስታ እያዘነ አለቀሰ:: ሰዎች ፍጹም የተሸነፉ ቀን ወይም በሞት ያለፉ ቀን ጥፋታቸው ሳይሆን እንዲህ ለሚቀረው ዓለም መጥፋታቸው ያሳዝነናል:: ሰውን የምናመርበት ቆሞ የሚቀር ስለሚመስለን ነው:: ከሞተ በኋላ በክፉ ለማንሣት እንኳ ኀሊናችን ይከለክለናል:: ያኔ የምናደርገውን ዛሬ ብናደርገው ብዙዎችን ማትረፍ በቻልን ነበር::

ሰውን በጎ ሥራ የሚያሠራው የመዳን ተስፋ ነው:: የመዳን ተስፋ የሌለው ሰው በክፉ ሥራ ለመርካት የሚዘጋጅ ነው:: እናቶቻችን ንስሐ እየገቡ፣ እየቆረቡ፣ ቤተ እግዚአብሔር እየተመላለሱ «የላይ ቤት እሳቱን ማን ይችለው ይሆን?» ይላሉ:: ነገር ግን ንስሐ የገቡት ቤተ ክርስቲያን የመጡት ለላይ ቤት እሳት ብቁ ለመሆን ነው? ለእርሱማ ባይመጡም እዚያው በዓለም እያሉ ብቁ ናቸው:: የዚህ ሁሉ ምክንያቱ የክርስቶስን የሞቱን ዋጋ አለማወቅ ነው:: የክርስቶስን የሞቱን ዋጋ አለማወቅ የመዳንን ተስፋ ማጣት ነው:: እናንተ መምህራን እባካችሁ አስተምሩ:: ሕዝቡን ስለ ነፍሱ ዕረፍት ብትነግሩት ከዚህ የበለጠ ይወዳችኋል:: ተስፋው ካበበ ያለድካም ለእግዚአብሔር ይገዛልና መምህራን ሆይ አስተምሩ::

ልጅ ያለ እናቱ ያድግ ይሆናል:: ያለ ሰው ግን ሊያድግ አይችልም:: ሰውም ያለ ሰው ሊኖር ይችል ይሆናል:: ሰው ግን ያለ እግዚአብሔር መኖር አይችልም:: ከእግዚአብሔር ጋር ሲኖርም ከሰው ጋር መኖር ይጀምራል::

እኛስ ወደ እግዚአብሔር ስንመጣ ሕይወታችን ነው የተለወጠው ወይስ አድራሻ ነው የለወጥነው? ድሮ በዓለም የነበረንን የቅጥፈት ሕይወት ዛሬ በቤተ ክርስቲያን እየኖርነው ይሆን? ክርስቶስ ሕይወት ይሰጣል:: ሕይወት እንቅስቃሴ ነውና እርሱ ወደ ሕይወታችን ሲገባ በቀድሞ ማንነታችን (አድራሻችን) ላይ አንሆንም:: ቃሉ:- *«ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም»* (ዕብ. 12:4) ይለናል:: አውግስጢኖስ ሮጠ:: እኛስ እንደራደራለን? ጥቅስ እንፈልጋለን? ወይስ እንሮጣለን? አንድ መነኩሴ ጽሞና ከያዘበት ዘንድ አንዲት ሴት የአትርሱኝ ምግብ ይዛ በመምጣት ባርኮ ካሰናበታት በኋላ አይርሱኝ እያለች እዚያው ተቀመጠች:: ሂጂ ቢላት የማትሄድ ሆነች:: በሁኔታዋ እየተማረከ የዝሙት መንፈስ እየከበበው ሲመጣ ሊሸነፍ ሲል ሰው ቢደርስልኝ ብሎ ኡኡታውን አቀለጠው:: ሴቲቱም ደንግጣ ቆመች:: ሰዎችም ተሰበሰቡና ምንድነው ነገሩ? ቢሉት «ዘንዶ መጥቶብኝ ሊውጠኝ ሲል ይኸው እናንተ ብትገቡ የት እንደ ደረሰ አጣሁት»





አላቸው:: እነርሱም ፈታኝ ነው ብለው ጸልየው ሴቲቱን ይዘው ወጡ:: እርሱም ነፍሱን አዳነ:: እኛ ግን የምንጮኸው ንብረት የሚወስድ ሌባ ሲመጣ ነው:: ቅድስናን የሚወስድ ሌባ ሲመጣ ግን እየሳቅን እናስተናግደዋለን:: የኃጢአት የመጀመሪያ ሳቅ፣ ዘላቂ ልቅሶ እንዳለው የሚገባን ቆይቶ ነው::

## <u>ጸሎት</u>

ጌታዬ ሆይ! ካንተ ርቄ፣ በምሽት ወጥቼ፣ በወንበዴ እጅ የወደቅሁ ነኝ:: ምን እጠቅምሃለሁ? አይጠቅምም ብለው የቀድሞ ባልንጀሮቼ ትተውኛል:: ጌታ ሆይ! እኔ የተበላሸሁ ሰው ነኝ:: ብርቅ ብጠፋ ይሻለኛል:: ከቤቴ ጣራ በታች ልትገባ አይገባኝም:: ድምፅህ አሁን በልቤ ይሰማኛል:: እኔ ባለሙያ ነኝ:: ተበላሸ ብዬ አልጥልም፣ ሠርቼ እጠቀምበታለሁ የሚል ድምፅህ ይሰማኛል:: ስሰማው ያሳረፈኝ ያንተ ድምፅ ነው፤ ጌታዬ ተቀበለኝ:: ዓለም አጎሳቁላኝ እንዲህ አጥቍራኝ መጥቻለሁ:: ልጅ ጨዋታውን ከመሰሎቹ ጋር ውድቀቱን ከወላጆቹ ጋር ያሳልፋል:: እኔም ጉልበቴን ለዓለም፣ መረታቴን ላንተ ይገፌ መጥቻለሁና እንደ ልጅ ተቀበለኝ:: የማልችልበትን ተግባር ጀምሬ ለራሴ አለቃ ሆኜ እንዲህ ተበላሸሁ:: የነፍሴ ንጉሥ አክመህ ግዛኝ! እንቅልፉ ይብቃኝ:: ደጄን ማንኳኳትህ በረታብኝ፣ በጭላንጭል ያሳየኸኝ ምልክትህ የተወጋው እጅህ ትዕግሥት ነሣኝ:: ውዴ ሆይ ወዴት ነህ? ሁሉን ትቼ ልከተልህ መጥቻለሁ:: የሠርክ እንግዳህ ነኝና ተቀበለኝ:: ዋጋዬ አንተ ሁንልኝ:: ከሙታን መንደር መጥቻለሁና ራቁቴን ነኝ:: ከሐፍረቴ አንተ አድነኝ:: ሁሉን በሚሰበስብ አባትነትህ አምናለሁ:: ለዘላለሙ አሜን!



www.ethiopinorthodox.org

## ምዕራፍ ዐሥራ አንድ
## ለአንድ አዳር

የእግዚአብሔርን መኖር የሚክድ አንድ የሰልሳ ዓመት ሽማግሌ በመንገድ መሸቶበት እንዲያሳድሩት ቢለምን አንድ አይሁዳዊ ልቡንና በሩን ከፍቶ ተቀበለው:: እራታቸውን ከበሉ በኋላ አይሁዳዊው ስለ እግዚአብሔር የኃይልና የማዳን ሥራ ሲያጫውተው ያ ሽማግሌ:- «እኔ በእግዚአብሔር መኖር አላምንም» አለው:: አይሁዳዊውም ደነገጠ:: በመቀጠልም ውስጡ ተበሳጨና:- «ይህ ቤት እኮ የእግዚአብሔር ነው:: ስለዚህ በዚህ ማደር አይገባህም ውጣልኝ» ብሎ በሌሊት አባረረው:: ሲጸልይም ልቡ ኩራት እየተሰማው:- «ጌታ ሆይ እኔ ያንተ ሎሌ፣ የእኔና የቤቴ ባለቤት የሆንከውን አንተን የሚክድ ከሃዲ እቤቴ ቢመጣ አባረርኩት» እያለ መጸለይ ጀመረ:: ልቡም ከእግዚአብሔር ታላቅ ሽልማትን ይከጅል ነበር:: እግዚአብሔርም በራእይ ተገልጦ በሀዘን ቃል:- «እኔ ስልሳ ዓመት የቻልኩትን አንተ ለአንድ አዳር ከበደህን?» አለው:: አይሁዳዊውም እግዚአብሔርን አከብራለሁ ብሎ የሠራው ሥራ እግዚአብሔርን እንዳሳዘነ ባየ ጊዜ ልቡ ተነካ:: በሩንም ከፍቶ በዚያ ሌሊት ያንን ሽማግሌ መፈለግ ጀመረ:: በረንዳ ለበረንዳ ዞሮ አገኘውና ወደ ቤቱ ይዞት ገባ::

ጥላቻችንን የሃይማኖት ካባ ለማልበስ እንጥራለን:: ስለ እግዚአብሔር ብለን እንጣላለን እንሳደባለን:: እግዚአብሔር ግን ቅዱስ ነውና በኃጢአት አይከብርም:: የሰዎችን ስህተታቸውን ልንጠላ እንችላለን:: እነርሱነታቸውን መጥላት ግን ተገቢ አይደለም:: እኛ ራሳችን ማን እንደነበርንና እንዴት ለዚህ ክብር እንደበቃን ብናስብ፣ እግዚአብሔር የሰወረልንን የዘወትር ውድቀታችንን፣ ኧረ የዛሬ ጠዋቱን ነውራችንን ብናስብ ኖሮ በሰዎች ተስፋ ባልቆረጥንና ባልጠላናቸው ነበር:: ኖሮ ባልጨረሰ ሰው ላይ በጣም መደገፍ፣ ኖሮ ባልጨረሰ ሰው ላይ በጣም ተስፋ መቍረጥ አይገባም:: ብርቱ ያልነው ሲወድቅ፣ ደካማ ያልነው ሲበረታ ገና ሁላችንም በቤተ ሙከራ ውስጥ እያለፍን ነው::

አንድ ሰው:- «የምንወደው ሃይማኖታችንን ነው ወይስ እግዚአብሔርን ነው?» ብሎ ከጠየቀ በኋላ መልሱን ሲሰጥ:- «የምንወደው ሃይማኖታችንን ከሆነ በሃይማኖታችን ውስጥ ያሉትን ሰዎች ብቻ ነው የምንወደው:: የምንወደው እግዚአብሔርን ከሆነ ግን እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉ እንወዳለን» ብሏል:: በሃይማኖት



ስም የሚጠላሉ፣ የሚነቃቀፉ፣ የሚሳደቡ፣ የሚጋደሉ ወገኖች ዕለት ዕለት እየበዙ ነው:: ዛሬ ለዓለማችን ታላላቅ ስጋቶች ሆነው የተቀመጡ ነገሮች አሉ:-

1. <u>የባለጠጎችና የድሆች መራራቅ</u>:- ባለጠጎች በጣም እየበለፀጉ፣ ድሆች በጣም እየደኸዩ መምጣታቸው ትልቅ የዓለም ስጋት ነው::

2. <u>በጥቁርና በነጮች እንዲሁም በዘርና በጎሣ መካከል ያለው መለያየት</u>:- በመላው ዓለም እየተቀሰቀሰ ያለው ይህ ስሜት የዓለም ስጋት ነው:: ሁሉም ሰው ቋንቋዬን፣ ባሕሌን እያለ ነው ያለው:: እግዚአብሔር የሰጠውን ባሕልና ቋንቋ ማክበር ተገቢ ቢሆንም ወደ ዘረኝነት ስሜት ሲሄድ ግን ከእርሱ ዘር ውጭ ያለውን ለማጥፋት ይነሣል::

3. <u>የበሽታዎችና ወረርሽኞች መበራከት</u>:- ከፍተኛ የሆነ የጤና ችግር በሰው ልጆች ላይ እየተከሰተ ሲሆን የምንተነፍሰው አየርና የምንበላው ምግብ በራሱም ጤንነታችንን የሚዋጋ እየሆነ መምጣቱ ለሰው ዘር ስጋት ሆኗል:: ከህክምና ባለሙያዎች ችሎታ በላይ የሆኑ በሽታዎች እየበረከቱ ነው::

4. <u>የጦርነት ስጋትና የኒውክለር ባለቤትነት</u>:- ከተፈጥሮ አደጋዎች በላይ የእርስ በርስ ጦርነቶች፣ የድንበር ውዝግቦች የዓለማችን ስጋት ሲሆኑ የተለያዩ አገሮች ይልቁንም ኃላፊነት የማይሰማቸው መንግሥታት የኒውክለር ባለቤት መሆናቸው የዓለም ስጋት ነው::

5. <u>የሃይማኖቶች መፋጠጥ</u>:- ሁሉም የሃይማኖት ቡድን ከፍተኛ መነቃቃት ላይ ያለ ይመስላል:: መነቃቃቱ ግን ከእርሱ ልዩ የሆነውን ወገን ለማጥፋት መሆኑ ከላይ ከተዘረዘሩት ችግሮች በላይ የሃይማኖት ግጭቶች አስጊ እንደሆኑ እንረዳለን:: እውነተኛ ሃይማኖት ለዓለም ሰላም የሚያበረክተው አስተዋጽኦ አለው:: ሃይማኖት ግን በግልግል የሚኖር ከሆነ ተቋማቱ ራሳቸውን መመርመር አለባቸው:: የሰው ልጅ የሞራል ሕግ መገዳደልን ካወገዘ ከሞራል ሕግ በላይ የሚሆን ሃይማኖት ይህን ማውገዝ ይገባዋል:: እግዚአብሔር በፍቅር እንጂ በጥላቻ አይከብርም:: ላንደባለቅ እንችላለን፣ ግን ጥላቻን ማራቅ ይገባናል:: ሰው የሚገናኝበት መስመር ሃይማኖት ብቻ አይደለም:: ሰብእናችንም ያገናኘናል:: ይልቁንም ክርስትና ስለ ኃጢአተኞች በሞተው ጌታ ማመን ስለሆነ በፍቅራችን ዓለሙን ልንማርክ ይገባናል:: አዎ እግዚአብሔር



www.ethiopinorthodox.org

የሚሳደቡለት ሳይሆን የሚያፈቅሩለት ልጆች እንዲኖሩት ይፈልጋል::

እናት ባለጌ ልጇን ትወደዋለች:: ከአባት ደብቃ ገንዘብና ምግብ ትሰጠዋለች:: ልጁ ቀን ቀን እቤት እየዋለ ማታ ማታ አባቱ ሲመጣ ይወጣል:: በልጇ ላይ የገዛ ወንድምና እህቶቹ የሚሰነዝሩትን ነቀፌታ አትቀበልም:: እናት ባለጌ ልጇን የምትወደው ብልግናው ተስማምቷት አይደለም:: ከእርሷ በቀር የሚወደው ሰው ስለሌለ ነው:: በዚህ ምክንያት ራሷን በራሷ በግዝት አስራ ልጇን በነፃ ታፈቅረዋለች:: ስለ እርሱም የሚነገራትን ክፉ ፍርድ የማትቀበለው ፍርድ የለሽ ለመሆን ፈልጋ ሳይሆን ልጄ እንደ ተበላሸ ይቀራል የሚል አስተሳሰብ በውስጧ ስለሌለ ነው:: በእርሱ ላይ ያላት ተስፋ እንዳትፈርድበት እንደ ተበላሸ ይቀራል ብላ እንዳትወስንበት ያደርጋታል::

የእግዚአብሔር ቅርበትና አሳቢነት ከእናት ይበልጣል:: እግዚአብሔር ኃጢአትን ቢጠላም ኃጢአተኛን ይወዳል:: ኃጢአተኛው ሰው ኃጢአተኛውን ይጠላል፣ ንጹሑ ጌታ ግን ኃጢአተኛውን ይወዳል:: በሽተኛውና በሽተኛው መቀራረብ አይፈልጉም:: ጤነኛው ሐኪም ግን ሁለቱንም ይቀርባቸዋል:: እግዚአብሔርም በሚፈርደውም በሚፈረድበትም አጠገብ ሆኖ የመለወጣቸውን ቀን ይጠብቃል:: ፀሐይ በቆሻሻ ስፍራ ብትወጣ እንደማትቆሸሽ ንጹሕ ጌታም ሥጋ ለብሶ በእኛ በኃጢአተኞቹ መካከል ቢገኝ ቅድስናው አልጎደፈም:: የእርሱ ቅድስና የሚቀድስ እንጂ የሚረክስ አይደለምና::

እግዚአብሔር ተስፋ ባልቆረጠበት ሰው ላይ ተስፋ መቊረጥ ተገቢ አይደለም:: ጌታችን:- *«ለቀደሙት:- አትግደል እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ÷ በወንድሙ ላይ የሚቈጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሀነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል»* (ማቴ. 5:21-22) ብሏል:: ብሉይ ኪዳን መግደልን ትከለክላለች:: አዲስ ኪዳን ግን ወደ መግደል የሚያደርሰውን አሳብንና ቃልን ትቆጣጠራለች:: ጌታችን ቊጣን፣ ንቀትንና በሰው ተስፋ መቊረጥን ከመግደል ኃጢአት ጋር አንድ አድርጓቸዋል:: ሰው የሚሞተው በአካል ብቻ ሳይሆን ስንንቀውና ተስፋ ስንቆርጥበትም በኅሊናው ይሞታል:: ሰውን ወድቆ ብቻ ሳይሆን ቆሞም ልንገድለው እንችላለን:: ጌታችን ይህንን ሞት ነው ያወገዘው:: ይህን አገዳደል ነው ከአካል መግደል እኩል የቆጠረው:: «ደንቆሮ» የሚለው ቃል «የማትረባ» ማለት ነው::



የማትረባ የሚለው ቃል ደግሞ በሰውዬው ተስፋ ከመቊረጥ የተነሣ የሚነገር ነው:: ሰው ግን የሚኖረው ለመለወጥ በመሆኑ በማንም ተስፋ መቊረጥ የለብንም:: ይልቁንም የማትረባ ስንል የማይረባውን ያስቀመጠውን እግዚአብሔርን እየተሳደብን ነውና ትልቅ ኃጢአት ነው:: ሰው የቀደመ ክፉ ታሪኩን በደቂቃ ንስሓ ሊለውጠው ይችላል:: ዕድሜ ልኩን የበደለ ሰው በመጨረሻዋ የሞት ደቂቃ የበደለውን ሕዝብና ወገን ይቅርታ ቢጠይቅ በደሉ ሳይሆን ይቅርታው ይኖራል:: ምንም መልካም ሥራ ባይኖረው እንኳ ይቅርታው ከመልካም ሥራ በልጦ ይኖራል:: ስለዚህ መኖር ተስፋ ነውና በሕይወት ባለ ሰው ተስፋ መቊረጥ አይገባንም:: በጌታ ቀኝ የተሰቀለውን ወንበዴ እናስብ:: ዘመኑን በሙሉ በግፍና በኃጢአት የኖረ ቢሆንም የመጨረሻዋ ንስሓ ግን ታሪኩን ሁሉ ለውጣዋለች (ሉቃ. 23:40-43):: ከነአብርሃም ከነዳዊት ቀድሞ ገነት እንዲገባ አድርጋዋለች:: ይህን ወንበዴ ዛሬ ማን ይነቅፈዋል? እምነቱን ከምግባር በላይ አይተን እናደንቃለን እንጂ::

አንድ ደራሲ:- «እያንዳንዱ ሕፃን ሲወለድ ለዓለም ይዞት የሚመጣው አዲስ መልእክት አለው:: ይኸውም:- እግዚአብሔር ገና በሰው ልጅ ተስፋ አለመቊረጡን ነው» ብሏል:: እግዚአብሔር በሰው ተስፋ ቢቆርጥ ኖሮ የሰውን ዘር ያቆመው ነበር:: የሰው ዘር ቀጣይነትን ስናይ እግዚአብሔር ገና ተስፋ እንዳልቆረጠብን ያሳያል:: ምን ዓይነት ትዕግሥት ነው!

ሐዋርያው ጴጥሮስ በራእይ ሰማይ ተከፍቶ በአራት ማዕዘን የተያዘ ታላቅ ሸማ የሚመስል ዕቃ ወደ ምድር ሲወርድ አየ:: በዚያውም አራት እግር ያላቸው ሁሉ አራዊትም በምድርም የሚንቀሳቀሱት የሰማይ ወፎች ነበሩበት:: ጴጥሮስ ሆይ÷ ተነሣና አርደህ ብላ የሚልም ድምፅ ወደ እርሱ መጣ:: ጴጥሮስ ግን:- ጌታ ሆይ÷ አይሆንም፤ አንዳች ርኩስ የሚያጸይፍም ከቶ በልቼ አላውቅምና አለ:: ደግሞም ሁለተኛ:- እግዚአብሔር ያነጻውን አንተ አታርክሰው የሚል ድምፅ ወደ እርሱ መጣ (የሐዋ. 10:10-15):: ራእዩ ከአሕዛብ ወገን የሆኑትን የቆርኔሌዎስን ቤተሰቦች የሚያመለክት ነበር:: ጴጥሮስ የራእዩን ፍቺ ያስተዋለው ራእዩ እንዳበቃ የሚፈልጉትን የቆርኔሌዎስ ወገኖች ተከትሎ በሄደ ጊዜ ነው:: ተከማችተውም ባገኛቸው ጊዜ:- *«አይሁዳዊ ሰው ከሌላ ወገን ጋር ይተባበር ወይም ይቃረብ ዘንድ እንዳልተፈቀደ እናንተ ታውቃላችሁ፤ ለእኔ ግን እግዚአብሔር ማንንም ሰው ርኵስና የሚያጸይፍ ነው እንዳልል አሳየኝ፤ ስለዚህም ደግሞ ብትጠሩኝ ሳልከራከር መጣሁ»* (የሐዋ. 10:28-29) አለ::



www.ethiopinorthodox.org

እኛ ወዳላመኑት እንኳን ለመሄድ ቢመጡስ እንቀበላቸዋለን ወይ? እንኳን የካዱትን ለማሳመን ያመኑትን እንዲክዱ ወደ ደጅ እየገፉን አይደለንም ወይ? በእነርሱ ላይ በቅንዓትና በቡድን ስሜታችን የለጠፍንባቸው የሐሜት ስም እውነት እንዲሆን የምንመኝ «ድሮም ብለን ነበር» ለማለት የምንጸልይ አይደለንም ወይ? ከሳሾቹ እኛ ፈራጆቹ እኛ አይደለንም ወይ? ገደል ከትተን ገደል ገቡ ብለን የምናወራ፣ ለእግዚአብሔር የሠራን እየመሰለን ሰይጣንን የምናገለግል አይደለንም ወይ? ክፉ ሥራችንን ታሪክ ሳይሆን እግዚአብሔር ይፈርደዋል:: የይሖዋ ምስክሮች አንዱን ሰባኪ አገልግለን ብለው ቢጠሩት የሚሄድ ማን ነው? የተላክነው እኮ «ወደ አሕዛብ ሁሉ ሂዱ» ተብለን ነው:: ከነ እገሌ ጋ ሰላም ስትባባሉ ታይታችኋል ተብለው ስንቶች ተባረሩ? በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የእነ እገሌን ጽሑፍ ስታነቡ ተገኝታችኋል ተብለው ስንት ደቀ መዛሙርትን አውጥተን ጣልን? የጴጥሮስን ሥልጣን ይዘናል እያልን ቆርኔሌዎሶች ቤት ገብተን መዳንን የምንሰብከው መቼ ነው? ለእኛ የሥልጣን ትርጉሙ መጨቆኛ፣ ሰውዬው በሕይወት እያለ የጥምጥም፣ ሲሞት የአፈር እያልን ማስገበሪያ ይሆን? በቁሙ አጽናኙኝ እያለን ርቀነው ሲሞት ግን የማይሰማውን ዳዊት፣ ቅዱስ ወንጌል፣ አህያ ለሸክም የሚከብዳትን በርካታ መጻሕፍት የምናነብ አይደለንምን? ሲታመም ያልጠየቅነውን ሬሳውን ግን እናጅባለን:: የሬሳ ሚዜነታችን መቼ ይሆን የሚያበቃው? ስለጠፉት ጸልዩ እንጂ ተሳደቡ የሚል ምን ጋ አለ? «የየጁ ደብተራ ቅኔ ቢያልቅበት ቀረርቶ ጨመረበት» እንዲሉ ስብከት ሲያልቅብን ስድብ ከመጨመር መቼ ነው ተቀምጠን የምንማረው? እንደ ጴጥሮስ *«ለእኔ ግን እግዚአብሔር ማንንም ሰው ርኩስና የሚያጸይፍ ነው እንዳልል አሳየኝ»* እንድንል እግዚአብሔር ይርዳን:: በእውነት ለእኛም ያሳየን! የወደድነውን ጠንቋይ መንግሥተ ሰማያት ስናስገባ፣ የጠላነውን የእግዚአብሔር ሰው ገሀነመ እሳት ስናወርድ ለምንውለው ለእኛም እንዲህ ያሳየን! መስቀል የሚሸከም ክርስቲያን ጠፍቶ መስቀል አሸካሚዎች ሆነናልና እግዚአብሔር ይማረን!

ወዳጆቼ ናቸው፣ ከአዲስ አበባ ለአገልግሎት ወጥተው አገልግለው ከቤተ ክርስቲያን ሲወጡ እዚያው በሩ ላይ አንድ እብድ «እናንተ» ብሎ ጠራቸው:: እነርሱም ምን ሊል ነው ብለው ቆሙለት:: እርሱ ግን ከስፍራው ሳይናወጥ:- «ይሄኔኮ ስታዩኝ ይህ እብድ ነው የምትሉኝ፤ እግዚአብሔር ግን ማን እንደሚለኝ ታውቃላችሁ?» አላቸው:: እነርሱም ተደንቀው «ማን ይልሃል?» አሉት:: «የእኔ ዕብድ ይለኛል» አላቸው:: እኛ አርቀን «ይሄ» እንላለን:: እግዚአብሔር ግን «የእኔ» ይላል:: ከሰው ኅሊና እንደ እብድ የተረሳችሁ፣ በማኅበረሰቡ ጆሮና ዓይን አጥታችሁ



የተጣላችሁ፣ ሰው ሁሉ «ያ» ወይም «ያቺ» የሚላችሁ ብትሆኑ እንኳን ማንነታችሁን ሳይሆን እናንተነታችሁን በማየት «የእኔ» የሚላችሁ አምላክ አላችሁና ደስ ይበላችሁ! በርግጥም እግዚአብሔር ከሰው ይለያል!

የሰውዬው መውደቅ ከማንም ይልቅ ለጌታው ያሳዝነዋል፣ መነሣቱም ከማንም ይልቅ ለጌታው ያስደስተዋል:: ስለዚህ የወደቀው ሰው ዕዳው ለጌታው ነውና እኛ መድከም የለብንም:: ቅዱስ ጳውሎስ:- *«አንተ በሌላው ሎሌ የምትፈርድ ማን ነህ? እርሱ ቢቆም ወይም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሊያቆመው ይችላልና ይቆማል»* (ሮሜ. 14፥4) ብሏል:: ሎሌውን ብንነካ ጌታው ራሱ ከሚነካው በላይ ይጣላናል:: ምክንያቱም ሎሌውን መንካት ጌታውን መንካት ነውና:: ሎሌህ ደክሟል አውጥተህ ጣለው ብሎ ጌታውን ማን ያማክራል? ይህ ፍጹም ጠብ ያመጣል:: ሰው የእኛ ሳይሆን ሰው የእግዚአብሔር ሎሌ ነው:: በሰው ሎሌ መፍረድ ወንጀል ነው:: ያ ጌታ የደከመውን ሎሌውን እንደ ጌታ አስተኝቶ ሲቀልበው ዳግም በብርቱ ኃይል ይቆማል:: እግዚአብሔርም ለደካማው ኃይል ይሰጣልና የእርሱን ሥራ ዝም ብለን ማየት ይገባናል::

ሰውን የእኔ ማለት ከባድ ነው:: ምክንያቱም ሰው የዓሣ ገላ ምልጭልጭ፣ የተልባ ስፍር ሸርታታ፣ ሲወዱት የሚያብድ በመሆኑ ሰውን የእኔ ስንለው እናፍራለን:: እኔ ብዙ ዘመን ሳፍር ኖሬአለሁ:: ለእግዚአብሔር ያልተማረከ ሰው ለእኔ ምንም ላላደረግሁለት እንዴት ሊታመን ይችላል? ሰውን የእኔ ማለት ከባድ ነው:: በሌላ አንጻር ሰው የእግዚአብሔር በመሆኑ ሰውን የእኔ ማለት ከባድ ነው:: ነገሥታቱና ጳጳሳቱ «ሕዝባችን» ሲሉ ኖረዋል:: ሰው ግን የእግዚአብሔር ነው:: ባለቤት አለው:: ባለቤቱ ብቻ ሲመለስ ደስ ይለዋል:: ለዚህ ነው በ «መልክአ ኢየሱስ» ድርሰት:- «የነፍሴ ባለቤት አንተ ኢየሱስ ክርስቶስ ነህና፣ በከንቱ የሞተውን ልጄን አግኝቼዋለሁ ብለህ መላእክቱን ተደሰቱልኝ በላቸው» የተባለው::

እኛ የምንወደው የእኛ የሆኑትን ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሁላችንን ይወደናል:: ዓለሙን ሁሉ ያፈቀረ ለእያንዳንዱ ግለሰብ የሞተ እርሱ ብቻ ነው:: እኛ የአደጋዎች ዜና ስንሰማ የምንለው «ስንት ሰው ሞተ?» ነው:: ቍጥሩ ያጽናናናል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ስለ አንዲት ነፍስ መጥፋት ይገደዋል:: እርሱ ያልበደሉ ዘጠና ዘጠኝ መላእክት እያሉት የበደለውን አንዱን አዳም ሊፈልግ የመጣ ባገኘውም ጊዜ ታላቅ ደስታን የተደሰተ ነው:: ቅዱስ አውግስጢኖስ:- «ሰዎች በሙሉ ጻድቅ ቢሆኑ በመካከላቸው ግን



www.ethiopinorthodox.org

አንድ ኃጢአተኛ ብቻ ቢኖር ክርስቶስ ለዚያ ሰው ወደዚህ ምድር መምጣቱንና መስቀሉን አይተውም ነበር፤ እርሱ እያንዳንዱን ግለሰብ ይወዳል» ብሏል::

ስለ ጠፉት በጎች ከርኅራኄ ይልቅ ፍርድ የሚቀናን ስላለፋንባቸው ነው:: እግዚአብሔር ግን በመፍጠር፣ በማዳን ስለደከመባቸው ይቆጫል:: የነፍስ ባለቤት እርሱ ነውና:: ስለ አንድ ሰውም ግድ የሚለው እርሱ ብቻ ነው::

የወደቁ ሰዎች የተዘረጉ እጆችን ይፈልጋሉ:: የወደቁ ሰዎች ለመነሣት መነሣታቸውን የሚናፍቁ ወገኖችን ማየት ይፈልጋሉ:: አሊያ እንደ ወደቁ ይቀራሉ:: ስለዚህ በወደቁት ወገኖች ላይ ተስፋ እንጣልባቸው:: የእግዚአብሔር ትዕግሥቱ ለዚህ ካበቃን እኛም ሌሎችን በተስፋ መጠበቅ አለብን:: እኛስ እግዚአብሔር ብዙ ዘመን የታገሣቸውን ለአንድ አዳር መሸከም አቅቶን ይሆን?

## እናስተውል

ታናሹ ወንድም እጅግ ክፉ ሆኖ የታላቁን ምክር ሊሰማ አልቻለም:: ታላቅየው በጣም ግድ ሲሉት:- «ድጋሚ ይህን አሳብ ብታነሣብኝ እገድልሃለሁ» በማለት ተናገራቸው:: ታላቅየው ግን:- «ልክ ነህ እኔ ወንድምህ መሆኔን ያወቅኸው ሰዎች ነግረውህ ነው:: ስለዚህ ልትገድለኝ ትችላለህ:: እኔ ግን ስትወለድ ስላየሁህ አልገድልህም» ብለው መለሱለት:: ስንወለድ ያዩ ይራራሉ:: እግዚአብሔርም ስንፈጠር አይቷልና ይራራልናል:: የሰባ ዓመት ሽማግሌ የስድሳ ዓመቱን ባልንጀራቸውን ልጅ ነው ይላሉ:: ሰው የዛሬውን ያያል:: ወዳጅ ግን የድሮውን ያያልና በስድሳ ዓመትም ልጅ ነው ይላል:: ለእግዚአብሔር ምሁሩም፣ ሽማግሌውም ሁሉም ልጅ ነው:: እንደ ልጅም ያየናል፤ ያዝንልናል:: የዛሬውን የቆሸሸ ማንነት ሳይሆን ሲፈጥረን የነበረውን ንጽሕና ያያል:: እኛ ያበላሸነውን ተፈጥሮ ሳይሆን እርሱ የፈጠረውን ብቃት ያያል:: የድሮውን የሚያይ ወዳጅ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ልጆቻችንን እኛ ስንመታቸው ልክ ነን:: ሌላ ሲመታቸው ግን ይከፋናል:: እንደ እኛ የሚችሉበት አይመስለንም:: እኛ ስንረግማቸው ያረካናል:: ከእኛ ጋር በዚያው ቅጽበት አንዱ ተደርቦ ቢራገም ግን እንቀየመዋለን:: ጭካኔአችን ጊዜያዊ እንጂ ለዘለቄታው አይደለም:: እግዚአብሔርም ለፍጥረቱ እንዲህ ያለ ርኅራኄ አለው:: ታግሦ ሲቀጣ ግን ለዓላማው ጨካኝ ነው:: ስለዚህ ርኅራኄውን ከጭከናው ጋር አስተባብረን ማመን ይገባናል::



የምናገለግላቸው ሰዎች ልጆቻችን ናቸው:: አንዳንዶቹ ዓመፀኛ ይሆኑና ስንማረር ዓመፀኛ ባይሆኑ ኖሮ የእኛ አገልግሎት እንደማያስፈልጋቸው እየተሰማን በደስታ እንጠብቃቸዋለን:: ምክንያቱም በሽተኛ ባይኖር ሐኪም፣ ችግረኛ ባይኖር ደግ፣ መሃይም ባይኖር መምህር፣ ዓመፀኛ ባይኖር ሰባኪ ባልኖረ ነበርና:: ታዲያ ዓመፀኛ ቢሆኑም እኛ እንውቀሳቸው እንጂ ሌላ ሰው ሲወቅስብን ቅር ይለናል:: ለምን? ስንል ያ ሰው የወቀሳቸው ተስፋን እያሳየ አይመስለንም፤ ዳግመኛም ተስፋ የቆረጠባቸው ስለሚመስለን ቅር ይለናል:: ይህ በራሴ ሁልጊዜ የማየው ነው:: የእኛ ወላጅነት የጸጋ ሆኖ እንዲህ ካራራ፣ የባሕርይው የሆነው የእግዚአብሔር አባትነትማ እንዴት ይራራ ይሆን? እርሱ ብዙ ዘመን የቻላቸውንም ሰዎች እኛ ለጥቂት ጊዜ በመሸከም እንድናግዘው ይፈልጋል::

በእንለ ማውታ ውስጥ ያደጉና ደህና ደረጃ ላይ የደረሱ ወገኖች ሌሎች ለእነርሱ ያደረጉላቸውን እነርሱም ለሌሎች ለማድረግ የድሆች መርጃዎችን ያቋቁማሉ:: የሚያደርጉልን ሰዎች ሳይናገሩ የ «አድርጉን» አደራ በውስጣችን ያስቀምጡብናል:: ብድር እንድንመልስ ሳይሆን እንድናበድር ያለ ድምፅ ይናገሩናል:: እንዲሁም እግዚአብሔር እንደ መገበን ስናስብ ለተራቡት፣ እንዳለበሰን ስናስብ ለታረዙት፣ እንደ ማረን ስናስብ ለካዱት እንራራለን:: አድራጎት አድራጎትን ይወልዳል::

በአንድ ወቅት ሽራተን አዲስ ሆቴል የምትሠራ ልጅ በጣም ተጨንቂአለሁ ብላ አንድ ጥያቄ ጠየቀችኝ:- «አንዲት ሙስሊም ልጅ ከእኛ ጋር ምሳ መብላት ትፈልጋለች፣ እኛ ግን በሃይማኖት ምክንያት አብረን መብላት አልፈለግንም:: ልጅቱ ደግሞ ትወደናለች» አለችኝ:: እኔም:- «ምሳውን የሚጋብዟችሁ የሆቴሉ ባለቤት የት ቤተ ክርስቲያን ነው የተጠመቁት?» ስላት ደነገጠች:: አዎ ባለጠጋ ከሆነ ምኑም አይታየንም:: ከእኩዮቻችን ለመለየት ግን ምክንያት እናበዛለን:: እምነታችንን እንሰብከዋለን እንጂ በኃይል በሰው ላይ አንጭነውም:: እምነት የሚፈልገው ልብን እንጂ ላይን አይደለምና:: ለሰዎች ስለሚያፈቅር አምላክ ከመንገራችን በፊት ስናፈቅራቸው ማየት ይፈልጋሉ:: እኛ ስናፈቅራቸው ካላዩ እግዚአብሔር እንደሚያፈቅራቸው በምን ያውቃሉ? ስለዚህ ስለ ፍቅር አምላክ ከመስበካችን በፊት እናፍቅራቸው! እንኳን ወደውን እኛ ሄደን ልናስተምራቸው ይገባናል:: ሃይማኖታችንን በጥላቻ ማስፋፋት አንችልም:: ሰዎች ጥላቻን በዓለም ጠግበዋል:: የክርስትና ሃይማኖት ከጥላቻ ዓለም የተለየ መሆኑን በማፍቀር ልናሳያቸው ይገባናል:: እግዚአብሔር የቻላቸውን እኛ ማሳደድ፣ ደግሞም በእርሱ ቸርነት ክርስቲያን እንደ ሆንን አለማሰብ ተገቢ አይደለም:: በሥጋና በደም



www.ethiopinorthodox.org

እንደ ተጋደሉ የመስቀል ጦረኞች እኛም በሥጋ መታገል ተገቢ አይደለም:: ክርስቲያን ሲሰደድ እንጂ ሲያሳድድ አያምርበትም::

## ጸሎት

እንደ ሰማህ ያልበየንክብኝ፤ እንዳየህ ያልፈረድክብኝ፤ የሰማህብኝን ያላሰማህብኝ፣ ያየህብኝን ያላሳየህብኝ መሐሪ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ:: አንተ ይህን ፀሐይ ለሁሉ አወጣህ፣ እኔ ግን የማምነውን ካላመኑ እያልኩ ወገኖቼን አስርባለሁ:: አንተ ይህን ዝናብ ለሁሉ አዘነብህ፤ እኔ ግን ሃይማኖትና ዘር እየለየሁ እመጸውታለሁ:: ጌታ ሆይ ብርሃን እንደሚያስተላልፍ ንጹሕ መስተዋት ያንተን ፍቅርና ቸርነት እንዳስተላልፍ እባክህ እርዳኝ:: እኔም ምርጫ በሚያውቀው ጥበቤ አንተን አልመረጥኩህም:: የመረጥከኝ አንተ ነህ:: እኔም በፍለጋዬ አላገኘሁህም:: ፈልገህ ያገኘኸኝ አንተ ነህ:: እባክህ የሚታደሱበት መስክ አጥተው በመንፈስ ረሀብና እስራት ለሚኖሩት ወገኖቼ የወንጌልን መስክ አሳያቸው:: ለራሴ ሳጣጥምህ ለሰው ተመኘሁህ:: አንተ ለሁሉ ትበቃለህና:: ወገኖቼ አንተን ውቡን ጌታ ሳያዩ እንዳያልፉ እማጸንሃለሁ:: ወደ እነርሱ በፍቅርና በወንጌል እውነት የሚፋጠኑ አገልጋዮችን እባክህ አስነሣ:: እኔም አውቄህ እንዳላወቀህ ከመሆን አድነኝ:: ሁሉን በተሸከመው ትዕግሥትህ ለዘላለሙ አሜን!





# ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

## የተዘረጋው መረብ

በአሜሪካ አገር ጐልደን ጌት ተብሎ የሚጠራ ድልድይ አለ:: ይህ ድልድይ ትልቅ ከመሆኑ የተነሣ አነስተኛ መርከቦችን በሥሩ ማሳለፍ ይችላል:: ታዲያ ይህ ድልድይ በሚሠራበት ጊዜ የድልድዩ ሠራተኞች ከድልድዩ ላይ እየወደቁ ይሞቱ ነበር:: የሟቾቹ ቍጥር መብዛት ያስጨነቃቸው መሐንዲሶች የሟቾቹ ቍጥር የሚቀንስበትን መፍትሔ ፍለጋ ለረጅም ሰዓት ከተወያዩ በኋላ መጨረሻ ላይ የደረሱበት መፍትሔ ከድልድዩ ሥር መረብ ማድረግ የሚል ነበር:: በዚህ አሳብ የተስማሙበት ምክንያት ሠራተኛው ከሚሠራው ድልድይ ላይ ቢወድቅ እንኳ መረቡ ስለሚይዘው ሕይወቱን ማትረፍ ይቻላል፣ የሚወድቀውን ሳይሆን የሚሞተውን ሰው ቍጥር እንቀንስ በማለት ነበር::

መረቡ ከሚሠራው ድልድይ ሥር ከተደረገ በኋላ ግን የሚሞት ሰው አይደለም መረቡ ላይ የሚወድቅ ሰው እንኳን ጠፋ:: ሁኔታው ግራ ካጋባቸው መሐንዲሶች መካከል አንደኛው የሚሞት አይደለም መረቡ ላይ የሚወድቅ ሰው እንኳን የጠፋበት ምክንያት ምን እንደሆነ ለማወቅ ከሠራተኞቹ አንዱን ቢጠይቀው ሠራተኛው እንዲህ በማለት መለሰለት:-

«መረቡ ሳይኖር በፊት ከድልድዩ ርዝመት የተነሣ ወደ ታች ስናይ ስለሚያስፈራን ልባችን ተከፍሎ እንወድቅ ይሆንን? በማለት ደጋግመን የቆምንበትን ቦታ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በምናደርገው ጥረት ትክክለኛውን ቦታ ከመርገጥ እንስትና እንወድቅ ነበር:: አሁን ግን መረቡ ከተደረገ በኋላ ብንወድቅ እንኳ መረቡ አለ በሚል እምነት ስለምንሠራ ትኩረታችን ሥራችን ላይ ብቻ ነው:: የሞት ፍርሃት ስለሌለብን ነው መረቡ ላይ እንኳ የሚወድቅ ሰው የጠፋው» በማለት መለሰለት::

ማንኛውም ሠራተኛ በሥራው ውጤታማ የሚሆነው በሥራው ዋስትና ሲኖረው ነው:: ማንኛውም ሰው ለመኖር የሚፈልገው ተስፋ ሲኖረው ነው:: ክርስቲያንም ፀንቶ የሚቆመው ብወድቅ እንኳ የሚያነሣኝ እግዚአብሔር አለ ብሎ ሲያምን ነው:: ስለዚህ የመውደቅን ባሕር ባሰብን ቍጥር በመውደቅ ባሕር ላይ



www.ethiopinorthodox.org

የተዘረጋውን ትልቅ መረብ የእግዚአብሔርን ፍቅር ስናስብ አንፈራም:: ደግሞም አንወድቅም::

የምንኖርበት ዓለም በፍርሃት የተሞላ ዓለም ነው:: ሰው ክፉዎችን ብቻ ሳይሆን ደጎችንም ይፈራል:: ሌሎችን ብቻ ሳይሆን ራሱንም ይፈራል:: ክፉዎችን ወጥመድ ያኖሩብኛል ብሎ ይፈራል:: ደጎችን በንግግራቸው ይገስጹኛል፣ በሕይወታቸው ያሳጡኛል ብሎ ይፈራል:: ሌሎችን ድንገት ቢለወጡብኝ ብሎ ይፈራል:: ራሱን የሚያፀፅት ውሳኔ ብወስንስ ብሎ ይፈራል:: ሰው ራሱን የሚፈራበት ትልቁ ፍርሃት ደግሞ ብሳሳትስ የሚለው ጭንቀቱ ነው:: የማይጀምሩ፣ የማይሞክሩ፣ ኅብረት የማያደርጉ፣ የማያገለግሉ፣ በአደባባይ መታየት አልፈልግም ... የሚሉ ሰዎች መሳሳትን የሚፈሩ ሰዎች ናቸው:: ስለዚህ ባለ መጀመር፣ ባለ መሞከር፣ ባለ መራመድ፣ ኅብረትን በመሸሽ፣ ባለ ማገልገል፣ ባለመታየት ስህተትን ለማራቅ ይሞክራሉ:: ባለመሥራት አለመሳሳት ይኖራል ብለን ማሰብ ተገቢ አይደለም:: ትልቁ ስህተት አለመሥራት ነው:: ስህተቶች ወደ ጠራ ነገር ያደርሳሉ:: ሙከራዎች ፍጹም ነገርን ይወልዳሉ:: በዓለም ላይ ያለው ፍርሃት ብቻ ሳይሆን ድልም ነው:: ፍርሃት የበደል ውጤት እንጂ የሰው የቀደመ ተፈጥሮው አይደለም:: ተፈጥሮ ቋሚ ነው:: መለወጥም አይቻልም:: ለምሳሌ:- ትላንት ያገኘነው ሰው ዛሬም ስናገኘው ሥጋና ነፍስ አለው:: ይህ ተፈጥሮ በመሆኑ ሊለወጥ አይችልም:: ትላንት ፈሪ የነበረውን ዛሬ ደፍሮ ስናገኘው፣ ይፈራው የነበረው የመጨረሻው ነገር ደርሶበት ከዚያ በኋላ ጀግና ሆኖ ስናየው ፍርሃት የሰው ባሕርይ /ተፈጥሮ/ አለመሆኑን እንረዳለን::

ሰይጣን ሰዎችን የሚያስርበት ትልቅ ማሰሪያው ፍርሃት ነው:: ሰዎች የሚፈሩበትን ዝርዝር ተናግረን መፈፀም አንችልም:: ነገር ግን በዓለም ላይ ተገቢ ፍርሃት መኖሩን ማወቅ አለብን:: ለምሳሌ:- ሰው እግዚአብሔርን መፍራቱ ቅዱስ ፍርሃት ነው:: ወንጀልን መፍራቱ ተገቢ ፍርሃት ነው:: በተቃራኒው ደግሞ ተገቢ ያልሆኑ ፍርሃቶች አሉ:: ከነዚያ ውስጥ አንዱ «እወድቃለሁ» የሚለው ስጋት ነው:: «እወድቃለሁ» የሚለው ስጋት ራስን መስጋት በመሆኑ የሰው ትልቁ ፍርሃት ራሱ መሆኑ ይገባናል:: በውስጣችን የፍቅር አየር እየተሟጠጠ ሲመጣ ሁሉም ነገር እያስፈራን እንመጣለን:: ሰዎችን ለደኅንነታችን አስጊ እንደሆኑ እየቆጠርን አለማግኘትና አለመገናኘት እንመርጣለን:: ችግሩ ያለው ሰዎች በትክክል አስጊዎቻችን ሆነው ሳይሆን የእኛ ልብ ከፍቅር መራቆቱ ነው:: ፍቅር ያለው ሰው ሺህ ሠራዊት በቀኙ፣ ሺህ ሠራዊት በግራው የከበበው ያህል ድፍረት ይሰማዋል:: ጭር ባለ መንገድ





በጨለማ ሲጓዝ አይፈራም:: ሰው ለእርሱ አስፈላጊው እንጂ አጥፊው አይደለም:: ስለዚህ ከተጠራጣሪዎች ይልቅ በሰላም ይኖራል:: የማይቀረውን ሞት አንድ ጊዜ ቆርጦ ሲመጣ ይጋፈጠዋል እንጂ እንደ ፈሪ ከመሞቱ በፊት ዘጠኝ ጊዜ በፍርሃት አይሞትም:: ለዚህ ነው ራሱ የፍቅር ደብዳቤ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፍቅር እንዲህ ያለው:- *«ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም፥ ፍርሃት ቅጣት አለውና፤ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም»* (1ዮሐ. 4:18)::

ሰዎች ያለፈው የውድቀት ታሪካቸው ፈሪ ስለሚያደርጋቸው በራቸውን ዘግተው መቀመጥን ይወዳሉ:: በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በጸጋ ሳይሆን በ «ይገባኛል» የሚያገለግሉ ደፋሮች ወይም የመሠረትነው እኛ ነን የሚሉ ትክለኞች ያሉትን ያህል በፍርሃት ጸጋቸውን ቀብረው የሚኖሩ ብዙ ወገኖችም አሉ:: ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ሲያስቡ ሰይጣን «የቀደመውን ስህተትህን አስብ» ይላቸዋል:: በቀደመ ታሪካቸው ታስረው የሚኖሩ፣ የሚወድቁ ሰዎችን በማየት አናገለግልም የሚሉ ብዙ ሰዎች አሉ:: እነዚህ ግን ፍቅራቸው ፍጹም አይደለምና እግዚአብሔር ያዝንባቸዋል::

## አለመናዘዝ አለማረፍ

አንድ ሕፃን ልጅ በቤታቸው ግቢ ውስጥ ወንጭፍ እየወረወረ በጊቢው ውስጥ የተተከለውን ዛፍ ለመምታት ሙከራ ጀመረ:: ደጋግሞ ቢሞክርም አንዲት ዛፍ እንኳን ለመምታት አልቻለም ነበር:: ሙከራው አለመሳካቱን አውቆ ወደ ቤቱ ለመግባት ፊቱን ሲያዞር በጊቢው ውስጥ ዳክዬ ቆማ አየ:: በመሰላቸት መንፈስም ወንጭፉን ወደ ዳክዬዋ ሲወረውር ጭንቅላትዋን መታትና ሞተች:: በዚህ ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ ደነገጠ:: እህቱም መጣችና:- «አይዞህ አትጨነቅ ያደረከውን ነገር ለማንም አልነግርም» አለችው::

በነጋታው አባትዬው ዓሣ ለማጥመድ ወደ ወንዝ ለመውረድ አሰበና ወንዱን ልጁን ና አብረን እንሂድ ቢለው፤ እህቱ ፈጠን አለችና:- «ወንድሜ ዛሬ በጣም ደክሞታል፣ ከቤት መውጣት አይፈልግም:: እኔ አብሬህ እሄዳለሁ» አለችው:: ልጁም ተቃውሞ ለማቅረብ ሲሞክር፤ ፈጠን ብላ:- «ዳክዬዋን አስታውስ» አለችው:: እርሱም ወዲያውኑ «ኦ እህቴ ትክክል ነች:: እኔ መሄድ አልፈልግም» አለ:: ማታውኑ እናትየዋ እራት ለመሥራት ፈልጋ ሴት ልጅዋን እንድታግዛት ስትጠራት፤ ለእናትዋ:- «እናቴ ላግዝሽ በጣም ፍላጎት አለኝ:: ነገር ግን ወንድሜ ዛሬ ከእናቴ ጋር እራት



www.ethiopinorthodox.org

ለመሥራት እፈልጋለሁ ስላሉኝ እርሱ ያግዝሽ» አለቻት:: ልጁ ተቃውሞ ለማቅረብ ሲሞክር እህቱ ፈጠን ብላ:- «ዳክዬዋን አስታውስ» አለችው:: እርሱም ቀበል አድርጎ:- «እህቴ ትክክል ናት ዛሬ እራት መሥራት እፈልጋለሁ» ብሎ ተነሣ::

ጊዜው እየቆየ በሄደ ቊጥር የእህቱ:- «ዳክዬዋን አስታውስ» የሚል ንግግር እየሰለቸውና ነጻነቱን በከፍተኛ ደረጃ እያሳጣው መጣ:: ነገሩን አሰላስሎ ለእናቴ ዳክዬዋን መግደሌን ብነግራት እኮ የምትቀጣኝ አንዴ ነው:: ለእናቴ ነግሬ እህቴን ብገላገላት ይሻላል» ብሎ ለእናቱ ነግሮ ቅጣቱን ሊቀበል ወሰነ::

ወደ እናቱም ሄዶ:- «እናቴ ሆይ የቤታችንን ዳክዬ አንድ ቀን ስጫወት በወንጭፍ መትቼ ገድያታለሁና ይቅር በይኝ» ብሎ ነገራት:: እናቱም:- «አይዞህ ልጄ ያን ቀን ዳክዬዋን በወንጭፍ መትተህ ስትገድላት በመስኮት ላይ ሆኜ እያየሁህ ነበር:: ይቅር ልልህ ፍላጎት ቢኖረኝም አንተ እስክትመጣና ጥፋትህን እስክትነግረኝ ነበር የምጠብቀው:: አይዞህ ምንም አላደረግህም» አለችው:: ልጁም ፍጹም የሆነ ዕረፍትን አገኘ:: የእህቱንም ክስ ናቀ::

ልጁ የምእመናን፣ ልጅቱ የሰይጣን፣ እናቱ የጌታ ምሳሌ ናቸው:: ደስታን በመፈለግ፣ ሁሉንም በመሰላቸት፣ በመሳሳትና በመድፈር ኃጢአትን እንሠራለን:: ኃጢአትን እስክንሠራው ዘላለም የሚኖሩ የሚመስሉ ድፍረትና «ይሁንታ» እናገኛለን:: ኃጢአትን ከሠራን በኋላ ግን ድፍረቱ በፍርሃት፣ ይሁንታው በክስ ይለወጣል:: ድፍረታችን እንደ ሸረሪት ድር የሚበጣጠስ፣ እንደ ጢስ ተና የሚጠፋ፣ እንደ ደመናም የሚበተን ይሆናል:: በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር አሁንም እንደሚወደን እየተጠራጠርን ከሰይጣን ጉያ ውስጥ ለመግባት እንሮጣለን:: ቢገሉኝም እንኳ አምላኬ ይሻለኛል የሚል እምነት እናጣለን:: ከኃጢአታችን በላይ ተስፋ ወደ መቍረጥ ውድቀት እናመራለን:: ከእባብ ጉድጓድ ወደ ዘንዶ ጉድጓድ መግባት ማለት ይህ ነው::

ሰይጣን ኃጢአትን እስክንሠራ ጎበዝ ይለናል:: ከሠራን በኋላ የማትረባ ውዳቂ ነህ ይለናል:: እስክንሠራው ያበረታን ጠላት መልሶ ይከሰናል:: ከኃጢአት በፊትና ከኃጢአት በኋላ ሰይጣን ሁለት ጠባይ አሉት:: ከኃጢአት በፊት ኃጢአትን ቀባብቶ የሚያቆነጅ ማታለል፣ ከኃጢአት በኋላ ደግሞ ምሕረት የማይገባህ ስለሆንህ እኖራለሁ፣ አገለግላለሁ አትበል ይለናል:: ሁለቱንም ጊዜ ጠላታችንን እናምነዋለን:: ሁለቴ ሰይጣንን ስንሰማ አንድ ጊዜ ግን እግዚአብሔርን አንሰማም::



መንፈስ ቅዱስ ወቃሽ ነው (ዮሐ. 16:8):: ሰይጣን ደግሞ ከሳሽ ነው (ራእ. 12:10):: ወቃሽ መመለስን የሚናፍቅ ወዳጅ፣ ለመንፈሳዊ መልካችን ተቆርቋሪ ነው:: ከሳሽ ደግሞ ተስፋ አስቆርጦ ገደል የሚከት ጠላት ነው:: መንፈስ ቅዱስ ኃጢአት ስንሠራ የሚወቅሰን ለንስሓ እንድንበቃ ነው:: ኃጢአታችንን ብቻ ሳይሆን ለኃጢአታችን የፈሰሰውን የክርስቶስን ደምም ያሳየናል (1ዮሐ. 1:7-9):: በመታጠቢያ ቤት ውስጥ መስተዋት አለ:: ዝቅ ስንል ደግሞ ውሃ አለ:: መስተዋቱ ቆሻሻን ያሳያል:: ቆሻሻን ካሳየ በኋላ መንጻትን ከፈለግህ ዝቅ በልና ታጠብ የሚል መልእክት ያስተላልፋል:: መንፈስ ቅዱስ በሕጉ መስተዋት ኃጢአታችንን ካሳየን በኋላ ለመንጻት ዝቅ ብለህ በንስሓና በክርስቶስ ደም ታጠብ ይለናል:: መታጠቢያ ቤት ያለው መስተዋት ብቻ ቢሆን ኖሮ ተወቅሶ መቅረት ብቻ በሆነ ነበር:: ነገር ግን ውሃም አለ:: እንዲሁም የክርስቶስ ደም ለኃጢአታችን ባይፈስልን ኖሮ በሕጉ ተወቅሰን በቀረን ነበር:: ነገር ግን:- *«የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል:: ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም:: በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው»* (1ዮሐ. 1:7-9) ይለናል::

ሰይጣን ግን ከሳሽ ነው:: የሚከሰንም ተስፋ ቆርጠን ከእግዚአብሔር ፍጹም እንድንርቅና እንድንሞት ነው:: እንደርሱ ያለ ኃጢአተኛ የለም:: ግን ልጥፋ አይልም:: ኃጢአተኞችን ግን «ጥፉ፣ ዋጋ የላችሁም» ይላል:: ሁላችንም የሰይጣንን ክስ እንፈራለን:: ከሆነ መፍራት ኃጢአትን ነበር:: ኃጢአት የሚያስፈራውን ያህል ሰይጣን አያስፈራም:: አካባቢያችንን ካፀዳን ዝንብ ከየት ይመጣል? ንጹሕ ቦታ ዝንብን ያሳድዳታል:: ሰይጣንም ዝንብ ነው:: ንጹሕ ከሆንን ይሰደዳል:: ቆሻሻችንን ካላፀዳን ግን ያንገበገብብናል:: መድኃኒቱ የዝንብ ማባረሪያ መግዛት ሳይሆን ራሳችንንና አካባቢያችንን በንስሓ ማጽዳት ነው::

ሰይጣን ሲከሰን ራሱ ንጹሕ ሆኖ ለእግዚአብሔር ሕግም ተቆርቍሮ አይደለም:: ራሱ ተከሳሽ ወንጀለኛ ነው:: የኃጢአታችን ጉዳይ የእኛና የሰይጣን ጉዳይ ሳይሆን የእኛና የእግዚአብሔር ጉዳይ ነው:: እግዚአብሔር ጠፍተን እንድንቀር ፈቃዱ አይደለም:: ደጅ ደጁን እያየ የሚጠባበቀን አባት ነው (ሉቃ. 15:20):: ስሜታችንን ያውቀዋል ግን ንስሓ እስክንገባ ይጠብቀናል:: በኀሊናና በጠላት ክስ ላይ ድፍረት የሚሰጠን የእግዚአብሔር ይቅርታ ነው:: እግዚአብሔር በትዕግሥቱ እየጠበቀን ነውና ተስፋ የቆረጠብንን ጠላት ንቀን ተስፋ



www.ethiopinorthodox.org

ያደረገንን ጌታ እንገናኝ:: ብፁዕ አቡነ ሺኖዳ:- *«አንተ በራስህ ተስፋ ብትቆርጥ እግዚአብሔር በአንተ ተስፋ አይቆርጥም»* ብለዋል::

እግዚአብሔር ከእኛ ኃጢአታችንን ከማመን የበለጠ ነገር አይፈልግብንም:: ሰይጣን የቀደመውን አስብ ይለናል:: ነገር ግን «ጠላቴ ሆይ አላወቅህም ወይ? የምትለውን ኃጢአት ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ ሠርዞልኛል» ልንለው ይገባናል:: ነቢዩ ሚክያስ:- *«ጠላቴ ሆይ÷ ብወድቅ እነሣለሁና÷ በጨለማም ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛልና በእኔ ላይ ደስ አይበልሽ»* (ሚል. 7:8) እንዳለው እኛም ማለት ይገባናል:: ዛፍ ላይ ለመውጣት የምትፈልግ ትል ብዙ ጊዜ ብትወድቅ እንደገና ትሞክራለች:: ከብዙ ሙከራ በኋላ ዛፍ ላይ ወጥታ የምትፈልገውን ፍሬ ትበላለች:: ታዲያ እኛ ከትል ያነሠ ተስፋ ይዘናል ወይ?

የሰው ልጅ የእርምጃ ሞተሩ ተስፋ ነው:: ተስፋ እግር ለሌለው እግር የሚሰጥ፣ ከጨለማው በስተጀርባ ያለውን ብርሃን የሚያሳይ ነው:: ተስፋ የድሆችና ቀን የከፋባቸው ማደንዘገር፣ ሰው ሠራሽም መጽናኛ አይደለም:: ተስፋ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ፣ በእግዚአብሔር ኃይል ለእግዚአብሔር ክብር የሚፈጸም ነው:: ከተስፋዎች ሁሉ የላቀው የመዳን ተስፋ ነው:: ከጥንት ጀምሮ የነበሩ ፈላስፎች እንደተናገሩት ሰው ለበጎ ሥራ የሚነቃቃው በልቡ የመዳንን ተስፋ ሲጨብጥ ነው:: በተቃራኒው የመዳን ተስፋ የሌለው በክፉ ሥራ ለመርካት የሚነሣሣ ነው:: ክርስትና በሰው ሕይወት የሚጀምረውም በመዳን ተስፋ መሆኑ ይደንቃል:: ወኅኒ ቤቶችን የመጎብኘት ዕድል ብናገኝ በጥብቅ የሚጠበቁ እስረኞች ቢኖሩ የሞት ፍርደኞች ናቸው:: የቁጥር እስረኞች ነገ እፈታለሁ የሚል ተስፋ ስላላቸው ጠባያቸውን ገርተው ለወኅኒ ቤቱ ሕግ ይገዛሉ፣ ትምህርቶችን በተልእኮ ይማራሉ፣ ገንዘብ ያጠራቅማሉ:: የሞት ፍርደኞች ግን ከዚህ በተቃራኒ ማንንም አይፈሩም፣ እንደውም ይፈራሉ:: አይማሩም፣ ታዲያ በአገራችን ባለው የምሕረትና የይቅርታ ሕግ ይቅርታ ተደርጎላቸው የሞት ፍርዱ ወደ ቁጥር ሲለወጥላቸው በማግሥቱ ሌላ ሰው ይሆናሉ:: እንደ ጠላት የሚያዩትን ሰው የነገ ወዳጃቸው እንደሆነ ያስባሉ፣ ለዘመናት የተደበቀውን ፍቅራቸውን በማውጣት መለማመጥ ይጀምራሉ:: ስለ ሞት የሚያደፋፍሩ የጭካኔ ጽሑፎችን በማራቅ ስለ ዓለም ነባራዊ ሁኔታ ማጥናት ይጀምራሉ:: የተልዕኮ ትምህርቶችን ይማራሉ:: የተፈቱ ያህል ይቦርቃሉ:: ጭምቶች ይሆናሉ:: ይቅርታውን ስለማይጠግቡ አሁንም ይቅር ለመባልና ዘመኑን ለማሳጠር ጨዋ ይሆናሉ:: ማረሚያ ቤቱ ስለ እነርሱ መልካም አስተያየት እንዲሰጥላቸው መልካምነት እንዴት ነው? እያሉ ይፈልጋሉ::



በጣም ታጋሽ በመሆን ከአንበሳነት የሰውነትን ጠባይ ይይዛሉ:: አዎ የመኖር ተስፋ ብቻ መልካም ሰዎች ያደርገናል::

በክርስትና ሕይወታችን በመንፈሳዊነት መመላለስ ከጀመርን በኋላ እንኳ ብዙ ፍርሃቶች አሉብን:: የመጀመሪያው ፍርሃታችን የክርስትና ሙቀቴን ጠብቄ እስከ መጨረሻው እዘልቀው ይሆን? የሚል ነው:: ሁለተኛው ፍርሃታችን ከቤተ ክርስቲያን አባላት ጋር በኅብረት ስንጓዝ የሚመጣውን መጋጨት እሸከም ይሆን ወይ? የሚል ነው:: ሦስተኛው ፍርሃታችን በአገልግሎታችን በጸጋ ማገልገልና ጸጋውን መተርጎም፣ ከውድቀትም መዳን ነው::

እነዚህ ሦስት ፍርሃቶች ያውኩናል:: ታዲያ በምትኩ ሦስት ዓይነት ድፍረቶችን በውስጣችን እናገኛለን:: የመጀመሪያው:- የወንድነት ድፍረት፣ ሁለተኛው:- የጀግንነት ድፍረት፣ ሦስተኛው የእምነት ድፍረት ነው:: የወንድነት ድፍረት አቅምን ሳያገናዝቡ፣ ስልታዊ ሳይሆኑ የሚጋፈጡበትና ለማንኛውም ተግዳሮት መልሱ ጉልበት ብቻ ነው ብሎ የሚያምን የጡንቻ ቋንቋ ነው:: እንዲህ ያሉ ሰዎች ሰይፍ የሚያነሡ በመሆናቸው የበለጠ ሰይፍ ሲገጥማቸው ይወድቃሉ:: የጀግንነት ድፍረት ያላቸው ደግሞ ኃይልን የሚጠቀሙት በመጨረሻ ነው:: እስከዚያ ድረስ ጥበብን ስለሚጠቀሙ የጠላታቸውን ማንነት ይረዳሉ:: በመጨረሻ ሲወጡ ያሸንፋሉ:: የእምነት ድፍረት ያላቸው ግን ያለ ሰይፍ መመጣጠን፣ ያለ ሥጋዊ ስልት በመንበርከክ ብቻ ያንበረክካሉ:: ያለ ደም መፋሰስ ድል የሚገኘው በእምነት ሰልፍ ነው:: እምነት ራስን ሳይሆን እግዚአብሔርን ማየት ነው:: እምነት በእግዚአብሔር ላይ ያለን እርግጠኝነት ነው:: እምነት ድልን ጨብጦ መዋጋት ነው:: ሥጋ ድል ለማድረግ ይዋጋል:: እምነት ግን ድልን ወርሶ ይፋለማል:: አንድ ሰው:- *«እንደምናሸንፍ እርግጠኛ ባልሆንበት ነገር ላይ እግዚአብሔር ድል አይሰጠንም:: እንደምናሸንፍ እርግጠኛ በሆንበት ነገርም ሰይጣን አይፈትነንም፣ ሌላ ፈተና ይቀይራል እንጂ»* ብሏል:: ሌላውም ሰው:- *«እግዚአብሔር የሚገኝበት ጣቢያው እምነት ነው:: ሰይጣን የሚገኝበት ጣቢያው ፍርሃት ነው»* ብሏል::

ያለንበት ዘመን በሥነ ልቡና የወደቁ ሰዎችን ለመርዳትና እንዲያንሰራሩ ለማድረግ ብዙ ባለሙያዎች ጠብ እርግፍ የሚሉበት፣ ብዙ እጆች በራስ ስለመተማመን ብዙ መጻሕፍት የሚጽፉበት ዘመን ነው:: መጻሕፍቱ ግን የበለጠ ባዶነትንና ተስፋ ቢስነትን ከማምጣት በቀር ትውልድን ሲያድኑ አልታዩም:: ከፍተኛ የሆነው የሥነ ልቡና ማነቃቂያቸውም:- «በውስጥህ እምቅ ኃይል አለ፣ ያን እምቅ ኃይል አውጣው» የሚል ነው:: የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሳይቀር



www.ethiopinorthodox.org

ስለዚህ እምቅ ኃይል በመስበክ ከዓለሙ ጋር ለመመሳሰል ጥረዋል:: ወይም ዘመናውያን ለመባል ተጨንቀዋል:: ሰው ያለ ክርስቶስ ሙት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል እንጂ በራሱ የሚያኖር ሕይወት እንዳለው አይናገርም (ኤፌ. 2:1-5):: ሰው በውስጡ እምቅ ኃይል ያለው፣ ራሱን በራሱ የሚያድን አምላክ ሳይሆን ደካማ ማንነት ያለው በክርስቶስ ሲያምን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚለውጠው መሆኑን ይናገራል:: ዓለም ትደልለናለች፣ እግዚአብሔር ግን ደካማ ናችሁ ወደ እኔ ስትመጡ ትበረታላችሁ ይለናል:: የአሁን ትውልድ ግን በእግዚአብሔር ከሚበረታ በአደንዛዥ ዕፅ ራስን በማነቃቃት ቢበረታታ ይመርጣል:: ምክንያቱም ዓለም የእግዚአብሔርን ህልውና አስክዳው ለራስህ አምላክ ራስህ ነህ አለችው:: አምላክነት ከብዶት ሲንገዳገድም ትስቅበታለች:: ሰው በተፈጥሮው ያለው ደካማነት ነው:: በክርስቶስ ሲያምን ግን ራሱ ያልቻለውን፣ ሕግም የማይሰጠውን የተለወጠ አኗኗር ይጎናፀፋል (ሮሜ. 8:3-4):: እግዚአብሔር በውስጡ ኃይለኛ ካልሆነ በቀር ሰው በውስጡ ያለው ባዶነት ብቻ ነው:: *«ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ»* (ፊልጵ. 4:13) የተባለው ለዚህ ነው:: ኃይሉን ካልተቀበለ ሁሉን አይችልም ማለት ነው:: ስለዚህ ሰው የሚያመነጨው ኃይል የለውም፤ የሚቀበለው ኃይል ግን አለ:: ስለዚህ በእምነት እጁን መዘርጋት አለበት::

እግዚአብሔር ሲጠራን ያሰበልንን ያያል:: እግዚአብሔር ከታሪካችን ጋር ሳይሆን ከዛሬ ጋር ጉዳይ አለው:: ዛሬን ሳይሆን ነገን ያይልናል:: የሆንነውን ሳይሆን የምንሆነውን ይነግረናል:: የሆንነው የሚያሸማቅቅ፣ ለመናገር የሚያሳፍር፣ ይለወጣል ብለን ተስፋ የማናደርገው ሊሆን ይችላል:: እግዚአብሔር ግን ባየልን ስም ይጠራናል:: ይህ የእግዚአብሔር ትዕግሥት ነው:: ይህ እርሱ በእኛ ላይ ያለው ተስፋ ነው:: ስምዖን ጴጥሮስን ሲጠራው «ዓለት» በሚል ስም ጠራው (ዮሐ. 1:43):: ጴጥሮስ ሕይወቱ ገና እንደ ሸንበቆ የሚወዛወዝና እርጋታ ያጣ ደካማነት ነበር:: ይህ ጠባዩ ለራሱም በድሎታል:: ጌታ ግን የዛሬውን ሸምበቆነት ትቶ በነገው ማንነቱ ጴጥሮስ አለው:: ጴጥሮስም ጌታ ወዳስቀመጠለት መለኪያ መጓዝ ጀመረ:: በሮም አደባባይ የቁልቁሊት ተሰቅሎ ዓለትነቱን አስመሰከረ:: ጌታ ያየልን ይበልጣል:: እርሱ በእያንዳንዳችን ላይ ዓላማ አለው:: መንግሥታት በብዙኃኑ ላይ ዓላማ አላቸው:: እግዚአብሔር ግን በእያንዳንዳችን ላይ ዓላማ አለው::

ጌዴዎንን ሁላችንም እናውቀዋለን:: ምድያማውያንን ከመፍራቱ የተነሣ በወይን መጥመቂያ ጉድጓድ ውስጥ ስንዴ ይወቃ ነበር:: እግዚአብሔር ግን የዛሬ ማንነቱ ይህ ቢሆንም ነገ ለሌሎች



ልብ ሰጪ እንዲሆን ማድረግ ነበረ:: ስለዚህ ጌታ:- *«አንተ ጽኑዕ ኃያል ሰው÷ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው አለው»* (መሳፍ. 6:12):: እግዚአብሔር ጌዴዎን ራሱን የሚያውቅበትን ፈሪ የሚለውን መጠሪያ ቢጠቀም ሐቅ አይሆንም ወይ? ብንል ውስጡ ፈሪ የሚለውንና ፈሪነቱን በተግባር የገለጸውን ሰው ፈሪ ማለት ከፍርሃት አያድነውም:: በእግዚአብሔር ኃይል የምትወረሰውን የድፍረትን ከተማ ማሳየት ግን ያስጀግነዋል:: ስለዚህ ጌታ ጌዴዎን በሆነው ሳይሆን በሚሆነው ስሙ ጠራው:: ጌዴዎን ፈሪ ነው:: ጌታ ግን ያሰበለት ሌላ ነው:: በኮሚኒዝም ርእዮተ ዓለም መፈክር በብዛት ይነገራል:: ዓላማው መፈክር ከውስጥ ያለውን ድፍረት ያወጣል ወይም ፍርሃትን ይዋጋል ተብሎ ስለሚታሰብ በመደጋገም ይፈከር ነበር:: ለእኛ የተሰጡን የእምነት መፈክሮች አሉን:: እነዚያን መፈክሮች ለፈራው ልባችን እንበላቸው:: ከእነዚህ መፈክሮች ውስጥ:- *«ደካማውም:- እኔ ብርቱ ነኝ ይበል»* (ኢዩ. 3:10) የሚለው ልብን ይነካል:: የጥቅሱ አሳብ ለራሱ አምላክ ሆኖ እችላለሁ ይበል ማለት አይደለም:: ይህ የዘመናዊው ዓለም ፉከራ ነው:: የዘላለሙ ዓለም ፉከራ ግን በእምነት እግዚአብሔርን እያዩ የሚያሰሙት ቃል ነው:: እንዲህ ያሉ የእምነት ሰዎች በመጨረሻ:-

*«ኃይል የሌለውን ምንኛ ረዳኸው!*
*ብርታት የሌለውን ክንድ ምንኛ አዳንኸው!*
*ጥበብስ የሌለውን ምንኛ መከርኸው!*
*ብዙ እውቀትንስ ምንኛ ገለጥህለት!»* (ኢዮ. 26:2-3) በማለት አመስግነዋል::

እግዚአብሔር ይታገሣል ስንል ይጠብቀናል ወይም ተስፋ ያደርገናል ማለት እንደሆነ አይተናል:: እግዚአብሔር የሚጠብቀን ከሆነ በራሳችን ላይ ተስፋ እንዳንቆርጥ ደግሞም እግዚአብሔር ተስፋ ባልቆረጠበት ሰው ላይ ተስፋ እንዳንቆርጥ መጠንቀቅ ይገባናል:: ለዚህ ክፍል ማጠቃለያ የምናደርገው በዘዳ. 32:10-11 ያለውን ቃል በማየት ነው::

## በክንፎቹ አዘላቸው

*«በምድረ በዳ በጥማት÷ የነፋስ ጩኸትም በሞላበት ውድማ አገኘው፤ ከበበው ተጠነቀቀለትም፤ እንደ ዓይን ብሌን ጠበቀው:: ንስር ጫጩቶቹን እንደሚያወጣ÷ በእነርሱም ላይ እንደሚሰፍፍ÷ ክንፎቹን ዘርግቶ ወሰዳቸው÷ በክንፎቹም አዘላቸው»* (ዘዳ. 32:10-11)::



www.ethiopinorthodox.org

ይህንን ጥቅስ በሙላት ለመተርጎም ሌላ መጽሐፍ መጻፍ ያስፈልገናል:: ጥቅሱ እግዚአብሔር ለእስራኤል ስላደረገው እንክብካቤ ሙሴ ምስጋና ያቀረበበት ክፍል ነው::

እግዚአብሔርና እስራኤል የተገናኙት በአገራቸው ሳይሆን በስደት አገር፣ በምቾት ሳይሆን በሚያንገዋልል የፈተና መድረክ ነው:: *«በምድረ በዳ በጥማት፥ የነፋስ ጩኸትም በሞላበት ውድማ አገኘው፤»* (ዘዳ. 32:10):: እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገው እንክብካቤም ንስር ለጫጩቶቹ እንደሚያደርገው እንክብካቤ ያለ ነው:: ይህንንም ራሱ እግዚአብሔር ተናግሯል:- *«በንስርም ክንፍ እንደ ተሸከምኋችሁ፥ ወደ እኔም እንዳመጣኋችሁ አይታችኋል»* (ዘፀ. 19:4) ብሏቸዋል:: ሙሴም:- *«ንስር ጫጩቶቹን እንደሚያወጣ፥ በእነርሱም ላይ እንደሚሰፍፍ፥ ክንፎቹን ዘርግቶ ወሰዳቸው፥ በክንፎቹም አዘላቸው»* (ዘዳ. 32:11) ብሏል::

ንስር እንቁላሎቹን ከማስፈልፈሉ በፊት በጎጆው ወለል ላይ እሾህ ዘርዘር አድርጎ ይሰካካል:: በተሰካካው እሾህ ላይም ቆዳ ይወጥርበታል:: ይህ በሙቀት እንዲፈለፈሉና ከተፈለፈሉም በኋላ እስኪያድጉ እንዳይበርዳቸው የሚረዳ ነው:: ጫጩቶቹ ማደግ ሲጀምሩ ከጎጆው ውጭ ያለውን ገደል በመፍራትና በጎጆው ውስጥ ያለውን ሙቀት (ምቾት) ባለመጥገብ ካሉበት አይንቀሳቀሱም:: በዚህ ጊዜ ንስር ቆዳውን ይልጠዋል:: ቆዳው ሲላጥም ምቾት ይጠፋና እሾኾቹ መዋጋት ይጀምራሉ:: እሾሆቹ ፊት ለቆዳ መወጠሪያ አሁን ደግሞ እየወጉ አላስቀምጥም ለማለት ያገለግላሉ:: ከእሾሁ የተነሣ ወደ ደጅ ለመውጣት ሲፈልጉትን ጫጩቶች ንስር የበረራ ልምምድ ያደርግላቸዋል:: የሚያለማምዳቸውም ጫጩቶቹ ከላይ ሲበሩ ከሥር ክንፎቹን ዘርግቶ በመጠባበቅ ነው:: ይህ ሁለት ጠቀሜታ አለው:: ድፍረትና ሕይወት! ጫጩቶቹ ሲለማመዱ መውደቅን ፈርተው ልምምዱን እንዳያቋርጡ የተዘረጋው ክንፍ ድፍረት ይሆንላቸዋል:: ዳግመኛም ጠላት ከሩቅ ከመጣ በፍርሃት ራሳቸውን ወደ ታች ይጥላሉ:: ነገር ግን ራሳቸውን ቢጥሉም የሚያርፉት በተዘረጋው ክንፍ ነው::

እግዚአብሔርም ለሕዝቡ ያደረገው እንክብካቤ እንዲህ ነው:: ወደ ክርስትናው ዓለም ስንመጣ ከድካም ዕረፍት፣ ከመቅበዝበዝ ወደ መርካት የተሸጋገርንበት ሰላማዊና ምቹ ጊዜ ነው:: ነገር ግን ይህ ሁሉም ነገር ፀጥ ያለበት ክፍለ - ጊዜ እስከ መጨረሻው አይዘልቅም:: በፈተና ውስጥ ያለውን ሰላም፣ በማዕበል ውስጥ ያለውን ፀጥታ እንድንለማመድ እግዚአብሔር በልምምድ ውስጥ ያሳልፈናል:: ይህ ለብዙዎቻችን የሚጥመን አይደለም:: ምክንያቱም





ልምምድ አድካሚና አሰልቺ በመሆኑ ነው:: ግን ለቀጣዩ ጥንካሬ መዘጋጃ ነው:: መንግሥት ወታደሩን የሚያሰለጥነው ጦርነት ሲመጣ ሳይሆን ከጦርነት በፊት ነው:: ዳግመኛም የሚያሰለጥነው በከተማ ሳይሆን በምድረ በዳ ነው:: ስልጠናውም ችግርን የሚቋቋም ማንነትን ለመፍጠር ነው:: እግዚአብሔርም ለመንፈሳውያን ሠራዊቱ እንዲህ ያለ የልምምድ ጊዜ አለው:: በዚህ ልምምድ ውስጥ ከምቾታችን ጣኦት ይለየናል:: ለሌሎች ራሳችንን እስክንሰጥ የቆረጥን የፍቅር ሰዎች ያደርገናል:: ከፍርሃትም ፈትቶ በየትም ስፍራ ለክርስቶስ ምስክር መሆን የምንችል አድርጎ ይሠራናል::

ለማገልገል የመጀመሪያው ፈተናችን ከመገልገል ሙቀት ውስጥ መውጣት አለመፈለጋችን ነው:: ሙቀት የሚፈልገውን የልጅነታችንን ዘመን እግዚአብሔር ያከብረዋል:: ሁሉም እኛን ለማገልገል፣ ለእኛ ለመጸለይ የሚተጋበት፣ እንደ ብርቅዬ ልጅ የምንታይበት ዘመን ነው:: የንስር ጫጩት ከሙቀት የበለጠ ነገር አላት:: እርሱም በከፍታዎች ላይ መብረር ነው:: ለእኛም የከፍታ ዘመን አለን:: እርሱም:- ከሚታሰብልን ልጅነት ወጥተን ወደሚያስብ ጉልምስና የምንደርስበት፣ አባብለኝ የሚለውን ሞልቃቃነት ጥለን እንደ ወታደር በረሃውን እያቋረጥን ወደ በረከት ምድር የምንገሰግስበት ከፍታ ተዘጋጅቶልናል:: እግዚአብሔር የጎጆውን ሙቀት በመንሣት ወደሚቀጥለው ደረጃ ሊያሸጋግረን ይፈልጋል:: እግዚአብሔር ለእስራኤል ያሰበላቸው ምድረ ርስትን ነው:: በግብፅ አንጻራዊ ሰላም ቢያገኙና የዕለት ጉርሳቸውን በሠራተኛ ክብር ቢቀበሉ ለዘላለም ከግብፅ መውጣት አይፈልጉም ነበር:: ግን ነጻ ሕዝቦች ሳይሆን የደለቡ ባሪያዎች ሆነው ይኖሩ ነበር:: እግዚአብሔር ወዳሰበላቸው ከፍታ ለመድረስ ግን ግብፅ ለእነርሱ እሾህ መሆን ነበረባት:: ስለዚህ እግዚአብሔር ምቾትን ነሣቸው::

ይህ የዘመናት የእግዚአብሔር አሠራር ነው:: ወዳሰበልን ደረጃ የሚያደርሰን ያለንበትን ስፍራ የማይመች በማድረግ ነው:: እግዚአብሔር በመገልገል ሙቀት ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች በትግል ውስጥ በማሳለፍ በውስጣቸው የተቀበረውን እውነት እንዲያወጡትና መንፈሳዊ ደረጃቸውን ከፍ እንዲያደርጉ ይፈልጋል:: በክርስትናችን ሁለተኛው ፈተናችን የመውደቅ ፍርሃት ነው:: በእምነት መመላለሱንና ማገልገሉን እሺ እንላለን:: ግን ብወድቅስ? እንላለን:: ሕፃን ልጅ መውደቅን ቢያስብ መቼም ቆሞ አይሄድም ነበር:: መውደቅ ለሰው መጨረሻው አይደለም:: ወድቆ መነሣት ያለመውደቅን ያህል አስደሳች ነው:: ሕይወት ተአምር እንድትሆንልን፣ ሳንደክም ሁሉም ነገር በዓይን ጥቅሻ እንዲሠራልን እንመኛለን:: እግዚአብሔር ተአምራት ቢያደርግም የሕይወትን ቋሚ



www.ethiopinorthodox.org

ሕግ ያደረገው ልምምድን ነው:: በኑሮ መለማመድ:: በአንድ ጊዜ የጠራ አገልጋይ መሆን አይቻልም:: እግዚአብሔር ያለማምዳል:: ሥር ለመስደድ፣ ብዙ ለመማር፣ የሰውን ድካም ለመረዳት ልምምድ ወሳኝ ነው:: እዚህ ላይ ልምምድ የምንለው ጸጋን መለማመድ አይደለም:: በጸጋ ለማደግ የምናደርገውን ልምምድ ነው:: ብዙ ፕሮቴስታንቶች ልሳንን ይለማመዳሉ:: ጸጋን ግን በመቀበል እንጂ በመለማመድ ማምጣት አይቻልም:: መለማመድ የምንለው በጸጋችን ለማደግ የምናደርገውን እንቅስቃሴ ነው::

ስንለማመድ የመውደቅ ፍርሃት ያስጨንቀናል:: ነገር ግን በእኛና በውድቀታችን መካከል እግዚአብሔር ረድኤቱን ዘርግቷል:: ነቢዩ:- *«በላባዎቹ ይጋርድሃል ÷ በክንፎቹም በታች ትተማመናለህ፤»* (መዝ. 90:4) ብሏል:: በልማድ የሚነገር ነገር አለ:: «እንደ አወዳደቁ ሞቼ ነበር፣ እግዚአብሔር ግን ተነጠፈልኝ» እንላለን:: በእኛና በውድቀታችን መካከል እግዚአብሔር ባይገባ ሞተን እንደነበር መግለጻችን ነው:: ዛሬም በእምነት ለመመላለስና ለማገልገል ስንነሣ በውድቀታችን ሥር የተዘረጋውን የእግዚአብሔርን ረድኤት ልናስብ ይገባናል:: በእውነት የእግዚአብሔር ትዕግሥት ትንሣኤያችን ነው::

## እናስተውል

ብዙዎቻችን ለሰይጣን ያለን አመለካከት እንደ ቃሉ አይደለም:: ሰይጣን እንደሚፈትነን እናምናለን:: እግዚአብሔር እንደሚረዳን ግን በበቂ አናምንም:: በርግጥ ጠላታችን ሰይጣን የተሸነፈ እንጂ የሞተ ጠላት አይደለም:: ይፈትነናል:: ከሚፈትነን ሰይጣን ግን የሚረዳን እግዚአብሔር ኃይሉ ታላቅ ነው:: ሰይጣን ፈታኝ ቢሆንም ፍጡር ነው:: ኃይሉና ፈቃዱ የተወሰነ ነው:: የሚረዳን መንፈስ ቅዱስ ግን ፈጣሪ፣ ወሰን የማይበጅለት፣ ፍጹማዊ ኃይል ነው:: የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ ያለው ሲሆን ይህን ነጻ ፈቃዱንም እግዚአብሔርም ሆነ ሰይጣን አይጋፉትም:: ነጻ ፈቃዱን ለእግዚአብሔር ሲሰጥ እግዚአብሔር ስለ እርሱ ይዋጋል:: ነጻ ፈቃዱን ለሰይጣን አሳልፎ ሲሰጥ ደግሞ ሰይጣን ባሪያ አድርጎ ይገዛዋል:: ሰይጣን በእኛ ላይ ኃይል ያለው ነጻ ፈቃዳችንን አሳልፈን እስከ ሰጠነው ድረስ ነው:: ነጻ ፈቃዳችንን አሳልፈን ካልሰጠነው በእኛ ላይ አንዳች ሥልጣን የለውም:: እኛ ያለነው መንፈስ ቅዱስ በመጣበት፣ መልካሙን ሥራ ለማድረግ በተፈታንበት፣ በቤተ ክርስቲያን በኩል ብዙ ጸጋ በሚታደልበት ዘመን ነውና ሰይጣን ኃይለኛ ሆነብኝ ከማለት ኃይሌን አላወቅሁኝም ማለት ይሻለናል:: የሰይጣንን ማንነት በቅጡ ያወቅን አይመስልም:: እርሱ የተዋረደ፣ መኖሪያው በታችኛው ሲኦል የሆነ፣ አሳብ እንጂ እግር የሌለው



እባብ ነው (ዘፍ. 3:14):: እርሱ ያሻውን ሊያደርግብን በፍጹም አይችልም:: የደሙ ማኅተም እስካረፈብን፣ የእግዚአብሔር ወገን እስከሆንን ድረስ በእኛ ላይ አንዳች ሥልጣን የለውም:: ኢዮብን ለመፈተን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠይቋል (ኢዮ. 1:6-12፣ 2:1-6):: እግዚአብሔርም የኢዮብ ፍቅር እንዲገለጥ፣ ሰይጣንም እንዲያፍር፣ የእግዚአብሔር ልጆችም የማያልቅ ትምህርት እንዲያገኙ ኢዮብን ይፈትን ዘንድ ለሰይጣን ፈቅዶለታል:: ሰይጣን ደጋግሞ ፈቃድ ጠየቀ እንጂ በኢዮብ ላይ አንዳች አላደረገም:: ሥልጣን ካለው ለምን አስፈቀደ? አሁንም የሌጌዎን ሠራዊት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ እሪያዎች መንጋ ለመግባት በጥብቅ ለመኑት (ማር. 5:1-13):: እሪያዎች ውስጥ ለመግባት እንኳ ሥልጣን የሌላቸው አጋንንት በደሙ በተገዛን በእኛ ላይማ ምን ሥልጣን አላቸው? አጋንንቱም በእሪያዎቹ ላይ ባደሩባቸው ጊዜ እያጣደፉ ወደ ባሕር ጨመሯቸው:: የቅጽበት ዕድሜ እንኳ አልሰጧቸውም:: አጋንንት በሰው ላይ ሥልጣን ቢኖራቸው የሰውን ዘር በቅጽበት በጨረሱት ነበር:: ይህንን ትምህርት ዮሐንስ አፈ ወርቅ አምልቶና አስፍቶ ጽፎልናልና የእርሱን ድርሳናት ብናገላብጥ ብዙ ትምህርት እናገኛለን::

የመውደቅ ፍርሃታችን አንዱ ሰይጣንን በእኛ ላይ ሥልጣን እንዳለው ማሰባችንና መፍራታችን ነው:: ሰይጣንም እኛን ከሚያስፈራራበት ነገር አንዱ የቀደመውን ውድቀታችንን በማስታወስ ማስፈራራት ነው:: ነገር ግን እግዚአብሔር ሕይወትን ሊያለማምደን ከውድቀታችንም ሊያነሣን ቆሟልና በእርሱ ልባችንን እናበርታ!

## ጸሎት

የወደቁትን የምታነሣ፣ የአማንያን ተስፋ፣ የዕድሜዬ ባለቤት፣ በጠፊው ዓለም ላይ ያገኘሁህ የማትጠፋው ሀብቴ እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ:: ያላሰብኩትን መልካም ነገር እንድጀምር፣ የጀመርኩትን እንድፈጽም የምትወተውተኝ አንተ ነህና አመሰግንሃለሁ:: የሕይወት አስታዋሼ አንተ ነህ:: ብዙ ዘመን ከወደቅሁበት አንሥተህ በክብር ስፍራ ያስቀመጥከኝ አንተ ነህ:: አሁንም ጌታዬ ሆይ ልቤን ባንተ አበርታው:: «አይሆንም» የሚለውን ፍርሃቴን ውሰደው:: ወደ አሳየኸኝ ግብ እግሬን አፍጥነው:: ወጥመዱን ሰብረህ አሻግረኝ:: ከኪራይ ዓለም ወጥቼ ወዳንተ እስክመጣ ያዘዝከኝን ለመፈጸም አትታኝ:: በዘላለማዊው ፍቅርህ አሜን!



www.ethiopinorthodox.org

# ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

## አይቻኩልም

በእግዚአብሐር ህልውና የሚያምንና በእግዚአብሐር ህልውና የማያምን ሁለት ባልንጀሮች ነበሩ:: ሁለቱ ባልንጀሮች በየዕለቱ ስለ እግዚአብሐር ህልውና ይሟገቱ ነበር:: አማኒው ከሃዲውን:- «እግዚአብሐር ከሌለ ይህ ዓለም እንዴት ተገኘ? ዓለም ፍጥረት ነው፣ ፍጥረት ማኀት ነው፤ ማኀት ደግሞ አስገኚ አለው:: ስለዚህ የፍጥረት ፈጣሪ ማነው?» ይለዋል:: ከሃዲው ግን:- «እንዲሁ ተገኘ» በማለት ይመልስለታል:: ከዕለታት በአንዱ ቀን አማኒው ሉል አዘጋጀ:: ሉል የምድርን ቅርጽ የያዘ ሞላላ የዓለም አገሮችን ካርታ የሚያሳይ ማሳያ ነው:: ሉሉን ጠረጴዛ ላይ አስቀምጦ ከሃዲ ባልንጀራውን ጠበቀው:: ከሃዲውም ሲመጣ ዓይኑ ያረፈው ሉሉ ላይ ነበርና «ከየት አመጣኸው?» አለው:: አማኒውም ሲመልስ:- «እንዲሁ ተገኘ» አለው:: «እንዲሁ እንዴት ይገኛል? አትቀልድ ከየት አመጣኸው?» አለው:: አማኒውም ፍርጥም ብሎ:- «እንዲሁ ተገኘ» በማለት መለሰለት:: ከሃዲውም:- «የማይሆን ነገር ነው፤ ከየት አገኘ ኸው?» ቢለው አማኒው:- «እኔ ምሳሌውን እንዲሁ ተገኘ ስልህ ደነቀህ:: አንተ ዋናውን ዓለም እንዲሁ ተገኘ ብለኸኝ የለም ወይ?» አለው:: በዚህ ጊዜ ከሃዲው ልቡ ተነካ:: ይህች ዓለምም አስገኚ አላት፣ እርሱም እግዚአብሐር ነው ብሎ አመነ ይባላል::

እግዚአብሐር የለም በማለት ዓለምን ባለቤት የሌላት ቤት ያደረጓት እነዚያ ከሃዲዎች ምንኛ በደሉን? የሞራል ውድቀት፣ የግብረ-ገብ መላሸቅ፣ የጋብቻ መፍረስ፣ ነውርና ሴሰኝነት ሁሉ በምድር ላይ የነገሠው የእግዚአብሐር ህልውና ከተካደበት ጊዜ አንሥቶ ነው:: እግዚአብሐር የለም ከሚል አዋጅ በኋላ የአንደኛውና የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ተካሂዷል:: ለሦስተኛውና ለኒውክለር ጦርነትም እየተዘጋጀን ነው:: እግዚአብሐርን አስወጥተን በሰላም መኖር አልቻልንም:: ዛሬ በሰለጠነው ዓለም የሚኖረው ትውልድ «መልካም መስሎ የተሰማህን አድርግ፣ በራሱ ትክክልና ስህተት የሆነ ነገር የለም» የሚል መመሪያ ውስጥ ገብቷል:: ሕይወትን ሚዛን የሚያሳጣና የመኖርን ዋጋ የሚጥል ይህ ክፉ መመሪያ የተወለደው «እግዚአብሐር የለም» ከሚለው ክፉ ሥርዓት በኋላ ነው:: ሰው በፊቱ የተሰማውን ለማድረግ የኅሊና፣ የሕግ፣ የመንፈሳዊነት ገደብ አለበት:: ገደቡ ለመልካም ሰብእና ጌጥ ነው:: «መልካም መስሎ የተሰማህን አድርግ፣ በራሱ ትክክልና ስህተት





የሆነ ነገር የለም» በሚለው መመሪያ የተያዙ ወጣቶች ግን በዝሙትና በአደንዛዥ ዕፅ ያበዱ ሆነዋል:: መልካምና ክፉን የምንለይበት መመዘኛ ከሌለን የምንቆምበት መሠረት የለንም፣ ሕይወትም ምክንያት አልባ ትሆናለች:: ለዛሬው ተስፋ መቍረጥና ራስን የማጥፋት ወንጀል ይህ ሰይጣናዊ አዋጅ ዋነኛው ምክንያት ነው:: የሰውን ሕይወት ያለ እውነት፣ ያለ ሚዛን ያስቀረው ምንድነው? ስንል ይህ እግዚአብሐር የለሽ ሥርዓት ነው:: በምዕራባውያን እንዲሁም በአገራችን በኢትዮጵያ በትምህርት ቤቶች ይሰጥ የነበረው የግብረ-ገብ ትምህርት ከቆመ በኋላ የተፈጠረው ትውልድ የሰብእናው ካባ የወለቀበት መሆኑን በተግባር አይተናል:: ስለ እግዚአብሐር የለሽ ሥርዓት ስንናገር ዛሬ ጊዜ ያለፈበት ወሬ እንደሆነ ይሰማን ይሆናል:: አዎን እግዚአብሐር የለም የሚሉ መፈክሮች ከአደባባይ ወርደዋል:: በሰው ልብ ግን ዙፋን ተቆናጠዋል:: በትልልቅ ትምህርት ተቋማት፣ በሥነ መለኮት ትምህርት ቤቶች ይህ ሥርዓት ገና እንደ ነገሠ ነው:: ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሐር የለሾች ናቸው:: የሚተዳደሩት ግን እግዚአብሐር አለ የሚሉ ምእመናን ስለ እግዚአብሐር ብለው በሚሰጡት ገንዘብ ነው:: እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ደም መጣጮች በቁማቸው የደረቁ ዛፎችና ለሚያያቸውም ሀዘን ናቸው:: ከአንገት እንጂ ከአንጀት የሆነ መልእክት ስለሌላቸው ለፍላፊዎች እንጂ መንፈሳዊ አዝማቾች አይደሉም::

በመልካም ሥነ ምግባር ወደ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች የሚገቡ ተማሪዎች ይህ እግዚአብሐር የለሽ ፍልስፍና ሲያገኛቸው በክፉ ኃጢአት ተበክለው ይወጣሉ:: ለማመዛዘን መንፈሳዊ መሠረት የላቸውም:: ያለ ተጠሪ መኖር ነጻነት ይመስላቸውና ባክነው ይቀራሉ:: እግዚአብሐርን ለምነው ኮሌጅ ገብተው እግዚአብሐርን ክደው ይወጣሉ:: ውጤታቸው ግን በአደንዛዥ ዕፅ መመራት፣ ማበድና ራስን ማጥፋት ነው:: ለእግዚአብሐር አንገዛም ብለው የተገዙት ለሱስ፣ ለዝሙትና ለጭካኔ ነው:: እግዚአብሐርን አናመልክም ብለው ያመለኩት እንደ እነርሱ ያለውን ሰው ነው:: እግዚአብሐርን የካዱ ሰዎች በነሌኒን፣ በነዳርዊን፣ በነስታሊን አመኑ:: ሰው ከእምነት ነጻ አይደለምና:: መገዛት ካልቀረ በፍቅር ለሚገዛው ጌታ ምነው በተገዙ! ቃሉ:- *«ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ፥ የማይጠፋውንም የእግዚአብሐርን ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለወጡ»* (ሮሜ. 1:23) ይላል:: የዚህንም ውጤት ሲናገር ሥጋቸውን የማይገዙ፣ ከእንስሳ ያነሱ፣ ለጭካኔና ራስ ወዳድነት የተሰጡ እንደሆኑ ይገልጣል (ሮሜ. 1:24-32):: ይህን ክስተት ዛሬ በግልጽ እያየነው ነው:: ሰይጣን አስቀድሞ እግዚአብሐርን ያስክድና ቀጥሎ



www.ethiopinorthodox.org

ኃጢአትን ምንም አይደለም እንድንል ያደርገናል:: ምክንያቱም እግዚአብሔርን ስናምን ብቻ ነው መልካም ሥራ ዋጋ፣ ክፉ ነገር ቅጣት አለው ብለን የምናምነው:: በእግዚአብሔር የማያምን ሰው በሥራው ጠያቂ ስለሌለበት በፊቱ የቀረበውን ክፉ ነገር ከመፈጸም አይመለስም:: ቃሉ:- *«ሰነፍ በልቡ:- አምላክ የለም ይላል:: በሥራቸው ረከሱ፥ ጎሰቆሉ፤ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም»* (መዝ. 13:1) ያለው ለዚህ ነው::

ማን ፈጠረህ? ለምን ትኖራለህ? ወዴት ትሄዳለህ? የሚሉት ጥያቄዎች የሕይወት ጥያቄዎች ናቸው:: ፈላስፎች ነን የሚሉት የሚደክሙት ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ነው:: እነዚህን ጥያቄዎች የምንጠየቀው ከውጭ ሳይሆን ከውስጣችን ነው:: መልሱ እስካልተገኘም ነፍሳችን ተደልላ መቀመጥ አይሆንላትም:: የሰው ልጅ ህልውናው ከራሱ በራሱ ለራሱ አለመሆኑ የታወቀ ነው:: ስለዚህ ለመኖሩና ለመገኘቱ ከራሱና ከአካባቢው የተለየ ምክንያት ይፈልጋል:: ይህንን መልስ ካላገኘ ዕረፍት አይሰማውም:: ለእኛ ቀላል ሆኖ የሚታየን መልሱን ስላገኘን ነው:: መልሱን ያጡ ግን በየበረሃው አጽም ፍለጋ ሲቆፍሩ ነው የሚኖሩት:: ከየት መጣሁ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እነሉሲ እነ ድንቅነሽ አሁንም መልስ አልሆኑም:: መልሱ እግዚአብሔር ነው:: ጠረጴዛን የሚሠራ ከጠረጴዛው የተሻለ ማንነትና ክብር ያለው ነው:: ሰውንም የፈጠረ ከሰው የተሻለ ማንነትና ክብር ያለው እግዚአብሔር ነው::

እግዚአብሔር የለም የሚሉ ሰዎች ሲለፈልፉ ነው የሚውሉት:: አለመኖሩን ካረጋገጡ ለምን ዝም አይሉም? ይህ ዕረፍት ስላልሰጣቸው ነው:: በኮሚኒዝም ርእዮተ ዓለም በራሺያ ውስጥ አንድ ሰው ኮሚኒስት ለመሆን ብርቱ ናፍቆት አደረበት:: ታዲያ በየማለዳው እየተነሣ በሚኖርበት አፓርታማ ደጃፍ ላይ:- «እግዚአብሔር የለም» እያለ ይጮኻል:: በጩኸቱ የተማረሩ ጎረቤቶቹ ተሰባሰቡና:- «ለመሆኑ በየጠዋቱ የምትጮኸውን እንተውና እግዚአብሔር የለም የምትለው ለምንድነው?» አሉት:: እርሱም:- «ውስጤ አለ ስለሚለኝ ያንን አጥፍቼ ኮሚኒስት ለመሆን ነው» አለ ይባላል::

የዓለማችን ትልቁ የኢኮኖሚ አቅም ግብረ- ገብ መሆኑ ታምኖበታል:: ግብረ- ገብነት የሰው ልጅ እውነተኛ ውበቱ ነው:: በምድራችን እጅግ ቆንጆ የነበሩ ግን ጨካኞች የሆኑ ሰዎችን አስተናግደናል:: ቁንጅናቸው ባሕርያቸውን አልሸፈነልንምና አልተቀበልናቸውም:: የሰው ልጅ እውነተኛ መልኩ የግብረ- ገብ አቋሙ ነው:: የሰብአዊ ርኅራኄና የመልካምነት ምንጩ ፈሪሃ



እግዚአብሔር ነው:: ለዚህም የእግዚአብሔርን መኖር ማመን ወሳኝ ነው:: በምዕራባውያን የታየው የሥልጣኔና የእውቀት ጮራ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ የመጣ መሆኑ ተረጋግጧል:: ለዚህም እንደ ዋናነት የሚጠቀሰው የተሐድሶው የወንጌል ስብከት ነበር::

በ19ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው ጀርመናዊው ፈላስፋ ኒች «እግዚአብሔር ሞቷል» ብሎ በድፍረት ተናግሮ ነበር:: እርሱ በሞተ ጊዜ ግን እንዲህ ተባለ:- «ኒች ሞተ እግዚአብሔር ግን አለ::» የለም ያሉት ዛሬ የሉም:: እግዚአብሔር ግን በዙፋኑ አለ:: በህልውናው ብቻ ሳይሆን በትዕግሥቱም እያስደነቀን ይኖራል:: እርሱም አይቸኩልም::

የእግዚአብሔር ህልውና በሰው ልብ ውስጥ የተጻፈ በመሆኑ የእግዚአብሔርን አለመኖር ከመቀበል መኖሩን መቀበል ይቀላል:: በእርግጥም የቱን መቀበል ነው የሚከብደው? አለ ወይስ የለም የሚለውን? በርግጥም የለም የሚለውን ክርክር የወለደው መኖር ነው:: ስለሌለ አንድ ነገር ማንም አይከራከርም:: የለምና:: የእግዚአብሔርን ህልውና ለካዱ ሰዎች መንፈሳውያን የሚሆኑ የሥነ መለኮት አስተማሪዎች ይህን ጥያቄ አቅርበዋል:- «እናንተ ለሰው ልጆች ንቃት የተጨነቃችሁ መስሏችኋል:: ነገር ግን የእግዚአብሔርን ህልውና መቀበል በሰው ልጅ ላይ ያመጣው ጉዳት ምንድነው? ደግሞስ እናንተ ጥቂቶች ሆናችሁ ሳለ መላው ዓለም ከታሪክ መነሻ ጀምሮ የተቀበለውን ነገር እንዴት ታስክዱታላችሁ?» በማለት ጠይቀዋል:: በርግጥም የለም ከሚሉ ሰዎች አለ ብለው የሚያምኑ ሰዎች ሰላማቸውና ሰብእናቸው የተሻለ መሆኑን ታምኖበታል::

አሁን ወደ እግዚአብሔር የተመለሰ በቀደመው የኮሚኒስት ሥርዓት ጎንደር ላይ ካድሬ የነበረ ሰው እንዲህ ሲል አጫወተኝ:- «እግዚአብሔር የለም» የሚለውን ትምህርት ስሰማ አዲስ ነገር ሆኖብኝ ለሰው ሁሉ መናገር ጀመርኩ:: «እግዚአብሔር የለም፣ ካለ አሳዩኝ» ስል ሁሉም ዝም ይለኛል:: እኔም የአሸናፊነት መንፈስ እየተሰማኝ በመንገድ ያገኘሁትን ሁሉ ዝም ማሰኘትን ተያያዝኩት:: ታዲያ ከዕለታት በአንዱ ቀን አንድ የቆሎ ተማሪ አገኘሁና:- «አንተ ተማሪ እግዚአብሔር የለም፣ ካለ አሳየኝ» አልኩት:: ተማሪም:- «እኔ አለ ወይም የለም ብዬ ከአንተ ጋር አልከራከርም:: ነገር ግን አለ ብለኸው ባይኖር ችግር የለውም፣ የለም ብለኸው ያለ እንደሆነ ግን ወዮልህ» ሲለኝ ደነገጥኩ:: መረጋጋት አቃተኝ:: የፍርድ መለከት ተሰማኝ:: ወዲያው ንስሓ ገባሁ:: እኔ ክጄው ነበር፣ እርሱ ግን አልካደኝምና አመሰግነዋለሁ» ብሎ በዕንባ አጫወተኝ::



www.ethiopinorthodox.org


የሚገርመው የቆሎ ተማሪው የተናገረውን በመላው ዓለም ያሉ የሥነ መለኮት ምሁራን ተናግረውታል:: ተማሪው ከእነርሱ እንዳልሰማ እርግጠኛ ነኝ:: ነገር ግን መንፈሳዊ መልእክት ስለነበር በሁሉ ቦታ ተነግሯል:: «እግዚአብሔርን አለ ብለኸው ባይኖር ችግር የለውም:: የለም ብለኸው ካለ ግን ወዮልህ!»

የእግዚአብሔርን ህልውና የማይቀበል የፈላስፎች ብዕር ቀጥሎ ያለውን ሥዕል ይስላል:-




የእግዚአብሔርን ህልውና ለማይቀበል ሕይወት ሳይክል (ዙረት) ናት::

እግዚአብሔር ግን የፈላስፋውን ሥዕል አጥፍቶ በሚያምር የተስፋ ቀለም ቀጥሎ ያለውን ሥዕል ይስላል:-




የእግዚአብሔርን ህልውና ስናምን ብቻ ሕይወት ግብ አላት::

- እግዚአብሔር ካለ ብቻ ሕይወት ግብ አላት::
- እግዚአብሔር ካለ ብቻ ስለ ሌሎች ማሰብ ይቻላል::
- እግዚአብሔር ካለ ብቻ መልካምነት ዋጋ ይኖረዋል::





- እግዚአብሔር ካለ ብቻ ክፉ ሥራ ይዳኛል::
- እግዚአብሔር ካለ ብቻ ተስፋ ማድረግ ይቻላል::

የእግዚአብሔርን መኖር የማያምን አንድ ሰው ነበረ:: የዚህ ሰው ዘበኛ ዘወትር በማለዳ እየተነሣ ይጸልያል:: አንድ ቀንም ሲጸልይ ሳለ:- «ምን እያደረግህ ነው?» በማለት ዘበኛውን ይጠይቀዋል:: ዘበኛውም በትሕትና:- «እግዚአብሔርን እየለመንኩ ነው» አለው:: ሰውዬውም:- «እግዚአብሔር እኮ የለም፣ ለምን ትታለላለህ?» ይለዋል:: ዘበኛውም ለማመን እየቸገረው:- «እውነት የለም?» ይለዋል:: ከሃዲውም:- «አዎ በትክክል የለም» ይለዋል:: በዚህ ጊዜ ዘበኛው:- «እኔ እኮ ያልገደልኩህ እግዚአብሔር አለ ብዬ ነው፣ ከሌለማ ዕረፍቴ አይደለም ወይ?» ብሎ ተኩሶ ገደለው::

ደርግና ኢሕአፓ ሁለቱም እግዚአብሔር የለሾች ናቸው:: ግን እግዚአብሔርን አስወጥተው በሰላም መኖር አልቻሉም:: ስለዚህ በአደባባይ ተራረዱ:: በሩስያ፣ በቻይና፣ በሩማንያ፣ እንዲሁም በአገራችን በኢትዮጵያ በሚሊየን የሚቆጠሩ የሰው ዘሮች ያለቁት እግዚአብሔር የለም በሚለው ሥርዓት ምክንያት ነው:: ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ፣ የኑሮ ውድቀትም መጥቷል:: እርስ በርሳችን በሰላም የሚያኖረን እግዚአብሔርን ማመን ብቻ ነው:: ሩስያ ዓለምን ክዳ አስካደች:: ውጤቱ መበታተን ሆኖ አቅሟ ተፈረካከሰ:: የጠላቻቸውና በአደባባይ ያወገዘቻቸው ምዕራባውያን እስኪረዷት ኢኮኖሚዋ ላሸቀ:: ያመኗትም አብረዋት ወደቁ:: ዛሬ የሩስያ መሪዎች በግልጽ ቤተ ክርስቲያን መሳለም ጀመሩ:: ሕዝቡ የካደውን አምላክ ማምለክ ጀመረ:: ውጤቱን ስናይ ሩስያ እንደገና አቅሟ እያንሠራራ፣ ኃያልነቷንም እየጨበጠች መጥታለች:: ክርስትና በተስፋፋባት በደቡብ ኮሪያና ክርስትና በሌለበት በሰሜን ኮሪያ መካከል የክህደቱን ዘመን የሚያህል የኢኮኖሚ ርቀት ተከስቷል:: በርግጥም እግዚአብሔርን መካድ ራስንና አገርን መካድ ነው::

ዛሬ የአምስት ሺህ ብር ዕቃ አምስት ብር፣ የአምስት ብር ዕቃ አምስት ሺህ ብር ተለጥፎበታል:: ዋጋ ተለዋውጧል:: ርካሹ ውድ፣ ውዱ ርካሽ ሆኗል:: ነውሩ ክብር፣ ክብሩ ነውር ሆኗል:: ቅንነትና ፍቅር ርካሽ፣ ባለጠጋነትና ቆንጆነት ውድ ሆነዋል:: ይህን የተለዋወጠ ዋጋ የፈጠረው እግዚአብሔር የለሹ ሥርዓት ነው::

ከሃምሳ ዓመታት በላይ የዓለምን 1/3ኛ ክፍል ተቆጣጥሮ የነበረው የኮሚኒስት ርእዮተ ዓለም እግዚአብሔርን ማስካድ ዋነኛ ዓላማው ነበር:: በየአደባባዩ፣ በየፋብሪካው፣ በየትምህርት ቤቱ ስለ እግዚአብሔር አለመኖር ታወጀ:: ግን እግዚአብሔር ላለመኖሩ



www.ethiopinorthodox.org

ያቀረቡት ማስረጃ አልነበረም። እግዚአብሔር ግን በዚህ የክህደት ዘመን ውስጥ በኃይልም ሆነ በተአምራት አለሁ አላለም። የዐፄ ቴዎድሮስ የታሪክ ፀሐፊ የነበሩት አለቃ ዘነብ፡- «እግዚአብሔር አይሰጋም፤ የሚሸረው የለምና» ያሉት እውነት ሆኖ ታየ።

እግዚአብሔር ይታገሣል ስንል ለመለወጥ ዕድል ይሰጠናል ማለት ነው ብለናል። በዚህ ምዕራፍ እያየን ያለው እግዚአብሔር ይታገሣል ማለት አይቾኩልም ማለት እንደሆነ ነው። የእግዚአብሔርን ህልውና የካዱ ብዙ ሰዎች እንዲኖሩና እንዲፎክሩ ዝም ማለቱ ትዕግሥቱን ያብራራል። አንድ መንግሥት ሁሉን ወንጀሎች ሊታገሥ ይችላል። ህልውናውን የሚክዱትን ግን አይታገሥም። በብርቱ ቅጣትም ይቀጣል። እግዚአብሔር ግን አይቾኩልምና ዝም ይላል። ትላንት እግዚአብሔርን የካዱ፣ የፈጠሩት ይመስል ሰውን ይሙት ሲሉ የነበሩ ዛሬ ንስሓ ገብተው እያመለኩት ነው። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በአንድ ወቅት የተናገሩትን እንድገመው፡- *«የሰው ልጅ ከዛሬ ብዙ ሺህ ዓመት ጀምሮ በታሪክ እንደምንረዳው ከእግዚአብሔር ጥገኝነት ተለይቶ የኖረበት ዘመን የለም። ያለ እርሱ ምንም ማድረግ ምንም መሆን እንደማይቻል እናስተውል። እኛም ጥገኛ ላለመሆንና ከእግዚአብሔር እጅ ለመውጣት በከንቱ አንድከም። ይልቅስ በእርሱ እንመን፣ በእርሱ እንደገፍ።»*

እግዚአብሔርን ካላየን አናምንም የሚሉት ወገኖች አእምሮ የሚባል ረቂቅ ነገር ተሸክመው፣ ሥዕልና ሙዚቃን የመሰሉ ረቂቅ ነገሮችን እወዳለሁ እያሉ እግዚአብሔርን መካዳቸው ይገርማል። ሰው በማየት ብቻ የተወሰነ ፍጡር አይደለምና። ከሁሉ የሚገርመው እግዚአብሔርን የካዱ ሰዎች የሰይጣንን መኖር እያመኑ ያስጠነቅቃሉ። የሰይጣንን መኖር ካመኑ የእግዚአብሔርን መኖር ማመን ግድ ይላቸዋል። የእግዚአብሔርን ህልውና የካዱ የምዕራብ ዘመናውያን ዛሬ በአስማትና በኮከብ ቆጠራ ፍቅር ተለክፈው ስናያቸው በጣም ይገርመናል። ስለ ቊስ አካል እንጂ ስለመንፈስ አናምንም ያሉ ሰዎች ይልቁንም ዘመናውያን ነን የሚሉ ምዕራባውያን እግዚአብሔርን እየካዱ በሰይጣን እያመኑ መሆናቸው ይደንቃል። በአሜሪካ 1750 የተለያዩ ጋዜጦች በየዕለቱ ለንባብ ይበቃሉ። ከእነዚህ ውስጥ 1220ዎቹ የኮከብ ቆጠራ ዘገባ (ፍካሬ ከዋክብትን) ያቀርባሉ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ዕድላቸውንና የሚገጥማቸውን ዕጣ ከጥንቆላው ለማወቅ ይፈልጋሉ፣ ያምናሉ። አዎ በሰይጣን መኖር ካመንን በእግዚአብሔር መኖር ማመን ግድ ይለናል። በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ እግዚአብሔር የለም እያሉ የሚያስተምሩ መምህራን ጠንቋይ ቤት እንደሚልከሰከሱ



ይታወቃል። በመንፈሳዊ ህልውና ካመኑ በፍቅር በሚገዛው ጌታ ቢያምኑ መልካም ነበር።

የእግዚአብሔርን ህልውና የካዱ ሰዎች ዛሬ የሉም። እግዚአብሔር ግን አለ። ዛሬም የሚክዱት ነገ የሚኖሩ አይደሉም። እርሱ ግን ኃይል አለኝ ብሎ ኃይሉን ለማሳየት አይቾኩልም። ታሪክንና ዘመንን እየመዘነ ይኖራል። የኮሚኒስት ርእዮተ ዓለም ዛሬ ወድቋል፤ እነ ሌሊን፣ እነ ዳርዊን፣ እነ ስታሊን ዛሬ የሉም። እግዚአብሔር ግን አለ። እርሱ ኃይሉን ለተወራረዱት ሳይሆን ለታገሡት ያሳያል። ለካዱት ሳይሆን ላመኑት ይገልጣል። እኛ ኃጢአተኞቹ ኃጢአተኞችን መታገሥ ሲያቅተን እርሱ ጻድቁ ግን ኃጢአተኞችን ይታገሣል።

ዓይተህ እንዳላየ ታልፈዋለህ ሁሉን፣
መዓቱም ምሕረቱም ሁሉም ያንተ ሲሆን፤

✠ ✠ ✠

ይመሻል ይነጋል እንዲህ ሲል ጊዜው ያልፋል፣
ግሩመ እግዚአብሔር ሥራህ ያስደንቃል፤

✠ ✠ ✠

## እናስተውል

ጥንቸልና መሬት ማኅበር ገብተው መሬት ማኅበሯን አወጣች። የጥንቸል ተራ ሲደርስ ጥንቸል መክፈል አልችልም ብላ እንቢ አለች። እንደውም ካንቺ ጋር አልኖርም የት ታገኚኛለሽ? ብላ ሩጫ ጀመረች። ሮጣ ሮጣ ስታርፍ መሬት፡- «አትከፍይም ወይ?» ትላታለች። አሁንም ሮጣ ሮጣ ስታርፍ «አትከፍይም ወይ?» ትላታለች። ጥንቸልም ከመሬት ማምለጥ ሞክራ ስላልቻለች ማኅበሯን ከፍላ ከእርሷ ጋር ኖረች ይባላል። ከእግዚአብሔር ተለይቶ መኖር አይቻልም። እርሱ ፈጥሮ፣ አድኖ በየዕለቱ በድንቅ መግቦቱ እየተንከባከበ ድርሻውን ተወጥቷል። የሰው የማመንና የመታዘዝ ድርሻ ግን ገና አልተፈጸመም። እንደውም ያለ እግዚአብሔር እኖራለሁ ብሎ እቅድ ያወጣል። ግን የሚተነፍሰው የእርሱን አየር፣ የሚሞቀው የእርሱን ፀሐይ ነው። ከተደረገልን በኋላ ከእርሱ ሸሽተን ለመኖር እናቅዳለን። ከእርሱ ተለይቶ መኖር ግን አይቻልም። እግዚአብሔር የለም ብለው በቃልም በሥልጣንም



www.ethiopinorthodox.org

ክደው ያስካዱ እነዚያ የቀድሞ ባለሥልጣናት ዛሬ ሁሉም ንስሓ ገብተው ምሕረቱን እየተጠባበቁ ነው:: ወፍም አውሮፕላንም በርረው በርረው ማረፊያቸው መሬት ነው:: ሰውም ባዝኖ ባዝኖ ከእግዚአብሔር አይቀርም:: ታዲያ ሳለ መልካችን፣ ሳለ አካላችን፣ ሳለ ሀብታችን መመለስ አይሻለንም ወይ? ከእነዚያ ባለሥልጣናት እኛ በሥልጣንም በሀብትም አንበልጥም:: ስለዚህ ከነቁመናችን ብንማረክ መልካም ነው:: መማረካችን አይቀርምና::

የአደባባይ ኃጢአት በአደባባይ ንስሓ ነው የሚወገደው:: ጠግበን ማደር ሳንችል በአደባባይ እግዚአብሔር የለም ብለን የካድን ሕዝቦች ነን:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር ርቆን የጦርነትና የረሀብ ውድማ ሆነናል:: ለአገራችን ብቸኛው መፍትሔ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ስለዚህ ንስሐ መግባት፣ በአደባባይ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ይገባናል:: በዓመፃችን ብዙ ወጣትና ስንት የሚሠራ አእምሮ በጥይት ወድቆ ቀርቷል:: እኛ ከተረፍን ለቀጣዩ ትውልድ ይህን መርገም ሳናሸጋግር በንስሓ እንገድበው! ትዕግሥቱ እንዴት ሰፊ ነው!

## ጸሎት

አቤቱ ጌታዬ የቆምኩበትን መሠረት፣ የተጠለልኩበትን ክዳን የካድኩ እኔ ምንኛ ጎስቋላ ነኝ? የተነሣሁበትን ጅማሬዬን፣ የታሪኬን ባለቤት፣ የመንገዴን ዋጋ ሰጪ አንተን ክጃለሁ እባክህ ይቅር በለኝ:: ድሮ በቃሌ ክጄህ ነበረ:: የዛሬው ብሶ በሥራዬ ክጄሃለሁ:: ያልካድከኝ አምላኬ እባክህ አነጋግረኝ:: አንተ መሐሪ ነህ:: አንተ እንደ እኔ አይደለህም:: እባክህን እንዳለፈው ዘመን ጊዜዬ አይለፍብኝ:: ፍጻሜዬ በቤትህ ይሁንልኝ:: የእነዚያን ባሪያዎችህን ፍጻሜ እኔም ተመኘሁ:: አምኜህ መሞትን ናፈቅሁ:: ጌታዬ ዘመኔ በቤትህ ይለቅ:: ከዚህ በኋላ እንኳን ደቂቃው ሴኮንዱ አይባክን:: ሁለመናዬን በፍቅርህ ግዛው:: በአባትህ ቤት ሰፊ መኖሪያ አለና ተቀበለኝ:: ዓለም ተጠቅማብኝ አርጅቷል ብላ ጥላኛለች:: የተበላሹ ሰብሳቢ፣ አክብረህ የማታዋርድ ሙሉ ብርሃን እግዚአብሔር ተቀበለኝ:: በሥላሴነትህ ዙፋን፣ በምስጋና ወግ በደመቀው አደባባይህ፣ ቀራንዮ በተሰፋው ነጩ ልብስ ተሸፍኜ ልመጣ ነው:: አንተ ቀድመህ ከተቀበልከኝ ንጹሓኑም አይጠሉኝም:: ያልካድከኝ አባቴ መጥቻለሁና ተቀበለኝ:: ለስምህ ክብር ምስጋና ይሁን! አሜን!





# ምዕራፍ ዐሥራ አራት

## የማዳን ኃይል

ሰውዬው የሚያርሰው መሬት ድንጋያማ ደግሞም ዘር የሚበላ መጥፎ መሬት ስለነበር ሁልጊዜ ይበሳጭ ነበር:: ከጉልበቱም ከምኞቱም አልሆን ሲለው:- «ወይ አዳም!» እያለ ያማርራል:: ባልተሳኩ ነገሮች ሁሉ «ወይ አዳም!» እያለ አዳምን መርገም የዘወትር ሥራው ሆኖ ነበር:: ካጠገቡ የሚኖሩ አንድ ባለጠጋም በመንገድ ሲያልፉ ይህ ሰው እየቆፈረም፣ እየደከመም:- «ወይ አዳም! ወይ አዳም!» ሲል ዘወትር ይሰሙታል:: አንድ ቀን እኚህ ባለጠጋ ሰውዬውን ጠጋ ብለው:- «ለምን እንዲህ ትላለህ?» ብለው ይጠይቁታል:: ያ ሰውም «አዳም ዕፀ- በለስን ባይበላ ከገነት ባልወጣን በወዛችንና በላባችን ለፍተን ባላጣን ነበር» አላቸው:: ባለጠጋውም ሊያስተምሩት ስለፈለጉ ባዶ ጠርሙስ አዘጋጁና አንዲት ትኝኝ አስገብተው ዘጉባት:: ያንንም ሰው ጠሩትና:- «ከዛሬ ጀምሮ በቤትና በደጅ ያለው ንብረቴ ያንተ ነው:: ያንተ መሆኑ የሚፀናው ግን ታማኝነትህን አይቼ ነው:: ሁሉን ሰጥቼሃለሁ:: ይህችን ጠርሙስ ግን እስክመጣ እንዳትነካት በዚህ ከታመንክ ንብረቴ ያንተ ይሆናል» አሉት::

ያም ሰው ገና ተደላድሎ መኖር እንደ ጀመረ የሰጡትን አይቶ አድንቆ ሳይጨርስ ሁሉን ሰጥተውት ያችን ባዶ ጠርሙስ ለምን? እንደ ከለከሉት ማሰብ ጀመረ:: ከሰጡት ይልቅ የተሻለና የበለጠ ሀብት ቢኖርባት ነው ብሎ ጠርሙሷን ከፈታት:: ሲከፍታትም ምንም አልነበረባትምና መልሶ ዘጋት:: ነገር ግን ያች ትኝኝ ወጥታ ሄደች:: እርሱም አላያትምና ራሱን እንደ ታማኝ ቆጥሮ መኖር ቀጠለ:: ባለጠጋውም ከሩቅ አገር ተመልሰው መጡ:: ሁሉም ነገር ሰላም መሆኑን ጠይቀው ሰላም መሆኑን ነገራቸው:: «ያችን እንዳትነካ ያልኩህን ጠርሙስ አልነካህምን?» አሉት:: «አዎን» አላቸው:: ጠርሙሱን ከፍተው ሲያዩ ትንኟ የለችም:: እርሳቸውም:- «ይህን ጠርሙስ ከፍተሃል፣ ምክንያቱም እኔ እዚህ ውስጥ ደህና ነገር አላስቀመጥኩም ያስቀመጥኩት ምንም የማትጠቅም ትኝኝ ነበረች፤ በከፈትከው ጊዜም ወጥታለች:: ይህም የአንተን ታማኝነት ለማረጋገጥ በቂ መለኪያ ነበር:: ስለዚህ ታማኝነትህን አጉድለሃል:: ከአሁን ጀምሮ ቤቴን ንብረቴን ለቀህ ውጣ አሉት:: ያ ሰውም ወደ በፊቱ አስቸጋሪው ኑሮው በመመለስ መሬቱን እየቆፈረና ላቡን ጠብ



www.ethiopinorthodox.org

እያደረገ:- «ወይ እኔ! ወይ እኔ!» እያለ ይቆፍር ጀመር:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ «ወይ አዳም» ማለቱን አቆመ::

በአዳም ላይ የታየው ልክ እንዲህ ነበር:: እግዚአብሔር ሁሉን ሰጥቶ አንዲት ቅጠል ከለከለው:: ቅጠሏ በገነት ካሉት ዛፎች በተፈጥሮ፣ በመልክ፣ በጣዕምና በጥቅም የተለየች አልነበረችም:: ልዩ የሚያደርጋት ትእዛዝ የወደቀባት የመታዘዝ ምልክት የሆነች ዛፍ መሆኗ ነው:: እግዚአብሔር እንዳትነካት ብሎት ነበር:: አዳም ግን ነካ:: ቅጠሏን በመብላቱ ያተረፈው ሀብት የለም:: የነበረውን አጣ እንጂ:: ወደ መከረኛይቱ ምድርም ተሰደደ:: እኒያ ባለጠጋ ለዚህ ሰው ሊያስተምሩት የፈለጉት ነገር ቢኖር በአዳም ቦታ እርሱም አዳም መሆኑን ነበር:: ብዙ ጊዜ የምንፈርደው ባልሞከርነው ነገር ላይ ነው:: የምንኮንነውም ድርጊቱን ሳይሆን ሰውዬውን ነው:: የምንኮንነውም ራሱን ስለጎዳ ሳይሆን እኛን ስለጎዳ፣ እውነትን ስለጣለ ሳይሆን የእርሱ ስህተት የእኛን ጽድቅ የሚያጎላ ስለመሰለን ነው::

ዙፋን ገልብጠው ወደ ዙፋን የወጡ መነሻ ዓላማቸው የሀገር ንብረት ባክኗል፣ የሕዝብ መብት ተነፍጓል የሚል ነበር:: ዙፋን ላይ ሲወጡ ግን እነርሱ እንደሚብሱ በታሪክ ሁሉ ታይቷል:: ዛሬ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያልተፈተነ ደግነታቸውን ሲያወሩልን ይውላሉ:: በክርስቶስ የሚያምኑ ሳይቀሩ በእነዚህ ፖለቲከኞች ወሬ ተታለው ዓለምን የሚያድናት ጥሩ የሆነ የፖለቲካ ፕሮግራም መሆኑን ያስባሉ:: ዓለምን የሚያድናት ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: አንድ የምወዳቸው አባት እንደነገሩኝ በኢሕአፓ ግርግር ወቅት እዚህ አዲስ አበባ ላይ አንድ ወጣት በዘመኑ ብርቅ የነበረውን አሳልፎ መስጣጠት ተለማምዶ አባቴ መሣሪያ አስቀምጧል ብሎ ጠቍሞ ያሳስራቸዋል:: እኒያም አባት ሲገርፏቸው የጅራፉ ምላስ ዓይናቸው ላይ ተጠምጥሞ ሁለት ዓይናቸው ጠፋ:: ልጃቸውም በሳምንቱ ኢሕአፓ ነው ተብሎ እቤቱ በር ላይ ተረሸነ:: ታዲያ እኚህ ዓይነ - ስውር በመሪ ጠዋት ቤተ ክርስቲያን ይወሰዳሉ፣ ውለው ማታ ይመለሳሉ:: ታዲያ ሲጸልዩ:- «ጌታዬ ዕድሜ ለመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ስጥልኝ» ይሉ ነበር:: የሚሰሟቸውም በጣም ተናድደው:- «ምን አደረገሎት ዓይኖትን አጠፋ እንጂ» ቢሏቸው «አይ ልጆቼ ከአዲስ ገራፊ የደከመው ገራፊ ይሻላል ብዬ ነው» አሉ ይባላል::

በሰው ቦታ ላይ ሁላችንም ሰው ነን:: ይልቁንም ሥልጣን የእግዚአብሔር ጥሪ ሲሆን እንጂ ይገባኛል ብለን የምንወጣበት ከሆነ የግፍ ወንበር መሆኑ የታወቀ ነው:: ክፉ አለቆች ዘበኞች የነበሩ፣



ክፉ እመቤቶች የቤት ሠራተኛ የነበሩ መሆናቸውን ብዙ ጊዜ እናያለን:: ዘበኛ ሳለ በአለቃው አምባገነንነት ያዝን ነበር:: የቤት ሠራተኛ ሳለች:- «እንዴት ሰው በቍራሽ ይበደላል፣ እህል ከተሠራ በኋላ ሬሳ ነው» ትል የነበረች ዛሬ ክፉ እመቤት ናት:: ጨካኝ መምህራን ያስተማሯቸው እነርሱም መምህር ሲሆኑ ተማሪ ሲያሰቃዩ እናያለን:: ክፋት ማብቂያ በሌለው ምድር ላይ መኖራችንና የክፋቱ ተዋናይም እኛው ራሳችን መሆናችን ይገርማል::

እነዚህ ጨካኞች በጭካኔ ተግባር አልፈው ወይም አድገው ለዚህ ቢደርሱም ሲብሱ እንጂ ሲሻሉ አይታዩም:: ክፋት በእኛ ላይ ይብቃ ከማለት የእነርሱን ጽዋ እየነሰነሱ ለሁሉ ማዳረሳቸው «ወይ እኛ!» ያሰኛል:: አንዲት የቤት እመቤት አስታውሳለሁ:: ያማረ ቤት፣ ያላት ብትሆንም እርሷ ግን ያማረ ኑሮና አስተሳሰብ የላትም ነበር:: ከሁሉ ሁሉ በሠራተኞቿ ላይ የምትፈጽመው ጭካኔ ወደር የለውም:: በቂ ሀብት ቢኖራትም ለሠራተኞቿ የዘንጋዳ ጤፍ፣ የበቆሎ ቂጣ ከውሃና ከጨው ጋር በመስጠት የታወቀች ናት:: ይህች ሴት ማለዳ ሲሆን የዕለቱን ታቦት እየቆጠረች ጥላ ይዛ መሄድ ሥራዋ ነው:: ታዲያ ታሪኳን መተረክና ለዚህ እንዴት እንደ ደረሰች መናገር ትወዳለች:: ታሪኳ የሚጀምረው ከቤት ሠራተኝነት ነው:: ጅማ ላይ የነበሩት አሠሪዎቿ በእህል እንዴት ይበድሏት እንደነበር ስትናገር በየዕለቱ ለ30 ደቂቃ ያህል በአሳብ ትጠፋለች:: እነርሱ ያደረጉባትን ዛሬ በሠራተኞቿ ላይ እያደረገች መሆኗን ግን ለማስተዋል አእምሮዋ የጨለመ ነው:: ቀኑን በሙሉ ሰው ክፉ ነው እያለች ስትናገር ትውላለች:: የእነዚያ ክፉ ሰዎች ቡድን መሪ መሆኗን ግን አታውቅም:: ሰው ክፉ እንደሆነ አብዝተው የሚናገሩ ራሳቸው ክፉ ሰዎች መሆናቸውን በልምድ እናውቀዋለን:: ምድር እነዚህን ሰዎች መሸከሟ ያሳዝናል:: የቤት ወጪ እየከለከሉ ስለ ሰብአዊ መብት የሚከራከሩ፣ ሠራተኞቻቸውን እያባረሩ ስለ ስደተኞች በጉባዔ የሚያለቅሱ የኪራይ አልቃሾችን ይህች ዓለም ሰብስባለች::

በዘመናችን ያለው ትልቁ ስህተት ያለመፍረድና የመፍረድ ኃጢአት ነው:: አለመፍረድ ስህተትን ስህተት አለማለት፣ እኔን እስካልነካኝ አይመለከተኝም የሚል አስተሳሰብ፣ ለዚያ ሰው ልክ ከመሰለው ልክ ነው፣ ወድቆ ይማረዋል የሚል ጭካኔ ነው:: ይህ ያለመፍረድ ኃጢአት ነው:: የመፍረድ ኃጢአት ደግሞ ራስን ነጻ እያደረጉ ሌላውን ተጠያቂ ማድረግ፣ ለዓለም መታወክ ምክንያቱ እነ እገሌ፣ እነ እገሌ ናቸው ብሎ ጣትን መቀሰር ነው:: በዛሬው ዘመን የመፍረድ ኃጢአት በዝቷል:: አብዛኛው ሰዓታችን የሚያልቀው በዚህ የፍርድ ኃጢአት ስንገባበዝ ነው:: የብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች



www.ethiopinorthodox.org

መሠረት ይህ መካሰስ ነው:: ጌታ በመጨረሻው ዘመን ከሚበዙት ኃጢአተኞች አንዱ መካሰስ መሆኑን ተናግሯል:: *«በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ:: እርስ በርሳቸውም አሳልፈው ይሰጣጣሉ እርስ በርሳቸውም ይጣላሉ፤»* (ማቴ. 24:10):: አዎ እገሌ በደለ እንጂ እኔ በድያለሁ የማይል አገርና ሕዝብ አይድንም::

ተካሰስን ተካሰስን፣ ፈርደን ተፈራርደን ሲደክመን «ከሁሉ የሚገርመው የእግዚአብሔር ዝምታ ነው» ብለን እግዚአብሔርን እናማርራለን:: ነፍሳችን የእግዚአብሔርን ፍርድ እንደ ተጠማች ለመግለጥ እንሞክራለን:: ግን በዛሬው ዘመን ማን ነው ያልወደቀ? ማን ነው ያልረከሰ? ራሳችንን ስለምንረሳው እንጂ ጠዋት ለማታ የምንቆሽሽ መሆናችንን ብናስብ ባልፈረድን ነበር:: በጎዳና ላይ እግር የሌለው ጉዳተኛ ከፊት እየተንፏቀቀ ዓይነ ሥውሩን በገመድ አስሮ ይመራል:: እንዲህ ተሟልተው ለምነው ያድራሉ:: አንዱ ዓይን አለው፣ አንዱ እግር አለው:: ስለተሟሉ ዓይንም እግርም አላቸው:: እኛ የምግባር ሽባና የእምነት እውሮቹ ግን በመካሰስ ልንሟላ አቅቶን ጎድለን ቀርተናልና ወዮልን! ንግግር ያሳመርን መስሎን:- «የምግባር ህፀፅ ቢኖርብኝም እንደ እነ እገሌ ግን የሃይማኖት ህፀፅ የለብኝም» እንላለን:: *«ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል»* (ማቴ. 7:17) እንደ ተባለ የምግባር ችግር የእምነት ችግር መሆኑ አልገባንም:: ዳግመኛም:- «እኔ እንደ እነ እገሌ የምግባር ነውር የለብኝም» እያልን የእምነት ጉድለታችንን በምግባር ለመሙላት እንፈልጋለን:: ነፍስና ሥጋ ካልተዋሃዱ በዚህ ዓለም መገለጥ እንደማይችሉ:- እምነትና ምግባር ተነጣጥለውም ክርስትና ሊኖር አይችልም (ያዕ. 2:14-26):: የምግባር ችግር የእምነት ችግር፣ የእምነት ችግር ?ምግባር ችግር ነው::

ራሳችንን የምንመዝነው በደከመው ወንድማችን እንጂ በቃሉ አይደለምና ትክክለኛ ማንነታችንን ማግኘት አልቻልንም:: እግዚአብሔር ግን የሰጠን መመዘኛ ቃሉ እንጂ ደካማው ወገን አይደለም:: ክርስትና በመሻል ሳይሆን በመብለጥ የሚገለጥ ነው:: በመሻልማ ሃምሳ ሰው ከገደለው 40 ሰው የገደለው ይሻል ይሆናል:: መሻል የክርስትና መስፈርትና መጽናኛ አይደለም:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ:- *«እላችኋለሁና:- ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም»* (ማቴ. 5:20) ብሏል:: ልብ አድርጉ የተወዳደረው ኃጢአት ከኃጢአት ሳይሆን ጽድቅ ከጽድቅ ነው:: ጽድቅ ከጽድቅ ተወዳድሮ መውደቅ ካለ ኃጢአትማ ስፍራው የት ይሆን? ዳግመኛም:- *«ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?»* (ማቴ. 5:47) ብሏል:: ፈሪሳውያን ለታይታ አዋጅ እያስነገሩ፣ እልል እያሰኙ ገንዘባቸውን ለእግዚአብሔርና ለድሃ



ይሰጣሉ:: አሕዛብ የእነርሱን እምነት የሚከተለውን ብቻ ያከብራሉ:: እኛ ግን ብልጫ ስናሳይ መልካም ተግባራችንን ሁሉ እግዚአብሔር ብቻ እንዲያየን አድርገን መሥራት ይገባናል:: ምክንያቱም የመልካም ነገር ደሞዝ ሰጪ እርሱ ብቻ ነውና:: እንዲሁም የምናከብረው በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረውን ሰው ነውና ከእምነታችን ውጭ ያሉትንም ማክበርና መውደድ አለብን:: አዎ ክርስትና የብልጫ እንጂ የመሻል መስፈርት አይደለም:: በመሻል ከምክትሉ ቢንላደን ይሻል ይሆናል:: የክርስትና መስፈርት ግን መብለጥ ነው:: ራሳችንን በክርስቶስ ቅድስና ፊት አድርገን ስንመዝን ብቻ ለንስሐ እንነቃቃለን:: በደካማው ወንድማችን ራሳችንን ከመዘንን ግን እንደነድናለን:: ምክንያቱም እንሻላለንና:: እግዚአብሔር ግን ሕይወታችንን እንድንመዝንበት የሰጠን ቃሉን መሆኑን ማስተዋል አለብን::

*የመንግሥቱ* ወራሽ እንደሆንን ካመንን በጣም ደስ ሊለን ይገባናል:: ይህ ግን የሥራችን ሽልማት ሳይሆን የእርሱ የቸርነት ስጦታው ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ *«ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ»* (ሮሜ. 3:11) ብሎ ደምድሟል:: ነገር ግን ከሰዎች ወገን ጻድቃንና ቅዱሳን የተባሉ ካሉ ይህ የእግዚአብሔርን የማዳን ኃይል ብቻ ይገልጣል ማለት ነው (ሮሜ. 1:16):: እግዚአብሔር እኛን ለማጥፋት በቂ ምክንያት አለው:: *«ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል»* (ሮሜ. 3:23) ይላልና:: ነገር ግን ካዳነን ምክንያቱ ራሱ ብቻ ነው:: እርሱ ሊያጠፋን ሊኮንነን ይቻለዋል፣ ግን አድኖናል:: ምክንያቱም ኃይሉን እኛን ለማዳን ስለሚጠቀምበት ነው:: አባቶቻችን ይህን አረጋግጠዋል:-

*«ለቅዱሳንህ ሁሉ በቸርነትህ ቅዱሳን ይሆኑ ዘንድ ሰጠሃቸው»* (የዮሐንስ ወ.ነ.ቅዳሴ)::

*«ካስነሣሃቸው ከሙታን ወገን፤*
*ከጠበቅሃቸው ከሕያዋን ወገን፣*
*ካነጻሃቸው ከርኩሳን ወገን፤*
*ካጸደቅሃቸው ከኃጥአንም ወገን፣*
*ከሰበሰብሃቸው ከተበተኑት ወገን፣*
*ከመለስሃቸው ከበደሉትም ወገን*
*ላንተ መታመን አለህ:: አሜን»*

(የዮሐንስ ወ.ነ.ቅዳሴ)::



www.ethiopinorthodox.org

አንድ አባትም የተናገሩት እስከ ዛሬ ይታወሰኛል፡- *«እግዚአብሔር ሲያጸድቅ ምን ሠርቼ ነው፣ ሲኮንንም ምን አጥፍቼ ነው አይባልም፤ የሚባለው ተመስገን ብቻ ነው።»*

## የፍቅር ኃይል

የፍቅር ኃይል ይበልጣል። እኛ ግን ከፍቅር ይልቅ ተአምራትን እንወዳለን። ነፍስን የሚማርክ ተአምር ግን ፍቅር ነው። ተአምራት ሥጋን የሚፈውስ፣ ሥጋውያንን የሚያስደነግጥ ግርማ ነው። የፍቅር ተአምር ግን ነፍስን የሚያድን፣ መንፈሳውያንን የሚያስደምም ሞገስ ነው። ብዙዎች የኃይል ስጦታን ይለምናሉ። መፈወስ፣ በልዩ ቋንቋ እየተናገሩ ዓለምን ማስገበር ይፈልጋሉ። ከኃይል ስጦታዎች ግን የመጀመሪያው ፍቅር ነው። በጦር ኃይላቸው ብዙዎችን ያሸነፉ በፍቅር ግን ሲሸነፉ አስተውለናል። ብዙ አገልጋዮች ተአምራትን ይወዳሉ። ከኃይል ጋር መስበክን ይመኛሉ። የማያምነውን እልኸኛ ዓለም ከእጃቸው ጨረር፣ ከአፋቸው እሳት ወጥቶ ቢያሳምኑት ይመኛሉ። ነገር ግን ዓለምን የምንለውጠው በተአምራት ሳይሆን በፍቅር ኃይል ነው። ፍቅር ከኃይል ይበረታልና (1ቆሮ. 13፡1-3)። እግዚአብሔር በኃይል ቢጠቀም ሰይጣንንም በአንድ ቀን አሳምኖት ባደረ ነበር። እምነት ግን መስማማት ነውና ይህን መንገድ አይጠቀምም።

የእግዚአብሔርን ፈራጅነቱን ብቻ በማየት ምሕረቱን ማየት ያቃታቸው፣ ፍቅሩን ብቻ በማየትም እንደሚፈርድ የዘነጉ ብዙ ወገኖች አሉ። እግዚአብሔር ግን አፍቃሪ ነው፣ ፈራጅም ነው። ፍቅሩ ፍርዱን አያጎድለውም፣ ፍርዱም ፍቅሩን አያስቀረውም። ይህች ዓለም የምትኖረው በእግዚአብሔር መሐሪነትና ፈራጅነት ሚዛን ላይ ነው። እግዚአብሔር መሐሪ ብቻ ቢሆን ኃጢአት የማያስፈራ በሆነ ነበር ወይም ማንም አይመለስም ነበር። እግዚአብሔር ፈራጅ ብቻ ቢሆንም ማንም አይኖርም ነበር።

እግዚአብሔር በፍቅር ኃይሉ ሰዎችን ወደ ራሱ ይስባል። ሰዎች ግን ፍቅሩን ካልተጠለሉ የቍጣው እሳት ይበላቸዋል። እግዚአብሔር ማዳንም መግደልም ይችላል። የሚጠቀመው ግን የማዳንን ኃይል ብቻ ነው። ሰዎች ግን በእንቢተኝነታቸው ሲፀኑ እግዚአብሔር ይቀጣል። እግዚአብሔር ፍቅር ብቻ እንዲሆንላቸው የሚመኙ ሰዎች «ይቀጣል» ሲባሉ አይመስላቸውም። እግዚአብሔር ግን ፍቅር ነው፣ ፈራጅም ነው። ፍቅሩና ፍርዱ አይነጣጠሉም። ምክንያቱም የፍቅሩም የፍርዱም መሠረቱ እውነት ነውና። እውነት



ደግሞ ራሱ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር ባሕርዩን ስለማይክድ አፍቃሪ ነው። ፈራጅም ነው። ፍቅርም አካል ነሥታ በመንገድ ብናገኛት ብቻዋን አናገኛትም። በቀኝና በግራ የከበቧት ሁለት ወዳጆች አሏት። እነርሱም፡- እውነትና ፍትሕ ናቸው።

እግዚአብሔር ይቆጣል ስንል ትዕግሥት ያጣል ማለታችን አይደለም። እርሱ ጻድቅ በመሆኑ ኃጢአትን ይቀጣል። እግዚአብሔር ኃጢአትን ባይቀጣ ኖሮ ጻድቅነቱ ባልታወቀ ነበር። እግዚአብሔር የሚቀጣው ኃጢአትን ነው። ኃጢአትን ሲቀጣም ከኃጢአት ጋር የሚያገኘውንም አብሮ ይቀጣል። ውድ አንባቢ ሆይ! ኢየሱስ ክርስቶስ ያስታረቀው ኃጢአተኞችንና እግዚአብሔርን እንጂ ኃጢአትንና እግዚአብሔርን አይደለምና ኃጢአትን እንደ ቀላል አትመልከተው። ቀራንዮን ስንመለከት እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ያለውን ጭካኔ እንረዳለን። አንድ ልጁን ለሞት አሳልፎ እስከ መስጠት የደረሰው ለኃጢአት ባለው ቊርጠኛ ውሳኔ ነው (ሮሜ. 8፡32)። ለአንድ ልጁ ካልራራ ለእኛማ እንዴት! «ጌታ ሆይ! አንተ ኃጢአትን በምትፀየፍበት መጠን ኃጢአትን መፀየፍ አልቻልኩምና ኃጢአትን ከሚያቆነጀው ዘመናዊነት ጋር ተላምጃለሁና እባክህን አንተ በኃጢአት ላይ ያለህን አቋም ለእኔም ለተላላው ልጅህ አድለኝ። አሜን።» አዎ ኃጢአት ቀላል የሚሆነው በንስሓ በእግዚአብሔር ምሕረት ፊት ሲያቀርቡት እንጂ ሲሠሩት አይደለም። በሽታ ቀላል የሚሆነው ሐኪም ዘንድ ሲያቀርቡት እንጂ ሸፍነው ሲንከባከቡት አይደለም።

እግዚአብሔር በመዓቱ ውስጥ ምሕረት አለውና ቅጣቱ ተግሳጽም ነው፣ ፍቅርም ነው። አባት የሚወደው ልጁን ሲያጠፋ ይቀጣዋል። ይህ የፍቅር መግለጫ ነው (ዕብ. 12፡5-11)። ቅጣት ግን ቀጥተኛው የፍቅር መግለጫ አይደለም። ሳይቀጡ የሚኖሩ ጨዋ ልጆችም አሉና። የቡራኬውን ፍቅርም መለማመድ አለብን።

እግዚአብሔር በበደሉን ሰዎችና በግፈኞች ላይ ቅጣትን ሲያወርድ ለማየት እንናፍቃለን። ሥልጣኑ የእኛ ቢሆን እንዴት እንደምንቀጣ እንናገራለን። «ግፈኛ ሰው ምንም ሲሆን ዓይቼ አላውቅም» እንላለን። ያን ሰው በግፉ ጠልተነዋል። ይህ ምንም ከመሆን በላይ መሆኑን እንኳ አንገነዘብም። ስለ እርሱ የሰማ ሁሉ ይረግመዋል። ሳያውቀው ይጠላዋል። ከዚህ በላይ ቅጣት የለም። ታዲያ «ግፈኛ ሰው ምንም ሲሆን ዓይቼ አላውቅም» እንዴት እንላለን? እግዚአብሔር የፍቅርና የቅጣት ኃይል አለው። ኃይል ብቻ ሳይሆን ሥልጣንም አለው። እርሱ እንደ እኛ አይቸኩልም።



www.ethiopinorthodox.org

እግዚአብሔር ባለመቻኮሉ ደግሞ የመጀመሪያው ትርፍ ፍጥረት ባለበት እንዲረጋ አድርጎታል።

እግዚአብሔር በሰው ላይ የነበረው ዕቅድ በሰው ክፉ ምርጫ ከመጀመሪያው ተበላሽቷል። እግዚአብሔር በሰው ላይ ያቀደው አኗኗር ይህ አልነበረም። እርሱ አሳቡ ከልካይ የለውምና ከሰው የጎደለውን በልጁ ቤዛነት ሞልቶ አድኖናል። ያንን የቀደመውን አሳቡንም በምትመጣው መንግሥቱ ይፈጽማል (ሮሜ. 8፡18-25)። አንድ አባት «ፍጥረት ሁሉ እግዚአብሔር ሁን እንዳለው ሆኗል፣ ሰማይና ምድር በቃሉ ፀንቷል። ሁን እንዳለው ያልሆነ የሰው ልጅ ብቻ ነው» ብለዋል።

ታዲያ እኛ ፈጣሪ ብንሆንና ድንጋይና ሰውም ፍጥረቶቻችን ቢሆኑ የፈጠርነው ሰው፣ ሰው አልሆን ሲለን ድንጋይ አድርገነው፣ ድንጋዩን ደግሞ ሰው እናደርገው ነበር፣ እግዚአብሔር ግን አይቸኩልምና ፍጥረት ባለበት ረግቷል። በእውነት እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ብርታቱ፣ ዓለምን የቻለበት ትዕግሥቱ ይበልጣል። ዐፄ ቴዎድሮስ፡- «የዛሬ ሥራው ተፈጥሮአችንን መሸከም ነው» ያሉት እውነት ነው።

እግዚአብሔር የማይፈርድ እየመሰላቸው ሌላ ፈራጅ አምላክ የሚፈልጉ ብዙዎች ናቸው። አንድ ሰው፡- «መፍረድማ ታውቃለህ፣ ዳተኛ ነህና ታስገድለኛለህ» በማለት ተናግረዋል። ትዘገያለህ ማለታቸው ነው። ደጃዝማች በለውም አፋር ላይ ታስረው በነበረ ጊዜ ገጠሙት የሚባለው ግጥም እንዲህ ይላል፡-

*የለህም እንዳልል ይመሻል ይነጋል፣*
*አለህም እንዳልል እንዲህ ይደረጋል፤*
*ልጅ እንዴት ባባቱ መዳኒት ያደርጋል።*

ያጎረስናቸው ሲነክሱን፣ የገዛ ልጆችን የጠላት ባንዳ ሆኖ መርቶ ሲያሲዘን፣ ያሳደግነው በክፉ ቀን ሲከፋብን የእግዚአብሔር ፍርድ ይርቅብናል። ግን እግዚአብሔር «ፍረድ» ለሚለው ቃላችን ሳይሆን የእውነት ዳኛ ስለሆነ ይፈርዳል። ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር ያመኑትን የሚያስጠቃ እየመሰላቸው የድግምት የጥንቆላ ከለላን ይጠቀማሉ። ሌሎችም እግዚአብሔር ይዘገያል እያሉ ጠንቋይና ቃልቻ ቤት መርፌ ለመስካት ይቸኩላሉ። በየጠንቋይ ቤቱ ሊያስፈርዱ ሄደው ተፈርዶባቸው የቀሩ፣ ሊያስቀጡ ሄደው ባሪያ ሆነው የቀሩ ብዙዎች ናቸው። የአገራችን የኢትዮጵያ ሰው ሲመስል፡- «ሁለት ቊና አጃ ቢጠፋባት አራት ቊና ስንዴ ይዛ



ከጠንቋይ ቤት ሄደች» ደግሞም «እግዚአብሔር በጊዜው ሲሠራ ጠንቋይ ቤት መሄድ ለወሬ መቸኮል ነው» ይላል።

እግዚአብሔር የቅን ፈራጅ ነው። በጊዜው በጽድቅ ይፈርዳል። ሲፈርድም ምስክር፣ ዐቃቤ ሕግ አይፈልግም፤ ፍርዱም ይግባኝ የሌለው ጽኑና የመጨረሻው ዳኝነት ነው። እግዚአብሔር ለጠላታችን ያሳየው ትዕግሥት ለእኛ በኃጢአታችን ያሳየው ትዕግሥት ዓይነት ነው። ለጠላታችን የተለየ እንክብካቤ አላደረገለትም። አንድ የጥንት ፈላስፋ፡- «እግዚአብሔር ጠላቴን በቶሎ አልተበቀለልኝም ብለህ አትዘን፣ አንተን በኃጢአትህ በቶሎ እንዳልተበቀለህ አስብ እንጂ» ብሏል።

እግዚአብሔር የቅጣት ኃይል አለው። በመጀመሪያ ግን የሚጠቀመው የማዳን ኃይሉን ነው። ለእኛ የተሰጠን የፍቅር ኃይል ብቻ ነው። ከፍቅር ውጭ የመበቀል ሥልጣን የለንምና የፍቅርን ኃይል ልንጠቀም ይገባናል። እግዚአብሔር ጠላታችንን ወዳጅ አድርጎ የሚሰጠን አሊያም በፍርዱ የሚቀጣው የእኛን ይቅርታ ካየ በኋላ ነው። እርሱ በማንኛውም ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ለእርሱ ካልተውንለት አይሠራም። ጠላታችን ቢቀጣ የእኛ ጉዳት አይካስም። እንዳመመኝ ይመመው ካልሆነ በቀር። እግዚአብሔር ልብ ቢሰጠውና ዳግም ገንዘባችን ቢያደርገው ግን ከቀድሞ ይልቅ ይክሰናል። ቢሆንም ግን እግዚአብሔር ክፋትን መቅጣት የመንግሥቱ ባሕርይ ነው። ስንመለስ ደግሞ እኛን ይቅር የሚልበት የይቅርታ ምክንያት አለው።

## <u>እናስተውል</u>

«ክበሮ በሰው እጅ ያምር፣ ሲይዙት ያደናግር፤» እንደሚባለው በሰው እጅ ያለ ኃላፊነት በሰው እጅ ያለ ሀብት እኛ ብንይዘው የተሻለ እንደምንሠራበት ይሰማናል። ነገር ግን እግዚአብሔር ካልገዛን በቀር ሥልጣንም ሀብትም ይገዛናል። በሥልጣናችን ማዘዝ፣ በሀብታችን በጎ መሥራት የምንችለው እግዚአብሔርን መፍራት ሲያድርብን ብቻ ነው። ያልተሰጠው የለምና ትልቅ የተቀበሉ በተሰጣቸው ልክ፣ ትንሽ የተቀበሉ በተሰጣቸው መጠን ይጠየቃሉ (ማቴ. 25፡14-30)። እንደውም ለትልቅ ኃላፊነት የምንበቃው በትንሹ ስንታመን ነውና ትንሽ የተሰጠው ጠንቃቃ መሆን አለበት። ቤታችንን መምራት አቅቶን አገር በሚመሩት ከፈረድን በራሳችን ማፈር አለብን። ሰዎች በትልቁ የማይጠነቀቁት በትንሹ ጥንቃቄን ስላልመዱ ነው። ድርሻችንን ካልተወጣን ከሳሽ መንፈስ ይጠናወተናል። የያዝነውን ሳንወጣ ሌላ



www.ethiopinorthodox.org

ያምረናል:: ባለጠጎች በድርሻቸው ልክ መስጠት አለባቸው:: እኛም በድርሻችን ልክ ማድረግና በረከትን መለማመድ አለብን::

በሰው ቦታ ላይ ሰዎች ነንና ከመፍረድ መጸለይ ይሻለናል:: እንዲህ ስንል እውነቱን እውነት፣ ሐሰቱን ሐሰት ማለት የለብንም ማለት በፍጹም አይደለም:: ርኅራኄ የሌለውን የቅጣት ናፍቆት በመያዝ መተቸት የለብንም ማለታችን ነው::

አንድ አባት:- «እግዚአብሔር ለሚሠራት ቤተ ክርስቲያን ለመሾም ሁላችንም በቤተ ሙከራ ውስጥ ነን» ያሉትን አስታውሳለሁ:: እያንዳንዱ እንቅስቃሴአችን በእጩነታችን ላይ ተጽእኖ አለው:: ስለዚህ በትንሹ ታማኝ መሆን አለብን:: ለምንገባው ቃልና ለሚሰጠን ኃላፊነት:- «እግዚአብሔር ቢረዳኝ፣ በምክራችሁ ልታተገኝ ብትወዱ ይህንን ኃላፊነት እንደምወጣ አምናለሁ» ማለት አለብን:: እግዚአብሔርም በትሕትና ስለጠራነው ስሙ ሲል ይረዳናል:: ልባችንም:- «ስሙን ጠርተሃልና ይህን ስም እንዳታሰድብ ትጋ» ይለናል:: ሰዎችም በስሙ ያምኑናል ለሚሆነውም መሳካት:- «እግዚአብሔርን ጠርቶ ነበር፣ እርሱም ረዳው» ብለው አምላካችንን ያመሰግናሉ::

እግዚአብሔር ሕመምን ችግርንና ጉስቁልናን የሚያሳየን በዚህ ውስጥ ለሚያልፉ ወገኖቻችን እንድንራራ ነው:: ብዙ ጊዜ ግን ድህነትን ያየ በድሃ፣ ችግርን ያየ በችግረኛ ይጨክናል:: ይህ የሚያሳየን ተምሮ እንደሚወድቅ ተማሪ መሆናችንን ነው:: ተማሪው ሲታይ ቀሪ የለበትም፡ ፈተና ላይ ግን ይወድቃል:: እንዲሁም ችግሩን ተካፍለነው ትምህርቱ ግን ካለፈን በፈተና ወድቀናል ማለት ነው::

ለእግዚአብሔር ፍርድ አመልካች፣ ቅጣት ሰንዛሪ፣ ቀን ቆራጭ መሆን የለብንም:: እግዚአብሔር ምስክር የማይሻ፣ የሁሉንም ጥፋት ከግንባሩ የሚያነብ የቅን ፈራጅ ነው (መዝ. 95(96):13):: ቅጣቱን ለበቀል ሳይሆን ለመመለሳችን ደወል የሚያደርግ፣ በፍጥረቱ መጥፋት የሚቆጭ፣ የለፋብን ጌታ ነው (ዕብ. 12:5-11፣ሕዝ. 18:32):: እርሱ አስታዋሽ የማያሻው፣ ጊዜን የሚያውቅ፣ የጊዜ ጌታ ነው (መክ. 3:1):: ስለዚህ እርሱን ፍርድ ለማስተማር አንከጅል::

እግዚአብሔር በፍርድ ቢነሣ ማንም አያመልጥም:: የሚሻለን የፍርዱን ሳይሆን የምሕረቱን ምክንያት ቢጠቀም ብቻ ነው:: የአስተዳደር ትልቅ ብልሃትን የምንማረው ከእግዚአብሔር ነው:: መልካም አስተዳዳሪዎች የሰላምን አማራጭ እስከ መጨረሻው





የሚጠቀሙ ትዕግሥተኞች ናቸው:: ይህ ትዕግሥት ካላሰቡት የሰውና የንብረት ውድመት ይጠብቃቸዋል:: የማይቀር ከሆነ እንኳ ለሚመጣው ችግር የመዘጋጃ ጊዜ ይሰጣቸዋል:: ለዚያኛው ወገን የሚያስበበት ጊዜና ለመመለስም ዕድል ይሰጠዋል:: የመጨረሻው ውጤቱ እኛም ከሚያፀፅት ነገር እንድናለን:: ያኛውንም ወገናችንን በትዕግሥታችን እንማርካለን:: ካልሆነም ድሉ የእኛ ሆኖ ከወቀሳ ድነን እናሸንፋለን:: እግዚአብሔር ፍርድም ምሕረትም በእጁ ሲሆን የምሕረትን አማራጭ የሚጠቀመው መልካምና ትዕግሥተኛ አስተዳዳሪ ስለሆነ ነው:: በእውነት እንደዚህ ያለ ገዥ ያስፈልገናል::

የበደለንን ሰው ምንም ቢያሳዝነን ሞቱን መመኘት የለብንም:: ምክንያቱም እሱ ሞቶ እኛ አንቀርምና:: ደግሞም ከሞት ትምህርት የለምና ለሰው ሞትን መመኘት የለብንም:: ትልቁ ጸሎት የሚሠሩትን አሳውቃቸው ማለት ነው:: አንዳንድ ጊዜ ስልክ ስናወራ የራሳችንን ንግግር ደግመን እንሰማዋለን:: የገዛ ድምጻችንን አስተጋብቶ እኛው ራሳችን ስንሰማው የመቀጠል ድፍረት አይኖረንም:: ምክንያቱም እያንዳንዱ ንግግር ኃላፊነትን የሚያመጣ ስለሚመስለን ነው:: «ሰላም ነህ ወይ?» የሚለውን ቃላችንን ደግመን ስንሰማው ሰላሙ በእርግጥ አስጨንቆኝ ነው ወይስ ልማድ ስለሆነብኝ ነው? የሚል ጥያቄ ከውስጣችን ይመጣብናል:: ስለዚህ ብዙ ጊዜ እናቋርጠዋለን:: አዎ ሰዎች ክፉ የሚናገሩትም ሆነ የሚሠሩት የተናገሩትንና የሠሩትን በዚያው ቅጽበት የመስማትና የማየት አቅም ስለሌላቸው ነው:: ደግመው መስማትና መመልከት ቢችሉ ክፉ ሥራን በጠሉ ነበር:: ስለዚህ ለሰዎች የሚሠሩትን አሳውቃቸው ብሎ መጸለይ ትልቅ ልመና ነው:: ለዚህ ነው ጌታችን:- *«አባት ሆይ÷ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው»* ያለው (ሉቃ. 23:34):: ማንም ሰው ዘላለማዊ በደል አልበደለንምና ዘላለማዊ ቅጣት ልንመኝለት አይገባንም:: ሌላውን የሚበድል ራሱን የሚበድል ነውና ለራሱ ደግ ያልሆነ ለእኛ ደግ ባይሆን መደነቅ የለብንም:: እግዚአብሔር በትዕግሥቱ ሰውን እንዲያድን መለመን አለብን:: ለሁሉ የሚጠቅመው የትዕግሥቱ ምሕረት ነውና::

የሰው ልጅ በራሱ ትግል እንዲሁም በሰዎች ቊጣ ሊተዋቸው የማይችላቸው ብዙ ስህተቶች፣ ሊሞላቸው የማይችላቸው አያሌ ጉድለቶች አሉበት:: እነዚህ ጉድለቶች የራሱን ደካማነት የሚያሳዩት የእግዚአብሔርን መቻል የሚያበስሩት ናቸው:: ስለዚህ እኛንና ሌሎችን እንዲረዳ እግዚአብሔርን መጠባበቅ አለብን:: ክረምትን በበጋ፣ ሌሊትን በቀን፣ ውርደትን በሹመት የሚለውጥ ጌታ ደካማነታችንንም በብርታት ይለውጣል::



www.ethiopinorthodox.org

## ጸሎት

በሁለት ዋጋ የገዛኸኝ፣ በመፍጠር በማዳን ባለቤት የሆንከኝ ፈላጊዬ ጌታዬ አመሰግንሃለሁ:: ሞት ለሚገባኝ ሕይወትን ያደልከኝ፣ ብዙ ሰው ያቆሰልኩትን በምሕረት ያየኸኝ፣ በሕግ ምክንያት ወደ ሲኦል ያመራሁትን በጸጋ ምክንያት ወደ መንግሥትህ ያፈለስከኝ፣ እኔ አልድንም ያልኩትን በችሎታህ ያዳንከኝ፣ ፍርዴን አንተ ወስደህ ምሕረትን ያደልከኝ፣ ስለ እኔ መስቀል ተሸክመህ ቀና ያደረከኝ፣ መግደል እየቻልህ ያዳንከኝ፣ የሚገባኝን ሞት ትተህ የማይገባኝን ሕይወት የሰጠኸኝ አንተ ነህና አመሰግንሃለሁ:: ሰው ሁሉ የሚኖረው የሚገባውን እየከፈልከው ሳይሆን የማይገባውን በጸጋህ እየሰጠኸው ነውና ተመስገን:: ጥሩነቴ አንተ ነህ፣ ብቃቴም አንተ ነህ፣ በጎነቴም አንተ ነህ:: ሰዎች ሁሉ የሚወዱልኝ የእኔ ጥሩነት ለእኔ እረፍት አልሰጠኝምና ባንተ ፍቅር አሳርፈኝ:: ሰውን ሁሉ ወዳንተ መልሰው:: የሚሠራውን አያውቅምና ይቅር በለው:: በትዕግሥትህ ካሰብክልን አድርሰን:: በሚያድነው ፍቅርህ ለዘላለሙ አሜን!



## ምዕራፍ ዐሥራ አምስት

## ያልታገሠነው ዕድል

የመቄዶንያው ፊልጶስ በሀብት እየደለለ፣ የግሪክን ግዛቶች እየከፋፈለ፣ ተራ በተራ በጦር ኃይል እያንበረከከ፣ ከእግር እንደሚጀምር መቀዝቀዝ የግሪክን ትንፋሽ አቴናን ሊይዝ እየተቃረበ ነበር:: የመቄዶንያው ፊልጶስ የተንኮል አሳቡና የወረራ ፍጥነቱን ልብ ያለው ባይኖርም ዴሞስቴን የተባለው የግሪኩ ፈላስፋ ግን አሳስቦት ነበር:: በእውቀቱና በንግግር ችሎታው ተጠቅሞ እንደ መሪ፣ እንደ ጦር አዝማች፣ እንደ አባት፣ እንደ መምህር በመሆን ሕዝቡን ያስጠነቅቅ ጀመር:: በጥበብ ጨዋታዎች፣ በአዳዲስ ፍልስፍናዎች፣ በንግግር ርቀቶች ልባቸው የተማረከው የአቴና ሰዎች ግን ስለ ዋነኛው ነገር ስለ ነጻነታቸውና ስለ ሰላማቸው የሚነግራቸውን ዴሞስቴንን መስማት ጠልተው ነበር:: ቀድሞ ስለ ሌላ ሲነግራቸው ይሰሙት ነበረ፣ ዛሬ ስለ ራሳቸው ሲነግራቸው መስማት አልፈለጉም:: በዛሬው ስሜታቸው ተስበው ስለ ነገ ዕጣቸው ማድመጥን ጠሉ:: አለማዳመጥ መብታቸው ነው፣ ያለማዳመጥን ውጤት መምረጥ ግን መብታቸው አይደለም:: ዴሞስቴን ባለመጠንቀቅ የሚያጡትን ነጻነት ኋላ ቢፈልጉት እንደማያገኙት ስላሰበ አብዝቶ መጮህ ጀመረ:: ሕዝቡ ግን ስንፍና አድሮበት ስለ ዋናው ነገር መስማት ትቶ የጥበብ ቁማር ለመጫወት ፈለገ:: በጥበባዊ ቋንቋዎች ነባራዊውን ነገር ለመርሳትና የነገን ዕጣ ላለመተመን ወሰነ:: ዴሞስቴን ግን የሚታየው ነገር እስኪታያቸው ዝም ማለትን ጠላ:: እነርሱም እርሱ የሚናገረውን ጠሉ:: አላስችልህ ብሎት በአደባባይ ቆሞ ሲናገር ሲል ስለ መቄዶንያው ፊልጶስ የሚያወራ ስለመሰላቸው ሁሉም ፊታቸውን አዞሩበት:: ዴሞስቴን ግን:-

«የአቴና ሰዎች ሆይ አይዟችሁ አትመረሩኝ፤ ሁለት ቃል ብቻ እንድናገር ፍቀዱልኝ:: ይኸውም ሌላ ነገር አይደለም፤ የአንድ አህያ ታሪክ ነው» አላቸው:: እነርሱም ይህን ሲሰሙ ሊያደምጡት መፍቀዳቸውን ገለጡለትና ፊታቸውን ወደ እርሱ መለሱ:: ዴሞስቴንም እንዲህ ሲል ንግግሩን ጀመረ:- «አንድ ቀን አንድ ሰው ከአቴና ወደ ሜላጋ ለመሄድ አስቦ አንድ አህያ ተከራየ:: ያህያው ባለቤትም ወደዚያው ቦታ የሚሄድበት ጉዳይ ስለነበረ አህያውን ከተከራየው ሰው ጋር እየተጫወቱ አንድነት ተጓዙ::



www.ethiopinorthodox.org

ሰዓቱ ቀትር ሆኖ የፀሐይዋ ሙቀት በበረታ ጊዜ ከመንገድ ዐረፉና ምሳቸውን ሊበሉ ተዘጋጁ:: በዚያ ቦታ የዛፍ ጥላ ስላልነበረ ያህያው ባለቤት ያከራየሁህ አህያዬን ነው እንጂ ጥላዋን ጭምር አይደለምና ከጥላዋ ሥር ሆኜ ምሳዬን እንድበላና ዕረፍትም እንዳደርግ ፍቀድልኝ ብሎ ጠየቀው:: ያኛው ደግሞ የተከራየሁት አህያህን በሙሉ ስለሆነ ጥላዋ የሚያገለግለው ለእኔ እንጂ ላንተ አይደለም ሲል እንቢ አለው:: ከዚህ የተነሣ ሁለቱ ሰዎች ተጣሉ ብሎ ዴሞስቴን ንግግሩን በዚህ አቆመና ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ መራመድ ጀመረ:: በአደባባዩ የነበሩት ሰዎች ግን «ታዲያ ታሪኩ በምን አለቀ?» ብለው ሁሉም በአንድ ቃል ጠየቁትና እንዲጨርስላቸው ለመኑት:: ዴሞስቴንም:-

«ወይ የአቴና ሰዎች እንዴት ያለ ሞኝነት አድሮባችኋል:: ላገራችሁና ለራሳችሁ የሚጠቅም ከፍ ያለ ቁም ነገር ያለበት ስንት ጉዳይ ልነግራችሁ ስሻ ለመስማት አትፈልጉም፤ ትሸሹኛላችሁ:: አሁን ግን ፍሬ ቢስ የሆነ የአንድ አህያ ታሪክ እንድነግራችሁ ትለምኑኛላችሁ» ብሎ ወቀሳቸው (ታላላቅ ሰዎች ከበደ ሚካኤል ገጽ 36-38)::

ያለ ሰላም ያለ ነጻነት የተሟላ ጥበብ፣ የተሟላ ህልውና፣ የተሟላ ፍቅር ሊኖር አይችልም:: «ማን ላይ ቆመሽ ማንን ታሚያለሽ?» እንዲሉ ነጻነት ላይ ቆመው ስለ ነጻነት መስማት አለመፈለጋቸው ይገርማል:: የሠዓሊ ቡሩሽ፣ የጠቢብ ልሳን የማይገልጠው ጥበብ ነጻነት ነው:: ጥበብ ያልገባቸው ሰዎች ጥበብ የሚሉት ዝሙትንና መሣሪያዎቹን ነው:: እውነተኛው ጥበብ ግን ወደ ሠሪው የሚያመለክት ቀስት አለው:: ጥበብ ከሚታየው በስተጀርባ ያለውን ማየት ነው:: በቆንጆ መደነቅ ሳይሆን ቆንጆን በሠራው ጌታ መደነቅ፣ በአዋቂዎች መገረም ሳይሆን አእምሮን በሠራው ጌታ መገረም ነው:: ጥበብ ያልገባቸው ሰዎች ዛሬን መደሰት እንጂ ስለ ነገ ማሰብ አይፈልጉም:: እውነት ለእነርሱ ንትርክ ነው:: ፌዝ ግን ዕድሜ ቀጥል ነው:: ሳቅና ደስታ የተለያዩ እንጂ የተቀላቀሉ አለመሆናቸውን አይረዱም:: ጥበብ የለሾች ስለ ነገ ማሰብ የማይፈልጉት «ስለ ነገ አትጨነቁ» በሚለው ቃል ተማርከው ሳይሆን ከድንዛዜ የተነሣ አሁን ካሉበት ሐሰተኛ ደስታ ላለመውጣት ነው:: ጥበበኞች ከዛሬ ውበት የነገ ፍጻሜ፣ ከዛሬ የሚመስል ሰላም የነገ ነጻነት የሚታያቸው፣ የታያቸውን የሚያሳዩ፣ ስለ ሕዝባቸው ራሳቸውን በማይታይ ገመድ ያሠሩ፣ ስድብና ትችትን የማይፈሩ፣ ዋጋ ክፈሉልን ሳይሆን ዋጋ እንክፈልላችሁ የሚሉ፣ የዛሬን ደሞዝ ንቀው የምትመጣዋን መንግሥት የሚጠባበቁ ናቸው::





በአቴና አደባባዮች የጥበብን ቃል ነገም ለመስማት፣ ምርምሮችን በስፋት ለማካሄድ ቀዳሚው ነገር ነጻነት ነበር:: የአቴና ሰዎች ግን ይህን አልተገነዘቡም:: የመጀመሪያው ሞኝነት የኑሮን ምሥጢር አለማወቅ ነው:: አላዋቂ ሆኖ አዋቂን መንቀፍ፣ እውር ሆኖም መሪን መግፋትና በትርን መጣል ሌላው ሞኝነት ነው:: አቅሙን የማያውቅ ማለት ትልቅ ስድብ ነው:: ስለ ራሱ ጉዳይ ሳይሆን ስለ ሌሎች ጉዳይ፣ ስለ ችግሩ ሳይሆን ስለ ሌሎች ምቾት፣ ስለ እውነት ሳይሆን ስለ ተረት፣ ስለ ዘላለሙ ሳይሆን ስለ ዘመን አመጣሽ ነገር መስማት የሚፈልግ የሞኞች ሞኝ ነው::

የአቴና ሰዎች የነጻነታቸውን ድምፅ የአህያዋን ተረት ያህል እንኳ አላከበሩትም:: ነጻነት ካላከበሩት አያከብርምና በመጨረሻ የአቴና ሰዎች ተወረሩ:: ዴሞስቴን አመለጠ:: የዴሞስቴንን ምክር በታገሡት ኖሮ አገራቸውን በነጻነት፣ ትውልዳቸውንም በሰላም መጠበቅ በቻሉ ነበር:: እውነትን ለመስማት ስለ ጠሉ ፍጻሜአቸው አላማረም:: የሞቱት የዴሞስቴንን ምክር የናቁ ቀን ነው:: የጠቢብ ሀዘን እስኪሆን ነው:: የደንቆሮዎች ሀዘን ግን ከሆነ በኋላ ለማይፈጸም ዘመን ነው::

ከመቃብርና ከሲኦል የሚያድነውን የትንሣኤውን ወንጌል ዛሬ ገሸሽ ብለናል:: ተራች ካልሆነ ሰባኪውን እንኳ እንጠላዋለን:: በአገራችን ፌዝ ለዘመናት፣ ከድሃ ቤት እስከ ቤተ መንግሥት ስለ ነገሠ እንኳን ልንፈጥር ፈጠራዎችንም መረዳት እያቃተን በጨለማ እንኖራለን:: ለቀልደኞች የምንመሰጠውን ያህል ለእውነተኞች አንመሰጥም:: በማደንዘገ ለመኖር እንጂ ለመፈወስ አሳብ እንደ ሌለን ይህ ይገልጥብናል:: ገንዘብን አምነን አሜሪካንን ለመውረስ እንጂ ክርስቶስን አምነን መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ የምናስብ ስንቶች ነን? ድሃ ከሆነ የሃይማኖትን መስፈርት በማንሣት «ሃይማኖቱ ምንድነው?» የምንል ባለጠጋ ከሆነ ለአሕዛብ ልጃችንን የምንድር ስንቶች ነን?

ከፈረንጆች ሀብት ስለ እኛ ድህነት ብንነጋገር ይመለከተናል:: ከኳስ ተጫዋቾች ግለ - ታሪክ ስለተመናመነው ደናችን ብንወያይ ይመለከተናል:: ስለ ሕልም እያወራን ሕልም ሆነን እንዳንቀር፣ ራሳችንን ጥለን ሁሉንም ሳንሆን እንዳንቀር፣ ሁብታችንን አስነጥቀን ማንነታችንንም እንዳናጣ፣ ምግባራችንን ሸጠን ጨርሰን ሃይማኖታችንንም እንዳንጥል ያሰጋናል:: ወንጌል ሲሰበክ እያንቀላፉ የዝሙት ወሬ ሲነሣ የሚነቁ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ ዓይኔን ያመኛል እያሉ የስፖርት ጋዜጦችን በአጉሊ መነጽር የሚያነቡ፣ ለጸሎት ደክሞኛል እያሉ ለኳስ ደጅ የሚያድሩ፣ ለእውነት እየፈዘዙ



www.ethiopinorthodox.org

ለሞት የሚነቁ ብዙዎች ናቸው:: ሁለት ሰባክያን በሚሰብኩበት ትልቅ ጉባዔ:- «የመጀመሪያውን ለእኔ አድርጉልኝ» ብሎ የለመነው ሰባኪ «ለምን?» ሲሉት:- «ማንቸስተር ግጥሚያ አለው፣ ቶሎ ሰብኬ ልሂድ» እንዳለ ስሰማ በጣም አዝኛለሁ:: እነዚህ የሚያስተምሩት ሕዝብ ባይለወጥ ምን ይደንቃል? እንደ እውነቱ ከሆነ ማንቸስተሮች እዚህ ጉባዔ ሊገኙና የሕይወትን ቃል ሊሰሙ ይገባቸው ነበር:: ያለንን አለማወቅ ትንሹን እንድንናፍቅ ያደርገናል:: የከበረውን ከተዋረደው መለየት ካልቻልን ብዙ በረከቶች ያመልጡናል::

የማይመለከቱንን ማስታወቂያዎች ለረጅም ሰዓት ከቴሌቪዥኑ ላይ አፍጥጠን እናያለን:: ከዚያ ውስጥ የምንጠቀመው ዕቃ በጣም ጥቂት ከወር አንድ ቀንም የሚነገረው ማስታወቂያ ላይሆን ይችላል:: የጋበዝነውን እንግዳ ረስተን «ወይ ጉድ» እያልን የምንባክነው እኛ ቃሉን ለመስማትና ለመመካከር ግን ትዕግሥት የሌለን መሆናችን ያሳዝናል:: ለእግዚአብሔር ቢዚዎች ለዓለም ንቁዎች ነንና እግዚአብሔር ያስበን::

ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ ልክ እንደ ዛሬው ያለ ትውልድ ገጥሞት እንዲህ ብሏል:- «ከእነዚህ ክርስቲያን ከተባሉት አንዱን አሞጽ ማነው? አብድዩስ ማነው? ወይም ስንት ነቢያት ስንትስ ሐዋርያት ነበሩ ብላችሁ ብትጠይቋቸው እንደ ዱዳ ዝም ይላሉ:: ነገር ግን በፈረስ ጉግስ አንደኛ እነማን ናቸው፣ እገሌ ቲያትር ምን ይላል? ብላችሁ ብትጠይቋቸው በልዩ አገላለጽ፣ በስሜትና በጥናት የተደገፈ መልስ ይሰጣሉ» ብሏል:: መንፈስ ቅዱስ ማን መሆኑን የማያውቁ ምእመናን አሉን:: አምላካቸውን ሳያውቁ ነው ክርስቲያን ነን የሚሉት:: እነዚህን ቆጥረን ነው ይህን ያህል አባል አለን የምንለው? እንኳን የሄዱት ያሉትም የእኛ አይደሉም:: ስለሚያምኑት ጌታ የሚናገሩት የላቸውምና:: ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ስለ ኢትዮጵያ ሳያውቅ ኢትዮጵያዊ ነኝ ማለት ይችላል፤ ስለ ክርስትና ሳያውቅ ክርስቲያን ነኝ ማለት ግን አይቻልም:: ዛሬ የሚዘራው የወንጌል እውነት ካለፈን እናገኘውምና ልናስብበት ይገባል:: ዕድልና ደግ ንጉሥ ሁል ጊዜ ስለማይኖሩ ቶሎ መጠቀም ያስፈልጋል:: ቃሉ:- *«እነሆ፥ በምድር ላይ ራብን የምሰድድበት ዘመን ይመጣል፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ እርሱም የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት እንጂ እንጀራን ከመራብና ውኃን ከመጠጣት አይደለም:: ከባሕርም እስከ ባሕር ድረስ፥ ከሰሜንም እስከ ምሥራቅ ድረስ ይቅበዘበዛሉ፤ የእግዚአብሔርን ቃል ለመሻት ይርዋርዋጣሉ አያገኙምም:: በዚያ ቀን መልካሞች ደናግል ጕበዛዝትም በጥም ይዝላሉ»* (አሞጽ 8:11-13) ይላልና::





ያልታገሡት ሥልጣን ሴባና አመንዝራ ያደርጋል:: ትውልድን ለመጥቀም፣ ድሆችን ለመርዳት፣ ለምስኪኖች ዘብ ለመቆም፣ አገርን ለማቅናት እንደ ሥልጣን ቅርብ የለም:: ሰው በሥልጣኑ ወገኑን ሳይሆን ራሱን ስለሚያገለግል ሥልጣን በስግብግብነት ይረክሳል:: ሰው ለራሱ ያለ ሥልጣንም በቂ ነው:: ለብዙዎች ለመብቃት ግን ሥልጣን ይረዳል:: ይህንን ብቃት ግን ስግብግብነት ያበላሸዋል:: ሥልጣኑን የወደደውን መጥቀሚያ፣ የጠላውን ማሳደጃ በማድረግ የሰውና የእግዚአብሔርን አደራ ያበላሻል:: በዚህ ምክንያት ዘመኑ በፍርሃት፣ ፍጻሜውም በእንግልት ያልቃል:: «በፍጡር እጅ ያለ ሥልጣን መባከኑ አይቀርም» እንዲሉ የፍጡር አዛዥነት እያደር የሚያንስ፣ ገገርው ተገገር የሚሆንበት ጉልበት ሰባሪ የቍልቍለት መንገድ ነው:: ፍቅር ግን ሥልጣን ነው:: የፍቅር ሥልጣን አይሻርምና ደስታው እንደ በራ ይኖራል:: ፍቅር ከፍርሃት ያድናል:: ፍቅር እገሌ ከእኔ ይሻላል ብሎ ሥልጣኑን ያስረክባል:: ፍቅር ጊዜን ያውቃል:: ያለ ጊዜው አይንገታገትም:: ከወገን ፍቅር የሥልጣን ፍቅር ያደረበት ግን ንጽሕናውን ያጣል:: እግዚአብሔርን በመፍራት ካልያዙት ሥልጣን መልካሙን ጠባይ ያበላሻል:: በደብረ ሊባኖስ ገዳም አንድ የበቁ የሚባሉ መነኵሴ ከዘጉበት ተጠርተው እርስዎ ያስተዳድሩን መንፈሳዊ ሥልጣን ይበልጣል ብለው ተለምነው በግዝት ተሾሙ:: እርሳቸው ግን አስተዳደሩን አላውቅበት ብለው ከፊት ይልቅ ተበላሹ:: በዚህ ጊዜ ማኅበሩ:- «አልሆነሎትምና ይውረዱልን» ብሎ ቢጠይቃቸው አልወርድም ብለው አዲስ አበባ ለክስ መጡ ይባላል:: በግድ ወጥተው በግድ አልወርድም አሉ:: የሥልጣን ፍቅር ብርቱ ነው:: የተሟላ እውቀትና መንፈሳዊነት ብቻ ሥልጣንን ይንቃል::

አንድ አባት:- «በባርነት የተገኘ ሹመት አገር አይበቃውም» ብለዋል:: ሥልጣን ለማግኘት ሲለሳለሱ፣ ደጅ ሲጠኑ፣ ሲሰግዱና ጉቦ ሲያበሉ የኖሩ ሥልጣኑን ሲይዙ ሰፊው አገር ይጠባቸዋል:: ሥልጣኑን ሳይለምዱት፣ የተሾሙት በሕልማቸው እንደ መሰላቸው፣ እንዳበዱ ይሞታሉ:: ሥልጣን ለወፈፌዎችና ላልተማሩ ከአረቄ በላይ ያሰክራል:: አንድ አባት:- «ላልተማረ ቄስ ሥልጣን መስጠት ለዕብድ ሰይፍ መስጠት ነው» ብለዋል:: ያልተማረን መሾም ሕዝብን ጨርስ ብሎ ፈርዶ መሸኘት መሆኑን መግለባቸው ነው:: በሥልጣኑ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሥጋዊና መንፈሳዊ ባለ አደራ (ባለሥልጣን) በግፍ ጽዋው ይሞላል:: እጁ በደም ይታጠባል:: የገዛ ወገኖቹንና ቤተሰቦቹን አገር ያሳጣል:: በኢትዮጵያ ታሪክ እንኳ ስንመለከት ባለፈው መቶ ዓመት ውስጥ እንኳ በወጉ የተቀበሩ ነገሥታትን አናይም:: ዐፄ ቴዎድሮስ፣ ዐፄ ዮሐንስ፣ ዐፄ ሚኒልክ፣ ልጅ ኢያሱ፣ ዐፄ ኃይለ ሥላሴን ስንመለከት አንድ ድሃ የማያጣውን



www.ethiopinorthodox.org

የቀብር ሽኝት አላገኙም። በሥልጣን የሚኖር የጨበጠውን ወገን እየረገጠ ወጥቶ፣ የረገጠውን ወገኑን እየጨበጠ የሚወርድ ነው። በእውነት ያልታገሡት ሥልጣን፣ ችኩላ የበዛበት ሹመት ጥፋቱ ብዙ ነው። ሥልጣን እግዚአብሔር ከሰጠን ዕድል ነው። ያልፋልና የማያልፍ ሥራ ልንሠራበት ይገባል። ዘመኑ አጭር ነው። የአንድ ሠራተኛን የሥራ ዘመን ያህል እንኳ የማይሞላ ጥቂት ጊዜ በመሆኑ ለትውልድና ለአገር የሚጠቅም ነገር ልንሠራበት ይገባናል።

ያልታገሥነው ምክርና ሥልጣን ብቻ ሳይሆን ያልታገሥነው ሀብትም ከውድቀት ያደርሳል። አንድ የድሮ ባላባት ሎሌያቸውን ጠርተው፦ «እንደው ወደ ቆላ ልልክህ ነበር» ብለው ትክዝ አሉ። ሎሌውም፦ «እሄዳለሁ ምን አሳሰቦት?» ቢላቸው «አይ ረሀቡን አትችለውም ብዩ ነው» አሉት። ሎሌው ግን መልሶ፦ «አይ ጌቶች እንኳን ረሀቡን ጥጋቡንም ችለነዋል» አላቸው ይባላል። አዎ ሰው ከረሀብ ይልቅ ጥጋብን አይችልም። ረሀብ አንድ ዓይነት ጠባይ ይሰጠዋል። ሰባራ ያደርገዋል። ጥጋብ ግን ብዙ የጠባይ አረም ያበቅልበታል። የራበውን መሬት ትችለዋለች። የጠገበ ግን መሬት አልችልህ ብሉት በአየር ሲበርር፣ ባሕር ሲቀዝፍ ይሞታል። አንድ ደራሲ፦ «ሰው ከእናቱ ማኅፀን ራቁቱን ስለወጣ ከጌትነት ይልቅ ድህነትን በቶሎ ይለምዳል» ብሏል።

የሰው ልጅ ብዙ የተደበቁ ነገር ግን ማግኘት የሚያወጣው ጠባያት አሉት። እስኪሞላ መቅለስለስ፣ እስኪያገኙ ተራመዱብኝ ማለት፣ እስኪጠግቡ ማቆላመጥ ካገኙ በኋላ ደረትን እንደ አፈ ሙዝ ማሞጥሞጥ፣ ልርገጣችሁ አመመኝ አትበሉ፣ ልስደባችሁ ተሰማኝ አትበሉ፣ ድሃን አታሳዩኝ፣ ሁሉም ሰው ይሸተኛል ማለት ማግኘት የሚያበላሻቸው የቀላሎች ጠባይ ነው። አንድ የጥንት ፈላስፋ የተናገረው ጠቃሚ ምክር ነው፦ «ዓለሚ የሰጠችህ ከሌላው ቀምታ ነው፣ ያንተንም ቀምታ ለሌላው ትሰጠዋለችና አትታበይ» ብሏል። ሌላውም አዋቂ፦ «ዓለም ሦስት ናት አንድ ቀን ላንተ፣ አንድ ቀን ባንተ አንድ ቀን ለሌላ ናትና» ብሏል።

የሰው ተፈጥሮ ደስታንም ሀዘንንም የማይችል በመሆኑ በዕድሉም በመከራውም መታገሥ ያስፈልገዋል። የሰው ልጅ ሲያጣ የሚያገኝ እንደማይመስለው ሁሉ፣ ሲያገኝም የሚያጣ አይመስለውም። ዓለሚ ግን እስስት ናትና መልኳን ትቀይርበታለች። ከታገሡት መከራ ያልታገሡት ዕድል አወዳደቁ ብርቱ ነው። ቀላል ልብ ያለው ሰው ማግኘት ይደንቀዋል። «ባለጌ በበቅሎ ላይ ሲሄድ ወደ ሰማይ የወጣ ይመስለዋል» እንዲሉ።



በዓለም ላይ መቆየት ካማረን ተደብቆ መኖርን እንውደድ። የትልቅ ሰው ውድቀት ለብዙዎች እርካታ ነው። በዓለም ላይ ግን በጥቂቱ መረሳት መከራን ይቀንሳል። ስለዚህ ያከበረችህ ዓለም ሳታዋርድህ እንቅልፍ አይዛትምና ተጠንቀቅ! ዓለም ሳትንቅህ አትቀርምና አስቀድመህ ናቃት፤ ከዚያ መናቋ አይደንቅህም። ከሁሉ ሁሉ ዕድልህን ታገሠው። በዓለም ላይ ቶሎ ልንጠቀምባቸው የሚገባን የማይቆዩ ሁለት ነገሮች አሉ። ሃይማኖትን የሚወድ ንጉሥና ዕድል ናቸው። ስለዚህ ዕድላችንን እንታገሠው እንጠቀምበት።

## እናስተውል

ስለ ቤርያ ሰዎች የተጻፈው ይደንቃል፦ *« . . .እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና፦ ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ»* (የሐዋ. 17:10-11)። የቤርያ አይሁድ አዲሱን የክርስትና እውነት ሲሰሙ የቀናቸው መቃወም አይደለም። ልበ ሰፊዎች ነበሩና *«እንደዚሁ ይሆንን?»* በማለት ቆም አሉ። የኖረው ሁሉ ትክክል፣ አዲሱ ሁሉ ስህተት ነው ብለው አላሰቡም። «ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል» ብለው ክፉ ተረት አልተረቱም። ምንም ባያውቁት መልአክ አይጠላም፣ ምንም ቢያውቁት ሰይጣን አይመረጥምና። በአገራችን ግን ራስን የማየት ልበ ሰፊነት የለንምና እናሳዝናለን። እውነት ነጻ ከምታወጣን የለማውን ውሸት በጥቅስ እያዳበርን ለመኖር የቆረጥን፣ ከእውነት ጋር ላለመገናኘት ተጠንቅቀን የምንኳዝ እንመስላለን። ስለዚህ እውነትንም እውነተኞችንም እንገፋለን።

*ዋርካ ምን ያፈራል ብለው ሳይጠይቁ፣*
*ሾላ ምን ያፈራል ብለው ሳይጠይቁ፣*
*ዋንዛ ምን ያፈራል ብለው ሳይጠይቁ፣*
*ቆርጠው ቆርጠው ጣሉት እነ ጣዕም አያውቁ።*

የቤርያ ሰዎች ሌላው ልበ ሰፊነታቸው ቆም ካሉ በኋላ *«ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ»* የአሁኑን እውነት ከድሮው ጋር ለማስማማት ሞከሩ። ማጣቀሻቸው ባሕል ወይም አንድ ሊቅ ሳይሆን እስትንፋሰ እግዚአብሔር የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ንጹሕ የእግዚአብሔር ቃል ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ከተጠራጠርን ያለነው አደጋ ውስጥ ነው። ሁሉን የሚያርም በማንም ግን የማይታረም መጽሐፍ ቢኖር መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የትኛውም አስተሳሰብ የትኛውም ትምህርት በዚህ መጽሐፍ ይዳኛ



www.ethiopinorthodox.org

ል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ያልደገፈውን ሐሰት ለማለት ድፍረት ካላገኘን ለመዳን አሳብ ያለን አይደለንም፡፡ የቤርያ ሰዎች *«ነገሩ እንደዚህ ይሆንን?»* ብለው ቆም ካሉ በኋላ መጻሕፍትን መመርመር የዘወትር ሥራቸው ሆነ፡፡ የሰሙት የሐዋርያት ትምህርት የእግዚአብሔር ቃል የሚደግፈው መሆኑን ባረጋገጡ ጊዜ *«ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ»* (የሐዋ. 17:11)፡፡ እኛም እየተጓዝን አቅጣጫችንን ማስተካከል አይቻለንም፡፡ ቆም ማለት ያስፈልገናል፡፡ የሰማነውን ሁሉ መቀበል አይገባንም፡፡ በእግዚአብሔር ቃል መፈተሽ ያስፈልገናል፡፡ በመጨረሻም ቃሉ ያረጋገጠልንን በሙሉ ፈቃድና ውሳኔ በመቀበል ማረፍ ይገባናል፡፡ ያልታገሥነው እውነት የደስታችንን ዘመን ያርቅብናል፡፡ ያልታገሥናቸው ብዙ ዕድሎቻችን ጎድተውናልና እናስተውል!

## ጸሎት

ከመልካምነቴ አብዝተህ፣ ከክፋቴ አሳንሰህ የከፈልከኝ፤ ሽባውን እኔን መለሎዬ ያልከኝ፣ በቁልምጫ ቃል ወዳጄ ብለህ የጠራኸኝ፣ የክብርን ካባ የደረብክልኝ አንተ አምላኬ ነህና አመሰግንሃለሁ፡፡ አባቶቼ በእሳት በሰይፍ ውስጥ አመለኩህ፡፡ እኔ ግን በሞቀ መቅደስ፣ ባማረ ቤቴ ላመልክህ ተሳነኝ፡፡ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ? እባክህ ከዚህ ታጥቦ ከማይጠራ ማንነት አድነኝ፡፡ ስለገፋሁት በጎ ምክር፣ ነውረኛ ስለሆንኩበት ሀብት፣ አንተን በመፍራት ስላልተወጣሁት ሥልጣን ይቅር በለኝ፡፡ አደራን ሥልጣን፣ ኃላፊነትን እልቅና በማለቴ ሰውን በደልኩ፡፡ እኔን አገልግሉኝ ብዬ ደንብ አወጣሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ ራሴን የበላይ ያደረግሁ ደፋር ባሪያ ነኝና እባክህ ይቅር በለኝ፡፡ ላንተ መሥዋዕትነትን አይደለም የጊዜን ዋጋ የአሥራት በኩራቴን ስጦታ እንኳ ለመወጣት የደከምሁ ነኝ፡፡ ጌታዬ ገድል መሥራትን ትቼ ገድል አደንቃለሁ፡፡ ቅዱስ የመሆን ምኞት እንጂ ውሳኔ የለኝም፡፡ አንተ የምትረዳው ምኞትን ሳይሆን ውሳኔን ነውና፣ አንተ የምትባርከው እውቀትን ሳይሆን እምነትን ነውና እባክህ የውሳኔና የእምነት ሰው አድርገኝ፡፡ በቻለኝ ትዕግሥትህ ለዘላለሙ አሜን!



# ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት

# በጊዜው ይሠራል

የአገራችን ተቀባይ ሲመርቅ፡- «ሰጪው ዘመን ነው፣ ዘመን ይስጥልን» ይላል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም የተሸነፈው ወገን፡- «የቀን እንጂ የሰው ጀግና የለውም» በማለት ይጽናናል፡፡ በዘመን ሰጪነት፣ በቀን አክባሪነት የሚያምኑ ብዙዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔርን ትተው የጊዜን ቸርነት ይጠባበቃሉ፡፡ ጊዜ ግን በራሱ ሕይወት ያለውና ፍርድን የሚያደላድል አይደለም፡፡ ጊዜ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው፡፡ ለዘመን መነሻና መድረሻ የሰጠ፣ በዘመን ውስጥ ታሪክን የሠራ፣ ከጊዜ ስፍር ውጭም የሚኖር፣ ሁሉን በጊዜ ሰሌዳ ያስገዛ፣ የቀን ባለቤት፣ የዘመን ጌታ እግዚአብሔር ነው፡፡ እርሱ በስፍራ ሳይወሰን እኛን በሚወሰን ተፈጥሮ የፈጠረ፣ በዘመን ሳይለካ ለእኛ የልደትና የሞት ቀንን የቆረጠ ድንቅ አምላክ ነው፡፡ *«አቤቱ÷ አንተ ለትውልድ ሁሉ መጠጊያ ሆንህልን፡፡ ተራሮች ሳይወለዱ÷ ምድርም ዓለምም ሳይሠሩ÷ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ አንተ ነህ»* (መዝ. 89(90)፡ 1-2)፡፡

ጊዜ ለእያንዳንዱ ሰው የተሰጠው ልክ ወይም መጠን ነው፡፡ ዕድሜ ተሰፍሮ የተሰጠን ሲሆን ፍጻሜው ከእኛ እውቀት የተሰወረ ነው፡፡ እንሞታለን ስንል እንኖራለን፣ እንኖራለን ስንል እናልፋለንና ተዘጋጅተን መቀመጥ ተፈልጎብናል፡፡ ዕድሜ በበረከት እንደሚጨምር ተነግሯል፡፡ አባትና እናትን ማክበር ዕድሜ እንደሚያረዝም የተስፋ ቃል ተሰጥቷል (ዘፀ. 20:12)፡፡ ይህን ቃል የማያከብር በተቃራኒው ዕድሜው ያጥራል፡፡ «ሽምግልናችንን ያልናቀች ወጣትነታችን እንዴት የተባረከች ነች!» እንደ ተባለ፡፡ ሽምግልናን ለማየት ሽምግልናን ማክበር ይገባል፡፡

እግዚአብሔር በጊዜ ውስጥ ይሠራል እንጂ ጊዜ እግዚአብሔርን ተክቶ ፍርድ አይሰጥም፡፡ የጊዜ ባለቤት እግዚአብሔር ነው፡፡ የምንጠብቀው ጊዜን ነው ወይስ እግዚአብሔርን? የጊዜ አምላኪዎች ከእግዚአብሔር ምንም አያገኙም፡፡ እግዚአብሔር ሥራን የሚሠራበት የራሱ ጊዜ አለው፡፡ እግዚአብሔር የዕቅድ፣ የውሳኔና የራእይ አምላክ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ዕቅዱን የሚተገብርበት፣ ውሳኔውን የሚፈጽምበት፣ ራእዩን የሚመታበት የራሱ ጊዜ አለው፡፡ የእግዚአብሔር ትዕግሥት ስንልም በጊዜው ይሠራል ማለታችን



www.ethiopinorthodox.org

ነው:: ሰዎች ስንፍናቸውን፣ ድንዛዜአቸውን፣ ቸልተኝነታቸውን፣ ሌላው ይሥራልኝ ማለታቸውን እንደ ትዕግሥትና ልበ - ሰፊነት ሊቆጥሩት ይችሉ ይሆናል:: ነገር ግን እነዚህ ነገሮች የጽድቅ ተቃራኒዎች በመሆናቸው ትዕግሥት ብለን ልንጠራቸው አንችልም:: የእግዚአብሔር ትዕግሥት ግን የፍቅሩ፣ የጥበቡና የጽድቁ መገለጫ ነው::

ያለበደሉ ነገር ግን ስለ ወገኖቹ መከራን እየተቀበለ ያነባ የነበረው ነቢዩ ኤርምያስ:- *«እግዚአብሔር በተስፋ ለሚጠብቁት ለምትሻውም ነፍስ መልካም ነው:: ሰው ዝም ብሎ የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ ቢያደርግ መልካም ነው»* (ሰቆ.ኤር. 3:25-26) ብሏል:: መከራ ተስፋን የሚታገል ታጋይ ነው:: መከረኛው ተስፋን ከጣለ በቀላሉ ይሸነፋልና መከራ የበላይ ለመሆን ተስፋን ይታገላል:: ተስፋ ከሁኔታዎች ግምገማ ተነሥተን የምንጠብቀው ሳይሆን ተስፋ እግዚአብሔር ነው:: ሁኔታዎች ምንም መልክ ይኑራቸው በሁኔታዎች የማይወሰነውን ጌታ መጠበቅ ተስፋ ይባላል:: እግዚአብሔር እንዲሠራ መንገዱን ከሚከፍት ነገር አንዱ በእርሱ ላይ ያለን ተስፋ ነው:: እርሱ በታመነው መጠን ይሠራል:: መከራ ለፍላፊ ያደርጋል:: መከረኛው እግዚአብሔርንና አገልጋዮችን ያለማቋረጥ የሚጠይቀው ጥያቄ «እንዲህ ለምን ሆነ? ዝርዝር ምክንያት ይነገረኝ» የሚል ነው:: እግዚአብሔር ግን ለሁሉም ነገር ማብራሪያ አይሰጠንም:: አያስፈልገንምና:: በመከራ ውስጥ የማይገቡን ብዙ ነገሮች ይኖራሉ:: በዚህ ውስጥ ግን በዝምታ እግዚአብሔርን መጠበቅ ጉልበት እንዳይባክን ያደርገዋል:: የምንጠብቀው እግዚአብሔርን ነው:: እርሱ የሥራ ጊዜ አለው (መዝ. 118:126)::

የትዕግሥትን ትርጉም እስካሁን እያየን ነው:: ትዕግሥት ማለት መቻል ነው ብለናል:: እግዚአብሔር በበደላችንና በፍላጎታችን ችሎናል:: እኛም የሌሎችን በደል ይቅር ማለት ዳግመኛም ለሚለምኑን ቸር መሆን ይገባናል:: ትዕግሥት ማለት መጠበቅ ነው ብለናል:: እግዚአብሔር እንደሚጠብቀን ማለት ተስፋ እንደማይቆርጥብን አይተን እኛም በራሳችንና በሌሎች ተስፋ መቍረጥ እንደማይገባን በሚገባ አይተናል:: ትዕግሥት አለመቸኮል ነው በማለት ሦስተኛውን ትርጉም ሰጥተናል:: እግዚአብሔር ስለማይቸኩል ህልውናውን የካዱትን እንዴት እንደታገሠ አይተናል:: እኛም ዕድላችንን መታገሥ እንደሚገባን አጥንተናል:: አራተኛው:- የትዕግሥት ትርጉም ጊዜን መጠበቅ ነው:: ስለዚህ እግዚአብሔር ትዕግሥተኛ ነው ሲባል በጊዜው ይሠራል ማለት ነው::



እግዚአብሔር ይታገሣል ስንል አይቸኩልም ማለት ነው ብለናል:: እግዚአብሔር ኃይል አለኝ ብሎ ኃይሉን ሲያሳይ የማይቸኩል እንደሆነ ፍጥረትም የረጋው በታጋሽነቱ ምሥጢር እንደሆነ አጥንተናል:: አሁን ደግሞ እግዚአብሔር ይታገሣል ስንል በጊዜው ይሠራል ማለት እንደሆነ እያየን ነው:: የእግዚአብሔር ትዕግሥት ከኃያልነቱና ከፍቅሩ ይመደባል:: እግዚአብሔር ይታገሣል ሲባል የእኛ ነገር የማይሰማው ወይም ቸልተኛ ነው ማለት አይደለም:: እግዚአብሔር በመታገሡ ከፍ ያለ ዓላማ አለው::

የእግዚአብሔር ትዕግሥት እንደጠቀመን እስከ አሁን አይተናል:: በጥፋታችን ቢያጠፋን፣ ለመመለስም ዕድል ባይሰጠን ኖሮ ዛሬ ለመለወጥና ቃሉን ለመስማት ባልበቃን ነበር:: ስለታገሠን እርሱን አውቀናል ወንጌልን ሰምተናል:: ታዲያ በበደላችን ሲታገሠን ደስ ካለን በጸሎታችንም ሲታገሥ ደስ ሊለን ይገባል::

ራሳችንንና አካባቢያችንን በማየት የእግዚአብሔር ትዕግሥት ጥያቄ የሚሆንብን ጊዜ ብዙ ነው:: በሕይወታችን እንዲሆኑ የምንፈልጋቸው ነገሮች ከመቅረብ እየራቁ፣ ከመሻሻል እየተባባሱ፣ ከስምረት ይልቅ እየተበላሹ መሆናቸውን ስናስብ ትዕግሥቱን እንቀየማለን:: ከራሳችንም ወጣ ብለን አካባቢያችንን ስናይ ከተማው በኃጢአት መቆሸሹ፣ ሰዎች ግፍን አለመፍራታቸው፣ አስተዳደሩ ትብትብ መሆኑን ስናይ እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል? እንላለን:: እኛ ኃጢአተኞች ነን እግዚአብሔር ግን በንጽሕናው እንዴት ግፍን ያያል? በጻድቅነቱ እንዴት የድሆችን መገፋት ቸል ይላል? እንላለን:: እግዚአ፡ነሔር ግን ለእያንዳንዱ ጥያቄአችን ዝርዝር መልስ ላይሰጠን ይችላል:: በጊዜው እንደሚሠራ ግን በርግጥ ይነግረናል:: እኛ እግዚአብሔርን እንደታገሥን ይሰማን ይሆናል፤ በተቃራኒው ግን የታገሠን እግዚአብሔር ነው:: («ጸሎት» የሚለውን መጽሐፍ ከገጽ 92-102 ተመልከቱ)::

እንደ እኛ በጥያቄ ማዕበል ይንገላታ የነበረ አንድ ነቢይን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን:: ያ ነቢይ ዕንባቆም ነው:: ዕንባቆም ከራሱ ባሻገር የእግዚአብሔር ፍትሐ ጽድቅና የደካሞች መጠቃት የተሰማው ነቢይ ነበር:: ስለዚህ ጥያቄዬ እውነተኛ በመሆኑ ፈጣን መልስ ያስፈልገኛል ብሎ የሚያስብ ነቢይ ነበር:: ዓይኑም በዕንባ ረጥቧል፣ ልቡም በጥያቄ ተወጥሯል:: ይህ ነቢይ የነበረበትን ዘመን ስናስብ ከምርኮ በፊት ወይም ከባቢሎን ምርኮ መዳረሻ ወቅት የነበረ ነቢይ ነው:: «ልትጠፋ ያለች ከተማ ነጋሪት ቢጎስሙባት አትሰማም» እንደሚባል የእስራኤል ልጆች የነቢያትን ቃልና የንስሓን አዋጅ ቸል ብለው በፊታቸው መልካም



www.ethiopinorthodox.org

የመሰላቸውን የሚያደርጉበት፣ አንዱ አንዱን ተው የማይልበት፣ ሁሉም በኃጢአት ጊዜ ያጣበት፣ በክፋት የሚወዳደርበት፣ ብሔራዊ ራስ ወዳድነት የሰፈነበት፣ ባቢሎናውያን ዓለምን እየወረሩ የበላይነታቸውን ለማረጋገጥ የሚጥሩበት ... ዘመን ነበር፡፡ ነቢዩ የአገሩና የዓለም ሁኔታ ጥያቄ ሆኖበት ነበር፡፡ ይህንን ጥያቄውን ሊያደምጠው ለሚችል ለእግዚአብሔር አቀረበ፡፡ የዕንባቆም ጥያቄዎች ብዙ ናቸው፡፡ ከጥያቄዎቹ ውስጥ፡-

## እየባሱ ያሉ ጥፋቶች

*«አቤቱ፥ እኔ ስጮኽ የማትሰማው እስከ መቼ ነው? ስለ ግፍ ወደ አንተ እጮኻለሁ፥ አንተም አታድንም»* (ዕንባ. 1:2) የሚለው የመጀመሪያው ጥያቄው ነው፡፡ ዕንባቆም ስለ ፍላጎቱ መሟላት ሳይሆን ስለ ሌሎች ከጥፋት ማምለጥ እየጸለየ በመሆኑ መሰማት አለብኝ የሚል ስሜት ውስጥ ገብቷል፡፡ እግዚአብሔር የእኔን ይተውና የሌሎችን ጥያቄ ይመልስ ወደሚል አስተሳሰብ ሄዷል፡፡ እግዚአብሔር የዕንባቆምን ጩኸት ቢሰማም ዕንባቆም የሚጮህላቸው ሕዝብ ግን በክፋት እየበረቱ፣ ፈቃዳቸውን ተጠቅመው ክፋን እየመረጡ ነበር፡፡ የዕንባቆም ጸሎት የንስሓ ጸጋን የሚያመጣ እንጂ ንስሓን መተካት አይችልም፡፡ መዓትን ለጊዜው ያዘገያል እንጂ እስከ ፍጻሜው አያድንም፡፡ መታሠሩ የተስማማውን ሕዝብ በጸሎት ብቻ ሳይሆን በስብከትም መፍታት ያስፈልጋል፡፡ ጸሎታችን እንዲጸልዩ የሚያበረታ እንጂ የሰዎችን ጸሎት የሚተካ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ዕንባቆምን ሰምቷል፡፡ ያ ሕዝብ ግን የሚለመንለትን ልመና መልሱ ቢመጣም ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረም፡፡

## ሕግ ላልቷል

*«በደልንስ ስለ ምን አሳየኸኝ? ጠማምነትንስ ስለ ምን ትመለከታለህ? ጥፋትና ግፍ በፊቴ ነው፤ ጠብና ክርክር ይነሣሉ፡፡ ስለዚህ ሕግ ላልቷል፥ ፍርድም ድል ነሥቶ አይወጣም፤ ኃጢአተኛ ጻድቅን ይከብባልና፤ ስለዚህ ፍርድ ጠማማ ሆኖ ይወጣል»* (ዕንባ. 1:3-4)፡፡

ዕንባቆም ዓይኑን እስኪጠላ የሚያየው ክፋ፣ ጆሮውን እስኪጠላ የሚሰማው ክፋ ሆኖበት በግራ በቀኝ የሚያጽናና ነገር አጥቶ ነበር፡፡ ጴጥሮስ በባሕር ላይ እየተራመደ ወደ ጌታ ሲሄድ የማይረገጠውን ባሕር ረገጠ፡፡ ዓይኑን በጌታው ላይ ባደረገ ጊዜ ሁሉ



ባሕር ጸንታለት እግሩም እንቅፋት አልገጠመውም ነበር፡፡ ነገር ግን ዓይኑን ከጌታ አንሥቶ ሰዓቱን ቢመለከት ጨለማ፣ በግራና በቀኝ ቢያዳምጥ የነፋስና የማዕበል ድምፅ ሆነበት፡፡ የጠራውን ጌታ ሲያይ የማይረገጠውን ባሕር ረገጠ፡፡ ከተፈጥሮ ድንጋጌ በላይ ተራመደ፡፡ ዓይኑን ከኢየሱስ ላይ አንሥቶ ጨለማውን ባየ፣ ነፋሱን ባዳመጠ ጊዜ ግን ወዲያው ፍርሃት አደረበት፡፡ ፍርሃቱ ጥርጣሬን፣ ጥርጣሬው መስጠምን አስከተለበት፡፡ በእምነት ጀምሮ በመስጠም ሊያበቃ ሲል፡- *«ጌታ ሆይ አድነኝ ብሎ ጮኸ፡፡»* ኢየሱስም እጁን ይዞ ከመስጠም አዳነው፡፡ ጴጥሮስ መጠራጠሩ ቢነቀፍም ሰጥሞ ሳያልቅ አድነኝ ማለቱ ግን የሚያስመሰግነው ነው (ማቴ. 14:28-33)፡፡

ዕንባቆምም ልክ እንደዚህ ሆኖበት ተቸግሯል፡፡ አገሩ የሌቦች፣ የጉልበተኞችና የአፈኞች ሆኖበት ነበር፡፡ የእርሱ ዓይን የኃጢአተኛ ዓይን በመሆኑ ይህንን ይይ፣ የንጹሑ የእግዚአብሔር ዓይኖች ግን እንዴት ግፍን ያያሉ? የሚል ጥያቄ ተፈጥሮበት ነበር፡፡ ዕንባቆም መቅጣት ቢችል ይቀጣ፣ ሁሉንም ሰው ደምስሶ ያድር፣ እንክርዳዱን እነቅላለሁ ብሎ ስንዴውንም ይነቀል ነበር፡፡ አለመቻሉ ግን የፍርድ እሳትን በውስጡ እንዲቀጣጠል ብቻ አደረገው፡፡

ይህን የፍርድ ቅንዓት በሰው ውስጥ ያስቀመጠው ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ሰው ግን ፍርድን ሲከተል ምሕረትን ሊተው፣ ምሕረትን ሲከተል ፍርድን ሊያዛባ ይችላል፡፡ እግዚአብሔር ግን ፍቅርና ፍትሕን ያስማማል (መዝ. 84(85):10)፡፡ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ግፍ ለምን ያያል? ስንል የፍርድን ሚዛን በውስጣችን ያስቀመጠ እርሱ ራሱ መሆኑን ማሰብ ይኖርብናል፡፡

ዕንባቆም ሕጎች የወረቀት ቀለብ ሆነው አየ፡፡ ሕግጋቱ ጥፋተኞችን የመዳኘት አቅም አጥተዋል፡፡ ሕጉ ምስኪኖችን ይገዛል፡፡ ባለጠጎችና ትልልቆች ደግሞ ሕጉን ይገዙታል፡፡ መውጣት መግባት አስፈሪ የሆነበት፣ ዳኝነቱ ፍጹም የረከሰበት ዘመን ነበር፡፡ የሚፈረድበት በነጻ ሲለቀቅ፣ የሚፈረድለት ሲፈረድበት እያየ «ዓለሙ ባለቤት አይኑረው አንተ እግዚአብሔር የዓለሙ ባለቤት አይደለህም ወይ? በንጉሥ ያዘነ፣ በፍርድ የተበደለ በማን ይካሳል? በአንተ አይደለምን? ለምን ዝም ትላለህ?» እያለ ይጮህ ነበር፡፡ የሕግ መላላት፣ የፍትሕ መዛባት ሰላማውያንን ፈሪ፣ ወንጀለኞችን ደፋር አድርጎ ነበር፡፡ በሌሊት የሚተራመሱ አራዊት በቀን ወጥተው ነበር፡፡ አራዊት በቀን የሚወጡበት ክፋ ቀን ገጥሞት፣ በክፋ ሥራው የሚያፍር ስላጣ «አቤት፥ አቤት» ይል ነበር፡፡



www.ethiopinorthodox.org

እግዚአብሔር ግን በጊዜው እንደሚፈርድ ነገረው (ዕንባ. 1:5-11)። እግዚአብሔር ሲፈርድ ምድሪቱ እንደምትፈርስ፣ ንጉሡ በሌላ ንጉሥ እንደሚታሰር፣ ሕዝቡም አገሪቱን ለቆ እንደሚጋዝ፣ ምድሪቱም ከግፍ ለሰባ ዓመት እንደምታርፍ የሚገልጥ የፍርድ አንቀጽን ነገረው። እግዚአብሔር ዝም ያለው በጊዜው ሲፈርድ ነበር። በርግጥም ያ ሕዝብ እምቢ በማለቱ ጥያቄ ሆኖ አልቀረም። የፍርድ መዓት ሲወርድበት እንደ ዕንባቆም ያሉ ዝም አይሉም። ፍርድ ሲመጣ፣ ሰው ሲወድቅ፣ ሰዎችም ዋይ ዋይ ሲሉ ዕንባቆም አንጀቱ አይጠናም። ባለጌ ልጅ እስኪይዙት ይጨክንበታል። ተይዞ ሲንሰፈሰፍ ግን መልሶ ያራራል። እግዚአብሔር ቶሎ ያልፈረደው የዕንባቆምንም ርኅራኄ አይቶ እንጂ አቅም አጥቶ አይደለም። የአገራችን ሰው «ላምጨው አይገደው» እያለ ፍርዱን ያወድሳል። አንድ ቄስም፡- «እግዚአብሔር ምሕረትን ይወዳል። እምቢ ካልን ግን የመከራ ደሃ አይደለም በዓይነት ያመጣዋል» ብለዋል።

እግዚአብሔር ሥራን የሚሠራበት የራሱ ጊዜ አለው። ሰው ለእግዚአብሔር ቀን ቆራጭ፣ ፍርድ አመልካች፣ ቅጣት ሰንዛሪ መሆን የለበትም። እርሱ በጊዜው ይፈርዳል። የእግዚአብሔር ዝምታው የረሳ፣ ያልሰማ፣ ሩቅ አገር የሄደ ይመስል ይሆናል። እርሱ ግን በፍርድ የመጣ ቀን ማንም አያመልጥም። ሠለስቱ ምእት በቅዳሴያቸው፡- «እንደማይሰማ ቸል ይላል፤ እንደማያይ ዝም ይላል፤ እንደማያውቅ ይታገሣል። እንደማይሰጥ ይዘገያል» ብለዋል።

ዕንባቆም እነዚህንና ሌሎችን ጥያቄዎች ጠየቀ። ጥያቄዎቹ ግን መልስ የለሽ አልነበሩም። እግዚአብሔርም ይመልስለት ነበር። የምናመልከው አምላካችን ጥያቄን የሚፈራ አምላክ አይደለምና። እርሱ መልስ አይሰጥም። ራሱ መልስ ነው። ዕንባቆም፡- *«በመጠበቂያዬ ላይ እቆማለሁ፥ በአምባ ላይም እወጣለሁ፤ የሚናገረኝንም፥ ስለ ክርክሬም የምመልሰውን አውቅ ዘንድ እመለከታለሁ»* (ዕን. 2:1) አለ። ዕንባቆም ከተናገረ በኋላ በዝምታ ሆኖ እግዚአብሔርን መጠበቅ ጀመረ። እግዚአብሔርም ድምፁን አሰማው። እግዚአብሔር በዝምታ ውስጥ ይናገራል። ነቢዩ ኤልያስ ኤልዛቤልን ፈርቶ በሸሸ ጊዜ በዋሻ ውስጥ ተደብቆ ሳለ እግዚአብሔር ተገለጠለትና ከዋሻው ውጣ አለው። ዋሻው የኤልያስን ፍርሃት የሚያደምቅ ስፍራ ነው። በፍርሃት ውስጥ ያለ ሰው ድምፅን መስማት አይችልምና እግዚአብሔር ከፍርሃት ምሽግህ ውጣ አለው። ኤልያስም በተራራው ላይ በቆመ ጊዜ ተራሮችን የሚሰነጥቅ ብርቱ ነፋስ፣ የምድር መናወጥ፣ እሳት ሆነ። እግዚአብሔር ግን በሦስቱም ኃይላት ውስጥ አልነበረም። ከእነዚህ ክስተቶች በኋላ ግን ትንሽ የዝምታ ድምፅ ሆነ። እግዚአብሔርም ተናገረ (1ነገሥ. 19:9-18)።





በኃይለኛ ነገሮች ውስጥ እግዚአብሔር አለ ብለን እናስባለን። እግዚአብሔር ግን ዓለትን ከሚሰነጥቅ፣ ተራሮችን ከሚያፈርስ ነፋስ ይልቅ በትንሽ ዝምታ ውስጥ ይገኛል። ዕንባቆም በዝምታ ውስጥ የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰማ።

*«እግዚአብሔርም መለሰልኝ እንዲህም አለ፡- አንባቢው ይፈጥን ዘንድ ራእዩን ጻፍ፥ በጽላትም ላይ ግለጠው። ራእዩ ገና እስከ ተወሰነው ጊዜ ነው፥ ወደ ፍጻሜውም ይቸኩላል፥ እርሱም አይዋሽም፤ ቢዘገይም በእርግጥ ይመጣልና ታገሠው፤ እርሱ አይዘገይም»* (ዕንባ. 2:2-3)። እግዚአብሔር የተናገረውን ያደርጋል። ስለዚህ ራእዩን ጻፍ ተባለ። እግዚአብሔር ሥራን በሚሠራባት በዚያች ቀን ራእዩ ይከናወናል። ግን ሁሉም ነገር ወደታሰበለት ግብ ይጓዛል። ራእዩም ወደ ፍጻሜው፣ ክፉዎችም ወደ ፍርድ፣ ጸሎተኞችም ወደ መልሳቸው ይቸኩላሉ። እግዚአብሔር ተስፋን ሲሰጥ ተገዶ አይደለም። ስለዚህ ለመፈጸምም አይቸገርም። «አይዋሽም» ቢዘገይም ይመጣል። ቀን አለፈበት አይባልም። እግዚአብሔር ቀን አያልፍበትም። መንገድ የማይዘጋበት ባሕር የሚራመድ፣ በጦርነት ቀን የሰላምን ቃል የሚሰጥ ነው። እግዚአብሔር አልሠራልኝም አትበሉ። እየሠራችሁ ነበር። እርሱ ከሰዓቱ አንድ ሰዓት በፊት አይቀድምም። ከሰዓቱም አንድ ሰዓት አያረፍድም። በፊቱ ሺህ ዓመት እንደ አንድ ቀን ነው። በዘላለማዊነቱ ሲኖር አንድ ሺህ ዓመትን እንደ አንድ ቀን እየቆጠረ ነው። አንድ ቀንም በፊቱ እንደ ሺህ ዓመት ነው። የሺህ ዓመትን ተግባር በአንድ ቀን ይሠራዋል። ለእርሱ አይረፍድበትም። አልዓዛር ታሞ ሳለ ሰማ። ሰምቶ አልሄደም። ቢሄድ በሽተኛ ፈዋሽ ይባል ነበር። በሞተ ቀንም እያወቀ አልሄደም። ሄዶ ቢያነሣው ትንፋሹ ደክሞ ነበር እንጂ ባይሞት ነው፣ እነ እገሌ ሣጥን ገብተው ተፈራግጠው ወጥተዋል ይባል ነበር። በባሕሉ ነፍስ ሦስት ቀን በዛፍ ላይ ትቆይና በሦስተኛው ቀን ከተለቀሰ በኋላ ትሄዳለች ይባል ነበር። ስለዚህ ሠለስት ተለቅሶ ሁሉም ወደ ቤቱ ሲበተንና አልዓዛር እንግዲህ አበቃ ሲባል በአራተኛው ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ መጣ። ከሙታንም መካከል ወዳጁን ጠራ (ዮሐ. 11:5-44)። አዎ፡- *«እርሱም አይዋሽም፤ ቢዘገይም በእርግጥ ይመጣልና ታገሠው፤ እርሱ አይዘገይም»* (ዕንባ. 2:3)።

ጠቢቡ ሰሎሞን፡- *«ለሁሉም ጊዜ አለው»* (መክ. 3:1) ብሏል። ዳግመኛም፡- *«ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው»* (መክ. 3:11) እንዳለ እግዚአብሔር በጊዜው ሁሉን ውብ ያደርጋል። በእቅድና በትዕግሥት በምትመራው ዓለም ላይ የእግዚአብሔርን ጊዜ መጠበቅ ተገቢ ነው። ጽንስ ያለ ጊዜው በጥሩ አይወለድም። ዘርም



www.ethiopinorthodox.org

ያለ ጊዜው ፍሬ አይሆንም:: ሌሊቱ ያለ ሰዓቱ አይነጋም:: እግዚአብሔር በጊዜው ሁሉን ያደርግልናል:: የሚያኖረን ለመሻቱ ብቻ አይደለም:: መሻታችንንም ሊፈጽምልን ነው:: *«በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፥ የልብህንም መሻት ይሰጥሃል»* (መዝ. 36(37):4) ተብሎ ተጽፎአልና::

በእኛ ጊዜ የተሠራውን አይተነዋል:: የእንቧይ ካብ ነበር ተንዷል:: በእግዚአብሔር ጊዜ የተሠራ ግን መሠረቱ የፀና ነው:: የእኛ ምርጫ ቁመናን ያይ ነበር፣ የእርሱ ምርጫ ግን ልብን የሚመዝን ነውና ውብ ነው:: የእኛ ምርጫ ሳያረካን ይኖራል:: የእግዚአብሔር ምርጫ ግን ውብና አስደሳች ነው:: ስለዚህ እንዲህ እያልን እንጸልይ:-

> «ልቤን ከፍ አድርጌ እንዲህ እያልኩ እጸልያለሁ:- እግዚአብሔር ሆይ! ልቤ የተለያየ ስሜት ሊሰማው ቢሞክርም አንተ ግን በእርሱ አፍቅርበት:: አእምሮዬንም ከፍ አድርጌ እንዲህ እጸልያለሁ:- እግዚአብሔር ሆይ! አእምሮዬ የተለያዩ ነገሮችን ሊያስብ ቢችልም አንተ ግን በእርሱ አስብበት:: እጆቼንም ዘርግቼ እንዲህ እጸልያለሁ:- እግዚአብሔር ሆይ! እጆቼ የተለያዩ ነገሮችን ሊሠሩ ቢችሉም አንተ ግን በእነርሱ ሥራባቸው አሜን::»

አንዳንድ ጊዜ ያለንበት ሁኔታና የምንሄድበት መንገድ እስኪጠፋን ፈተናው ያዳፍነን ይሆናል:: ተስፋችንም ከእኛና ከሰዎች የተቆረጠ ይሆናል:: ይህ ግን ለእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ ነው:: በብርቱ ፈተና ባለፍኩባቸው የቀደሙ ዓመታት ውስጥ እስከ ዛሬ ድረስ የማልረሳውን ጸሎት መጸለይ ጀመርኩ:-

ጌታ ሆይ!

ካንተ የሆነውን ፈተና የምችልበት ጉልበቱን፣
ካንተ ያልሆነውን ፈተና የማሸንፍበት ትዕግሥቱን፣
ከሁሉ በላይ ነገር ሁሉ ለበጎ ነው የምልበት
ማስተዋልን ስጠኝ::»

ወገኖቼ!





የሰው የትዕግሥት መጨረሻው፣ ለእግዚአብሔር የሥራ መጀመሪያ ነው::

የአቅማችን መድከም፣ የሁኔታዎች መጨለም፣ እያለፈ ነው የምንለውን ጊዜ ማሰብ ትዕግሥት ያሳጣናል:: እግዚአብሔርንም መጠበቅ ያቅተናል:: ያስፈራን የአቅማችን መድከም ከሆነ *«ለሰው የማይቻል ለእግዚአብሔር ይቻለዋል»* (ማቴ. 19:26):: ያስፈራን ጨለማው ከሆነ *«ጨለማ ከእግሩ በታች ነበረ»* ተብሎለታል (መዝ. 17(18):9):: ያሰጋን መንገድ መዘጋቱ ከሆነ *«በወጀብና በዐውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው»* (ናሆ. 1:3):: ያስጨነቀን የጊዜው ማለፍ ከሆነ እግዚአብሔር የሺህ ዓመቱን ተግባር በአንድ ቀን ይሠራዋል:: *«በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት»* ነውና (2ጴጥ. 3:8):: አዎ በጊዜው ይሠራል:: ዕንባቆም ይህንን በተረዳ ጊዜ ራሱንና ሕዝቡን መውቀስ ጀመረ:: በመጨረሻም እንዲህ እያለ ዘመረ:-

*«ምንም እንኳ በለስም ባታፈራ፥*
*በወይንም ሐረግ ፍሬ ባይገኝ፥*
*የወይራ ሥራ ቢጐድል፥*
*እርሾችም መብልን ባይሰጡ፥*
*በጎች ከበረቱ ቢጠፉ፥*
*ላሞችም በጋጡ ውስጥ ባይገኙ፥*
*እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፤ በመድኃኒቴ*
*አምላክ ሐሤት አደርጋለሁ::*
*ጌታ እግዚአብሔር ኃይሌ ነው፤*
*እግሮቼን እንደ ዋላ እግሮች ያደርጋል፤*
*በከፍታዎችም ላይ ያስሄደኛል»* (ዕንባ. 3:17-19)::

## እናስተውል

የእግዚአብሔርን ጊዜ ለመጠበቅ ትዕግሥት የምናጣው ለምንድነው? ስንል ጊዜዬ አለፈ፣ አቅሜ ደከመ፣ ሳንጋጥጥ አንገቴ ተሰበረ፣ ስጠብቅ ዓይኔ ፈዘዘ፣ ጉልበቴ ደነዘዘ ብለን ነው:: እግዚአብሔር ግን በጊዜው ሲሠራ እኛን ለበረከታችን ብቁ በማድረግ እንጂ ሬሳችን ላይ ማዕድ በማስቀመጥ አይደለም:: እኛ ከሁሉ የሚያስፈራን ሞት ነው:: ምክንያቱም ለዚህ ዓለም ህልውና ሞት መጨረሻ ነው ብለን ስለምናምን ነው:: ለእግዚአብሔር ግን ሞት አያስፈራውም:: እርሱ ሞትን የሥራ መጀመሪያው ሊያደርገው ይችላልና:: ስለዚህ የእርሱን ጊዜ



www.ethiopinorthodox.org

እንጠብቅ:: ለእርሱ የሚያልፍ ጊዜ የለም:: በእርሱ ጊዜ የሚሆን ነገር ሁሉ ለልብ ደስታ፣ ለውስጥ ዕረፍት የሚሰጥ ነው::

ቀጥሎ የሚሆነውን ለማወቅ እኛ አንችልም:: ብናውቅም የመለወጥ አቅም ስለሌለን ማወቃችን ፍርሃት ከመሆን በቀር አንዳች አይረባንም:: እግዚአብሔር ግን ቀጣዩን ያውቃል:: ለእርሱ ስንገዛ ቀጣዩ አያስፈራንም:: ምክንያቱም ትላንትን በምሕረቱ ያስረሳን ነገን ደግሞ በኃይሉ የሚያስደፍረን አምላክ ነው:: እግዚአብሔር ለትላንት ታሪካችን ይቅርታ፣ ለዛሬ ሙላት፣ ለነገ ተስፋችን ነውና::

ከእኛ ይልቅ ለእኛ የሚያስብ ጌታ አለን:: እኛ ለራሳችን የምንመኘው ትልቅ ቤት ነው:: እግዚአብሔር ግን የተመኘልን መንግሥተ ሰማያትን ነው:: እኛ ለራሳችን ያሰብነው ቁሳቁስ ለማግኘት ነው:: እግዚአብሔር ግን ያሰበልን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ነው:: እኛ ለራሳችን የተመኘነው ዝናን ነው:: እግዚአብሔር ግን ያሰበልን የውስጥ ሰላምን ነው:: ከእኛ ይልቅ ለእኛ የሚያስብ አምላክ ነውና አሳቤን አሳብህ ይውረሰው ብለን መጸለይ አለብን::

ከእግዚአብሔር ይልቅ ፍትሓውያን አይደለንም:: እኛ በምናየው እንፈርዳለን:: እግዚአብሔር ደግሞ በሚያየው መጠን ይፈርዳል:: ከጎን ማየትና ከላይ ማየት ልዩነት አለው:: እግዚአብሔር ግን ከላይ ብቻ ሳይሆን የተሰወረውን አሳብ ይመረምራል:: ስለዚህ በሚሆኑት ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ጥያቄ ማንሣት አይገባም:: ከእኛ ይልቅ ያያልና ይራራልምና:: ግን ድርሻችንን ስንወጣ ድርሻውን የሚወጣ አምላክ መሆኑን መዘንጋት የለብንም:: በዛሬው ዘመን ግን በጎ ማድረግ አንፈልግም፣ በጎ እንዲደረግልን ብቻ እንፈልጋለን:: ያልዘራነውን ለማጨድ የምንፈልግ፣ ካላስቀመጥንበት ባንክ ቤት ገንዘብ ለማውጣት የምንፈርም ሰዎችን እንመስላለን::

ጥፋት በዝቷል፣ ፍርድም እየተጓደለ ነው:: እኛስ ራሳችንን አንጽተናል ወይ? በዓለም ላይ ትልቅ ስህተት የእኔ አስተዋጽኦ ምን ይለውጣል ብሎ ማሰብ ነው:: እኔ ቤቴን ማስተካከሌ በአገር ላይ ምን ለውጥ ያመጣል? የእኔ የግል ኃጢአት በወገን ላይ ምን ተጽእኖ ይፈጥራል? ማለት ትልቅ ስህተት ነው:: የምንኖረው ኑሮ የአካል ኑሮ በመሆኑ መልካምነታችንም ሆነ ስህተታችን በሌላው ላይ ተጽእኖ



ያመጣል:: እኛ ድርሻችንን መወጣት አለብን:: እግዚአብሔር ግን በጊዜው ይፈርዳል:: ሲፈርድም አይተናል::

ትላንት የገነኑ ሰዎች ዛሬ ሲለምኑ አየን:: ያኔ ፍርድን ናፍቀናል፣ ዛሬ ስናያቸው የእኛም አቋም ያጠራጥረናል:: ታሪክን እንወቅሳለን:: እኛም በታሪክ ፊት መሆናችንን ግን አንረዳም:: ቢሆንም እየሆኑ ያሉትን ነገሮችና የሚተላለፉትን ተግሳጾች እንመዝግባቸው:: እግዚአብሔር ዋጋ ሲከፍል እናያለን:: ሲሆን እየረሳን ነው እንጂ እግዚአብሔር ዛሬም እየፈረደ ነው:: እግዚአብሔር በመጨረሻ ሲናገር ትክክለኛነታችንን እናጣዋለን:: ራሳችንም ያንስብናል:: ዕንባቆምም እግዚአብሔር ሲናገር ክርክሩን አቆመ:: ኢዮብም እግዚአብሔር ሲናገር ሙግቱ ሁሉ ጠፋበትና:- *«ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደ ሆንህ፥ አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ»* አለ (ኢዮ. 42:2):: እኛም እግዚአብሔር ሲናገረን ሙግታችንን እንደ ሞኝነት እንቆጥረዋለን:: አንድ ሰባኪ ዕንባቆም ማለት ዕንባ ይቁም ማለት ነው ብሏል:: አዎ እግዚአብሔር በጊዜው ይበይናልና ዕንባ ይቁም!

## ጸሎት

የአጽናፈ ዓለሙ ንጉሥ አንተ ጌታዬ ሰላም እልሃለሁ:: ሰላም ሆነኸኛልና:: ክብርህ አይለመድም፣ ፍቅርህ አይጠገብም፣ መናህ አይሰለችም፣ ጥበብህ አይደረስበትም፣ ቸርነትህ አያልቅም፣ ምሕረትህ አይነገርም፣ በረከትህ አይጨረስም:: በየብስ ስጠብቅህ ባሕር ከፍለህ አሻገርከኝ፣ ምክንያት ስፈልግ ያለ ደመና ሸለቆዬን ሞላህ:: እኔ ያንተ ሎሌ ምን ከፍቶኝ? ሳለህልኝ ምን ቸግሮኝ? ጊዜ አለህ፣ ዘመን አለህ:: ያነጋኸውን የሚያስመሸው ማንም የለም:: ያንተን ብርሃን ጭጋግ አይጋርደው፣ ደመና አይገድበው:: በጊዜው ስለመጣው ብርሃንህ አመሰግንሃለሁ:: አቅሜ አንተ ነህ ማሸነፊያዬ፣ ቃሌም አንተ ነህ መርቻዬ፣ ዋሴ አንተ ነህ የተያዝኩ ዕለት፣ ትዳሬ አንተ ነህ የቤቴ ሙላት፣ ወዳጁ አንተ ነህ አጫዋቹ፣ ኑሮዬ አንተ ነህ ምክንያቴ፣ አገሬ አንተ ነህ ነጻነቴ:: አሳብህንና ጊዜህን የሚያከብር ልብ ስጠኝ:: በማይሻረው ሥልጣንህ ለዘላለሙ አሜን!



www.ethiopinorthodox.org

# ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት
# አንቀድመውም

ከእግዚአብሔር የምንደብቀው ሁሉ የተረገመ ነው:: ለዘመናት የፈለግነውን ነገር ያገኘን ሲመስለን ቶሎ እግዚአብሔር ሳይሰማ ጨራርሰን:- «ጌታዬ ይኸው አገኘሁት» ለማለት እንፈልጋለን:: ይህ ነገር ከእግዚአብሔር ነው ወይስ ከሰይጣን? ለማለት ጊዜ የምናጣበት ወቅት ጥቂት አይደለም:: እግዚአብሔር ሰጥቶን የሚከለክለን፣ እግዚአብሔር ነሥቶን የሚሰጠን ማንም አለመኖሩን ብንረዳ:- «ፈቃድህ ነው ወይ?» ለማለት ባልተፈተንን ነበር (ራእ. 3:7):: ሰይጣን በሚመስል ነገር ድንጋይን ዳቦ አድርጎ በማሳየት ብዙ ዘመን አታሎናል:: በዓይን እንጂ በእምነት የማይመላለስ ሰው በሚመስል ነገር፣ ባልተጨበጠ ዕድል፣ በወሬ በተሳለ ስዕል አምላኩን ገሸሽ ይላል:: በንጉሡ ዘመን አንድ ድሃ ሎተሪ ደረሰውና ድህነት ደህና ሰንብቺ ብሎ ልብሱን አውልቆ አቃጠለ:: ለካ በምኞት ሠክሮ ኖሮ ሎተሪውንም አብሮ አቃጥሎታል:: ብዙ አተርፋለሁ ብሎ የለበሰውንም አጣ:: ደህና ሁኚ ያላት ድህነት እንደምን ዋልክ? ብላ ማታ መጣችበት:: ለእግዚአብሔር የምንደብቀው ነገር የተረገመ ነው:: እንኳን ከእግዚአብሔር ከትዳራችንና ከልብ ወዳጆቻችን የደበቅነውም አይረባም:: የበረከት ደስታ ያለው ለእግዚአብሔር ነግሬ ሰመረልኝ ስንል ብቻ ነው:: ያየልንን ማየት፣ የመረጠልንን መቀበል ፍጻሜው ደስታ ነው:: በኑሮአችን ከእግዚአብሔር ደብቀን የምንሄድበት መንገድ የአቋራጭ መንገድ ነው:: ቀጥ ያለው፣ ግልጽ የሆነው የእግዚአብሔር መንገድ ሩቅ ይመስለናል:: ጠመዝማዛውና ስውሩ የእኛ መንገድ ደግሞ ቅርብ ይመስለናል::

የወደድኩት እየራቀኝ የጠላኹት ተጣበቀኝ እያልን የምናጕረመርም ነን:: በዚህ ውስጥ ግን «አንተ ታውቃለህ» ማለት ብንችል ዕረፍትን ባገኘን ነበር:: እኔ ባውቅ ምን እለውጣለሁ? ባወቀ ይለውጠው ማለት መታደል ነው:: የቅርቡን ወዳጅ እያራቀ፣ በሩቁ ሰው ሲረዳን፣ የእኛ ያልነውን አክፍቶ፣ የጠላነው ለእኛ ሲሟገት፣ ብልህ ያልናቸው ከሥር ሲነቅሉን፣ የማያከብሩን የመሠሉን ሲደግፉን ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው:: እጅግ የምንወዳቸውና መልካም ያደረግንላቸው ሰዎች ሲጠቅሙን አናይም:: ለምን? ስንል እግዚአብሔር «ዕድሜ ለእገሌ ጥንትም እርሱ ለእኔ ልዩ ነው» እንዳንል ስለሚፈልግ «ዕድሜ ለእገሌ» የማይባልበትን ሥራ በሕይወታችን ይሠራል:: የሩቁ ሲደርስልን፣ የጠላነው ሲያስጠጋን



ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው ከማለት በቀር ምንም ለመናገር አንደፍርም:: በዚህ ሁሉ ውስጥ የሚሆኑት ነገሮች ሁሉ ባይገቡንም ከእግዚአብሔር እውቀት አልፎ እኛን የሚጎዳን ምንም ነገር አለመኖሩን ማሰብ ግን ደስታን ይሰጠናል::

አብርሃም እግዚአብሔርን ለመቅደም እንደ ተነሣ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ዘፍ. 16.):: እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ እንደ ሰጠው እናነባለን (ዘፍ. 12:1-3፣ 13:15፣ 15:5):: እግዚአብሔር የተስፋ አምላክ፣ በተስፋው መሠረትም ሕዝቡን የሚመራ አምላክ ነው:: የእግዚአብሔር ተስፋ እግዚአብሔር ራሱን በተስፋ አስሮ የእኛን መልካምነት ሳያይ የሚያደርግልን የነጻ ስጦታው መንገድ ነው:: የእግዚአብሔር ተስፋ ማባበያ ሳይሆን አለኝታ፣ ምናልባት ሳይሆን እርግጠኛ ነው:: ሰው ተስፋ ሲሰጥ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል እያለ ነው:: እግዚአብሔር ግን የማያደርገውን አይናገርም፣ የተናገረውንም አያስቀርም:: በዘመናት ሁሉ እግዚአብሔር ሕዝቡን ያለ ተስፋ አልመራም:: ሰው ያለ ተስፋ መኳዝ አይቻለውምና:: በሕይወት መንገድ ላይ የሰው እግሩ ተስፋ ነው:: ተስፋ ባይኖር መኖር ባላስፈለገ ነበር:: ተስፋ ከሌለው ባለ እግር ተስፋ ያለው ሽባ ካሰበበት ይደርሳል:: አሁንም ደግመን እንላለን ዛፍ ሥር ብንቀመጥ አንዲት ትል ዛፍ ላይ ለመውጣትና ያሰበችውን ፍሬ ለመብላት ብዙ ሙከራ ታደርጋለች:: 40 ጊዜ ወድቃ በዐርባ አንደኛው ከዛፉ ላይ ወጥታ ፍሬውን ትበላለች:: የሰው ትግል እንግዲህ ከዚህች ትል ላለማነስ ነው::

እግዚአብሑር አብርሃምን በተስፋ ጠራው፣ በተሳፋ መራው፣ በተስፋ አኖረው፣ በተስፋ አበዛው፣ በተስፋ አፀናው፣ በተስፋ አከበረው:: የሰው ልጅ ተስፋው ካንተ፣ ጊዜው ግን ከእኔ እያለ እግዚአብሔርን ይሞግታል:: የእግዚአብሔር ተስፋ በእግዚአብሔር ጊዜ የሚፈጸም ነው:: የዕቅዱን መፈጸሚያ ጊዜ ሊያወጣ የሚችለው የዕቅዱ ባለቤት ነው:: የዕቅዱ ባለቤት ዕቅዱንና የጊዜ መለኪያውን ያስቀምጣል:: እግዚአብሔርም ተስፋን ሲሰጥ ተስፋን የሚፈጽምበት የራሱ ጊዜ አለው:: ተስፋው ያንተ፣ ጊዜው የእኔ ስንል ግን ከእግዚአብሔር ጋር በሽርክና ለመሥራት ፈልገናል ማለት ነው:: እግዚአብሔር ግን ሉዓላዊ ፈቃድ ያለው አምላክ በመሆኑ እሺ አይለንም:: በዚህ ጊዜ አቋራጭ መንገድ መጠቀም የሰው ጠባይ ነው:: አብርሃም የእግዚአብሔርን ተስፋ የሚቀድም አቋራጭ መንገድ አበጀ:: እግዚአብሔርን መቅደም ግን አይቻልም::

እግዚአብሔር አብርሃምን በሰባ አምስት ዓመት ዕድሜው ሲጠራው ከወገን ከዘመድ ከአገር ተለይ ብሎት ነው:: አብርሃም



www.ethiopinorthodox.org

እግዚአብሔርን ብቻውን ለማየት ከሚያየውና የእኔ ከሚለው ሕዝብና ወገን አገርም መለየት ነበረበት:: አብርሃም እግዚአብሔርን ዘመድና ዜግነት አድርጎ ወዴት እንደሚሄድ በቅጡ ሳያውቅ እግዚአብሔር ወዳየለት አገር ጉዞ ጀመረ:: አብርሃም የጨበጠውን ትቶ ተስፋን አምኖ ወጣ:: አብርሃም የልጅ አሳብ ከውስጡ ከተሟጠጠ ቆይቷል:: እግዚአብሔር ግን ሲጠራው ከጥሪው ጋር የልጅ ተስፋ ስለ ሰጠው የሞተው ልቡ መነቃቃት ጀመረ::

እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ሳይፈፀም ዐሥር ዓመት ያህል ቆየ:: አብርሃምም በምሽት፣ በድንኳኑ ውስጥ በጠባብ ቤት በጠባብ አሳብ ተጨንቆ ሲተክዝ እግዚአብሔር ከድንኳኑ አውጥቶ የሰማይ ከዋክብትን እያሳየ ዘርህ እንዲህ አይቆጠርም አለው (ዘፍ. 15:5):: አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት (ዘፍ. 15:6):: አብርሃም ታላቅ ውሳኔ ባደረገበት ዓመት ታላቅ ፈተና፣ ታላቅ ነገር በተደረገለት ዓመት ታላቅ ስህተት መጣበት:: ይህ ስህተት የመጣው አካሉ ከሆነች ከሚስቱ ነው:: ሰው ሲያባብሉት የበለጠ እንደሚያለቅስ ተስፋ ሲሰጥ ሣራ የበለጠ መጠራጠር ጀመረች:: ስለዚህ ለአብርሃም ገረዷን አጋርን ልስጥህና ከእርሷ ውለድ አለችው (ዘፍ. 16.)::

ሣራ በገዛ እጇ ትዳሯን እያፈረሰች፣ ባሏን ከእግዚአብሔር ተስፋ እያፈናቀለች መሆኗን አላወቀችም:: የወንድ ጠባይም በሚስቱ ክፉ ምክር መተባበር መልካም ምክሯን መናቅ ነውና አብርሃም በሣራ ምክር ሳተ::

አጋርንም እንደ ሚስቱ ወሰዳት:: አጋር ፀነሰች፤ በዚህ ጊዜ አጋር ሣራን ናቀቻት:: ሣራም በጣም አዘነች:: እርሷ ያላከበረችውን ትዳሯን አጋር ባለማክበሯ ተበሳጨች:: የቤታቸው ሰላም ተናጋ:: አቋራጩ መንገድ ፍንጭ አሳይቷል:: ልጅ ተፀንሷል፣ ግን ሰላም ጠፋ:: የጥርጣሬአቸው መጠቀሚያ ያደረጓት አጋር እንደ ገና ለስደት ተዳረገች:: እግዚአብሔር ግን የምድረ በዳ ዘመድ ሆኗት በበረሃ አገኛት:: እርሷም እነ አብርሃም በድንኳን ውስጥ የሚያወሩለትን ጌታ በዓይኗ አየችው (ዘፍ. 16:13)::

አጋር እስማኤልን ወለደች:: አብርሃም የፈለገውን ልጅ ቢያገኝም ልጅ በሌለው ዘመን እንደሚሰማው ስሜት ባዶነት ይሰማው ጀመረ:: በአቋራጭ የሚፈልገውን ልጅ አገኘ:: ግን እርካታ አልሰጠውም:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ያለው የተስፋው ቃል ዘር አይደለምና:: የተስፋው ቃል ዘር የሚፈጸመው የሥጋ እችላለሁ ባይነት ሲያበቃ ነው:: አብርሃም ጉልበቱ ሳይደክም ተሽቀዳድሞ





ወለደ:: እግዚአብሔር ደግሞ አብርሃም እስኪደክም ጠበቀ:: አብርሃም በራሱ የነበረውን መተማመን እስኪተው እግዚአብሔር መቶ ዓመት ጠበቀው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ከሥጋ ጋር በሽርክና አይሠራምና:: አብርሃምን መቶ ዓመት፣ ዮሴፍን ዐሥራ ሦስት ዓመት፣ ሙሴን ሰማንያ ዓመት ጠበቀ:: እኛንስ ስንት ዓመት ጠብቆን ይሆን?

አብርሃም በአቋራጭ ልጅን ቢያገኝም ሰላምና እርካታን ግን ማግኘት አልቻለም:: እስማኤል ከተወለደ በኋላ ልጅ የለኝም በሚል ትካዜ ተውጦ ነበር:: አብርሃም በአቋራጭ መንገድ ሄዶ ያመጣው ነገር ምንድነው? ስንል የሦስት ሺህ ዓመት ጦርነት ነው:: ዛሬ በማያቋርጥ ጦርነት የሚኖሩት ዐረቦችና እስራኤል የእስማኤልና የይስሐቅ ዘሮች ናቸው:: እነ አብርሃም የተስፋውን ቃል መጠራጠር ሲጀምሩ የትዳር ቃል ኪዳናቸውን አቃለሉት:: ትዳር ራሱን በራሱ የሚጠብቅ ኃይል የለውም:: ትዳርን የሰመረ የሚያደርገው ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ነው:: አሊያ የትዳር ህልውናው እንኳ አስጊ ይሆናል:: ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት ለኅብረቶቻችን ሁሉ መሠረትና ሕይወት ሰጪ ነው:: ሕይወታችን ከእግዚአብሔር የፍቅር ምንጭ ጋር እስካልተቀጠለች ራሳችንንም ሆነ የትዳር ጓደኞችንን መውደድ አንችልም:: የትዳርን ሰላም ገንዘብና ልጆች ሊጠብቁት አይችሉም:: እንደውም እግዚአብሔር የሌለበትን ትዳር ገንዘብና ልጆች ጥፋቱን ያፋጥኑታል እንጂ አያድኑትም:: እግዚአብሔር የሌለበት ትዳር ያለ የሚመስል ሲሆን ባለትዳሮቹም እያነከሱ የሚኖሩበት ነው:: ከእግዚአብሔር ጋር ያለን አንድነት ከትዳር በፊት ለትዳር ትልቅና ዋና መስፈርት ሲሆን በትዳር ለመቀጠልም እጅግ አስፈላጊ ነው:: አብርሃምና ሣራ ጎደለን የሚሉትን ነገር የእርካታቸው መሠረት አደረጉት:: እርሱን ማግኘት እርካታን ማግኘት እንደሆነ አሰቡ:: እርካታ ግን በምንም የማይደገፍ እግዚአብሔር ብቻ የሚሰጠን ሰላም መሆኑን አልተገነዘቡም:: ስለዚህ እርስ በርሳቸው ተካካዱ::

ዛሬ የትዳራቸው ጣዕም ፍቅር መሆኑን ዘንግተው በልጅ ምክንያት የሚፋቱ በአቋራጭ መንገድ የሚሄዱ ብዙዎች ናቸው:: ልጅ የሁለቱ ፍቅር ውጤት እንጂ የፍቅራቸው መሠረት እንዴት ይሆናል? ለኋላ በረከት የፊት ፍቅራቸውን (በረከታቸውን) እንዴት ይጥላሉ? ደግሞስ ልጅን እግዚአብሔር ይሰጠዋል እንጂ ሴት አትሠራው? ከአንዳንድ መውለድ አለመውለድ የተሻለ መሆኑን እግዚአብሔር አይቶልንስ ቢሆን?



www.ethiopinorthodox.org

በትዳራቸው የጎደላቸውን ለማግኘት ኃጢአትን የሚሠሩ፣ በትዳራቸው ላይ የሚያመነዝሩ ብዙዎች ናቸው:: ነገር ግን እስከ ዕድሜ ልክ ኀሊናቸውን የሚወጋ መርፌ ያተርፋሉ:: አብርሃምና ሣራ ተስፋን አለመጠበቅ ችኩልነትን፣ ችኩልነት አቋራጭ መንገድን፣ አቋራጭ መንገድ እንደ ተሞከረ ወዲያው መካሰስን ቀጥሎ ለትውልድ የሚተርፍ ጦርነትን አስከተለባቸው:: ዛሬም እግዚአብሔርን መጠበቅ አቅቶን የምንመርጠው አቋራጭ መንገድ ይህን ያስከትልብናል:: ስለዚህ እግዚአብሔርን መጠበቅ አለብን:: አበው:- «እግዚአብሔር ዘግይቶ ቢነሣም ሳይመሽ ይደርሳል» ይላሉ::

እግዚአብሐር በሕይወታችን በብዙ ነገሮች የዘገየ ይመስለናል:: እግዚአብሔር የሚዘገይበት የተለያዩ ምክንያቶች አሉ:-

## 1. ፍላጎታችን ጣኦት እንዳይሆንብን

እግዚአብሔር ልባችን የተጋጋለበትን፣ ስሜታችን የተቀጣጠለበትን ነገር ወዲያው አይሰጠንም:: ምክንያቱም ያን ነገር ቢሰጠን ጣዖት እንደሚሆንብን ያውቃል:: ጠባያችንን ይለውጥብናል፣ ስጦታ ስጦታውን ስናይ ገደል እንገባለን:: ስለዚህ እግዚአብሔር ለፍላጎታችን ያለን የጋለ አሳብ እስኪበርድ፣ ስጦታውን ሳይሆን ሰጪውን ማየት እስክንጀምር ያዘገይብናል:: አብርሃም በመቶ ዓመቱ ልጅ ቢወልድም ያ ልጅ ለእግዚአብሔር የነበረውን እምነት፣ ተስፋና ፍቅር ወስዶበት ነበር:: ስለዚህ እግዚአብሔር ልጅህን ሠዋልኝ አለው (ዘፍ. 22:1):: አብርሃም በዚህ ጊዜ ልጁ ጣዖት ሆኖበት እንደ ነበር ተረድቶ በልቡ ሳይሀሰት አልቀረም:: ሳያመነታም ልጁን ለመሠዋት ገሰገሰ:: አብርሃም ልጁን ቢል ልጁን እንደሚያጣ፣ እግዚአብሔርን ቢል ግን ይስሐቅን እንደሚያተርፍ ተረድቷል:: ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ግንኙነት የታደሰው አብርሃም ልጁን ለመሠዋት በጨከነ ጊዜ ነው:: ከእግዚአብሔር ይልቅ እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር የምንጥልበት ማንኛውም ነገር ጣዖት ነው:: እግዚአብሔር ደግሞ ከእርሱ በቀር ማንም እንዲመለክ አይፈቅድምና ይሰብረዋል:: ፍላጎታቸውን አጥብቀው የሚፈልጉና ፍላጎታቸው ጣዖት የሆነባቸው ሰዎች ፍላጎታቸውን ሲያገኙ ሰው ይበድሉበታል፣ ጥሩ ሰብእናቸውንም ይከስሩበታል:: እግዚአብሔር መልካም ጠባያችንን የሚያዳብር እንጂ የሚቀይር ስጦታ ሊሰጠን አይፈልግም:: ስለዚህ ያዘገይብናል::





## 2. እኔነታችን እስኪሞት

እኔነት ራሱን የቻለ መንግሥት ነው:: በንግግራችን እንኳ የሚበዛው ቃል «እኔ» የሚለው ቃል ነው:: እኔነታችን በሀብታችን፣ በዝናችን፣ በእውቀታችን በአጠቃላይ አለኝ በምንልበት ነገር ያለን ትምክሕት ነው:: እግዚአብሔር ደግሞ እያላቸው እንደሌላቸው የሚኖሩ «የመንፈስ ድሆችን» እንጂ እኔነትን የሚከተሉትን አይወድም (ማቴ. 5:3)::

አብርሃም የመውለድ አቅሜ ሳይሟጠጥ በጉልበቴ ልውለድ ብሎ ወለደ:: እግዚአብሔር ግን አብርሃምን መቶ ዓመት የጠበቀው እኔነቱ እስኪሞት ነበር:: አብርሃምን መቶ ዓመት፣ ዮሴፍን ዐሥራ ሦስት ዓመት፣ ሙሴን ሰማንያ ዓመት ጠብቋል:: አብርሃም ችሎታውን እስኪረሳ፣ ሙሴ ጉብዝናውን እስኪጥል፣ ዮሴፍ በሰዎች ያለውን መታመን እስኪያቆም እግዚአብሔር ታገሣቸው:: እኔነታቸው ከሞተ በኋላ ግን እግዚአብሔር በሕያውነት ሲሠራባቸውና ዛሬም ሕይወታቸው መጽሐፍ ሆኖ ሲያስተምረን እያየን ነው:: አዎ እግዚአብሔር የሚዘገየው ትምክሕታችንን እስክንጥል ነው::

## 3. ሊያስደንቀን ነው

እግዚአብሔር ተአምራትን የሚሠራ የተአምራት አምላክ ነው:: ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ፣ በሰው የማይቻሉ ነገሮችን በመሥራት የታወቀ ነው:: እኛ በተፈጥሮ ሕግ እንገደባለን፣ እግዚአብሔር ግን በተፈጥሮ ሕግ የማይገደብ ሉዓላዊ ፈቃድ ያለው አምላክ ነው:: አብርሃም በመቶ ዓመቱ መውለዱ ለማንም አስገራሚ ነው:: እግዚአብሔር ግን እስከ ዛሬ ትውልድን ሁሉ የሚያስደንቅ ሥራ ለመሥራት አብርሃምን ዘገየበት:: ዮሴፍ በባዕድ አገር ጠቅላይ ሚኒስትር መሆኑ አስደናቂ ነው:: ከዚያ በፊት ግን እግዚአብሔር ዐሥራ ሦስት የእስርና የእንግልት ዓመታትን ሲያሳልፍ ዝም ብሎታል:: ሙሴ በጉልበቱ ተማምኖ በወጣ ጊዜ እግዚአብሔር አልተደሰተም:: በምድረ በዳ ወስዶ ለዐርባ ዓመታት ያህል ጠበቀው:: ከዚያም እኔነቱ ሲሞት የእስራኤል መሪ አደረገው::

እግዚአብሔር የሚዘገየው አስደናቂ ነገሮችን ሊያደርግ ነው:: በእኛ ከመሥራቱ በፊት እኛን ለመሥራት እግዚአብሔር ይዘገያል:: በተሠራ ማንነት የሚሠራ ሥራ ከዘመን ዘመን አይጠፋምና:: ሰው ግን እግዚአብሔር ሲዘገይበት ለመቅደም አቋራጭ መንገድ



www.ethiopinorthodox.org

ያዘጋጃል:: ከሰው ብልሃት የእግዚአብሔር ሞኝነት፣ ከሰው ፍጥነት የእግዚአብሔር መዘግየት እንደሚበልጥ አይረዳም:: በእግዚአብሔር ጊዜ የሆነ ነገር ብቻ እርካታ አለው:: ዛሬ በዘመናዊው ዓለም በቤተ ሙከራ ምግቦችንና እንስሳትን ቶሎ ቶሎ ማድረስ ተችሏል:: እነዚህ የቶሎ ቶሎ «በረከቶች» ብዛት እንጂ ጥራት የላቸውም፣ ማማር እንጂ ጣዕም የላቸውም:: ከዚህ ሁሉ በላይ ለአደገኛ በሽታዎች የሚያጋልጡ ሆነዋል:: የተፈጥሮ ጊዜአቸውንና አቅማቸውን አልጠበቁምና:: እንዲሁም በአቋራጭ ፍላጎታችንን ለመሙላትና እግዚአብሔርን ለመቅደም ስንነሣ የምንፈልገውን የሚመስል እናገኛለን፤ ነገር ግን ጣዕምና ጤና የሌለው ይሆናል:: በእርሱ ጊዜ ግን የምናገኘው ለሰው ዓይን ባይሞላ እንኳ ደስታና ጤና ያለው ነው:: ጊዜዬ አለፈ ብለው እንደ ፈቃዱ ያልሆነ ትዳር የመሠረቱ ሰዎች ዛሬ የማያቋርጥ ዕንባ ያፈስሳሉ:: ክርስቶስ ከሌለበት ኅብረት ከክርስቶስ ጋር በዱር መኖር እንደሚሻል አላወቁምና:: ገንዘብ ለማግኘት ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች ገንዘቡ ቢገኝም ኅሊናቸው ግን በጥዝጣዜ የሚኖር ነው:: ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ከምንበላው ጮማ እርሱን በመፍራት ያለ ትንሽ ነገር ደስታ እንዳለው አላወቁምና:: አዎ የምንፈልገውን የሚመስል ነገር በአቋራጭ ልናገኝ እንችላለን፤ ግን ጤና የለውም:: የምንፈልገው ውጭ አገር መሄድ፣ ትዳርና ሀብት ሊሆን ይችላል:: እርሱን በአቋራጭ ማግኘት ይቻል ይሆናል:: በእግዚአብሔር ጊዜ ካልሆነ ግን ጤና የለውም:: ስለዚህ እግዚአብሔርን በትዕግሥት መጠበቅን መለማመድ አለብን::

እግዚአብሔር አምላክ የእስራኤልን ልጆች በየብስ ሳይሆን በባሕር መራቸው:: ቃሉ እንዲህ ይላል:- *«እንዲህም ሆነ፤ ፈርዖን ሕዝቡን በለቀቀ ጊዜ÷ ምንም ቅርብ ቢሆን እግዚአብሔር በፍልስጤማውያን ምድር መንገድ አልመራቸውም፤ እግዚአብሔር:- ሕዝቡ ሰልፉን ባየ ጊዜ እንዳይጸጸተው ወደ ግብፅም እንዳይመለስ ብሎአልና»* (ዘፀ. 13:17):: የእስራኤል ልጆች የሰፈሩት በሰሜናዊው ግብፅ በጌሤም ነበር:: በዚያ በኩል በየብስ ቢጓዙ በቅርብ ቀን ወደ አገራቸው ይገቡ ነበር:: እግዚአብሔር ግን ያንን ተወና ወደ ምሥራቅ ደቡብ አውርዶ የኤርትራን ባሕር ከፍሎ አሻገራቸው:: እግዚአብሔር ቅርቡን የየብስ መንገድ ሳይሆን የሩቁን የባሕር መንገድ የመረጠላቸው ለምንድነው? ስንል:- የመጀመሪያው:- የእስራኤል ልብ ሰልፈኛውን በማየት ይህንን ያህል ሕዝብ እንዴት ወደማያውቀው አገር ይሄዳል፣ በበረሃ ከምንጠፋ በግብፅ ብንሞት አይሻልም ወይ? ሬሳን ማራቅ ሞኝነት አይደለም ወይ? ብለው እንዳይመለሱ ሩቅ በሆነው በባሕር መንገድ መራቸው:: ምንም ግብፅ የጭንቅ ቦታቸው ብትሆንም የእስራኤል ልጆች ግብፅን ለምደዋት ስለ ነበር መውጣት ያስፈራቸዋል:: የባርነት ጠባዩ ካለህበት የተሻለ





የለም በማለት ባሪያ ማድረግ ነውና:: ዛሬም በኃጢአትና በሱስ የሚኖሩ ሰዎች አልለቅም የሚላቸው ኃጢአትና ሱሱ ብቻ ሳይሆን እነርሱም ከዚያ የሚሻል ሕይወት ያለ ስለማይመስላቸው ነው:: «አይጥ ከጎሬዋ ውጭ ዓለም ያለ አይመስላትም» እንዲሉ:: ነገር ግን እርስዋን አይምሰላት እንጂ ስንት ዓለም እንዳለ ምስክር ነን:: መጠጥ፣ ዝሙት ከሚሰጠው ደስታ የተሻለ ደስታ እንዳለ ምስክሮች ነንና ወገኔ ሆይ አምልጥ::

እግዚአብሔር ከፈርዖን ያድናቸዋል:: እስራኤል ግን እንቢ ካሉ አያድናቸውም:: ምክንያቱም መዳን ከባለቤቱ ፈቃድ የተነሣ መሆን አለበትና:: እንዲሁም እግዚአብሔር ከኃጢአት ያድናል:: ነገር ግን የሚያድነን ከምንጠላው እንጂ ከምንወደው ኃጢአት አይደለም:: ከኃጢአት እኛን ከማዳኑ በፊት በኃጢአት ላይ ያለንን መመረር ማየት ይፈልጋል::

እግዚአብሔር የባሕርን መንገድ የመረጠላቸው ሁለተኛው ምክንያት ክንዱን ሊያሳያቸው ነው:: ያለ መርከብ በባሕር ማሻገር የሚችለውን የአዳኝነት ክንዱንና በአንዱ ባሕር ወዳጆቹን አሳልፎ ጠላቶቹን የሚያስጥመውን የበቀል ክንዱን ሊያሳያቸው በባሕር መንገድ መራቸው:: የባሕር መንገድ ሩቅ ቢሆንም የእስራኤል ልጆች ግን እንኳን በውን በሕልም የማይታመነውን የኤርትራን ባሕር በጫማቸው ረግጠው ተሻገሩ:: የኤርትራ ባሕር ወለል ፀሐይ አይቶ አያውቅም ነበር:: የዳነ ሕዝብ ቢረግጠው ግን ለእርሱም ፀሐይ ወጣለት:: ዓለሙ ባሕር ነው:: እግዚአብሔር ልጆቹን በድል ሲያሻግርበት፣ ዓመፀኞች ግን ይሰጥሙበታል:: አንዱ ሰው ብርሃን ሲወጣለት ጓደኞቹም ብርሃን ይወጣላቸዋል:: አንዱ የቤተሰብ አባል ሲድን ቤተሰቡ ይድናል:: የእግዚአብሔር እውነት የግል አይደለችም፣ ደግሞም መሐን አይደለችምና:: ነጻ ስንወጣ እንኳን ወገናችን ቤታችንም፣ ገንዘባችንም ፀሐይ ይወጣለታል:: የዓመፅ መሣሪያ የሆነው ገንዘብ የጽድቅ አገልጋይ ይሆናል፣ የሚዘፈንበት ቤት ይዘመርበታል:: እግዚአብሔር የሩቁን መንገድ ባይመርጥላቸው ኖሮ እስከ ዛሬ ድረስ የሚተረከውን ተአምራት ባላዩ ነበር:: ቶሎ እንዲሆንልን እንፈልጋለን:: የእግዚአብሔር መዘግየትም ተስፋ ያስቆርጠንና አቋራጭ መንገድን እንፈልጋለን:: እግዚአብሔር ዘላቂ ክብሩን ሊገልጥልን ያዘገየናል ወይም በሩቁ መንገድ ይመራናል::

እግዚአብሔር የባሕርን መንገድ የመረጠላቸው ሦስተኛው ምክንያት:- እነርሱ በግብፅ፣ ግብፃውያንም በእነርሱ ተስፋ እንዲቆርጡ ነው:: ባሕሩን ሲሻገሩ ግብፃውያን በእስራኤል ተስፋ ቆረጡ፣ እስራኤልም በግብፅ ተስፋ ቆረጡ:: ወደ ኋላ ለመመለስ



www.ethiopinorthodox.org

ቢያስቡ እንኳ እግዚአብሔር ወደ ፊት ለሚሉ ልጆቹ እንጂ ወደ ኋላ ለሚሉ ልጆቹ ባሕር አይከፍልምና ልባቸው እንዲጨክን በባሕር መንገድ መራቸው:: እግዚአብሔር የሩቅ መንገድን የሚመራን ለዓለም ተስፋ እንድንቆርጥ ዓለምም በእኛ ተስፋ እንድትቆርጥ ነው:: ቀናቶች በዘገዩ ቍጥር የታመንባቸው እየተንሸራተቱ፣ ዓይናችን ያያቸው ከፍታዎች ሁሉ እየሰጠሙ እግዚአብሔር ብቻ ቆሞ ይታየናል:: እግዚአብሔር የሚዘገየው ከእርሱ ውጭ የታመንባቸው ጣኦታት ተሰብረው እስኪያልቁና ዓይናችንን በእርሱ ላይ ብቻ እስክናደርግ ነው:: በእውነት ቀናቶች ሲገፉ፣ ወራቶችም ሲገሰግሱ የሚታዩ ነገሮች ሁሉ ሕልም እየሆኑ የእግዚአብሔር ህልውና ብቻ እያበራ ይመጣል:: እግዚአብሔር የሚዘገየው በቃኝ ብለን ከኃጢአትና ከርኩሰት እንድንላቀቅ ነው:: ቶሎ ቢያደርግልን ያንን አድራጎት ለኃጢአት ተጨማሪ ኃይል ማድረጋችን እርግጥ ነው:: ዳግመኛም እግዚአብሔር የሚዘገየው የእኛን በድንቅ መሻገር የጠላትን በድንቅ መውደቅ ሊያሳየን ነው:: ውበት ጊዜ ይወስዳልና እግዚአብሔር በውበት ሊሠራን ጊዜ ይወስዳል:: ዳግመኛም ትምክሕቶቻችን እስኪሰበሩና በእግዚአብሔር ላይ ባለን መታመን እስክንጸና እግዚአብሔር ይዘገያል ወይም በሩቅ መንገድ ይመራናል:: ስለዚህ መዘግየቱ ራሳችንና አካባቢያችንን እንድናይ ስለሚረዳን በትዕግሥት መጠበቅ ይገባናል::

## እናስተውል

እግዚአብሔር ዘወትር በሥራ ላይ ነው:: ወይ ጉዳያችንን እየሠራ ነው ወይ እኛን እየሠራን ነው:: መሠራት ያማል፣ መቀረጽ መጠረብ ያስመርራል:: ፍጻሜው ግን ውበት ነው:: ዘመን አለፈ እንላለን፣ ዘመን የማያልፍበት ጌታ ግን ፀሐይን አቁሞ ውጊያን የሚፈጽም፣ ባሕርን ከፍሎ ልጆቹን የሚያሻግር እንደ ሆነ እንዘነጋለን (ኢያ. 10:13፣ ዘፀ. 14:21):: ዛሬ በእጃችን ያለው በእግዚአብሔር ጊዜ ያገኘነው ነው:: በእኛ ጊዜ ያገኘነው ግን እንደ ጉም በኗል:: የእግዚአብሔር ስጦታ መሠረት አለው:: የእኛ ሩጫ ግን እንደ እምቧይ ካብ ድርድሩ (ካቡ) ሳያልቅ ለመፍረስ የሚቸኩል ነው:: እግዚአብሔርን ማንም አያማክረውም (ኢሳይ. 40:13):: ለፍርዱም ምስክር አይሻም:: እርሱ ጥበቡ ፍጹም ነው:: ለሰው ዘመናት እውቀትን ቢያተርፉለትም ኃይሉን ግን ያደክሙታል:: እግዚአብሔር ግን በዘመናት ሽምግልና በጥበብና በኃይል ተሞልቶ ይኖራል:: ፍጡር ተስፋ ሰጥቶ ይቆጫል:: እግዚአብሔር ግን በተስፋው የማይጸጸት አምላክ ነው:: ፍጡር ቀጠሮ ያፈርሳል:: እግዚአብሔር ግን የ5500 ዘመናትን ቀጠሮ አክብሮ በሥጋ የተገለጠ





አምላክ ነው:: ስለዚህ እርሱን በተስፋ መጠበቅ ይገባናል:: ይህ ማለት ሥራ አንሥራ ማለት አይደለም:: መታገሥ አቅቶን የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃረን ጎዳና መምረጥ የለብንም ማለታችን ነው::

ዛሬ ስንመኘው ትልቅ የሚመስለንና ደስታችንን የመሠረትንበት ነገር ስንጨብጠው እንደ ተመኘነው አይደለም:: ብዙዎች በትልቅ የጠበቁት ነገር ሲጨብጡት ባዶ ይሆንባቸዋል:: ብዙ ጊዜ በባዶነትና በመንፈስ ጭንቀት ይመታሉ:: የደከምኩት፣ የሮጥኩት፣ ዕድሜዬን የሰጠሁት ለዚህ ነውን? በማለት ሲታመሙ እናያለን:: ፊት አጣሁ የሚል ጭንቀት፣ አሁን ደግሞ «አገኘሁ ግን ባዶ ሆነብኝ» የሚል ጭንቀት ይገጥማቸዋል:: እግዚአብሔር የሚያዘገይብን ዓይናችንን ከነገሮች ላይ እንድናነሣና ከልብ ስብራት እንድንድን ነው:: ስለዚህ አቋራጭ መንገዳችንን ትተን ፈቃዱን መጠበቅ አለብን:: እግዚአብሔር ተስፋ ለሚያደርጉት የማይሰበር ተስፋ ነው::

በአቋራጭ ፍላጎታችንን ማግኘት ይቻላል:: እርካታን ግን በአቋራጭ ማግኘት አይቻልም:: እርካታን የሚሰጥ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: በብዙ ደስ የማይለው የሰው ልጅ እግዚአብሔር ሲባርከው ግን በጥቂት ደስ ይለዋል:: ሁላችንም የምንፈልገው ነገር ከተሟላ እርካታ በግድ ይመጣል ብለን እናስባለን:: እርካታ ግን የአንድ ነገር ተከታይ ሳይሆን ራሱ የተለየ ሀብት ነው:: ይህ ብቻ አይደለም መንፈሳዊ ሥልጣንም ነው:: ይልቁንም እግዚአብሔር በሌለበት ምርጫ ውስጥ እርካታን መፈለግ ትልቅ ሞኝነት ነው:: እርሱ ዓመተ ኵነኔን በዓመተ ምሕረት የለወጠ አምላክ ሲሆን በእኛ ላይ የከፋብንን ነገርም ይለውጣል:: የእኛ ፈጣን እርምጃ፣ የእኛ ሠረገላና መርከቦች እርሱን አይቀድሙትም:: እርሱ ሲነሣ ሺህ ዓመት ወደ ኋላ፣ ሺህ ዓመት ወደ ፊት መሥራት የሚችል አምላክ ነው:: ማድረግ ከምንችለው ውጭ ፈንታው የእርሱ ነው:: ማድረግ በምንችለውም እርሱን እያስቀደምን መጓዝ አለብን:: እኛ እንኳን የሌለውን ማምጣት ያለውንም ማደራጀት አይቻለንም:: እርሱ ግን የሌለውን እንኳ እንዳለ አድርጎ መጥራት የሚችል፣ ለሞተው ነገርም ሕይወትን የሚሰጥ፣ ባለቀ ነገር አዲስ ሥራ የሚጀምር ነው (ሮሜ. 4:16-17፣ራእ. 21:5):: ስለዚህ እርሱን እንጠብቀው:: በትዕግሥቱ የተዋበ ነገርን ይሠራል:: እርሱ በኃይሉ ዓለምን ፈጠረ፣ በትዕግሥቱ ፍጥረትን ጠበቀ፣ በፈቃዱ ሁሉን አሳልፎ ዘላለም ይኖራል:: ለእርሱም ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይገባዋል:: አሜን::



www.ethiopinorthodox.org

## ጸሎት

እኔን ያጽናናኸኝ፣ እኔን ያነሣኸኝ፣ እኔን የደገፍከኝ ጌታዬ ክርስቶስ ሆይ አመሰግንሃለሁ። ያለፍኩት ሲመስለኝ ገና በድካሜ ውስጥ ነኝ፣ ዕድሜ ያስተማረኝ ሲመስለኝ ገና ሕጻን ነኝ። ራሴን ሳስብ ደስታ አይሰማኝም፣ ሳስብህ አንተ ብቻ ደስታዬ ነህና አከብርሃለሁ። ጌታ ሆይ፣ ብርቱ ነኝ ስል ትንሽ ነገር የሚያሸንፈኝ ደካማ ሆኜ ራሴን አገኘሁት፣ ጥበበኛ ነኝ ስል ከሞኞችም ሞኝ ሆኜ ራሴን አገኘሁት። እኔ፣ እንኳን ያንተን ከፍታ የራሴንም ልክ ማወቅ የማልችል ብናኝ ፍጡርህ ነኝ። መንገዱን እንደሚያውቅ ከፊት ቀደም ቀደም እላለሁ፣ እንደሚችል እፎክራለሁ፣ እንደሚያውቅ አስተያየት አበዛለሁ። እባክህ ጌታ ሆይ ባለፈው ስህተቴ ይቅር በለኝ። አሳቤን እንደ አሳብህ ፈጽምልኝ። የምመኘውን አገኘሁት ነገር ግን እርካታ የለውም። አንተ የኑሮ እርካታ ሁንልኝ። ጌታ ሆይ፣ በክፉ ምርጫዬ ያመጣሁት መከራ እስከ ዛሬ ያስለቅሰኛል። ከዚህ በኋላ ማንከሴ አይብዛ። ለጭንቄ ድንበር ስጠው። ከገዛ ምርጫዬ አንተ አድነኝ። ለፈቃዴ አሳልፈህ አትስጠኝ። ካለፈው መማር አልሆነልኝምና በመንፈስህ ለውጠኝ። ያንተን ጊዜ የሚታገሥ ልብ፣ የሚጠብቅ እምነት አድለኝ። ሁሉ ሲደክም በማይደክመው ኃይልህ ለዘላለሙ አሜን!





## ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት
## ትዕግሥተኛ እንሁን

እግዚአብሔር የፈጠረን በመጀመሪያ እርሱን እንድናውቀውና እንድናመልከው ነው። እግዚአብሔርን ለማምለክ እግዚአብሔርን ማወቅ ያስፈልገናል። እውነተኛ አምልኮ በእውነተኛ እውቀት ላይ ይመሠረታልና (ዮሐ. 4:22፣ ሆሴ. 4:6፣ ዮሐ. 17:3)። እግዚአብሔር የፈጠረን እንድናውቀውና እንድናመልከው ብቻ ሳይሆን ባሕርዩን እንድንላበስና ለዓለም እንድናንፀባርቅም ነው። እግዚአብሔር የፍቅር፣ የቸርነት፣ የጥበብ፣ የጽድቅ፣ የትዕግሥት ባሕርያት አሉት። እነዚህን ባሕርያት ለፍጥረቱ አካፍሏል። ባሕርያቱ በፍጡር ዘንድ በውስንነት ሲገኙ በእርሱ ዘንድ ግን በምልአት ይገኛሉ። ብርሃንን በሙሉነት የሚያስተላልፍ ንጹሕ መስተዋት ነው። እንዲሁም የእግዚአብሔርን ባሕርያት ለማሳየት የኅሊና፣ የቃልና የተግባር ቅድስና ያስፈልገናል። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረ ዘመን አንድ ሰው ደቀ መዛሙርቱን እግዚአብሔር ባሕርዩ እንዴት ነው? ብሎ ቢጠይቅ ደቀ መዛሙርቱ ልክ እንደ ኢየሱስ ብለው ሳይመልሱለት አይቀሩም። የእግዚአብሔርን ባሕርያት ያንፀባረቀ፣ የማይታየውን መለኮት በሚታይ ማንነት የገለጠ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና (ቆላ. 1:15)። እንዲሁም የእግዚአብሔርን ጠባያት ዓለሙ የሚያውቀው በእኛ አኗኗር ነውና እንደ ቆሸሸው መስተዋት ባሕርዩን አፍነን እንዳንይዝ መጠንቀቅ ይገባናል።

ትልቁ የቅድስና ጥያቄ «ኢየሱስ ክርስቶስ በእኔ ቦታ ቢሆን ምን ያደርግ ነበር?» የሚለው ነው። የሚለምነን ሰው ወደ እኛ ሲመጣ ከራሳችንና ከስስታችን ጋር ከመታገል «ኢየሱስ ክርስቶስ በእኔ ቦታ ቢሆን ምን ያደርግ ነበር?» የሚለውን ማሰብ አለብን። እኛ የእርሱ እንደራሴዎች፣ ለራሳችን የማንኖር የእርሱ ወኪሎች ነን (2ቆሮ. 5:20)። አምባሳደር ወይም እንደራሴ ከራሱ አይመልስም፣ የመንግሥቱን አሳብ ያንፀባርቃል። እኛም የክርስቶስ የመንግሥቱ እንደራሴዎች ነንና እርሱ የሚሰጠውን ምላሽ ብቻ መስጠት አለብን። ሰዎች ክፉ ሲናገሩን:- «ኢየሱስ ክርስቶስ በእኔ ቦታ ቢሆን ምን ያደርግ ነበር?» ብለን መጠየቅ አለብን። የምንኖርበት የራሳችን ምክንያት የለንም። እንኳን የምንኖረው የምንሞተውም ለክርስቶስ ነው (ሮሜ. 14:8)። ስለዚህ እርሱ የሚለውንና የሚያደርገውን ብቻ እኛም መድገም አለብን። ኑሮአችን የተጻፈ እጅ ጽሕፈት ላይ ደርቦ እንደማድመቅ፣ የተረገጠ የእግር ዱካ ላይ አስተካክሎ እንደ መርገጥ፣ እንደ ባዶ አዳራሽ የተነገረውን ንጹሕ ድምፅ ማስተጋባት



www.ethiopinorthodox.org

ነው። የክርስቶስን አኗኗር እንደገና መኖር አለብን። እኛ ክርስቶሳውያን ነንና (የሐዋ. 11:26)።

አንድ ልጅ አባትና እናቱን መምሰሉ የልደት ጸጋ ነው። አንድ ልጅ የወላጆቹን መልካቸውን፣ ባሕርያቸውንና አንዳንዴም በሽታቸውን ተካፍሎ ይወለዳል። ልደት ጥብቅ የሆነ ቊርኝት አለውና። እንዲሁም ከእግዚአብሔር ስንወለድ እግዚአብሔርን እንመስላለን ማለት ባሕርዩን እንካፈላለን (ሮሜ. 8:29)። ልጅ ወላጆቹን የሚመስለው በጥረት ሳይሆን በመወለድ ነው። እንዲሁም እግዚአብሔርን የምንመስለው በጥረታችን ሳይሆን በወንጌል (በክርስቶስ) አምነን በመወለድ ብቻ ነው (ዮሐ. 1:12)። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣ ከእርሱ ስንወለድ አፍቃሪዎች እንሆናለን። እግዚአብሔር ቸር ነው፣ ከእርሱ ስንወለድ ቸሮች እንሆናለን። እግዚአብሔር ትዕግሥተኛ ነው፣ ከእርሱ ስንወለድ ትዕግሥተኞች እንሆናለን።

እግዚአብሔር የፈጠረን በእርሱ መልክ ነው። ያ መልክ የሰውነት ክብራችን ነው (ዘፍ. 9:6)። ያ መልክ እውቀት፣ ቅድስናና ጽድቅ ተብሎ ይጠራል። ይህ መልካችን በኃጢአት ተወሰደ። ስለዚህ አዋቂው ሰው አላዋቂ እንስሳትን መሳይ ተባለ (መዝ. 48:20)። እንደውም ከእንስሳት ያነሰ ሆነ (ኢሳ. 1:3)። ቅድስናውም ጎድፎ ከጎረቤቱ ጋር በሰላም የማይኖር የሚካሰስ፣ የሚገዳደል ሆነ። ጽድቅን አጥቶ በእግዚአብሔር ፊት የማይቀርብ ሆነ። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ጥበባችን፣ ቅድስናችን፣ ጽድቃችንና ቤዛችን በመሆን የባሕርያችን ትምክሕት ሆኖልን የተሰበረውን መልካችንን አደሰልን (1ቆሮ. 1:30-31)። እውነተኛው መልካችን በክርስቶስ ተመልሶልናል። ከዚያ መልክ አንዱ ትዕግሥት ነው። እውነተኛ የውበት መለኪያ ትዕግሥት ነው። የማይፈርስ የማይበሰብስ ውበት ትዕግሥት ነው። በትዕግሥት የተበጠሰውን የቀጠሉ፣ የሞተውን ሕያው ያደረጉ፣ የነደደውን እሳት ያጠፉ ብዙዎች ናቸው (ምሳ. 25:15)። ትዕግሥት ራስን የመግዛት ትልቁ መገለጫ ነው። ትዕግሥት ስንፍና፣ ታካችነት፣ ለመጀመር መፍራት፣ ጋግርታምነት አይደለም። ትዕግሥት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው (ገላ. 5:22)።

በዓለማችን ላይ መንግሥት ከበደለው ራሱን የበደለ፣ ጠላት ከገደለው ራሱን የገደለው ይበዛል። ከመልካም እየራቅን ከክፉ ከምንዳረግበት ነገር አንዱ ትዕግሥት ማጣት ነው። የትራፊክ መብራትን እንኳ የሚታገሥ ትዕግሥት የለንም። ለምን እንደምንቸኩልም አናውቀውም። አንዳንዱ የሚበርረው የCNN እና



የBBC የቴሌቭዥንን ጣቢያ ላይ ሁሉም ነገር ሲሯሯጥ ስለሚያይ ዓለሙ ጥሎት የሄደ መስሎት ለመድረስ ነው። ግን የሚያደርገው ተግባራዊ ርምጃ የለም። የሚሮጠው በስሜቱ እንጂ በውሳኔው ኃይል አይደለም። ግን ነፋስም ይሮጣል። የሠራው ሥራ የለም እንጂ። እንዲህ የሚሯሯጡት ሰዎች፣ ትንፋሻቸውን አውጥተው ለማስገባት ጊዜ ያጠራቸው፣ ቆመው የሚኖሩ፣ እንደ ሮጡ የሚሞቱ ሰዎች ቁም ነገራቸው ትንሽ ነው። ምክንያቱም ጅምራቸው ይበዛና ውጤታቸው ያንሣል። በጎዳና ላይ ሰውን እያስደነገጠ የሚሮጠው ቢሮው ገብቶ የኮምፒዩተር ጌም የሚጫወት ነው። ወይም እጮኛውን ቀጥሮ ስለ አለቃው ክፉነት፣ ሲወልዱ ልጃቸው ስለሚለብሰው ሹራብ ለማውራት ነው። ሌላውም ሕይወቱንና ትዳሩን አደጋ ውስጥ ጥሎ ገንዘብን ብቻ እያየ ይሮጣል። ከገንዘቡም ከሕይወቱም ሳይሆን በአጭር ሲቀር፣ ሞቱ መተረቻና መማሪያ ሆኖ «እገሌን ተመልከቱ» የሚባልበት ይሆናል። መብረርን እንጂ እንቅፋትንና ገደልን ለማያስብ ሰው ወዮለት! ትዕግሥት የለሽ ስንሆን በረከታችንን ብቻ ሳይሆን ሕይወታችንንም እናጣለን። ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለሌሎች መጥፋትም ምክንያት እንሆናለን። የደቂቃ ትዕግሥት አጥተው ወጥተው የቀሩ፣ ትዳራቸውን የናዱ፣ ልጆቻቸውን ለጎዳና የሰጡ፣ ቤተ ክርስቲያናቸውን ለቅቀው የባዘኑ፣ አገራቸውን ክደው የመንግሥትና የሕዝብ ጠላት የሆኑ ብዙዎች ናቸው። መክነፍ ሁሉ ትጋት አይደለም። መስነፍም ትዕግሥት አይደለም። የእግዚአብሔር ቃል ነፍሳችንን ሳይቀር የምናተርፈው በሩጫችን ሳይሆን በትዕግሥት መሆኑን ይነግረናል።

በሕይወት ላይ ትልቅ መመሪያ «ቊም» የሚለው ነው። «ቁም» የሥልጣን ቃል በመሆኑ በእኛ ላይ ሥልጣን እንዳለው የሚሰማው አካል ብቻ ሊናገረው የሚችለው ቃል ነው። «ቁም» ትልቅ መመሪያ ነው። ካልቆምን ቀጣዩን መንገድ አጥርተን ማየት አንችልም። ካልቆምን ኃይላችን አይታደስም። ካልቆምን የመጣንበትንና የምንሄድበትን መንገድ በቅጡ አናይም። ካልቆምን ትርፋችንንና ኪሣራችንን መመዘን አንችልም። ካልቆምን ቀጣዩ ጉዞ አይታየንም። መልካምን ለማበርታት፣ ክፉውን ለማረም መቆም ግድ ይላል። አሊያ እየሮጥን የምንታጠቀው እየሮጥን መፈታቱ አይቀርም። ስለዚህ እግዚአብሔር «ቁሙ» ይለናል (ኤር. 6:16)። በዚህ ሰዓት እንኳ ትምህርታችሁን ለማቋረጥ፣ ሥራችሁን ለመልቀቅ፣ ትዳራችሁን ለመፍታት፣ ወዳጅነታችሁን ለማፍረስ፣ ... እያሰባችሁ ይሆናል። ቆም በሉ። ቢያንስ ዛሬን በትዕግሥት እደሩ። የነገ ዕይታችሁ ከዛሬ ይሻላል።



www.ethiopinorthodox.org

በብዙ ነገሮች ትዕግሥት የለንም:: የምንኖረው ከራሳችን፣ ከሰዎችና ከእግዚአብሔር ጋር ነው:: ከራሳችንም ከሰዎችም ሆነ ከእግዚአብሔር ጋር የምንኖርበት ምሥጢሩ ትዕግሥት ነው:: ትዕግሥት ፍጡር እንጂ ፈጣሪ አለመሆናችንን የምናምንበት፣ በጉልበት ሳይሆን በመጠበቅ የምንወርስበት፣ ከእግዚአብሔር ዋጋ የምንቀበልበት ምሥጢር ነው:: «የሰው ትዕግሥቱ መከራውን ያርቀዋል:: የነፍስ ስህተት የስቃይ እናት ናት:: ትዕግሥት ደግሞ የጸጋ ምክንያት ናት:: ኃይልም ከሰፊ ልብ ትወለዳለች» በማለት አባቶቻችን ተናግረዋል:: ችኩልነት ጣፋጭን አያጣጥምም:: ትዕግሥት ግን መራራን ያጣፍጣል:: በሽለቆዎች መካከል እንዲሁም በተለያዩ ወገኖች መካከል ያለው ሕያው ድልድይ ትዕግሥት ነው:: ጨለማን በብርሃን የሚለውጥ ትዕግሥት ነው:: ተማሪዎቻችንን በትዕግሥት እንጠብቃቸው:: የቃል ትምህርታችን አልገባቸው፣ ፍቅራችን አላሸነፋቸው ይሆናል:: እግዚአብሔር በሕይወት እንዲያስተምራቸው ደግሞ ጊዜ እንስጣቸው:: በተስፋ መልቀቅ በተስፋ መጠበቅ እርሱ ነው ትዕግሥት! ትዕግሥት በሌሎች ላለመበደልና ሌሎችን ላለመበደል ይረዳል:: ከዚህ ሁሉ በላይ ይቅርታ ለማድረግ ኃይል ይሰጣል:: ነገ ዛሬ ካልሆነ ከሚል ችኩልነት፣ ትላንት ምነው ዛሬ በሆነ ከሚል ቊጭት የምንድነው በትዕግሥት ነው::

ምግብ ቤት ገብተን ምግባችን እስኪበስል እንኳ ትዕግሥት የለንም:: ምግቡ ደርሶ ሲመጣ ተሳድበን እንወጣለን:: እዚያኛው ቤትም እንደ ገና እንደምንጠብቅ እንረሳለን:: ያልበሰለ ምግብ ለጤና አይበጅም:: ጥሬ በልቶ ለመታመም ችኩልነት ይዋጋናል:: የእኛንና የበሰለውን ማዕዳችንን ሲመጣ እያየነው ጥለነው እንሄዳለን:: ትዕግሥት የማይጠይቅ የኑሮ አቋም ግን የትም እንደሌለ መሄድ (እግር) ያስተምረናል:: «እዚያም ቤት እሳት አለ» እንዲሉ:: ተናጋሪው እስኪጨርስ መታገሥ እያቃተን ራሳችንን የምናስገምትበት፣ ባላለቀ ነገር ውሳኔአችንን የምናሳውቅበት ጊዜ ጥቂት አይደለም:: ብናስጨርስ ምን ጉዳት አለው? ወሬው እስኪያልቅ ምን ዓይነት ጥፋት በእኛ ላይ ይመጣል? ዝም ብንል ችግር የሚመጣ ስለሚመስለን ችኩልነት ያመጣብንን የፍርሃት ዱላ እንሰነዝራለን:: አንገት ትተን እንደ ጴጥሮስ የጆሮ ቀንበጥ እንበጥሳለን:: ብዙ ጊዜ ጌታ የበጠስነውን ባይቀጥል ኖሮ እነዚያ የሮማ ወታደሮች በገደሉን ነበር (ማቴ. 26:47-56)::

ዓለም በጊዜ መለኪያ እየተጓዘች ነው:: ስለዚህ ባለመታገሣችን ምን እናተርፋለን? ሰዎች እንኳን የፎከሩት የወረወሩትም ልጥ ሲሆን (ወደ ራሳቸው ሲመለስ) አይተናል::



www.ethiopinorthodox.org



ትዕግሥት ስናጣ ለእርምጃ እንቸኩላለን:: የገዛ ልፋታችን እንኳ ሳያሳዝነን በዓመት የገነባነውን በዕለት እናፈርሳለን:: ወታደር ጨክኖ በመዋጋት ብቻ ሳይሆን ስልት በመጠየቅ ያሸንፋል:: ትዕግሥትም የድል ምሥጢር ነው:: ገበሬ በመጠበቅ ፍሬን ይሰበስባል:: ትዕግሥት አዝመራን በመከር የሚለውጥ ኃይል ነው::

ትዕግሥት በማጣት የተለየናቸውን እነዚያን ሰዎች እናስብ:: ያን ጊዜ ትክክለኞች እኛ ነበርን:: ዛሬ ላይ ቆመን ስናስብ ግን ራሳችንን እንወቅሳለን:: ትዕግሥት ስናጣ ወዳጅ ብቻ ሳይሆን የገዛ ኅሊናችንን ምስክርነትም እናጣለን:: ከሰዎች ጋር የሚለየን የሰዎቹ ስህተት ብቻ ሳይሆን የእኛም ድል ያልተነሣ ባሕርያችን ነው:: ራሳችን እንኳ የማንወደው መጥፎ ባሕርይ አለን:: ባሕርያችን ምርጫችን አይደለም:: ግን ለመተው ፍላጎቱ ብቻ ኖሮን ኃይል የለንም:: እነዚያም ሰዎች ለመተው የሚፈልጉት ግን ለመተው ኃይል ያጡበት ባሕርያቸው አስቀይሞናልና ሰው ናቸው ብለን ልንታገሣቸው ይገባናል::

ቊጣ ቤትን ያፈርሳል:: ቊጣ አንደበትን ያረክሳል:: ሰው ያሰበውን ይናገራል:: በቊጣ ግን ያላሰበውን ይናገራል:: ሰው ያሰበውን መናገር ብቻ ሳይሆን የተናገረውንም ያስባል:: በድንገተኛ ስሜት በቊጣ የሚናገረውን ነገር እንደ ገና ማሰብና ማራመድ የሚጀምርበት ጊዜ ብዙ ነው:: ውስጣችን በቂ ዝግጅት ሳያደርግ «እገሌን አልወደውም» ብለን ስንናገር ቀጥለን ያንን ሰው ስለ መጥላት ማሰብ እንጀምራለን:: ቊጣ እውቀትን ያጠፋል:: ክብርን ያስገፍፋል:: ሰዎች እንዲወዱን ሳይሆን በጥንቃቄ እንዲቀርቡን ስለሚያደርጋቸው የአራዊት ወገን ያደርገናል:: ቊጣ ረጅሙን የራእይ ጉዞ ያደናቅፋል:: ካልተነሣንበትና ካላሰብነው ነገር ላይም ያደርሰናል:: ከንቱ ዋጋ ያስከፍለናል:: ቊጠኛ ሰው በቀን ብዙ ጊዜ ያብዳል:: ቊጣው ይለመድና እንደ ዘፈን ይቆጠራል:: ጠባዩ ነው ስለሚባል በእውነተኛ ነገርም ቢቆጣ እንኳ ሰሚ ያጣል:: ቊጣ የተፈጥሮ ቀላልነትን ያመለክታል:: የውስጥ ጥንካሬ መላላትን ይናገራል:: ከውጣ ውረዱ የተነሣ እጅ መስጠትን ያመለክታል:: ይህ ብቻ አይደለም ፍርሃትም ቊጣን ይወልዳል:: ቢጠይቁን የምንመልሰው፣ ቢጠሩን የምንሰጠው፣ ቢወዱን የምንናገረው የሌለን መስሎ ሲሰማን በቊጣ እናርቃለን:: ቊጣ ጉዳዩ የሚፈጸመው በኃይል ነው ከሚል የተሳሳተ አስተሳሰብም ይመነጫል:: አንድ ፈላስፋ:- «ድምፅን ከፍ አድርጎ በማስጮህ ቤት የሚሠራ ቢሆን፤ አህያ በአንድ ጊዜ ጨኸቱ ሁለት ቤት በሠራ ነበር» ብሏል::

ቁጣ ስድብንና ሐሜትን ይወልዳል፡፡ ቁጣ ካልተገታ በመግደል ይደመደማል፡፡ ሰዎችን በፍቅር እንጂ በቁጣ ልናስተምራቸው አንችልም፡፡ ቁጠኛ ሰው ከነፕሮቶኮሉ ያበደ ሰው ነው፡፡ አገር የሚያላምደን፣ በመንገድ ስንቅ የሚሆነን ትዕግሥት ብቻ ነው፡፡ ቁጣ ካላሰብነው ያደርሰናል፡፡ ዛሬ በውስጣችን ቀረኝ የምንለው ነገር ሁሉ በትዕግሥት ያተረፍነው ብቻ ነው፡፡ በቁጣ ያገኘነው ነገር ሁሉ እንዳላገኘነው የሚቆጠር ነው፡፡ ትዕግሥት ለጊዜው መራራ ቢሆን በመጨረሻ ግን ጣፋጭ ነው፡፡ ከሁሉ በላይ ኀሊናን ማትረፊያ ነው፡፡ አንድ አባት፡- «በሕይወት እልፍኝ የሚገኝ የትዕግሥት ምሥጢር ብቻ ነው» ብለዋል፡፡

በዓለም ላይ ምንም አዲስ ነገር የለም፡፡ ሰውም ታጥቦ የማይጠራ ነው፡፡ ቁጣ ግን ይህን ካለማወቅ የሚመነጭ ነው፡፡ እንኳን ሌላውን ራሳችንንም መታገሥ ያስፈልገናል፡፡ ቁጣ ሀብትን ያጠፋል፡፡ ጸጋን ያስነጥቃል፡፡ ተወዳጅነትን ያሳጣል፡፡ ትዕግሥት ግን አገርን ያስወርሳል፡፡ የነገሥታት አማካሪ ያደርጋል፡፡ የተለዩንን ሰዎች እንደገና የእኛ ያደርጋቸዋል፡፡ መልክን ያሳምራል፡፡ ውበትን ያፈካል፡፡ ምሥጢር ጠባቂ ያደርጋል፡፡ ደስታን ያበዛል፡፡

ቁጣ ግን የተፈጥሮን ድንጋጌ ያስፈርሳል፡፡ ሰው ሁሉ የማይረባ ነው የሚል ውሳኔ ላይ ያደርሳል፡፡ ከሰው ጋር የመኖርን የተፈጥሮ ድንጋጌ ጥሶ ከሰው መለየትን ይመርጣል፡፡ ነገር ግን ችግሩ ያለው ከሰው ሳይሆን ድል ካልተነሣው ቁጣችን ላይ ነው፡፡

በአንድ ገዳም ውስጥ በጣም ቁጠኛ የሆነ መነኩሴ ነበር፡፡ ይህ መነኩሴ ዘወትር ከባልንጀሮቹ ጋር አይስማማም ነበር፡፡ ቁጣውም ወደ ስድብ እስኪያደርሰው ይታገለው ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ተበሳጭቶ፡- «ከሰው ተለይቼ በበረሃ ብኖር የሚያሳዝነኝን ሰው ባላይና ባልሰማ ከበስጭት እድናለሁ» ብሎ ወደ በረሃ ተጓዘ፡፡ በአንዲት ዋሻ ውስጥም ገብቶ ኑሮውን መሠረተ፡፡ ከዋሻው አጠገብ ንጹሕ ምንጭ ነበርና አንድ ማሰሮ ውሃ ቀድቶ አስቀመጠ፡፡ ነገር ግን መሬቱ ያልተስተካከለ ነበርና ማሰሮው ተፈንግሎ ውሃው ፈሰሰ፡፡ ለሁለተኛው ጊዜ ማሰሮውን ውሃ ሞልቶ ቢያስቀምጥ እንደ ገና ተፈነገለበት፡፡ በዚህ ጊዜ በቁጣ ነዶ ማጉረምረም ጀመረ፡፡ ለሦስተኛ ጊዜ ውሃውን ሲሞላና ሲፈስበት ቁጣው እንደ እሳት ገሞራ ፈነዳበት፡፡ ሞልቶ ፈሰሰ፡፡ ማሰሮውንም አንሥቶ እስኪደቅ ሰባበረው፡፡



ቁጣውም ከበረደ በኋላ ቁጭ ብሎ ማሰብ ጀመረ፡፡ «በስጭትን ጠልቼ ከሰው ተለየሁ፡፡ ነገር ግን ብቻዬንም ብሆን ከመናደድና ከመቆጣት አልዳንኩኝም፡፡ የሚያስቆጣኝ ነገር የራሴ እንጂ የባልንጀሮቼ ነገር አይደለም፡፡ ሰው ቁጣውን ለማሸነፍ በሚገጥመው ነገር ሁሉ ታጋሽ ለመሆን የሚያስፈልገው ረድኤተ እግዚአብሔርን መለመን ነው» ብሎ ባደረገው ነገር በመፀፀት ንስሐ ከገባ በኋላ ወደ ባልንጀሮቹ ተመለሰ፡፡ ከዚያ በኋላ በትዕግሥትና በመቻል ከባልንጀሮቹ የበለጠ ሆኖ ኖረ፡፡

አዎ ትዕግሥትን ገንዘብ ማድረግ እንጂ በረሃ መግባት፣ በርን ዘግቶ መቀመጥ መልስ አይሆንም፡፡ ሰዎች እንዲለወጡ ከመፈለጋችን በፊት እኛ መለወጣችን ወሳኝ ነው፡፡ ሰዎች ከክፋ ጠባያቸው፣ እኛም ከቁጣችን መለወጥ ያስፈልገናል፡፡ የቁጣ መንፈስ ካደረብን በምክንያት ብቻ ሳይሆን ያለ ምክንያትም ራሳችንን አውከን ሌሎችንም እናውካለን፡፡ ራሳችንን ለማየት ጊዜና ማስተዋል እናጣለን፡፡ ስህተት ፈላጊና ተመጻዳቂ እንሆናለን፡፡ ሰዎች ሁሉ ሲርዱልንና ሲንቀጠቀጡልን የጀግንነት መንፈስ እየተቆራኘን ግብዝ ደግሞም ትዕቢተኛ እንሆናለን፡፡ በመጨረሻ ላይ እንኳን አብሮን የሚኖር በአንድ ጎዳና ላይም አብሮን የሚሄድ ሰው እናጣለን፡፡ የገዛ ልጆቻችንም ለውድቀታቸው ሁሉ እኛን ምክንያት አድርገው ይጠቅሳሉ፡፡ በታላላቅ ስብሰባዎች ያለፉበትን ሕይወት ሲናገሩ የእኛን ቁጣ ሳይጠቅሱት አያልፉም፡፡ ከሰው ጋር ለመገናኘት ቁጣችን ተጽእኖ ስለሚያሳድርባቸው ሲረግሙን ይኖራሉ፡፡ የእኛ ቁጣ ራሳቸውን እንዲጠራጠሩና ሥራቸውን በመተማመን እንዳይሠሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለዚህ ቁጠኛ ስንሆን የገዛ ልጆቻችንንም ለማጣት ወስነናል ማለት ነው፡፡

በመከራችን መጽናናትን ከመለመን ትዕግሥትን መለመን ይሻላል፡፡ ምክንያቱም በዚህኛው መከራ ብንጽናና ሌላ መከራ ደግሞ ይመጣል፡፡ ትዕግሥትን ብንለምን ግን በሁሉ እንጸናለን፡፡ ሥራችንን ለመፈጸም፣ ጅምራችንን ታላቅ ለማድረግ፣ ፈተናችንን ለማለፍ፣ መከራችንን ድል ለመንሣት፣ እኛን ከሚመስለው ሰው ጋር ለመኖር ትዕግሥት ያስፈልገናል፡፡ ለትዕግሥታችን ግን ረድኤተ እግዚአብሔርን መለመን ያስፈልገናል፡፡ ክረምትን በበጋ፣ ሌሊትን በቀን፣ ውርደትን በሹመት የሚለውጥ ጌታ ደካማነታችንን በብርታት ይለውጣል፡፡ ስለዚህ በሁሉ ትዕግሥትን እንለምን፡፡



www.ethiopinorthodox.org

## እናስተውል

«አንድ ሰው ነበር:: ሚስቱም ባልዋ የጠላት፣ ሰነፍና ክፉም ነበረች:: እርሱም ወደ ሌላይቱ መሄድ ጀመረ:: ሚስቱንም አስቀናት:: እርሷም ተነሥታ ወደ ባለመድኀኒት ሔደችና ባሌ ጠልቶኛል እንዲወደኝ መድኀኒት ዛሬ አድርግልኝ አለችው:: እርሱም እሺ፣ በጀ አላት:: ነገር ግን ከአንበሳ ግንባር፣ ሦስት ጠጉር ነቅለሽ አምጭልኝ:: ለዚሁ መድኀኒት ይፈለጋሉና አላት:: እሷም ኼደችና አሰበች:: ወደ አንበሳ እቀርብ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል? አይበላኝምን? አለች:: አንድ በግ ይዛ ወደ በረሀ ኼደች:: አንበሳም ወጥቶ ይበላት ዘንድ ወደ እርሷ ሮጠ:: እርሷም በጉን ለእርሱ ሰጥታ ሸሸች:: አንበሳውም የሚበላውን አግኝቶ መከተሉን ተዋት:: በማግስቱም እንዲሁ አደረገች:: በዚሁ ሥራ ብዙ ቀን ጸንታ ቈየች፤ የባልዋ ቅናት ይዟታልና:: አንበሳው ግን ይህች ሴት ምግብን እንድታመጣለት ባየ ጊዜ አልጠላትም:: ከዚያ ወዲያ ወደዳት እንጂ:: እርስዋ ከበግ ጋር ስትመጣ ጅራቱን በማወዛወዝ በደስታ ይቀበላታል:: እንደ ውሻ ሰላምታ እየሰጠም ከእሷ ጋር ይጫወታል:: ያን ጊዜ ከግንባሩ ሦስት ጠጉር ነቅላ ወደ ባለመድኀኒቱ መጣችና «ለመድኀኒት የምትፈልገውን እነሆ አመጣሁልህ» አለችው:: እርሱም፣ «ጠጉሮቹን መንቀል እንዴት ተቻለሽ?» አላት:: እርሷም የሆነውን ሁሉ ነገረችው:: «ለአንበሳው እንዳደረግሽ ሒደሽ ለባልሽ አድርጊለት፤ ባልሽም ይወድሻል፤ ከአንበሳው ይልቅ ባልሽ እንዲከፋ ትጠራጠሪያለሽን? ምግብን በመስጠት የአንበሳን ፍቅር እንዳገኘሽ እንዲሁም የባልሽን ፍቅር ታገኛለሽ» አላት:: እርሷም ኺዳ እንደ ባለመድኀኒቱ ምክር ታደርግ ዘንድ በሁሉም ነገር ታግሣ ባልዋን ደስ ታሰኝ ዘንድ ጀመረች:: ከጥቂት ቀኖች በኋላም ያ ሰው በልቡ አሰበ:: «ከሚስቴ ይልቅ ሌሎቹን ሴቶች እንደምን እወዳለሁ? ከእነርሱ ይልቅ እርሷ የምታምርና የምትሻል ስትሆን» ብሎ ወደ እርሷ ተመለሰ:: እጅግም ወደዳት /ሐተታ ወልደ ሕይወት አለቃ ያሬድ ፈንታ ከተረጎሙት የተወሰደ ያልታተመ/::

ባለንበት ዘመን ሰዎች አራዊትን ለማልመድ ብዙ ሲጥሩ እናያለን:: ከሰው ጋር ለመኖር ግን አቃተን እያሉ ከሰው የሚሸሹበት ዘመን ሆኗል:: እግዚአብሔር ሁሉን ከወገኑ ጋር ፈጥሯል:: የሰው ወገን ሰው ነውና መዋደድ ይገባናል:: እግዚአብሔር ከአስቸጋሪ ሰዎች ጋር እኛን በማስቀመጥም ትዕግሥታችንን ያንጻል::



አንድ ሰው ከመዝሙረ ዳዊት 5 ምዕራፍ ከመጽሐፈ ምሳሌ 1 ምዕራፍ በየዕለቱ በማጥናት ወር ላይ ሁለቱንም ክፍሎች ይጨርሳሉ:: እኚህ ሰው «መዝሙረ ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር ላለኝ ግንኙነት፣ መጽሐፈ ምሳሌ ከሰው ጋር ላለኝ ግንኙነት መጠበቂያ ነው» ብለዋል:: የምንኖረው ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር በመሆኑ ትዕግሥት ያስፈልገናል:: የሰው ጠባይ እየከበደን ከመጣ ጉልበታችን ተመትቷል ማለት ነው:: በዛሬው ዘመን ሰው የሰውን ጠባይ መሸከም አልቻለም። ስለዚህ በቶሎ እንጀራውን፣ ትዳሩንና ንብረቱን ያፈርሳል:: ገና ካሁኑ በሰው ጠባይ እንዲህ ተማርረን በዕድሜያችን መጨረሻ ላይ እንዴት ያለን ሰዎች ልንሆን ነው? ሁሉም ሰው የብጉንጅ ቍስል እንደ ያዘው አትንኩኝ ባይ ሆኗል:: ፍቅራችን አልፎ በመጠባበቅ ነው የምንኖረው:: አፋፍ ላይ የቆመው ግንኙነታችን ትንሽ ቍጣና ወቀሳ ከተሰነዘረበት በቶሎ የሚወድቅ ነው:: በእውነት ትልቅ ጸጋ የሰውን ጠባይ መሸከም መቻል ነው::

ሐዋርያው ጳውሎስ የሮሜን መልእክት ሲጽፍ የክርስትናን ፍሬ ገልጿል:: የክርስትናው ፍሬ ግላዊ ቅድስናን (ምዕ.12.)፣ ታማኝ ዜግነትን (ምዕ.13.)፣ ከሌሎች ጋር ያለንን ግንኙነት (ምዕ.14.) የሚመለከት ነው:: የበረታው የደከመውን እንዳይንቅ፣ የደከመውም በበረታው እንዳይፈርድ ሲገልጽ ማንም የማንም ዕዳ ሳይሆን ሁላችንም የእግዚአብሔር ዕዳ መሆናችንን ይገልጻል:: በክርስትናው መበርታታችን የሚለካው ገፍተን በመሄዳችን ሳይሆን ሌሎችን ለመሸከም ትከሻን በማስፋታችን ነው (ሮሜ 14:13)::

ፊት የምናነሣው ሃምሳ ኪሎ አሁን ካቃተን ሃምሳ ኪሎው ሳይሆን እኛ ተለውጠናል ማለት ነው:: የእኛ አቅም ደክሟል:: እንዲሁም የወንድማችን ጠባይ ዛሬ ከከበደን የእርሱ መባስ ሳይሆን የኛ መድከም ምልክት ነው:: አንዲት ሴት ሰባኪውን:- «እኔ ብቆጣም ከተናገርኩ በኋላ ሆዴ ባዶ ነው» አለችው:: ሰባኪው ግን መልሶ:- «ጥይትም ከተተኮሰ በኋላ ውስጡ (ቀለሃው) ባዶ ነው:: ግን ሰው ገድሏል» አላት ይባላል:: በቍጣ የምንናገራቸው ነገሮች ሰዎችን ሊሰብሩ ይችላሉ:: ቍጣችን ቢበርድ እንኳ በቍጣ ተነሣሥተን ያወራነውን ሐሜት ማጽዳት አንችልም:: ይልቁንም የእግዚአብሔርን ፍቅርና ትዕግሥት የምናስተላልፍ ንጹሕ መስተዋት መሆን አለብን:: የእግዚአብሔርን ባሕርያት እንዳናስተላልፍ የሚጋርዱንን ቍጣ፣ ቂምና በቀል ማስወገድ ይገባናል:: ቍጣ የምናውቀውን የሚያስረሳ እውቀትን የሚሰርዝ ነው:: በቃላችን የምናውቀውን የወዳጃችንን ስልክ ቍጥር በእርሱ ተበሳጭተን ልንደውል ስንል የሚጠፋን ጊዜ በዚያውም እንደ ጠፋን



www.ethiopinorthodox.org

የሚቀርበት ጊዜ ጥቂት አይደለም። ቁጣ መርሳትን ያስከትላል። ይህ ብቻ አይደለም ጤንነታችንን ይጋፋል። ቁጣ ይቅርታን ይዋጋል። ብዙ ጊዜ ለይቅርታ የምንቸገረው የሰዎቹ በደል ከበደል በላይ ሆኖ ሳይሆን በቁጣ ለተናገርነው አፍራሽ ቃል ታማኝ ለመሆን ብለንም ነው።

ትዕግሥት የእግዚአብሔር ባሕርይ ደግሞም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በመሆኑ ከሰው ችሎታ በላይ ነው። እንደ ሌሎቹ ጸጋዎች በቶሎ የምናገኘው ሳይሆን ከብዙ ፈተናና ትግል በኋላ የሚመጣ ነው። አንድ ሰው፦ «ትዕግሥት የሚጀምረው ቻልኩኝ ቻልኩኝ አሁንስ በቃኝ ስንል ነው» ብሏል። ትዕግሥት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነውና የሰው ችሎታ ካለቀ በኋላ የሚጀመር ነው። በሕይወታችን የትዕግሥትን ፍሬ ማየት እንድንችል ወደ ትዕግሥት አምላክ መጸለይ አለብን።

## ጸሎት

የግዙፍ ከዋክብት ባለቤት አንተ እግዚአብሔር የራሴ እንኳን ብርሃን የሌለኝን እኔን እንደምን ወደድከኝ? የፀኑ ተራሮች ጌታ ፍንግልግሉን እኔን እንዴት አፈቀርከኝ? በትልልቅ ፍጥረታትህ ፊት እኔን ቁጫጩን እንደምን ፈለግሽኝ? ሳልመችህ የተመቸሽኝን አከብርሃለሁ። ስለ መረጥኩህ ሳይሆን ስለ መረጥከኝ፣ ስለ ወደድኩህ ሳይሆን ስለ ወደድነኝ፣ ስለማልተውህ ሳይሆን ስለማትከዳኝ ደስ እያለኝ አመሰግንሃለሁ። ዘላለም አንተ ነህ፣ ችግሬ አይደለምና ዘላለም ተመስገን። መሬት ለተሰነጠቀበት፣ መርከብ ለተሰበረበት፣ ሸለቆ ለተንሸራተተበት እጅህን የምትዘረጋ ጌታ፣ ዓመት ሙሉ የካብኩትን በደቂቃ ቁጣ የማፈርሰውን እኔን ተዋሰኝ። ልጅ ያጠፋውን ወላጅ ያስተካክላል። የሰው ዕቃ ሲሰብር ወላጅ ይከፍላል። እኔም ያንተ ሕጻን ያጠፋሁትን አስተካክልልኝ፣ በቁጣ ያራቅኋቸውን ወዳጆቼን ሽማግሌ ሆነህ አንተ አስታርቀኝ። ጌታ ሆይ፣ ላንተ ክብር ብቻ ሳይሆን ለእኔም ጤና ከቁጣዬ አድነኝ። ስለ ተቆጣሁ የሆነ፣ ስለታገሥሁ የቀረ የለም። እባክህ ክፉውን በክፉ እንዳልመልስ ባሪያህን ጠብቀኝ። ትጋት ከሚመስል መክነፍ፣ ትዕግሥት ከሚመስል መስነፍ አንተ አድነኝ። በዘላለማዊው ጥበብህ አሜን።



www.ethiopinorthodox.org



# ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ
# አንሸበር

ማዕበል ያለው በወደብ ላይ ሳይሆን በመሐል ባሕር ላይ ነው። ሕይወትም የምታታግለው በመነሻው ሳይሆን በመካከል ላይ ነው። ሕይወት በማዕበል የተሞላች ናት። አንዱን ስናልፍ ሌላው ይተካል። ከአንደኛው ቊስለት ሳናገግም የሌላኛው ቊስል ይጠናብናል። ማዕበሉ የሚነሣው ከተወሰነ ስፍራ አይደለም። ማዕበሉ ብዙ መንገዶች አሉት። ትልቁና ከባዱ ማዕበል ግን የሚነሣው ከራሳችን ነው። ምኞታችን የሚረክስብን፣ አሳባችን በእሾህ አሜኬላ የሚዋጥብን፣ እኔ ማን ነኝ እስክንል አቅጣጫው የሚጠፋብን ጊዜ ጥቂት አይደለም። የባለጠግነት ምኞታችን፣ የሥጋ ፈቃዳችን፣ በሰዎች ላይ ከዚህ በፊት የፈረድንበት ነውር ሁሉ በውስጣችን የሚገለብጥ ማዕበል ሆኖ ይነሣብናል። የጨበጥነውን እየጠላን የሌለንን በብርቱ መናፈቅ፣ እወዳችኋለሁ ብለን ቃል የገባንላቸውን መውደድ አለመቻል፣ አቅፈናቸው እየተቀመጥን ውስጣችን በሺህ ኪሎ ሜትሮች እንደ ራቃቸው ማሰብ፣ እንዳይገድሉን የምንቀልባቸውን ሰዎች ዘወትር ማየትና የጋራ ነውራችንን ለመሸፈን ፍቅር በሚመስል መጠባበቅ አብሮ መኖር፣ ምን ላድርግ? ሳይሆን ምን ያደርጉልኛል? የሚለው ስሜት በውስጣችን ዘወትር ከሚነሡ ማዕበሎች አንዱ ነው።

ይቅር ያልነው ን በደል እንደ ገና ማስታወስ፣ የጀመርነውን ተግባር መንገድ ላይ ጥለን ለመመለስ መፈለግ፣ ይህ የሆነው እነ እገሌ እንዲህ ስላደረጉ ነው የሚል የክስ ኑሮ ከማዕበሎቻችን ውስጥ ቀዳሚነትን የሚይዙ ናቸው። ብዙ ጊዜ በውስጣችን የሚነሡት ማዕበሎች በራሳችን ጥረት የማናስወግዳቸው፣ ሌሎችም ሊረዱን የማይችሉት እግዚአብሔር ብቻ ፀጥ የሚያደርጋቸው ናቸው።

ራሳችንን በቅጡ ስናየው ምኞትም ችግርም የማይስማማን፣ ያ ሁሉ ደስታችንና ምስክርነታችን በጥቂት ነገሮች አለመሟላት የሚዳፈንብን፣ ስሜት እንጂ መሠረት ያለው ሕይወት የሌለን፣ እንደ ቅጠል እሳት ተውለብልበን የምናልቅ፣ ፍም የሌለን ጊዜያዊ ወገግታ፣ ሙቀት የማንሰጥ የአሁን ብቻ ብልጭታ መሆናችንን ስናስብ ከእኛ ዘንድ ያለው ድካም ብቻ መሆኑ ይገባናል። ይህ ብቻ አይደለም የቅድሙ መጽናናታችንም የእኛ ሳይሆን የጸጋው ስፍር መሆኑም ይገባናል። በድንገት አገራችንን እንረግማለን። በድንገት የትዳር ምርጫችንን እንኰንናለን፣ በድንገት የሚመሩን መሪዎች

ካልሞቱ ሰላም የለኝም እንላለን:: ማዕበል በምን ሰዓት እንደሚመጣ አይታወቅም፤ የሕይወትም ወጀብ ባልታሰበ ሰዓት ያደፈርሰናል:: ሰላም ነው ስንል ሁከት ይሆናል::

ሰላም የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ፍሬ ነው:: ነገር ግን ለደቂቃ ላይለየን የተሰጠን አይደለም:: በጽኑ ተስፋ የተሰጠን መዳናችን ብቻ ነው:: ስለዚህ ሰላማችን ሊደፈርስ፣ ፍቅራችን ሊቀዘቅዝ፣ በረከታችን ሊጎድል ይችላል:: ይህ ነገር በዘላለማዊነት የተሰጠን ከመሰለን ሲሄድብን መደናገጥ ይገጥመናል:: ዘላለማዊ ጸጋችን ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ሌላው ነገር ሁሉ በየዕለቱ በቃሉና በጸሎት የምንሞላው ነው:: ደስታችንን ያዘኑትን ካላጽናናንበት እግዚአብሔርን ካላከበርንበት ይሄዳል:: ታላቅ ፀጥታ፣ ፍጹም የሆነ ጭርታ፣ ስፍራ ሁሉ ከድምፅ የሚፀዳበት ጊዜ ጥቂት አይደለም:: እግዚአብሔር ሊፈትነን ራሱን በውስጣችን ደብቆ ለጥቂት ደቂቃዎች ለራሳችን ይተወናል:: ያን ጊዜ ረጅም የሚመስለው ሰማይ ያጥርብናል:: ሰፊ የምትመስለው ምድር ትጠበናለች:: ጉበዝ ነኝ የሚለው ፉከራችን ሁሉ ይጠፋል:: እንኳን ክርስቲያንነትን ወንድነታችንንም እናጣዋለን:: ሁሉም ነገር አለን ግን የሌለን ያህል ይሰማናል:: ምንም አልጐደለብንም ግን ውስጣችን እንደ ባዶ አዳራሽ እንደ ሽለቆ ይጮህብናል:: ከዚህ የባዶነት ስሜታችን ጋር ለግማሽ ቀን መቆየት ከባድ ነው:: ሰላማችን የጥንቃቄአችን ውጤት፣ በሰው ነገር ውስጥ ያለ መግባታችን ፍሬ ሳይሆን የእርሱ ስጦታ መሆኑን የምንገነዘበው ያን ጊዜ ነው::

ፍጹም የመጣል (የውዳቂነት) ስሜት የሚሰማን፣ በሰማይና በምድር የተተውን የሚመስለን ሰዓት፣ ትዳራችን የእኛ እስከማይመስለን ብቻዬን ነኝ የምንልበት ጊዜ፣ ቀትሩ ከእኩለ ሌሊት ይልቅ ጨለማ ሆኖ የሚታየን ቀን አለ:: ሰውን ለመቆም እህል ያፀናዋል፣ ለመኖር ግን የእግዚአብሔር ህልውና ያፀናዋል:: ብርቱ መንፈስ ባዶ ሆድን ተሸክሞ ይጓዛል:: የጠገበ ሆድ ግን ባዶ መንፈስን መሸከም ስለማይችል ይወድቃል:: ያለ እግዚአብሔር የእኛ ሕይወት ኢምንት፣ ለመኖርም በቂ ምክንያት የሌለው፣ ጉዞውም ግብ ያልተወሰነለት፣ ከርታታና ጨለምተኛ መሆኑ የሚገባን እግዚአብሔር ለራሳችን በሚተወን ጊዜአቶች ነው:: የእግዚአብሔር ሰላም ሲደግፈን ሰማይ ለእኛ የውበት ሰሌዳችን ነው:: ያ ሰላም ሲሄድ ግን እንደ ሰማይ አስፈሪ ነገር የለም::

ጨለማውን በብርሃን፣ ክረምቱን በበጋ፣ ሀዘኑን በደስታ፣ መከፋቱን በሳቅ፣ ድካሙን በብርታት፣ ጭንቀቱን በመጽናናት የሚለውጥ ጌታ መንፈሱን ሲልክ የደረቁ አጥንቶቻችን መለምለም



የሄደች ትንፋሻችን መመለስ፣ የተቋረጠው ድምፅ መሰማት ይጀምራል (ሕዝ. 37:1-14):: የመቃብር መንደር ወደ ሕያዋን መኖሪያነት ይለወጣል:: ቀድም የከበደን ተፈጥሮ አሁን የእግዚአብሔርን አሻራ ያስነብበናል:: ሁሉም ነገር ገናና የማይጠገብ፣ ሕይወትና ዕድሏ ያላባራ መሆኑ ይገለጽልናል::

አዎ ትዕግሥት ስንል አለመቆጣት ነው ማለት ብቻ አይደለም:: ይህ የትዕግሥት ትንሽ ደረጃ ነው:: ከፍ ያለው ደረጃ ያልተሸበረ መንፈስ ነው:: በእንዲህ ያለ የባዶነትና የውስጥ ማዕበል ዘመን ትዕግሥት ወሳኝ ነው:: ይህም የሕይወት አንዱ ክፍል ነው:: ማዕበሉንና ባዶነቱን ይህም ሕይወት ነው ማለትን መለማመድና ንጋትን መጠባበቅ ትዕግሥት ይባላል::

ኤልያስ ከታላቅ የድፍረት አገልግሎት በኋላ ትልቅ ፍርሃት ገጥሞታል:: ያየው የእግዚአብሔር እጅ ያላየውን የኤልዛቤልን ዛቻ ሊያሸንፍለት አልቻለም:: እሳት የወረደለት ነቢይ ዛቻ ፈርቶ ሸሸ:: ብዙ ያየ በጥቂቱ እጅ ሰጠ:: ይህ በሕይወት ላይ ተመሳሳይ ገጠመኝ ነው:: ከብዙ ችግር ወጥተው ሀብትና ንብረትን ያበጁ፣ የሚበላ የሚጠጣ የተረፋቸው ለትንሽ ሳቃቸው ብዙ ልቅሶ ይከፍላሉ:: ሐሰተኛ ፈገግታ እውነተኛ ልቅሶ አላቸው:: ይህ ለምን ሆነ? ስንል የደስታ ምሥጢር እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን እንዲያውቁ ይህ ሆኗል:: አዎ ሁሉን ያየ በቶሎ አይደነግጥም:: በድፍረት የምንሻገር ሰዎች እንድንሆን እግዚአብሔር ሁሉን ያሳየናል:: በዓለም ላይ የማንታገሥበት የኑሮ ደረጃ፣ የሕይወት አቋም እንደሌለ ሊገልጥልን በዚህ ሁሉ ውስጥ ያሳልፈናል:: ምድራዊው ኑሮአችን እንዳይታወክ እንፈልጋለን:: ጌታ በምድራዊው ሁከት ዘላለማዊውን ሁከት እያሳየ በወንጌል እንድናምን ይጎተጉተናል:: በምድራዊ መከራ ምሳሌ ሰማያዊውን መከራ እያስገነዘበ ከኲነኔ እንድናመልጥ ይተጋልናል:: ሰው ግን ኃላፊውን መከራ ሲሰቀቅ ዘላለማዊው መከራ ግን አያስፈራውም:: የመከራውን ኪሣራ እንጂ ትምህርቱን አላወቀም:: ይሸበራል እንጂ አይማርም:: ይታወካል እንጂ ጌታዬ ምን ላድርግ? አይልም:: ከማዕበሉ ይልቅ የእግዚአብሔርን ድምፅ አለመለየትና አለመስማት ትልቅ ማዕበል ነው:: በትዕግሥት ስንሆን ይህን ድምፅ መስማት እንጀምራለን:: ድምፁ ዘላለማዊ ነው:: መከራው ግን ጊዜያዊ ነው:: አዎ ያልተሸበረ መንፈስ ያስፈልገናል::

በሕይወታችን ካለብን ሸብር ውስጥ ላለመጠላት፣ ላለመገሰጽና ላለመጋለጥ ያለን ጭንቅ ጉልህ ነው:: ሰዎች እኛን ወድደው እግዚአብሔርን እንዲወዱ እንጂ እግዚአብሔርን ወደው እኛን እንዲወዱ ፈቃደኛ አይደለንም:: በፍቅር ስም ራሳችንን ትንንሽ



www.ethiopinorthodox.org

ጣኦት አድርገን ቆመናል:: ስለ ሰዎቹ ያለንን ፍቅር አበክረን ተናግረን ፍቅራቸውን ቀጥሎ እንዲያሰሙን፣ የተናገሮ አናጋሪ ሥራ እንሠራለን:: ያለ እነርሱ ሕይወታችን ምንም እንደሆነ እንናገርና መልስ ፍለጋ መቅረፀ ድምፁን ወደ ሰውየው እንደሚቀስር ጋዜጠኛ «ያለ እናንተ መኖር አልችልም» የሚል ድምፅ እንጠባበቃለን:: በሁሉም ዘንድ ተወዳጅ ለመሆን፣ ሁሉንም ላለማስቀየም፣ ሁሉንም ለማስደሰት ጥረት እናደርጋለን:: ውጤቱ ግን ሁሉም የሌለን ሰዎች መሆን ነው:: ላለመጠላት ውስጣችን ይፈልጋል:: ዓለም ግን ሁለት እንጂ አንድ አይደለምና አሳባችን አይሟላም:: ዓለም ፍቅርና ጥላቻም ያለባት ውድማ ናት እንጂ እንደ ተለቀመው ስንዴ የጠራ ነገር ያለባት ሰማይ አይደለችም:: ለመወደድ ብለን የምናደርገው መልካም ነገር ሁሉ ሐሰተኛ ምግባር፣ ምግባርን መሸጥ በመሆኑ የበለጠ ርኩሰት ይሆንብናል:: መልካም ነገር አስፈላጊ ስለሆነ ብቻ መልካምን ማድረግ የቅድስና ፍሬ ነው:: የእግዚአብሔርን ክብር ብቻ እያየ መልካምን የሚያደርግ፣ ሰዎች ምን ተሰማቸው እያለ ፊት የማያይ፣ ከውሻነት ጠባይ የዳነ ነው:: «ምን አሉ?» ብሎ የማይጠይቅ፣ ሙገሳን ለመስማት ካለው ጥማት የተነሣ እንዴት ነበር አድራጎቴ? ብሎ የማይጠይቅ የሚሠራውን የሚያውቅ ነው:: ክፉ ቢሰማ ሊበሳጭ እንዴት ነው? አስተያየት ስጡኝ የሚል ደጋፊ ፈላጊ እንጂ የመለወጥ አሳብ ያለው አይደለም:: ለመወደድ የምናደርገው ጥረት መጠላትን እየወለደ፣ እርግጠኝነት የጎደለን ሰዎች መሆናችንን እያስመሰከረብን ይመጣል::

የመወደድ ስሜት አፍቅረን ለመፈቀር የምንሻበት ሳይሆን መደለያ ሰጥተን ንጹሑን ፍቅር የምንጠብቅበት ነው:: ፍቅር ግን የሚገኘው በፍቅር ነው:: ሰዎች ስንወዳቸው ይወዱናል:: እንዲወዱን ከፈለግን መቼም አይወዱንም:: ፍቅርም ሳያዳምጡ መውደድ መቻል ነው:: ፍቅር ዕቁብ ሳይሆን ፍቅር ስጦታ ነው:: መጠላትንም ለመቀበል መዘጋጀት ያስፈልገናል:: ለመረገምም ለመነቀፍም ዝግጁ መሆን ያስፈልገናል:: የምንኖረው እግዚአብሔር ስለ ወደደን እንጂ ሰዎች ስለ ወደዱን አይደለም:: የሕዝብ ፍቅር ሲናፍቀን የአንድ ሰው ፍቅር ሳናገኝ እንቀራለን:: ራሱን መውደድ ካቃተው ሰው እኛን እንዲወደን መፈለግ ተገቢ አይደለም:: የፍቅር ደስታው ሲሰጡት እንጂ ሲቀበሉት አይደለም:: ማለት ሲያፈቅሩ እንጂ ሲፈቀሩ አይደለም:: ልወደድ የሚል ስሜት ያደረባቸው ከንቱ አስተሳሰብ ያደረባቸውና የአእምሮ ድህነት ያለባቸው ሰዎች ናቸው:: ሰዎች ፍቅር ብቻ አይደለም ያላቸው:: ጥላቻም የእነርሱ ናት:: ስለዚህ ደስ ሲላቸው ይወዱናል፣ ደስ ሲላቸው ይጠሉናል:: እግዚአብሔር ግን ታምኖ የማይከዳ፣ ወዶ የማይጠላ ፍቅር ብቻ ነው:: አዎ ዙሪያውን ሳይሆን ሰማይን ብቻ ስንመለከት እንጽናናለን:: ዙሪያው ብዙ



www.ethiopinorthodox.org



ቪላዎች ፈርሰዋል፣ ብዙ ፎቆች ሰጥመዋል፣ ብዙ መሠረቶች ተናውጠዋል፣ ብዙ እሳቶች ጠፍተዋል፣ ብዙ ምንጮች ደርቀዋል:: ሰማይን ስንመለከት ግን እግዚአብሔር በሦስትነቱ፣ መላእክት በምስጋና ረድፋቸው ዛሬም አሉ:: የእግዚአብሔርን ፍቅር ብቻ ስናስብ ያልተሸበረ መንፈስን እናተርፋለን::

ላለመጠላት ብቻ አይደለም ላለመገሰጽም ፍርሃት አለብን:: ስህተታችን በሰዎች ፊት እንዳይነገር፣ የምንመኘው መልአክነት እንዳይጓደል ፍርሃት አለብን:: እውነተኛ ሰው ግን ስህተቱ ሲነገረው ያመሰግናል:: ለመለወጥም ይናፍቃል:: ከሌለው ጽድቅ ያለውን ኃጢአቱን ያምናል:: ያለ ይሉኝታ የሚገስጹን ሰዎች ካገኘን ዕድለኞች ነን:: እነዚህ ሰዎች አይገኙም:: ዛሬ በሕይወታችን ላይ የተለወጥንባቸው ነገሮችን ስናይ ያለ ይሉኝታ የተገሰጽንባቸው ስህተቶች ናቸው:: ብዙ ተግሳጾችን ብናገኝ በብዙ እንለወጥ ነበር:: የስህተት ተግባሩን ይዘን ስሑት የሚለውን ስም ለምን እንፈራለን? በብዙ ምስክሮች ፊት ስንገሰጽ ተነሥተን ማመስገንና የጸሎት እርዳታ መጠየቅ ትልቅ ድልን ያመጣልናል:: ባለንበት ዘመን ጽድቅን የሚሠራ አይደለም ኃጢአቱን የሚያምን ሰው እየጠፋ ነው:: እግዚአብሔር ግን ንስሐ በሚገቡና በደላቸውን በሚያምኑ ይደሰታል::

በስህተታችን ስንወቀስ አስቀድመን ይቅርታ መጠየቅ እንጂ መሸፋፈን ተገቢ አይደለም:: የተደበቀ በሽታ ለሞት እንደሚያደርስ የተሰወረ ኃጢአትም ይገድላል:: ዘወትር ራሳችንን በቃሉ መስተዋት ማየትና መመርመር ይገባናል:: ከትላንቱ ደረጃችን ምናልባት ዝቅ ሳንል አልቀረንም:: ስለዚህ በቃሉ ደረጃችንን ማስተካከል ይገባናል:: ወዳጆቻችንንና መምህሮቻችንን ስህተቴን ንገሩኝ ልንላቸው ይገባናል:: ለእኛ የማይታዩን ብዙ ጉድለቶች፣ እንደ ጽድቅ የያዝናቸው ብዙ ስህተቶች አሉብንና:: ያልተሸበረ መንፈስ ሲኖረን ማንነታችንን ስንሰማ ደስ ይለናል:: ለመታረምም እንዘጋጃለን::

የሰዎችን ነቀፋ ለመስማት በጣም ጉጉዎች ነን:: የምንገዛው መጽሐፍ እንኳ ራሳችንን የሚያንፅ ሳይሆን የሰዎችን ስህተት የሚያጋልጠውን ነው:: የሰማነውንና ያነበብነውን የሰዎች ጉድ ለማውራት በጣም እንቸኩላለን:: ራሳችንን በሚመለከት ግን ሰዎች እንኳን ክፉ እንዲናገሩን ክፉ ፊትም እንዲያሳዩን አንፈቅድም:: እንኳን እንዲጽፉብን እንዲያስቡብንም አንሻም:: ሰዎች በሐሜት እንኳ ሲያነሡን ጤንነታችን ይታወካል::

ስለ ሌሎች ክፉ አለማውራት የራስንም የሌላውንም ኅሊና ከማርከስ ይጠብቃል። ስለ ሌሎች ላለመናገር መጠንቀቅ እንችላለን። ሌሎች ስለ እኛ እንዳያወሩ ግን መጠንቀቅ አንችልም። ማማት እንጂ መታማት አስፈሪ አይደለም። እኛ ግን የሚያስፈራን ማማቱ ሳይሆን መታማቱ ነው። ሰዎች ስለ ሰዎች ማውራት ደስ ይላቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ትንሿን ስህተታችንን አጉልተው ሌላ ጊዜ ደግሞ ያልወለድነውን አሳቅፈውን ያወራሉ። ከእኛ በላይ እኛን እንደሚያወቁ ሆነው ይናገራሉ። ብዙዎቹ የራሳቸው ጥላቻ እንኳ የሌላቸው የደቦ ሐሜተኞች ናቸው። የሰሙትን ነገር የሚያስተላልፉ የሬዲዮ ጣቢያዎች ናቸው። በአካል የማያውቁትን ሰው ስለ እርሱ በብዙዎች ፊት ክፉ ምስክርነት ይሰጣሉ። ለዚህ ጥማታቸው መጽሐፍ ያሳትማሉ፣ ጋዜጣ ያዘጋጃሉ፣ ሬዲዮ ጣቢያ ይመኛሉ። ሰዎች ስለ እኛ በሚያወሩትና ገና ያወራሉ በምንለው ነገር መሸበር የለብንም። ሰዎች ለማለት ነው የሚኖሩት። ትልቁ ነገር ሆኖ አለመገኘት ነው። አንዳንድ ጊዜ የሚሉትን መስማት ጥሩ ነው። እንደ ጨረስነው አድርገው የሚያወሩትን ወሬ ገና በኅሊናችን ውስጥ ሲተራመስ እናገኘዋለን። ስለዚህ ብጨርሰው እንዲህ ነው የምባለውና የምሆነው ለማለት ይረዳናል። ሥጋ የሚወዱ ሰዎች ሥጋ ያውቃሉ። ሐሜተኞችም የሚያሙን ሲፈሩን እንጂ ሲንቁን አይደለም። እነዚህ ሐሜተኞች የሞቱትን አያሙም። ያበዱትን በአፋቸው አያነሡም። ስለዚህ ሰዎች ካሙንና ከነቀፉን «አለን» ማለት ነው።

ሐሜተኞች የበታችነት መንፈስ የሚያሰቃያቸው መሆናቸው በጥናት ተደርሶበታል። ስለዚህ የበለጣቸው የሚመስላቸውን ሰው በሐሜት ዝቅ እያደረጉ ማጣጣል ከራሳቸው ጋር እኩል የሚያደርግላቸው ይመስላቸዋል። በዚህ ምክንያት ሐሜትን ሥራዬ ብለው ይያያዙታል። በዚህ ዘመን የሰው ኃጢአት ዜና ተብሎ ይሸጣል። መረጃ ተብሎ ይወደሳል። ሰው ሆኖ ስለ ሰው መደነቅ ግን ራስን አለ ማወቅ ወይም ከራስ ጋር ላለመገናኘት የሚደረግ ጥረት ነው።

አዎ ላለመጠላት፣ ላለመነቀፍ፣ ላለመጋለጥ ብዙዎች አስመሳይ ኑሮ ይኖራሉ። ትዕግሥት ሲኖረን ግን የመጠላትን ዕዳ እንሸከማለን። ሰዎች ሳይነቅፉን ስህተታችንን እናምናለን። ስለ እኔ ተወራ ብለን አንጨነቅም። አሁን እየሆነ ያለው ሲሆን የነበረ እንጂ አዲስ ነገር የለምና (መክ. 1:9)።





ትዕግሥተኛ የሚባለው ሰው ማን ነው? ቢባል የማይሳደበው፣ የማይማታው ሰው አይደለም። ትዕግሥተኛ ሰው «ያልተሸበረ መንፈስ» ያለው ነው።

ውድ አንባቢ ሆይ! ይህች ዓለም መከራ ያለባት ዓለም ብትሆንም ጨርሶ ግን ገሀነም አይደለችም። በገሀነም የእግዚአብሔር ድምፅ የለም፣ በዚህች ዓለም ግን የእግዚአብሔር ድምፅና የመዳን ተስፋ አለ። ዘመኑ የመጨረሻው ዘመን ነው። ግን ከእግዚአብሔር ቊጥጥር ውጭ አይደለም። ስለዚህ መሸበር የለብንም። የእግዚአብሔር የፈጣሪነቱ አሻራ ያለባት ይህች ዓለም ከነልፋቷ ውብ ዓለም ናት። ስለዚህ መኖራችንን አንርገም። ችግራችንን እናዳንቀው። የጠላታችን ማደግም አያስደንግጠን። ሕይወትን ከነ ሸክሟ ተቀብለን ለመኖር እንጨክን። ከመከራው ውስጥ መማር ያለብንን እናስተውል እንጂ ስለ መከራችን እንጉርጉሮ አንጀምር። ችግራችንን በልባችን መሸከም አቅቶን በፊታችን አደባባይ ላይ ማስነበብ የለብንም። ዛፎችን እንመልከት ቁመናቸውን ሳይደብቁ በኩራት ቆመዋል፣ አበቦች በደስታ ፈክተዋል። ከእነዚህ የምንበልጥ የዚህች ዓለም ትልቅ ፍጥረቶች በመሆናችን ከእነዚህ ይልቅ የመኖር መብት አለንና ደስ ይበለን!

## <u>እናስተውል</u>

በሕይወት ውስጥ የሚገጥሙንን ፈተናዎች እንደ አደጋ ከመቀርል ሂደት መሆናቸውን መረዳት ይገባናል። አደጋ ድንገተኛ፣ አስደንጋጭ፣ ብዙ ርእስና ዜና የሚወጣው፣ ስሙልኝ እዩልኝ የሚባል፣ አስተዛዛኝ የሚያስመኝ ነው። በሕይወት ላይ የሚደርሰው ግን ድንገተኛ ነገር ሳይሆን በመንገድ ላይ የተቀመጠ እንቅፋት ነው። ያለ ትግል ለመኖር እያቀድን ካለን ድካም ነው። በትግል ውስጥ ግን ያለውን መልካም ነገር መተመን ያስፈልገናል። ትግል ጠንካራ ማንነትን ይፈጥራል። ቀላል ምሳሌ ብንጠቀም አይስክሬም ከሚበሉ ልጆች ጥሬ የሚቆረጥሙ ጥርሳቸው ጠንካራ ነው። የሚያታግል ማንኛውም ነገር ጠንካራ ማንነትን ይፈጥራል። እግዚአብሔርም ትግል ባለው ሕይወት ውስጥ የሚያሳልፈን ሊገነባን እንጂ ሊያፈርሰን አይደለም። ጠንካራ አካል ለማዳበር የሚፈልጉ ወጣቶች በጫካ ውስጥ ሆነው በድብቅ ድንጋይ ይገፋሉ። የለፉበት አካል ማበጥ ሲጀምር የልፋታቸውን ውጤት ለማሳየት ጠባብ ልብስ ለብሰው በጎዳና ላይ ይንጎማለላሉ። እንዲሁም በድብቅ ትግል የሚሠራው ሕይወታችን ለሁሉ ምሳሌ እንዲሆን በአደባባይ ይታያል። ብዙዎችን የሚያሻግር ይሆናል። ብቻ የሚያታግሉ ነገሮች



www.ethiopinorthodox.org

ጠንካራ ማንነትን ይፈጥራሉ:: በሕይወት ውስጥ ያለው ትግል መልካም ነው::

በትግል ውስጥ የምናልፈው ክርስቲያን ስለሆንን አይደለም:: ሰው ስለሆንን ነው:: ነገር ግን ሰዎች ሰው ስለሆኑ የሚቀበሉትን መከራ እኛ በክርስትናችን ስንቀበለው ዋጋ ያለው አድርጎ እግዚአብሔር ይከፍለናል:: ስለዚህ ክርስትናችን የመከራ ምንጭ ሳይሆን መከራችንን የሚያከብር ወይም ዋጋ ያለው የሚያደርግ ነው::

በሕይወት ውስጥ ባዶነት ሲገጥመን፣ የመቆም ብቃት ሲያጥረን መደናገጥ የለብንም:: ይህን ሳናይ ኖርን ብለን መናገር አንችልም:: ኢትዮጵያን ጎበኘሁ የሚል ቱሪስት አዲስ አበባን ግን አላየሁም ቢል የልፋቱን ወሬ ይቀንስበታል:: እኛም ባዶነትን፣ መጨነቅን ካላየን ሕይወትን አይቻለሁ ብለን መናገር አንችልም:: እነዚህ የሕይወት ክፍሎች ናቸውና:: የሕይወትን መንገድ እኛ መርቀን የምንከፍተው ሳይሆን ብዙ ትውልድ፣ ብዙ ታላላቅ ሰዎች፣ ከሁሉ በላይ የሚሆን ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ያለፈበት ጎዳና ነው:: ስለዚህ የለማ መንገድ አያስፈራም:: በባዶነት ስሜትና በጭንቀት ውስጥ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች አልፈውበታል:: ነቢዩ ዳዊት፣ የሰማርያው ነቢይ ኤልያስ በዚህ በረሃ ተጉዘዋል:: መኖርን እስኪጠሉ ተፈትነዋል:: ስለዚህ ጭንቀትና ባዶነት መጨረሻችንን የሚያረዳን ሳይሆን ወደ ሕይወት አስኳል ውስጥ መድረሳችንን የሚያመለክት ነው::

ሰዎች በምክንያትም ያለ ምክንያትም ሊጠሉንና ስማችንን ሊያጠፉ ይችላሉ:: ሁሉም ሰው ለእኛ መልካም አመለካከት ሊኖረው አይችልም:: መውደድ የሚለው ቃል በራሱ መፍቀድ ማለት ነውና ፍቅር ነጻነት ስለሆነ በግድ አፍቅሩን አንልም:: የተገለጠ ስህተታችንን ግን መናዘዝና ይቅርታ መጠየቅ ይገባናል:: የተገለጠ ስህተት የበለጠ የሚገለጠው ለመሸፋፈን በሞከርን ቊጥር ነው:: ስንናዘዘው ግን ራሳችን እየጸዳን ብቻ ሳይሆን ሰዎች ዳግመኛ እንዳያወሩትም እያተረፍናቸው ነው:: ብቻ በሚሆኑ ነገሮች ሁሉ ሳንሸበር መቆም ይገባናል:: የሚሆን ነገር ከመሆን አይቀርምና:: ቢሆንም ማንኛውም ክፉ ነገር እንኳ ከእግዚአብሔር ቊጥጥር ውጭ ሊሆን አይችልምና በእምነት መቆም አለብን:: ትዕግሥት ማለት ያልተሸበረ መንፈስን መደረብ ነውና!



## ጸሎት

ክብርህ ሞገስ ያለው፣ ግርማህ የሚያስፈራ፣ ፀዳልህ የሚያበራ፣ እውነትህ እንደ ቀትር የሚፈካ አምላኬ ሆይ አመሰግንሃለሁ:: እኔን ያስፈራኝ ነገር አንተን አያስፈራህም፤ ፈቃድህንም አልፎ አንዳች አይደርስብኝምና ሁኔታው አያስደነግጥህም:: እኔ ግን አይዞህ ባልከኝ ቊጥር በጣም እፈራለሁ:: ወደፊት ይሆናል በምለው ነገር እሸበራለሁ:: እባክህ ጌታ ሆይ እንዳምንህ እርዳኝ:: እግሬ እንዳይናወጥ ዓለት በሆነው ቃልህ ላይ አቁመው:: ፈቃዴ እንዳይገዛኝ የፈቃድህን ክብረት ልለየው:: ሰዎች የሚሉኝን ያደረግሁት ከሆነ እንዳስተካክል፣ ያላደረግሁት ከሆነ እንድጠነቀቅ እርዳኝ:: የሚያስፈራ ሳይኖር እፈራለሁ፣ ጌታ ሆይ አንተን እንደ ታላቅነትህ መጠን ብፈራህ የሚያስፈራኝ አይኖርም ነበር:: እባክህን ያንተን ቅዱስ ፍርሃት ጨምርብኝ:: በምንም የማይሸነፍ በፍቅር የታነፀ ማንነትን ስጠኝ:: ሰዎች ለሚሉት ሳይሆን አንተ ላልከው አኑረኝ:: የሁኔታ ሳይሆን የእውነታ ሰው አድርገኝ:: መባል የምፈልገውን ቅዱስነት እንድሆነው፣ እንዳልባል የምፈልገውን ዓመፀኛነት እንድተወው እርዳኝ:: በሚሆነው ሁሉ እንዳልሰጋ የማዕበሉ አዛዥ አንተ መሆንህን አስተምረኝ:: አንተን አልፎ እኔን የሚነካ ጎበዝ የለምና ጋሻዬ ሆይ አመሰግንሃለሁ:: የፀጥታው ወደብ በሆነው ስምህ ለዘላለሙ አሜን!



www.ethiopinorthodox.org

# ምዕራፍ ሃያ
# የማይበርድ ተስፋ

ታጋሽ ሰው የሚታገሥበት ምሥጢር ተስፋ ነው:: በትዕግሥት ውስጥ የተደበቀውን ነገር ብንፈልግ ተስፋ ሆኖ እናገኘዋለን:: የተፈጥሮ ብርሃን እንኳ ከተስፋ ጋር ግንኙነት አለው:: ዓመት ከዓመት ክረምት በሆነበት ክፍለ ዓለም የሚኖሩ ሕዝቦች ራስን በማጥፋት ወንጀል ብዙ ጊዜ ይጠቃሉ:: የፀሐይ ብርሃን በራሱ ከተስፋ ጋር ግንኙነት እንዳለው በዚህ እንረዳለን:: ጨለምለም ሲል ጭጋግና ደመና ሲሰፍን እንጉርጉሮ የሚጀምሩ፣ ከዝናብ ነጠብጣብ ጋር ዕንባቸውን የሚያፈሱ ወገኖች ብዙ ናቸው:: «በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ» እንዲሉ:: እነዚህ ሰዎች ለማልቀስና ለመከፋት አየር ንብረቱ በቂ ምክንያታቸው ነው:: ነገር ግን በተፈጥሮ ብርሃን የማይደገፍ አንድ ኃይል አለ:: ከፀሐይ ብርሃን በበለጠ የሚወዱትን ሰው ማግኘት ተስፋ ይጭራል:: እርሱን ስናይ ፊታችን ይበራል:: ስለ ራሳችን እንኳ መኖር በጠላን ጊዜ ስለ እርሱ ፍቅር መኖር እንፈልጋለን:: የወዳጅ ፍቅር ዕድሜ ይቀጥላልና:: ነገር ግን ከወዳጅም የሚበልጥ ወዳጅ አለ::

እቤታችን ያለው አምፑል የሚያበራው በውበቱ አይደለም:: ሩቅ አገር ካለው የኃይል ምንጭ ጋር በመገናኘቱ ነው:: ኃይሉ ከተቋረጠ ውበቱም ይጠፋል፣ ብርሃኑም ይጨልማል:: እንዲሁም የተስፋችን ብርሃን ከራሳችን የሚወጣ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር የተያያዘ ነው:: በራሳችን ማፍቀር፣ በራሳችን ተስፋ ማድረግ፣ በራሳችን መደሰት አይቻለንም:: ከኃይላት ጌታ ጋር መቆራኘት አለብን::

የፀሐይ ብርሃን ከተስፋ ጋር ግንኙነት አለው አልን፣ ነገር ግን የፀሐይ ብርሃንም የማያፈካው ቀቢፀ ተስፋ በሰው ውስጥ አለ:: ወዳጅም የተስፋ አጋዥ ነው አልን:: ነገር ግን ወዳጅም በክዳቱ የቀቢፀ ተስፋ ምክንያት ይሆናል:: ፀሐይ ትጠልቃለች:: ወዳጅም ይከዳል:: ሁልጊዜ በፀሐይ ብርሃን፣ ሁልጊዜ በወዳጅ መደሰት አይቻልም:: ታዲያ በዚህ በጨለማ ዓለም የብርሃን ዋስትናችን፣ በዚህ የብቸኝነት ዓለም የወዳጅ ዋስትናችን ማነው? የማይጠልቀውን ፀሐይ፣ የማይከዳውን ወዳጅ መፈለግ የሰው ልጅ ዙረት ነው:: አንድ ሰው ስለዚያ ስለማይጠልቀው ፀሐይ ሲናገር:- «ይህች ወኅኒ ዓለም አንድ መስኮት አላት፤ ይህም መስኮት ዘላለማዊነትን የምናይበት መጽሐፍ ቅዱስ ነው» ብሏል:: ወኅኒ ቤት ያለች ጠባብ መስኮት



የብርሃን በር ናት:: ይህችን መስኮት የሚነፈጉ በቁማቸው እንዲሞቱ የተፈረደባቸው፣ ወደው ሳይሆን በግድ ዓለም በቃኝ ያሉ እስረኞች ናቸው:: ዓለም በራሷ ሰፊ ወኅኒ ቤት ናት:: የፀሐይ ብርሃን የማይደርስበትም ጨለማ አለባት:: ለዚህች ጨለማ ዓለም ያላት አንድ ተስፋ፣ አንድ መስኮት መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: እርሱም የሚያሳየን ዘላለማዊ ሕይወትን ነው:: ላለፉት ሦስት ሺህ ዓመታት በክብርና በናፍቆት የተነበበ፣ የሰው ልጅ የቅርብ ጓደኛ የሆነ፣ የምሥጢሩ ጥልቀት ዛሬም ተጨልፎ ያልተፈጸመ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው:: ቀትሩ ለጨለመባቸው፣ ወርቅና ብራቸው የዝገት ያህል ለከበዳቸው፣ እውቀት ፍልስፍናቸው ትርጉም ላጣባቸው፣ ወዴት እንደሚሄዱ ግራ ለተጋቡ፣ የሚወስኑትን ላላወቁ፣ ነገ አልታይ ላላቸው ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ተስፋንና መጽናናትን ሲለግስ ኖሯል:: ዛሬም ተስፋን እያበራ ይገኛል:: ሄለን ኬለር:- *«መጽሐፍ ቅዱስ ተነዋዋጭ በሆነው በዛሬው ዓለም ውስጥ አስተማማኝ መልሕቅ ነው:: በሐሴት ስንሞላም ይሁን ስናዝን መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ መቻል ይኖርብናል:: ያለበለዚያ ሕይወትን አቻችለን ለመምራትም ሆነ ለመቋቋም አቅም አይኖረንም:: የመጽሐፍ ቅዱስ አሳቡም በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት ከሌለ ሕይወት አስቸጋሪና መራራ እንደምትሆን መግለጥ ነው»* ብላለች::

መጽሐፍ ቅዱስ ወይም የእግዚአብሔር ቃል የተስፋ ችቦ ነው:: እንዲሁም አካላዊ ቃል የሚሆን ኢየሱስ ክርስቶስም የማይከዳ ወዳጅ ነው:: ተስፋችን ከዚህ ጥብቅ ወዳጅነት ውስጥ ይመነጫል:: አንድ አባት:- «ታምኖ የማይከዳ፣ ወዶ የማይጠላ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው» ብለዋል:: የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር የተለየ ነው:: በእርሱ ፍቅር ፊት እኛ ለልጃችን አለን የምንለው ፍቅር እንኳ አዳፋ ነው:: በእርሱ ለጋስነት ፊት የእኛ ቸርነት ቍጥሩ ከስስት ነው:: ፍቅር ከራሱ ውጭ ምንም አይቀበልም:: ፍቅር ፍቅርን ይፈልጋል:: የኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር ግን በስብከት አገልግሎት፣ ሙዳየ - ምጽዋት ውስጥ በምንከተው ድቃቂ ሳንቲም ልንመልሰው እንሞክራለን:: እርሱ ግን እንድንወደው ይፈልጋል:: መሥዋዕታችንን ብቁ የሚያደርገው ለእርሱ ያለን ፍቅር ነው:: እርሱ ፍቅሩን በሞቱ ገለጸልን:: የክርስትናችን ወጉም:- «ለሞተልኝ ጌታ ልኑር» የሚል ነው:: ለሞተልን መኖር ትንሽ ነው:: እርሱ ግን ከዚህ በላይ አልጠየቀንም:: ወዳጅ መልካም ጠባያችንን ብቻ የሚያውቅ ሳይሆን ጉድለታችንንም ያውቃል:: ኢየሱስ ክርስቶስም ሁለንተናችንን እንድንገልጽለት የሚፈልግ ወዳጅ ነው:: እርሱ ምን አላችሁ? ሳይሆን ምን ልስጣችሁ? የሚል አፍቃሪ ነው:: ወዳጅ ስለ እርሱ ብለን ብዙ ነገሮችን የምንተውለት ነው:: ስለ እርሱ ብለን የምንተውለት ከሌለ ወዳጅነታችን ጥብቅ አይደለም:: ኢየሱስ



www.ethiopinorthodox.org

ክርስቶስም ስለ እርሱ ብለን ኃጢአትንና ዓመፃን እንድንተው የሚፈልግ ወዳጅ ነው። የወዳጅ ፍቅር ብርቱ ነውና የምንወደውን ሁሉ ያስተወናል። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርም ልዩ ነው። እንኳን የሚጎዳንን ኃጢአት የሚጠቅመንንም መረብና ታንኳ ያስጥላል (ማቴ. 4:18-22)።

ኢየሱስ ክርስቶስ የተለየ ፍቅርን ከእኛ ይፈልጋል። ጓደኞቻችንን አሊያም ራሳችንን በምንወድበት መጠን ሳይሆን በተለየ ፍቅር እንድንወደው ይፈልጋል። የእርሱ ፍቅር ልዩ ነውና። ስለ እርሱም ወዳጅነት ስንል እርሱን ከማይወዱ ባልንጀሮቻችንና እርሱን ከሚያሳዝን ኃጢአት መለየት ይገባናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጴጥሮስን የጠየቀው የፍቅር ጥያቄ፡- *«የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?»* (ዮሐ. 21:15) በማለት ነው። ጥያቄው የእነዚህን ያህል ትወደኛለህን? የሚል ቢሆን ቀላል ስለነበር ጴጥሮስ ባልከበደው ነበር። ጥያቄው ግን ከእነዚህ ይልቅ የሚል ስለ ነበር ጴጥሮስ ከበደው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የወዳጆቻችንን ያህል መውደድ ቀላል ነው። እርሱ ግን የተለየ ፍቅር ይፈልጋል።

የሰው ፍቅር አስመሳይ ነው። እንደ ፍጡርነቱ የተፈጠረ ነው። የእርሱ ፍቅር ግን ዘላለማዊና ያልተፈጠረ ነው። ቅብ ሳይሆን እውነተኛ ነው። ቆይቶ የሚወይብ ሳይሆን በመልኩ የሚኖር ነው። የሰው ፍቅር በተግባር ሳይሆን በቃል የሚገለጽ፣ አብልቶ አጠጥቶ የሚያስተፋ ነው። የእርሱ ፍቅር ግን እንደ ወንዝ የሚያረሰርስ፣ እሮሮ የሌለበት ነው። የሰው ፍቅር እንደ ቅል አበባ ዛሬ ያብባል። ልምላሜው ልዩ ነው። ነገር ግን ይጠወልጋል። የሰው ፍቅር በጣም መውደዱን በተናገረ ማግስት የማስመሰል ፍቅሩም አልቆበት መጣላት ይጀምራል። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ግን ከሰማይ ምሰሶ፣ ከምድር መሠረት የፀና ነው። የሰው ፍቅር አሳሳች ነው። የኃጢአት ግብገፍ ያቀርባል፣ ባሪያ ያደርጋል፣ መፈተኛ ያስቀምጣል፣ በግምገማ ያስጨንቃል። የሰው ፍቅር የነፋስ ሠረገላ ነው። ቀላል ዕቃዎች ነፋስ ሲመጣ መሬትን ጠልተው ይንሳፈፋሉ። የነፋስ ሠረገላ ግን ሜዳ ሜዳውን ተሽከሞ ሸለቆ ላይ ጥሎ ይሄዳል። የሰው ፍቅርም ለጊዜው ያሳብዳል፣ ዕረፍት ያሳጣል፣ ከተማው ጠበበኝ ይላል። መከራ ሲመጣ ግን ይከዳል። ጥሎ ይሄዳል። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ግን በዘመናት ተፈትኖ ያለፈ ነው።

የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር የዘላለም ሕይወት ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር በጨለማ ውስጥ መብራት ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ከብዙ መባዘን በኋላ ተቀባያችን ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ተስፋን የምንመሠርትበት ነው። የሰው ፍቅር በማጣት





በመውደቅ ይለየናል። ያም ባይሆን በሞት በግድ እንለያያለን። ከሞት በኋላ የሚቀበለን ፍቅር ግን የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ደካሞች ሳለን የሚቀበለን፣ ጠላቶች ሳለን የሚወደን፣ ኃጢአተኞች ሳለን የሚያክመን ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ከነማንነታችን የሚቀበለን፣ ተስፋ የሚያደርግብን፣ ሲያየን የሚደሰት፣ በከሳሽ ፊት የሚሟገትልን ፍቅር ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ታሪክ አይሆንም፤ ሕያውነቱን ጠብቆ ይኖራል። ምንም ሳያደናቅፈው እንዳሸነፈ ይጓዛል። የትውልድ ሁሉ ወዳጅ፣ እኛ እንኳ የማንወዳቸው የኃጢአተኞች፣ የነገሥታት፣ የዓለማውያን ብቸኛ ወዳጃቸው የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ነው። ስንክደው የማይክደን፣ ስንተወው የማይተወን፣ ሲመሽብን ብቻ ብንፈልገውም በር የማይዘጋብን ከእናት ይልቅ የሚወደን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

በሥጋና በነፍስ መማፀኛ፣ በጦርነት ሰዓት ጽኑ ምሽግ፣ በቀስት ፊት ጋሻ፣ በጠላት ፊት መከታ፣ በወደረኞቻችን ፊት አንደበት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከሞት በኋላ በዓለም ላይ ካፈራናቸው ወርቅና ንብረት አንዱም አይከተለንም። ወዳጆቻችንም ከመቃብር ወዲህ ይመለሳሉ። የዘላለምን አገር የሚያስጎበኘን፣ ከሞት በኋላ የሚረባን፣ ለዘላለም የሚኖረው ወዳጃችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። እምነትና ተስፋ የሚጣልበት ወዳጅነት የእርሱ ብቻ ነው። መሠረቱ የማያረገርግ፣ ምሰሶነቱ የማይነቃነቅ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ብቻ ነው። የእርሱ ፍቅር የነፍስ መልሕቅ ነው። የፀዳ ብቻ የማይፈልግ ቆሻሻውን ማንነት አጽድቶ መንገሥ የሚፈልግ ወዳጅነት የኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ትልልቆችንና ትንንሾችን የሚጠይቀው ልብን ብቻ የሆነ፣ ልብ ፈላጊ የልብ ወዳጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ጠቆራችሁ፣ ከሳችሁ፣ አጣችሁ ነጣችሁ፣ መከናችሁ፣ ወደቃችሁ ብሎ በምክንያት የማይርቅ ያለ መስፈርት የሚወድ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። በበረሃው ዓለም ላይ ለምልሞ የሚታይ፣ ፊቱን በሰው ልጅ ላይ የማያጠቍር፣ የቃጠሎው ጥላ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ነው። እርሱን ያገኙ ሁሉን አገኙ፣ እርሱን የተጠጉ ድላቸው እንዳሸበረቀ ኖረ። የልብ ሀብት፣ የአንደበት ጣዕም፣ የእጅ መክሊት፣ የመንገድ ካርታ፣ የመኖር ደስታ፣ የኑሮ መከታ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ነው። አዎ አንተ ከምታስፈልገው በላይ ላንተ የሚያስፈልግህ ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስን ወድዶ በበረሃ መኖር አያስፈራም፣ በክፉዎች ጉባዔ ተወግዞ መለየት አያስጨንቅም። እርሱን ይዞ የሀብት መወረስ፣ የርስት መቀማት፣ የወዳጅ ክዳት አሳብ አይሆንም። ከዓለም ጉድለት፣ ከዓለምም እሴት በላይ የኢየሱስ



www.ethiopinorthodox.org

ክርስቶስ ፍቅር ገንኖ ይኖራል:: ራሳችንን ብንፈልግ ድካማችንን እናገኛለን:: ኢየሱስ ክርስቶስን ብንፈልግ ግን ተዘግኖ የማያልቀውን የዕንቊ ክምር እናተርፋለን:: ከእርሱ የራቁ በጦር ከተወጉ በላይ ራሳቸውን ወጉ:: እርሱን ቻል ያሉ ዘላለምን ቻል አሉ:: ከእርሱ ርቀው ለመበልጸግ የፈለጉ በጣም ድሃ ሆኑ:: ይህ ወዳጅ ለጆሮ ሳይሆን ለልብ የሚናገር ነው:: ምድረ በዳ ውሃን እንደሚጠማ የነፍስ ሁሉ ናፍቆት ነው:: የሙታን ሰፈር የሕያዋን አገር የሚሆነው፣ ያለቀው ተስፋ የሚቀጠለው፣ የልቅሶ ቤት የሠርግ ቤት የሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ነው:: ዓለምና ሞላዋ ዝናና ክብሯ ቢቀርብልን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ከሌለን በሬሳ ላይ እንደ ተቀመጠ በረከት ነው:: ቢመነዝሩት የማያልቅ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ነው:: የዓለም ሀብት አይበቃምና ያሰራርቃል፣ ያጋድላል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሚያፋቅር ሀብት ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ካለን በበረሃ ውስጥ ብቸኛ አንሆንም:: የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ያዋራል:: ግንዛቤ ሳይሆን መፍትሔ ይሰጣል:: ያላሰብነውን በጎ ነገር የምናቅደው፣ ያልፈጸምነውን ውጥን ከግብ የምናደርሰው በኢየሱስ ክርስቶስ የፍቅሩ ኃይል ብቻ ነው:: ምድር ለሰው መኖሪያነት ምቹ እንደሆነች፣ ሌሎች ዓለማት የሚይዘን ስበት፣ የምንተነፍሰው አየር እንደ ሌላቸው፣ ከምድር ውጭም ሰው መኖር እንደማይችል፤ ከሚይዘን ከኢየሱስ ክርስቶስ የፍቅር ስበት ውጭ፣ ነፍስ ከሚዘራብን የፍቅሩ አየር በቀር ህልውናችን አስተማማኝ አይሆንም:: ታዲያ ይህን ወዳጅ የለወጥነው በምን ይሆን?

ሰዎችን ላለማጣት ብለህ ኢየሱስ ክርስቶስን ልታጣ ወሰንክ? ነገር ግን ምድር ሁሉ ባዶ ሆኖ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ብትኖር ይሻልሃል:: ወዳጆችህን ላለማሳዘን ብለህ ኢየሱስ ክርስቶስን አፈርክበት? በሚታፈርብህ ባንተ እርሱ እንዳላፈረብህ አስብ:: ኢየሱስ ክርስቶስን ትተህ የሰበሰብከው ሀብት፣ ደግሞም ወዳጆችህ የጥፋትህ ምክንያት እንደሆኑ እወቅ:: ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ብለህ ሌሎችን ውደድ:: ኢየሱስ ክርስቶስን ግን ስለ ራሱ ብለህ ውደደው:: ስለ እርሱ ካልተናገርህ ዲዳ ሆነህ ኑር:: ለእርሱ ካልተማረክህ የጉዶች ጉድ መሆንህን እወቅ:: እርሱ ሲሰበክ ከከፋህ ሰይጣን መሆንህን ተረዳ::

ወደ ታላቅ ደስታ ለመግባት፣ መከራን በድል ለማሸነፍ፣ ከሁሉ በላይ ተስፋ ለማድረግ የኢየሱስ ክርስቶስን የፍቅሩን ጥልቀት፣ የወዳጅነቱን ግለት፣ የማፍቀሩን ብዛት፣ የንድነቱን ንጽሕና መመርመርና ማግኘት ያስፈልገናል:: ኢየሱስ ክርስቶስን ስንወደው፣ እናምነዋለን፣ ስናምነው እንከተለዋለን፣ ስንከተለው ተስፋ እናደርገዋለን፣ ተስፋ ስናደርገው እንታገሣለን፣ ስንታገሥ



ፍሬንና ድልን እናያለን:: የተስፋችን መጋቢዎች ቃሉና የጥብቅ ወዳጃችን ኢየሱስ ክርስቶስ ናቸው:: በዚህ የዘመን መጨረሻ መጨረሻ የሌለውን የኢየሱስን ፍቅር፣ በዚህ በክፉ ቀን የማይከፋውን የክርስቶስን ወዳጅነት፣ በዚህ በተጨካከነ ቀን ሩኅሩኁን የአማኑኤልን ፍቅር ያዝ:: የዓለምን ቊስለት የሚያስረሳ ዜማ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ነው::

## <u>በዛሬው እንፍረድ</u>

ህልውናችንን ቀጣይ የሚያደርገው ተስፋ ብቻ ነው:: ያለ ተስፋ ሁሉም ነገር ባለበት ይቆማል:: ተስፋ ከመኖር ጋር የተያያዘ ነገር ነው:: ለዚህ ነው:-

የሰው ልጅ በዚህ ምድር ላይ:-

40 ቀናት ያለ ምግብ፣
3 ቀናት ያለ ውሃ፣
8 ደቂቃ ያለ አየር፣
1 ሴኮንድ ያለ ተስፋ መኖር አይችልም የሚባለው:: በጉልበትም፣ በጥበብም፣ በዘመድም የማይቻሉ ነገሮች ብቸኛ ብልሃታቸው ትዕግሥትና ተስፋ ነው:: ተስፋችንን የሚጋፋን ነገር ምንድነው? ስንል በአሁኑ ሁኔታ ነገሮችን የሚወስነው ችኲልነታችን ነው:: ቦታው ላይ ስንደርስ ቀጣዩ ይታየናል:: ከወዲሁ ያለው ግምታችን ግን ባዶ ይሆንብንና ከተስፋ መቊረጥ ያደርሰናል:: ጭጋግ ቆመ'ን ካየነው አያሳየንም፣ የራሱን ጨለማ ብቻ ያሳየናል:: ወደ ራሱ እየተራመድን ስንሄድ ግን ልናይ የፈለግነው ነገር እየተገለጠ ይመጣል:: ዛሬ የሆነው ምንም ይሁን ሕይወት በዛሬው ሁነት አትገመገምም::

ነቢዩ:- *«ያልተሠራ አካሌን ዓይኖችህ አዩኝ፤ የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ»* (መዝ. 138(139):16) ብሏል:: ሕይወት ብዙ ገጾች ያሏት ትልቅ መጽሐፍ ናት:: የታሪካችን ደራሲም መንፈስ ቅዱስ ነው:: የመጨረሻው ምዕራፍ ሳይቀር ተጽፏል:: የምንኖረውም የተጻፈ ሕይወትን ነው:: መጽሐፍን በአንድ ገጽ አንገመግመውም:: ይህኛውንም ገጽ በማንበብ ቀጣዩን መወሰን አይቻለንም:: ሲገለጽ ብቻ ነው የምናውቀው:: ሕይወትንም የምንኖራት በገጽ በገጽ ነው:: ቀጣዩ ቀን ምን እንደሆነ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም አያውቅም:: ታዲያ ከዚህ ትልቅ መጽሐፍ ውስጥ ስላልተሳኩ ነገሮች የሚያወራው አንድ ገጽ ብቻ መሆኑ ይገርማል! በሕይወት ውስጥ ከጕደለብን የተሰጠን



www.ethiopinorthodox.org

ይበልጣል፡፡ «ሸንኮርት ብዙ ክፍሎች አሉት፣ ሲላጥ ሲላጥ ነው መጨረሻው ላይ የሚደረሰው፤ ሕይወትም እስኪገለጥ አናውቀውም፡፡ በምናየው ብቻ ብንፈርድ በውስጥ ያለውን መልካም ነገር እናጣዋለን፡፡»

አንድ ክፍል ብቻ አይተን ቤት እንገዛለን? አንድ መኪናንስ ጐማውንና የኋላ መብራቱን በማየት ብቻ እንገዛለን? በአዲስ አበባ አየር ንብረት ስለ መላው ኢትዮጵያ የአየር ሁኔታ መናገር እንችላለን? መልካም ዳኝነት ሰፋ ያለ ነገር ይፈልጋል፡፡ ሕይወትንም ለመገምገም ሰፋ አድርጎ ማየትን ይጠይቃል፡፡ በሕይወት ውስጥ ያለውን ነገር እስክናውቅ ከፍርድ መታቀብ አለብን፡፡

ሰውዬው እንጨት ፈላጭ ነው፣ ግን ጥበበኛ ነበር፡፡ በብዙ ሰዎች ዘንድ የማይገኝ አንድ ነገር ነበረው፡፡ ያ ነገር ምን ይመስላችኋል? ሕይወትን ዛሬ በሆነው አይፈርዳትም ነበር፡፡ ይህ ሰው በጣም የሚወደውና የሚንከባከበው እንደ ሰውም የሚያየው አንድ ነጭ ፈረስ ነበረው፡፡ ይህን ፈረስ ብዙ ባለጠጎችና የቤተ - መንግሥት ልዑላን ይመኙት ስለነበር በብዙ ገንዘብ እንግዛህ ብለውት እምቢ ብሎ ነበር፡፡ የመንደሩ ሰዎችም «አንተ! ሞኝ ነህ? ፈረሱን ሸጠህ ለምን ከድህነት አትላቀቅም» ይሉታል፡፡ እርሱ ግን «ይህ ፈረስ ለእናንተ ፈረስ ነው፣ ለእኔ ግን ጓደኛዬ ነው፤ ጓደኛ ደግሞ ይዞታ አይደለም እንዴት ይሸጣል? ሰው ራሱን ይሸጣል?» ሲላቸው እያጉረመረሙ ይመለሳሉ፡፡

ከጥቂት ቀን በኋላ ያ የሚወደውና የሚንከባከበው ፈረሱ ጠፋ፡፡ የመንደሩ ሰዎችም «ምን ዓይነት የተረገምክ ሰው ነህ? ሸጠው ስንልህ እምቢ ብለህ ይኸው ፈረሱ ጠፋብህ» አሉት፡፡ እርሱ ግን «እንደ ተረገምኩ በምን ታውቃላችሁ? ልትሉ የምትችሉት አንድ ነገር ብቻ ነው፣ ፈረስህ ጠፋ» በመቀጠልም «ዐረፍተ ነገሩን ሳታዩ በአንድ ቃል ነገርን ትገመግማላችሁ? ሕይወትም በጣም ሰፊ ናት፣ ሰፊ ከሆነው ነገር ቊራጩን በማየት ለምን ትዳኛላችሁ?» ሲላቸው እየተበሳጩ ተመለሱ፡፡

ከሳምንት በኋላ ግን ያ የጠፋ ፈረሱ ሌሎች ያልተገሩ 12 ፈረሶችን ይዞ ተመለሰ፡፡ የመንደሩ ሰዎችም ወደዚህ ሰው በመምጣት «ተረግመሃል በማለታችን በጣም ተሳስተናል፣ የተባረክ ሰው ነህ! አንድ ፈረስ ቢጠፋብህ 12 ፈረሶች ይዞልህ መጣ» አሉት፡፡ እርሱ ግን «የተባረኩ መሆኔን በምን አወቃችሁ? ልትሉ የምትችሉት አንድ ነገር ብቻ ነው? ፈረስህ ተገኘ» በመቀጠልም «የአንድ ነገር



ከመጀመሪያው የመጨረሻው ይሻላል» አላቸው፡፡ እነርሱ ግን መርካት እንደማይችል ሰው ቆጥረውት ተመለሱ፡፡

ከጥቂት ቀን በኋላ የእንጨት ፈላጩ ልጅ ከእነዚያ ካልተገሩ ፈረሶች መካከል በአንዱ ሲጋልብ ወድቆ ተሰበረ፡፡ የመንደሩ ሰዎችም ተሰባስበው በመምጣት «ምን ዓይነት የተረገምክ ሰው ነህ? ፈረስህ ጠፋ፣ 12 ፈረሶች ይዞ መጣ፣ ግን ምን ዋጋ አለው ልጅህን አጣኸው» አሉት፡፡ እንጨት ፈላጩ ሰው ግን፡- «እናንተ ሰዎች በመፍረድ ተይዛችኋል፣ ሕይወት የሚመጣው በቊራጭ በቊራጭ ነው፡፡ ታዲያ የሚሆነውን ሳታዩ ለምን ድምዳሜ ላይ ትደርሳላችሁ?» አላቸው፡፡

ከወር በኋላም በአገሩ ጦርነት ተነሣ፡፡ የመንደሩም ወጣት ሁሉ ሲዘምት የእንጨት ፈላጩ ልጅ ግን አልዘመተም ነበር፡፡ የመንደሩም ሰዎች ጠላቶቻቸው ኃያላን ስለነበሩ በልጆቻቸው መመለስ ተስፋ ቆረጡ፡፡ ወደ ጥበበኛውም እንጨት ፈላጭ በመምጣት፡- «ያልከው ሁሉ ትክክል ነው፡፡ እኛ የምናውቀው የአሁኑን ብቻ ነው፡፡ ቀጣዩ ምን እንደሆነ ግን እግዚአብሔር ብቻ ያውቃል» አሉት፡፡

ውድ አንባብያን ሆይ!

## የዛሬ አለመሳካት የሁልጊዜ

## አለመሳካት አይደለም

ዛሬ በሆነው ነገር ከመጠን በላይ አንከፋ፡፡ የሚያላቅሱንን ሰዎች አንፈልግ፡፡ በሀዘን ለመሰንበትም ምንጣፋችንን አናስተካክል፡፡ ሁኔታውን ለመርሳትም መደበቂያ አናዘጋጅ፡፡ ሰው አላናግርም ብለንም በራችንን አንዝጋ፡፡ ራሳችንን ብቸኛ አድርገንም ጫካ አንግባ፡፡ ምክንያቱም የዛሬ አለመሳካት የሁልጊዜ አለመሳካት አይደለምና፡፡

አዎ! ጉዳታችን ቀላል ላይሆን ይችላል፡፡ ጤናን ተቸግረን ሊሆን ይችላል፣ መንገድ በመሳትም ወኀኒ ወርደን ይሆናል፣ ተበድረን የጀመርነው ንግድም ተበላሽቶ ይሆናል፣ የውጭ ዕድላችንም ተደናቅፎ ይሆናል፣ የምንወዳቸውም ከድተውን ይሆናል፡፡ እነዚህ ሁሉ የመኖር መብታችንን አይወስኑትምና ደስ ይበለን! እኛ ስናገኝ የምናጣ አይመስለንም፣ ስናጣም የምናገኝ



www.ethiopinorthodox.org

አይመስለንም:: ሁለቱም ይከብደናል:: እግዚአብሔር ከስሜት ኑሮ አውጥቶን በእውነት ላይ እንዲሠራን እንፍቀድለት:: ዛሬ ስላልሆነልን ጊዜያችን በከንቱ ያለፈ ይመስለናል:: ነገር ግን ጊዜያችን በከንቱ አላለፈም፤ እግዚአብሔር ሠርቶበታል:: ደግሞም ታላቁ ድርጊት ትዕግሥት መሆኑን አንርሳ:: እስቲ ከባለቅኔው ጋር እንዲህ እያልን እናመስግን:-

*እመኒ ትሁብ ሀብተ መከራ ወሀብተ ፍስሐ ትሁብ፤*
*እምርእስየ ለርእስየ አንተ ትቀርቦ፤*

ትርጓሜ:- *«ደስታንም ብትሰጠው ሀዘንም ብትሰጠው*
*ከእኔ ይልቅ ለእኔ አንተ ነህ የምትቀርበው::»*

## የዛሬ ስኬት የሁልጊዜ አይደለምና

## እንጠንቀቅ

ድህነታችንን እንኳን ረሳነው:: ያለፈውን ጉዳታችንን እንኳን ፍጹም ዘነጋነው:: የረዳንን እግዚአብሔር ግን ምነው ረሳነው? እስከ የትኛው ዕድሜያችን ነው እግዚአብሔርን ያመለክነው? እግዚአብሔር የሕጻንነት ወይም የሽምግልና አምላክ እንጂ የወጣትነት አምላክ አይደለምን? ገና ትልቁን ጸጋ ሊሰጠን ሲል ምነው የማያጠግበውን እንጀራ ይዘን ሮጥን? ተቀብሎ የማያመሰግን ቀማኛ መሆኑን ምነው ዘነጋነው? እግዚአብሔርን የሕይወታችን እስትንፋስ ልናደርገው ሲገባን ምነው የእሳት አደጋ ሠራተኛችን አደረግነው? እርሱ የማያስፈልገን ወቅትና ቦታ የለም:: ቃሉም እንዲህ ይለናል:- *«ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና»* (ራእይ. 2:4)::

የዛሬ ጤንነት ሁልጊዜ አይኖርም፣ የዛሬ ማግኘትም ሁልጊዜ አያኮራም፣ የዛሬ ወዳጆችም ሁልጊዜ አይከቡንም፣ የዛሬ ውበትም ፀንቶ አይኖርም:: እንኳን ገንዘባችን እኛም የማንኖርበት ቀን አለና ጓዴ ሆይ ተመለስ! ቃሉም:- *«ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል ስለሆንህ፥ ጉስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ . . . »* ይለናል (ራእይ 3:17)::



አንድ ሰው:- *«ይህ ዓለም:- የምሥራች ቃልና የመርዶ ቃል የያዘ መልእክተኛ ነው:: ዛሬ ጠዋት ሹመትህን ካበሰረህ ነገ ጠዋት ሞትህን ያረዳሃል»* ብለዋል::

## የዛሬ ውድቀት የሁልጊዜ ውድቀት አይደለምና

## እንነሣ

እግዚአብሔር ለምን በደልክ? ሳይሆን ለምን አልተመለስክም? የሚል አምላክ ነው:: ታዲያ ለምን ጨለመብህ? ከእነዚህ ክፉ አድራጊ ባልንጀሮች ሌላ የተሻለ ሰው ለምን አልታይም አለህ? ለምን ዞረብህ? አሁን በኃጢአት ከምታገኘው የበለጠ ደስታ አለልህ:: ለምን ትቅበዘበዛለህ? ከዚህ የሞት ኑሮ ሊያድንህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶልሃል::

በዓለም ላይ አንተን ከነማንነትህ የሚቀበሉህ እጆች የሉም:: የክርስቶስ እጆች ግን በፍቅር እየደሙ ተዘርግተውልሃል:: የተዘረጉ እጆች ብታገኝ እንኳ እንደ ክርስቶስ እጆች በፍጹም አይሆኑም:: ወዳጅህ ከፊት ለፊትህ እጁን በዘረጋልህ ሎጥር ያንተም እርምጃ ይፈጥናል:: የክርስቶስ እጆች ግን ያውም በምስማር ተቸንክረው ተዘርግተውልሃልና ወደ ዘላለም እቅፍ ግባ! ወዳጅ እያለህ ብቸኛ፣ አገር እያለህ ስደተኛ ለምን ትሆናለህ?

እንደ ነቢዩ:- *«ጠላቴ ሆይ ብወድቅ እነሣለሁና፥ በጨለማም ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛልና በእኔ ላይ ደስ አይበልሽ»* (ሚክ. 7:8) በል:: ደግሞም *«እግዚአብሔር አምላኬ ጨለማዬን ያበራል»* (መዝ. 17(18):28) እያልክ የድል ቋንቋ ተናገር:: የዛሬ ውድቀትህ የሁልጊዜ ውድቀት አይደለምና ተነሥ::

## የዛሬ ስህተት የሁልጊዜ አይደለምና

## እንቀበለው

ወንድማችንን የምንወደው እስካልበደለን ድረስ ነው? ፍቅራችን ይቅርታ የሌለው ከሆነ እውነተኛ ፍቅር አይደለም:: እስቲ እግዚአብሔር ለእኛ አንድ ዕድል ብቻ እንዳልሰጠን እናስብ:: እንደውም በየቀኑ ሁለተኛ ዕድል ይሰጠናል:: እኛ ግን ለወንድማችን በሕይወት ዘመናችን እንኳ አንድ ዕድል ለመስጠት ፈቃደኛ



www.ethiopinorthodox.org

አይደለንም:: ጴጥሮስ ሁለተኛ ዕድል ባይሰጠው ኖሮ በሮም አደባባይ የቊልቊሊት በመስቀል ጌታውን አያከብርም ነበር:: እኛም ካልበደሉን ሰዎች ይልቅ ሁለተኛ ዕድል የምንሰጣቸው ሰዎች ታማኝ ወዳጆች እንደሚሆኑልን አንዘንጋ::

እግዚአብሔር ይመለሳል ብሎ የሚጠብቀውን ሰው እርሱ ዋጋ የለውም ማለት ትልቅ ኃጢአት ነው (ማቴ. 5:21):: እግዚአብሔር ከኃጢአተኞች ጋር ጉዳይ አለው:: አረመኔውና ሰካራሙ ምን እንደሚሆን አናውቅም:: እግዚአብሔር ሠርቶት ለክብሩ ሊያቆመው ይችላል:: የዛሬ መውደቅ ያን ሰው የዘላለም ውዳቂ አያሰኘውም::

## ሕይወት እንግዳ ናት

ነቢዩ የመንፈስ ምሪት ስለ ነበረው ስለ ጌታችን አኗኗር ሲናገር:- *«ዓይኑ እንደምታይ አይፈርድም፣ ጆሮውም እንደምትሰማ አይበይንም»* (ኢሳ. 11:3) ብሏል:: ዓለም የሚፈርደው /የሚወስነው/ በማየትና በመስማት ነው:: ክርስቶስ ግን በማየትና በመስማት አይወሰንም ነበር:: እኛም እንደ እርሱ በመንፈስ ምሪት እንጂ በማየትና በመስማት ልንወሰን (ልንበይን) አይገባንም::

በሕይወት ውስጥ ያለውን ነገር እስክናውቅ ከፍርድ እንታቀብ:: ነገ ምን እንደሚሆን አናውቅም:: ሰዎችም ነገ ምን እንደሚሆኑ አናውቅም:: ስለዚህ ትንሹን ነገር በማየት ሕይወትን አንወስናት! ነገ የእግዚአብሔር ምሥጢር ናት:: አዎ ተስፋችንን ከሚመቱ ነገሮች አንዱ በዛሬው ሁኔታ ፍርድ መስጠታችን ነው:: ቃሉ የተስፋ መስኮታችን ነው:: የክርስቶስ ፍቅር የተስፋችን ኃይል ነው:: ትዕግሥት ማለት የማይበርድ ተስፋ ማለት ነው:: ትዕግሥተኞች ስንሆን ተስፋችን አይቀዘቅዝም::

## እናስተውል

የእግዚአብሔር ቃልና የክርስቶስ ፍቅር በነፍሳችን እስካልፈሰሰ ድረስ ተስፋ የማድረግ አቅም የለንም:: መርፌው በቀደመበት ክሩ ይከተላል:: በመርፌው ላይ ታስሯልና:: እኛም ክርስቶስ በሄደበት ሁሉ ለመሄድ በእርሱ ላይ በእምነትና በፍቅር መታሰር አለብን:: ሁሉን የሚመረምር ብርሃን፣ ሁሉን ያደራጀ ጥበብ፣ የድሆች ጌጥ፣ የምእመናን መዝገብ፣ ቸር ጠባቂ፣ ትሑት ንጉሥ፣ ኃይለኛ አምላክ፣ የሚመጣ ተስፋ፣ የዘላለም አባት እጅግ





ታዛዥ፣ የዋህ ትሑተ ልብ፣ በመለኮቱ የአብ ልጅ (ወልደ አብ) በሰውነቱ የማርያም ልጅ (ወልደ ማርያም)፣ የተስፋ አየር የጽድቅ ፀሐይ፣ የኃጢአተኞች ወዳጅ የምስኪን አለኝታ፣ የጥበብ ሰባኪ የሰላም አለቃ፣ ሕይወት ሰጪ የኃይላት ጌታ፣ በሰልፍ አሸናፊ የስደተኞች መኖሪያ፣ የድሆች አባት የሞኞች ተሟጋች፣ መድረሻው መንገድ፣ ነጻ የሚያወጣው እውነት፣ የዘላለም ደጅ የማይጠፋ ሕይወት፣ እጅግ የሚታገሥ፣ የማይጨረስ ቸርነት፣ የመላእክት ደስታ፣ የጥማተኞች እርካታ፣ የክብር ንጉሥ፣ የደስታ ፀዳልና የንጽሕና ወዳጅ፣ የደናግል ተስፋ፣ የምእመናን መዝገብ፣ የሃይማኖት ፋና፣ የአበው ንጉሥ፣ የሊቃውንት መምህር፣ የቅዱሳን አክሊል፣ የመኖር ኃይል፣ ... እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የተስፋችን መሠረት ሁሉ በሁሉ የሆነው ይህ ጌታ ነውና ተስፋችን የማይበርድ ይሁን::

## ጸሎት

ምን ያህል እንደምትወደኝ በቃል ሳይሆን በችንካርህ ምልክት የነገርከኝ፣ ፍቅርህን በብዕር ሳይሆን በደምህ የጻፍክልኝ፣ መሃይሙ እኔ ያነበብኩህ የሕይወት ፊደል ጌታ ክርስቶስ አመሰግንሃለሁ:: ስምህ ሲጠራ የሚጠሉህ ይሸሹ፣ ሞት ይደንግጥ፣ ደዌያትም ይገሰጹ፣ መቃብር ይከፈት፣ ሙታንም ያምልጡ፣ ሸባዎች ይተርተሩ ዕውሮች በብርሃን ይመላለሱ፣ ደንቆሮዎች የሕይወትን ዜማ ይስሙ፣ ዲዳዎች ለክብርህ ይዘምሩ፣ ሸካራ መንገዶች ይለስልሱ፣ በቀቢፀ ተስፋ ጨለማ የሚኖሩ የነጻነት አዋጅ ይስሙ:: የአብ መልእክተኛ፣ የምክሩ አበጋዝ ወልድ ሆይ አንተን ብሎ ሁሉን ማጣት ቀላል ነው:: ክርስቲያን የተባልኩብህ ስሜ ሆይ ስሜ አንተ ነህና ስሜ ይጠፋል ብዬ አልሰጋም:: ባንተ በንጉሥ ብታማ ዕድሌ ነውና አልፈራም:: የሕይወት ፀዳል ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ለማያውቁህ ራስህን ግለጥላቸው:: ተስፋ ነፍስ ላጡ የዘላለም መድኅን ሁንላቸው:: በአየሩ ላይ የተለቀቀውን ተስፋ መቍረጥ በተስፋህ አየር አንተ ለውጠው:: በተገፋፋንበት ዘመን ፈንታ እንድንተቃቀፍ እርዳን:: የመንፈስ ማሰሪያ ያለህ አንተ ነህና ለዘላለሙ አሜን!



www.ethiopinorthodox.org

## ምዕራፍ ሃያ አንድ
## ተጨማሪ ሙከራ

ትዕግሥት ማለት ያልተሸበረ መንፈስና የማይበርድ ተስፋ ነው ብለናል:: ትዕግሥት ከዚህም ያለፈ ትርጉም አለው:: «ተጨማሪ ሙከራ ማድረግ ነው::» ትዕግሥት እጅና እግርን አጣጥፎ ጊዜን ወይም እግዚአብሔርን መጠበቅ ማለት አይደለም:: ትዕግሥት እንቅስቃሴ ነው:: ሁላችንም እንደሚገባን የወደቀ ሰው ዳግመኛ ለመነሣት የሚያደርገው መፍጨርጨር፣ የከሰረው ሰው እንደገና ውጤታማ ለመሆን የሚያደርገው ሩጫ ትዕግሥት ወይም ውስጣዊ ብርታት ነው::

ብዙዎቻችን ተጨማሪ ሙከራ ማድረግ አንፈልግም:: ለሰበባችን አንድ ነገር እናደርግና በቃ አልሆነም ምንም ማድረግ አልችልም እንላለን:: ራሱ ማድረግ የማይፈልግ ሰው ግን ሌሎች እንዲያደርጉለት ይሻል:: በሌሎች ልፋት መብላት፣ በሌሎች መጋፈጥ ተጋርዶ መኖር ይሻል:: ይህ ግን ራስን ለማኘና አካለ ስንኩል ማድረግ በራስ ላይም ውድቀትን መፍረድ ነው:: የምንኖርበት ዓለም የሙከራ ዓለም ነው:: ጠዋት የሚኀርፈው ሠራተኛ ሁሉ ማግኘትን ተስፋ አድርጎ ብቻ ሳይሆን ከትላንቱ ዛሬ እንደሚሻል አምኖ ይወጣል:: ይህንን ባያምን የቀኑን ፀሐይ እንኳ ለማየት ባልደፈረ ነበር:: ዛሬ ባይሳካም ነገ ደግሞ በማለዳ ለመውጣት ያስባል:: ሙከራዎች ከስኬት ላይ ያደርሳሉ:: ከዚህ ሁሉ በላይ የመኖርን ፍላጎት ይጨምራሉ:: ሙከራዎች ከጠራ ነገር ያደርሳሉ::

እንዳንሞክር ፈተና የሚሆንብን የመውደቅ ፍርሃት፣ የትላንት ክፉ ገጠመኝ፣ ተስፋ መቍረጥ ናቸው:: ሕፃን ልጅ በእግሩ ፀንቶ የሚቆመው ብዙ መውደቅ መነሣትን በማየትና ተስፋ ባለመቍረጥ ነው:: ከዚያም ደጋፊዎችን በመያዝ መንገዱን ይለማመዳል:: በሁለት እግር የሚሄድ ሰው ልምምድ ያስፈልገዋል:: በአራት እግር የሚሄዱ እንስሳት ግን በተወለዱ ቀን ይቆማሉ:: በሁለት እግር በኵራት መሄድ ከባድ ነው:: ከልምምድና ከሙከራ በኋላ ግን በሁለት እግር መሄድና መሮጥ ይቻላል:: ዓላማችን መቆም ከሆነ እስክንቆም ድረስ መሞከር አለብን:: ዓላማችን ውድቀት ከሆነ ግን አለመሞከር እንችላለን:: መሞከር ብቻ ሳይሆን በመራመድ የቀደሙንን መያዝ ወይም ምክራቸውን መቀበል ያስፈልገናል:: በመራመድ የቀደሙን ሰዎች በአካል ብቻ ሳይሆን በመጽሐፋቸውና



በምክራቸውም ይደግፉናል:: በእውቀት ለመቆም አዋቂዎችን በትሕትና መቅረብ፣ በሀብት ለመቆም አዛገሮቻችንን በአክብሮት ማገልገል ይገባናል:: አዋቂዎችን የምንፈልገው ባወቅነው ላይ ጨምረው እንዲነግሩን ከሆነ ምንም አናገኝም:: ራሳችንን ባዶ አድርገን ካልቀረብን አዋቂዎች ሊቀርቡን አይችሉም:: እኛም የሚነግሩንን ልንይዝ አንችልም:: እንዲሁም መታዘዝን ያላወቀ አዛዥ መሆን አይችልም:: ስለዚህ በእውቀት ለመብሰል አዋቂዎችን በትሕትና መቅረብ፣ በሀብት ለመቆም አዛገሮቻችንን በአክብሮት ማገልገል ይገባናል::

ዕለቱን ተወልዶ ዕለቱን ብቁ የሚሆን ተግባር የለም:: የተፈጥሮ ጊዜውን ሲጠብቅ ግን ደስታው እንደ ፀሐይ ብርሃን እየፈካ ይመጣል:: መሠረት ያለው በመሆኑ ፀንቶ ይቆያል:: ደክመንበታልና ደስ ያሰኛል:: ተአምር ናፋቂዎች ብንሆንም ተፈጥሮም የተአምራት አካል ነውና ሂደትን ማክበር ይገባናል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀስ በቀስ አደገ እንጂ አምላክ ነኝ ብሎ ዕለቱን አላደገም:: የተፈጥሮን የዕድገት ሥርዓት ጠበቀ (ሉቃ. 2:52):: ቀስ በቀስ ማደግ ተፈጥሮአዊ ነው::

ብዙ ትልልቅ ሰዎች ለደረሱበት ከፍታ የበቁት ከብዙ ትዕግሥት ወይም ሙከራ በኋላ ነው:: ከብዙ ሙከራ በኋላ ትልቅ የሆኑ ሰዎች፣ ጊዜ ካነሣቸው ደግሞም ገጠመኝ ካገነናቸው ዝነኞች ይልቅ ክብራቸውን እንደ ጠበቁ ማለፍ ችለዋል:: ለትዕግሥተኞች የዛሬ አለመሆን ሌላ አቅጣጫ እንዲያዩ ማስተዋላቸውን ያድሰዋል እንጂ መሬት ላይ ተቀምጠው ስለ ውድቀታቸው እንዲተክዙ አያደርጋቸውም:: የአብርሃም ሊንከንን ታሪክ ብንመለከት ትዕግሥት ብዙ ሙከራ እንደሆነ በመጨረሻም ድልን እንደሚያተርፍ ያስተምረናል:: ስለ አብርሃም ሊንከን ያነበብኩትና አሁንም ድረስ የሚመስጠኝ ታሪክ አለ:: አብርሃም ሊንከን:-

- በ32 ዓመቱ ለፓርላማ ምርጫ ተወዳድሮ ወደቀ::
- በ35 ዓመቱ ፍቅረኛው ከዚህ ዓለም በሞት ተለየችው::
- በ36 ዓመቱ በነርቭ በሽታ ተያዘ::
- በ38 ዓመቱ ለአስመራጭነት ተወዳድሮ ወደቀ::
- በ40 ዓመቱ ለምርጫ ቀርቦ ሳይሳካለት ቀረ::
- በ48 ዓመቱ በኮንግረስ ምርጫ ተወዳድሮ ወደቀ::
- በ50 ዓመቱ ለሕግ መወሰኛ ም/ቤት ተወዳድሮ ወደቀ::
- በ56 ዓመቱ ለም/ ፕሬዝዳንትነት ተወዳድሮ ወደቀ::
- በ58 ዓመቱ እንደገና ለሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ተወዳድሮ ወቀደ::



www.ethiopinorthodox.org

ተስፋ ሳይቆርጥ ታግሦ በመጨረሻ በ1860 ለፕሬዝዳንትነት ተወዳድሮ ተመረጠ። የጥቍሮችን መብት ያስከበረና አሜሪካንን አንድ ያደረገ ትልቅ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ሆነ። አብርሃም ሊንከን በ32 ዓመቱ ለፓርላማ ምርጫ ተወዳድሮ እንደ ወደቀ በቃኝ ለእኔ ያልተሰጠ ነው ማለት ይችል ነበር። የሚወዳት እፍቃሪው በሞት ስትለየው ዓለም ለምኔ ብሎ ሁሉን ነገር መተው ይችል ነበር። በአደባባይ የሚታወቁ ዘጠኝ ሙከራዎቹ መልሳቸው ውድቀት ነበር። በዐሥረኛው ሙከራው ግን ካሰበው ላይ ደረሰ። ለእነዚያ መከረኛ ጥቁሮች መብት ቆመ። የእርሱ ጅምር ዛሬ ከፍጻሜ ላይ ደርሶ አሜሪካ በማይታመን መልኩ በጥቁር ለመመራት በቃች። ወድቆ ለመቅረት ካለን ምክንያት ለመነሣት ያለን ምክንያት ይበልጣል። እግዚአብሔርና ደጋግ ሰዎች እየጠበቁን ነውና።

እንስሳት፣ አራዊትና ነፍሳት እንኳ ሳይቀሩ የሚፈልጉትን እስኪያገኙ ተስፋ አይቆርጡም። ድጋሚ ይሞክራሉ። በመጨረሻ ካሰቡት ላይ ይደርሳሉ። እነርሱ ለባውያን ወይም በአሳብና በዕቅድ የሚመሩ አይደሉም። በደመ ነፍስ እውቀታቸው ግን መሞከር ተገቢ እንደሆነ ያምናሉ። ነብርን ብንመለከት ከብዙ መንጋ ውስጥ አንዷንና መጀመሪያ ያያትን እርሷን ብቻ ያባርራል። መንጋ ሙሉ የሚያባርር ነብር የለም። እኛ ብዙ ነገሮችን እንጀምራለን። ብዙ ነገሮችን ከግብ ለማድረስ እንጥራለን። ውጤቱ ግን ፍሬ አልባ ነው። ጉንዳን የምትፈልገውን ፍሬ ባሪያ ሆና የምትሸከመው፣ ኋላ በክረምት ወራት ጌታ ሆና ለመብላት ነው። ዛሬ በወጣትነት ዘመናቸው የሚደክሙና የሚሠሩ የሽምግልናቸውን ስፍራ ያመቻቻሉ። እኛ ከእንስሳት፣ ከአራዊትና ከነፍሳት ይልቅ በእውቀት ተፈጥረናል። ስለዚህ ልባሞች መሆን ይገባናል። የምንጠቀምበት ሥልጣኔ ሁሉ የብዙ ሙከራዎች ውጤት ነው። ለእኛ ለማቅለል እነዚያ ትጉሆች ብዙ ሞከሩ። እኛስ በየትኛው የሕይወት ክፍተት ለመቆም አሳብ አለን? ለዚህ ግን የምንበቃው በአንድ ሙከራ ተደናግጠን በመቀመጥ ሳይሆን ብዙ በመሞከር ነው። በጅምር ፍጹም ነገር የለም። መደጋገም ግን ፍጹምነትን ይወልዳል። እግዚአብሔር እንደገና መሞከርን በሰው ውስጥ ብቻ ሳይሆን በእንስሳትና በአራዊት ደግሞም በነፍሳት ውስጥ እንኳ ማስቀመጡ ቶሎ ተስፋ መቍረጥን የማይወድ አምላክ ለመሆኑ ማስረጃ ነው።

አንድ ትዕግሥቱ የሚፈተንበት ሰው ነበር። ብዙ ነገሮችን ይጀምራል፣ በስልቹነት ያቋርጣል። መታገልን ፍጹም አይፈልግም። መሞከርም የሞት ያህል ይሰማዋል። ታዲያ ከዕለታት በአንዱ ቀን አንድ ዛፍ ሥር ቁጭ ብሎ ከእግሩ ሥር ያሉትን ተንቀሳቃሽ ፍጥረቶች ማየት ጀመረ። አንድ ጉብረ ጉንዳንም አንድ የስንዴ ፍሬ



www.ethiopinorthodox.org

አገኘና ወደ ማደሪያው ሊወስደው ፈለገ። ለመውሰድ ግን አስቸግሮት ዳግም ይሞክር ነበር። ፍሬውን ይዞ ለመሄድ ቢያስብም ከመንገዱ ላይ ከዛፍ የወደቀ የእንጨት ቁራጭ ተጋድሞ ስለ ነበር ፍሬውን ተሸክሞ የእንጨት ቁራጩ ላይ ተሻግሮ መሄድ አቃተው። ሳይሰለች ደጋግሞ ሞከረ። ስልሳ ዘጠኝ ጊዜ ሲሞክር ለመሻገር ጥቂት ሲቀረው እየደጋገመ ይወድቅ ነበር። ተስፋውን አበረታና በሰባኛው ሙከራ ያንን የስንዴ ፍሬ ተሸክሞ ወደ ቤቱ አገባው።

እንዲህ ሲያደርግ ያ ወጣት ያይ ነበርና በጉብረ ጉንዳኑ ትዕግሥት ተገረመና እርሱም ትዕግሥትን ተማረ። በሥራው የሚሳካለት፣ በጦርነት የሚያሸንፍ ትልቅ ሰው ሆነ። ጅምሩን የሚፈጽም፣ ትግሉን የሚያሸንፍ መሆኑን ያዩ ሰዎች ተገርመው ቢጠይቁት፦ «ወጣት ሳለሁ ይህንን ከአንድ ጉብረ ጉንዳን የተማርኩት ነው» አላቸው ይባላል። እንግዲህ ዛሬ ያለብን ትግል ከጉብረ ጉንዳን ላለማነስ ነው።

የሕይወት መንገድ «አልጋ ባልጋ ነው» ተብሎ የሚዜምለት አይደለም። የሕይወት መንገድ ብዙ ከፍታና ዝቅታ፣ መብዛትና ማነስ ያለበት ነው። ሁሉም ነገር ተሰናድቶ፣ ቀራርቦና በስሎ የሚጠብቀን አይደለም። «ድል ያለ ትግል አይገኝም።» የሚያታግሉ ነገሮች በመጨረሻ ላይ ለፍሬው ደስታን ይጨምራሉ። ከዚያ ሁሉ በላይ ታጋዩን ጠንካራ ያደርጉታል።

ስለ ዕድል ብዙ በሚወራበት ማኅበረሰብ የምንኖር መሆናችንን አምናለሁ። እኔ ዕድል የለኝም፣ ዕድሌ ጠማማ ነው የምንል ነን። ዕድል ግን ምንድነው? በአጋጣሚ የሚሆንልን ደግነት ይሆን? ቃሉ፦ *«በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ* (ያዕ. 1፡17) ይላል። ከሰጪው ከእግዚአብሔር እንቀበላለን እንጂ ለእኛ የሚቸረን ዕድል የሚባል አደላዳይ የለም። መስጠት መንሣት የእግዚአብሔር ሥልጣን ነውና። ይልቁንም የአማንያን ዕድል እግዚአብሔር ነው። ነቢዩ፦ *«እግዚአብሔር የርስቴ እድል ፈንታና ጽዋዬ ነው፥ ዕጣዬንም የምታጠና አንተ ነህ። ገመድ ባማረ ስፍራ ወደቀችልኝ፥ ርስቴም ተዋበችልኝ»* (መዝ. 15(16)፡5-6) እንዳለ እግዚአብሔርን ዕድላችን ስናደርግ የበሰለ ማዕድ፣ የተከፈተ መንገድ እንደሚገጥመን እንረዳለን። ዕድላችን እግዚአብሔር ከሆነ ዕድላችን አንድ አይደለም። ሚሊዮንም አይደለም። ከዚያ በላይ ነው። እግዚአብሔር መልካም እንዲያደርግልን ተግተን መማር፣ መሥራትና መሞከር አለብን። ትዕግሥት ማለት ተጨማሪ ሙከራ ማድረግ እንጂ እጅና እግርን

አጣጥሮ መቀመጥ አይደለምና:: በርግጥ አምላካችን የሰማይ ወፎችን የሚመግብ ነው:: ነገር ግን የሰማይ ወፎችም ምግባቸውን ለማግኘት ይራራጣሉ:: ዛሬ ማድረግ ስለማንችለው ማልቀስ ተገቢ አይደለም፣ ዛሬ ማድረግ የምንችለውን ስናደርግ ነገ ማድረግ የማንችለውን እናደርጋለን::

## ተግተን እንሥራ

ከእግዚአብሔር ትእዛዝ አንዱ ሥራ ነው:: ብዙ ሰዎች እንደሚያስቡት ሥራ መርገም አይደለም:: ሥራ በረከት ነው:: በርግጥ ለአዳም:- *«በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ»* (ዘፍ. 3:19) ተብሏል:: ይህንን ቃል በመጥቀስ ሥራ ርግማን ነው የሚሉ አሉ:: ነገር ግን አዳም ከመበደሉ በፊት ከተፈጠረበት ዓላማ አንዱ ሥራ መሆኑን ቃሉ ይነግረናል (ዘፍ. 2:15):: ታዲያ ርግማኑ ምንድነው? ስንል ሥራው ሳይሆን የሥራው ጫናና ውጤቱም አነስተኛ መሆኑ ነው:: ሥራችን በረከታችን ነው:: በአደባባይ የሚሰብከውን ሰባኪ ያህል የጽዳት ሥራችንን በታማኝነት መሥራት አገልግሎት ነው:: የእግዚአብሔር ልጆች ሥራቸውን በታማኝነት በመሥራት ሊታወቁ ይገባል እንጂ ከንቱ ነው በሚል ፈሊጥ ስንፍናቸውን ሊያዳብሩት አይገባም:: ጊዜያዊ ተግባር አለን ዘላለማዊ ተግባር አለን:: ሁለቱንም ማከናወን ይገባናል:: ጊዜያዊ ተግባራችን ሥራችን ነው፣ ዘላለማዊ ተግባራችን መንፈሳዊው አገልግሎታችን ነው:: ስንሠራ አሥራት በኵራታችንን ማውጣት እንችላለን:: ስለዚህ የእግዚአብሔር ሥራ ይፋጠናል:: ስንሠራ የድሆችን መባ መስጠት እንችላለን:: ስለዚህ ብዙዎችን ከረሀብ እናድናለን:: በተግባራችን ሁሉ እግዚአብሔርን እያስቀደምን ተግተን ስንሠራ ባለጉዳያችንን በመልካም ሁኔታና በቶሎ ማስተናገድ እንችላለን::

የሚሠራ ሰው የተከበረ ሰው ነው:: ለኃጢአትም ጊዜ የለውም:: ደካሞችን መርዳት፣ ሕመምተኞችን ማሳከም ይችላል:: የሚሠራ ሰው መንፈሱ ጠንካራ ነው:: የሚሠራ ሰው ጭንቀቱ አነስተኛ ነው:: አካሉ ይዳብራል:: ጤንነቱም የተጠበቀ ነው:: ከቅምጥል ጌቶች፣ ሠራተኛ ሎሌዎች ሰውነታቸው እንደ ፈለጉት ይታዘዝላቸዋል:: ጤነኞች ናቸው:: ዕድሜያቸው ከጌቶቻቸው ይረዝማል:: የገንዘብ ሀብት ያላቸው ጌቶች ያላቸውን እንኳ አይበሉም:: የእነርሱን ሀብት በደስታ የሚበሉት ሠራተኞቻቸው ናቸው:: የዚህ ምሥጢሩ መሥራታቸው ነው:: ከማይሠራ ጌታ፣ የሚሠራ ሎሌ ባለጠጋ ነው:: የጤና ሀብታም ነው::



ሀብት የሚበዛውና ተጠብቆ የሚኖረው በሥራ ነው:: ያለ ሥራ የመጣ ሀብት ተመልሶ ይሄዳል:: ዳግም አይመጣም:: በኃጢአት የሚበለጽጉ አሉ:: በሥራ የሚበለጽጉም አሉ:: የኃጢአት ብልጽግና ግን ታይቶ ጠፊ ከመሆኑም በላይ ቅጣትንና ጭንቀትን ሳያመጣ አይቀርም:: ስንፍና ኃጢአት ነው:: እግዚአብሔር ሰነፍ ልጆች የሉትም:: የተሰጠንን ክቡር ጊዜ በመኝታ፣ በዋዛ ፈዛዛ እንዳንጨርሰው መጠንቀቅ አለብን:: ጊዜ ክቡር ነው:: በጸጋ እንጂ በገንዘብ አይገኝም:: እግዚአብሔር የሚፈርድብን በሠራነው ኃጢአት ብቻ ሳይሆን ባላደረግነውም መልካም ነገር ነው::

እንስሳት እንኳ ሳይቀሩ እስከ ጊዜ ሞታቸው ያገለግሉናል:: ውሻ ተግቶ ይጠብቃል:: በሬ ባለመታከት ያርሳል:: ከእነርሱ ይልቅ ይህች ዓለም የእኛ ናት:: ባለአደራዎቹም እኛ ነን:: ከእነርሱ ይልቅ አእምሮ አለን:: ስለዚህ ለምንኖርበት ዓለም አስተዋጽኦ ልናደርግ ይገባናል:: ሥራችንን መሥራት ያለብን እግዚአብሔር እንደሚያየን ሆነን ነው:: ምክንያቱም ሥራችን ስጦታችን ነውና:: የሥራ ዋጋው ደሞዙ ብቻ አይደለም:: አሳብን መጋራቱ ሥራ አለኝ ብሎ ከቤት መውጣቱ የሥራ ዋጋው ነው:: ብዙ በሠራን ቍጥር የጠራ እውቀት እናገኛለን:: ጉልበታችንም ይጠነክራል:: አሊያ የተማርነው እየጠፋን፣ ጉልበታችንም እየሟሟ ይመጣል:: ጉልበት ባንክ ቤት የሚቀመጥ፣ ዛሬ አጠራቅመውት ነገ የሚወልድ አይደለም:: እግዚአብሔር ሁሉን ሰጥቶናል፣ መሥራት በሚገባን ነገር ተአምር መጠበቅ የለብንም:: ዛሬ ልንሠራው የምንችለውን ማድረግ አለብን:: የትልቅ ነገር መነሻው ትንሽ በመሆኑ ትንሹን ተግባር በትጋት ማከናወን ይገባናል:: ብዙ ሀኬተኞችና ሰነፎች ቢኖሩም ዓለሙ ግን እየቀጠለ ያለው በትጋትና በሩጫ ነው:: ሰነፎች የሌሎችን ትጋት ይበላሉ እንጂ ስንፍናቸው እያኖራቸው ሆኖ አይደለም::

በጽሕፈት ሥራ፣ በኃላፊነት ስፍራ ባጠቃላይ የአእምሮ ጫና ባላቸው የሥራ ተግባሮች የሚሳተፉ ሰዎች የአእምሮአቸውን ጫና ለመቀነስ ተግባረ- ሥጋን ማከናወን አለባቸው:: ሥራ መዝናኛም ነው:: አእምሮን ነጻ ያደርጋል:: የማያስከፍል ስፖርት ቤት ቢኖር ሥራ ነው:: ገበሬ የአዝመራውን ጊዜ ዝናብና ጭቃ ተፀይፎ ቢተኛ በመከር ወቅት ይለምናል:: በወጣትነት ዘመናችንም ሥራን ከናቅንና ከጠላን በሽምግልናችን በሰው እጅ እንወድቃለን:: የቅዱስ ጳውሎስን መመሪያ በሕይወታችን ልንይዘው ይገባናል:- *«ሊሠራ የማይወድ አይብላ»* (2ተሰ. 3:10)::

ተማሪ ከሆንን ተግተን መማር አለብን:: አገልጋይ ከሆንን ተግተን ማገልገል አለብን:: የቀን ሠራተኛ ከሆንን ተግተን መሥራት



www.ethiopinorthodox.org

አለብን:: ሐኪምም ከሆንን ተግተን በሽተኛን መርዳት፣ የቢሮ ሠራኛም ከሆንን ሥራችንን በአግባቡ መሥራት አለብን:: እግዚአብሔር ባስቀመጠን ስፍራ ሁሉ በታማኝነት መገኘት ይገባናል:: ሥራችንንም በትምህርት ብቁ ማድረግ፣ በትጋትም መፈጸም ይገባናል:: የምግብ ለነገ እንጂ የሥራ ለነገ አይጠቅምምና ተግተን መሥራት ይገባናል:: ድካም ያለው ከልባችን ላይ እንጂ ከጉልበታችን ላይ አይደለም:: ሥራ ለቅድስናም ደጋፊ ነው:: የሚሠራ ሰው አሳቡ በሥራ ስለሚያዝ በሰይጣን ፈተና ቶሎ ተማርኮ የሚወድቅ አይደለም:: አእምሮ ሥራ ሲፈታ ግን ሰይጣን በቀላሉ ያጠቃናል:: ከዚህ በተቃራኒ ሥራቸው ጣኦት የሆነባቸው፣ የሚኖሩት ብዙ በማከማቸት እየመሰላቸው አእምሮአቸውን እስኪስቱ፣ ትዳራቸውን እስኪዘነጉና ልጆቻቸውን እስኪበትኑ፣ አምልኮአቸውን እስኪለቁ የሚሮጡ አሉ:: እነዚህም ከሰነፎች ትይዩ ባለው በዚያኛው ጫፍ ላይ የተቀመጡ በመሆናቸው ማሰብ ይገባቸዋል::

## ከወደቅንበት እንነሣ

ስለ እግዚአብሔር ብርታት ከተነገሩት ቃሎች አንዱ እርሱ ለሙታን ሕይወትን የሚሰጥ፣ የሌለውንም እንዳለ አድርጎ የሚጠራ የሚለው ቃል ማራኪ ነው (ሮሜ. 4:17):: እንደ ወደቅን ከተሰማን የማይወድቅ አምላክ አለን:: የወደቁትን የሚረግጥ ሳይሆን ከመቃብር አውጥቶ ስምና ታሪክን የሚለውጥ ጌታ አለን:: እግዚአብሔር የትንሣኤ አምላክ ነው:: በአንድ ወቅት አንድ የቤተ ክርስቲያን ልጅ ሰባኪውን አግኝቶ «ወድቄአለሁ ምንም ተስፋ የለኝም» ብሎ ሲነግረው ሰባኪው «ወድቀሃል?» ብሎ ጠየቀው:: ያም ሰው «ወድቄአለሁ፣ ወድቄአለሁ» ብሎ መለሰለት:: ሰባኪውም:- «ታዲያ ምን ትጠብቃለህ እጅህን ዘርጋ እርሱ ጎትቶ ያነሣሃል» በማለት መልሶለታል::

በብዙ የሕይወት መንገዶች አልፈናል:: ብዙ ውድቀትም ገጥሞን ራሳችንን፣ ሰዎችንና እግዚአብሔርን አፍረን ተቀምጠን ይሆናል:: ውድቀታችን ሰው መሆናችንን የሚገልጥ ነው:: የሰው ድካሙ ባሕርያዊ ነው:: ከእኛ ምንም በጎ ነገር የለም:: በጎነታችን እግዚአብሔር ብቻ ነው (መዝ. 15(16):2):: የምንኖርበትና የምናገለግልበት ብቃትም እርሱ ብቻ ነው (1ጴጥ. 4:11):: እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ስህተታችንን አምነን እንድንፀፀት ነው:: ከዚያ በኋላ ድርሻው የእርሱ ነው:: አመዱን አራግፎ ወርቅ መደረብ፣ ትቢያውን አስወግዶ ክብር ማልበስ፣ ስምን ቀይሮ ከሰው ቊጥር መደመር ያውቅበታል (መዝ. 29(30):11፣112(113):7-9)::



መጽሐፍ ቅዱስ የመጽናናት መጽሐፍ የሆነው በመጀመሪያ:- የተጻፈበት ዓላማ የሰውን ብርቱነት ለማስረዳት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ኃይል ለመግለጥ በመሆኑ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በኃይሉ ደካሞችን ረግጦ የሚያልፍ ሳይሆን ውዳቂዎችን የሚያነሣ አምላክ እንደሆነ ይነግረናል:: ይልቁንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመከራው ወቅት የሸሹትን፣ የካዱትን ደቀ መዛሙርት ከትንሣኤው በኋላ ደጋግሞ እንደ ፈለጋቸው ይነግረናል (ሉቃ. 24.):: ፍቅራቸው ተፈትኖ የወደቀ ቢሆንም በሞት ያልተሸነፈው ያ ፍቅር ግን ሊፈልጋቸው መጣ:: እርሱ:- *«እንደ ገና ተገለጠላቸው»* (ዮሐ. 21:1) ይላል:: የእንደገና አምላክ ነው::

የትላንት ዘማሪ የዛሬ ዘፋኝ፣ የትላንት ድንግል የዛሬ አመንዝራ፣ የትላንት አገልጋይ የዛሬ ቀራጭ ሆነን ይሆናል:: ኃጢአት ባሕርይው ዋጋ የለህም እያለ ተስፋ የሚያስቆርጥ፣ ካለህበት የተሻለ ኑሮ የለም እያለ ባሪያ የሚያደርግ ነው:: ወገኖቼ ብዙ የተሻለ አለ:: እስካሁን በኃጢአት እንዳልረካችሁ ኅሊናችሁ ይመሰክርላችኋል:: ኃጢአትም ቆይ ቀጥሎ ትረካለህ ይላችኋል:: ነገር ግን እንክርዳድ ዘርቶ ስንዴ ማጨድ፣ ኃጢአት ሠርቶ ሰላምን ማትረፍ አይቻልምና (ኢሳይ. 48:22) ዘመናችሁ ሳያልቅ ወደ ቤቱ ግቡ:: ቃሉ:- *«ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃልና፥ ይነሣማል»* (ምሳ. 24:16) ይለናል::

እግዚአብሔር ከታሪካችሁ ጋር ጉዳይ የለውም:: ጉዳዩ ከዛሬው እሺታችሁ ጋር ነው:: ስለዚህ ወደ ተዘረጋው እቅፍ በቶሎ ግቡ:: ነገ የእናንተ አይደለም:: ዛሬ ተመለሱ:: ወገኖቻችሁ ካጠገባችሁ ሲንሸራተቱና ሲያልፉ እያያችሁ ቀጥሎ የእናንተ ተራ መሆኑን ለምን አታስቡም? እግዚአብሔር እናንተን የሚወድ ልብ፣ እናንተን የሚቀበል እጅ አለው:: ምንም ሁኑ:: ከእርሱ ምሕረት በላይ የሆነ ኃጢአት አልሠራችሁም:: ኃጢአታችሁ ራሳችሁ ጋ ሲሆን ይገድላችኋል:: ወደ እግዚአብሔር ይዛችሁት ስትመጡ ግን ሸክሙን አውርዶ ነጻነት ይሰጣችኋል (ማቴ. 11:28):: ከእግዚአብሔር ጋር በብቃቱ የተገናኘ ማንም የለም:: የሰው ሁሉ መነሻ ታሪኩ ብላሽ ነው:: የሰው መነሻው አዳም ከሆነ እርሱ የወደቀ በመሆኑ የሁሉም ሰው ጅምሩ ብላሽ ነው ማለት ነው:: የተበላሸ ታሪካችሁን እግዚአብሔር ለዓላማው ይሠራዋል:: ያቆማችሁትን አገልግሎት ዳግም ለመጀመር አስቡ:: ያንን የተባረከ ባልንጀርነት እንደገና ቀጥሉት:: ዕድሜአችሁ ዕድላችሁ ነውና እንደ ወደቃችሁ አትቅሩ:: እናንተን ሊፈልግ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መቃብር የወረደው:: ከሙታን መንደር ውጡ:: በሕያዋን ተራራ ተቀመጡ:: እግዚአብሔር በእናንተ ላይ ያሰበውን ዓላማ እንዲፈጽም ዛሬ



www.ethiopinorthodox.org

ፈቃዳችሁን ስጡት:: ከሳሻችሁ ብዙ ቢሆንም ዳኛው ግን አንድ ነው:: እርሱ ደግሞ ይቅርታ ሰጪ ደግሞሞ የምሕረት አምላክ፣ የፍቅር ጌታ ነው::

አንድ ሰው «መሸነፍ የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉሙ መውደቅ ሳይሆን ወድቆ መቅረት ነው» ብሏል:: ሼክስፒርም፡- «ተስፋ በመቍረጥ አንድ ቦታ ከመቆም በተስፋ ሲጓዙ መኖር ይሻላል» ብሏል:: ትዕግሥት ወድቆ አለመቅረት ነውና ተነሡ!

## ገና ነው

ሕይወትን ሂጂና ቁሚ የሚላት የሕይወት ትራፊክ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ሕይወት በእኛ ፈቃድ ወይም በሰዎች ፈቃድ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ ትቀጥላለች:: ብዙ ጊዜ ተስፋ ከመቍረጣችን የተነሣ አሁንስ በቃ አልን:: እግዚአብሔር በቃ ሳይል ግን አይበቃምና ይኸው አለን:: «መኖር የሚፈልጉ እነ እገሌ እየሞቱ መኖር የማልፈልገውን ለምን አኖርከኝ?» እንላለን:: ሞት ግን ባንፈልገውም አይቀርም፣ ካልፈለግነው ግን የማናገኘው ብዙ ነገር በሕይወት ውስጥ አለና ያንን ልንፈልግ ይገባናል:: አንድ አባት፡- «ግደለኝ አትበሉ አኑረህ አሠራኝ ነው የሚባለው» ይሉ ነበር:: አዎ እየኖርን ያለነው እንደ እኛ ማን ኖሮ፣ እንደ እግዚአብሔር ማን ጠፍቶ? ሆኖ ነው:: በቃ የሚባልበት ጊዜ አለ:: እርሱም የሞት ቀን ነው:: በዚያን ቀን ለዚህ ዓለም ኑሮአችን ፍጻሜ እናገኛለን:: ታዲያ ከመሞታችን በፊት ለምን እንሞታለን? መልአከ - ሞት ሳይመጣ ተስፋ የመቍረጥ መልአክ - ሞትን ለምን እንጠራለን?

አብዛኛው ቋንቋችን ሁሉ የሸንፈት ነው:: «ዋጋ የለውም፣ አብቅቷል፣ የእኔን ነገር ተውት፣ እኔ ሰው አልሆንም» በሚሉ ቃላት ራሳችንን አስረናል:: እነዚህ ቃላት የሚራመዱ እግሮችን ሸባ፣ ሕያውን ልብ ሙት ያደርጋሉ:: ሰይጣን ካሰረው ይልቅ የገዛ ቃሉ ያሰረው ወገን ይበዛል:: ከልምዳችን መገንዘብ እንደምንችለው እነዚህን ቃላት ስንጠቀም ነገሮቻችን እየባሱና እየጨለሙ ይመጣሉ:: ለምን? ስንል በእነዚህ እምነት አልባ ቃላት የእግዚአብሔር መንፈስ ስለሚርቀንና ጠላት ስለሚከበን ነው::

የእግዚአብሔር ሰዎች ግን ልባቸውን በጌታ አምላክ ያበረታሉ እንጂ ሸንፈትን አይናገሩም:: መጽሐፍ ቅዱስ ከዳር እስከ ዳር በድል ቃላት ያሸበረቀ ነው:: ከእምነት ሰዎች አንዱ የሆነው





ካሌብ በ85 ዓመቱ የተናገረው ቃል ገና በጠዋቱ ተስፋ ለቆረጡ ወጣቶች ተግሳጽ ነው፡- *«... የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ምድርን እሰልል ዘንድ ከቃዴስ በርኔ በላከኝ ጊዜ እኔ የአርባ ዓመት ሰው ነበርሁ እኔም በልቤ የነበረውን ቃል መለስሁለት:: ከእኔ ጋር የወጡ ወንድሞቼ ግን የሕዝቡን ልብ አቀለጡ፤ እኔ ግን አምላኬን እግዚአብሔርን ፈጽሜ ተከተልሁ:: ... እግዚአብሔር እነዚህን አርባ አምስት ዓመት በሕይወት አኖረኝ፤ አሁንም፥ እነሆ፥ ለእኔ ዛሬ ሰማንያ አምስት ዓመት ሆነኝ:: ሙሴም በላከኝ ጊዜ እንደ ነበርሁ፥ ዛሬ ጕልበታም ነኝ፤ ጕልበቴም በዚያን ጊዜ እንደ ነበረ፥ እንዲሁ ዛሬ ለመዋጋት ለመውጣትም ለመግባትም ጕልበቴ ያው ነው»* (ኢያሱ 14:6-11)::

ዘመናትም ይርዘሙ፣ ቀኖችም ይራቁ፣ ሁሉም ነገር ይለወጥ የእግዚአብሔር ሰው ግን ከተስፋው አይናወጥም:: አዎ ገና ነው!! ትዕግሥት ተጨማሪ ሙከራ ማድረግ ነው:: እኛ እንክባለን፣ ጠላት ያፈርሳል:: አሁንም እንክባለን፣ ጠላት ያፈርሳል:: በመጨረሻ ግን ጠላት ተስፋ ይቆርጣል፣ የእኛም ቤት ይጸናል:: የተስፋ ቃልና ረዳት አምላክ የሌለው ሰይጣን ተስፋ አይቆርጥም:: ምን እጠቀም ብሎ ይለፋል? ኩነኔ እጨምር ብሎ ይተጋል:: እኛ የተስፋ ቃል፣ ረዳት አምላክ ያለን ክብር የተቀጠረልንማ አሁንም መሞከር ይገባናል:: ቃሉ፡- *«ወይም ይህ ወይም ያ ማናቸው እንዲበቅል ወይም ሁለቱ መልካም እንዲሆኑ አታውቅምና በማለዳ ዘርህን ዝራ፥ በማታም እጅህን አትተው»* (መክ. 11:6) ይላል:: መዝራትን ማቆም የለብንም፣ በመጨረሻ የትኛው እንዲበቅል አናውቅምና:: የጠበቅነው ቀርቶ ያልጠበቅነው ያጠግበናል:: ገበሬ ዘንድሮ የሚዘራው ለመጨረሻ ጊዜ አይደለም:: እስካለ ድረስ ይዘራል:: እኛም የጽድቅ ገበሬዎች እስካለን ድረስ መዝራት አለብን:: ከውጫዊው ፈተና ይልቅም ተስፋ መቍረጣችንን ልንዋጋው ይገባናል:: እንደ ገና መሞከር ተገቢ ነው!

## እናስተውል

2001 ዓ.ም. የዘራው ገበሬ የሚያጭደው በሌላኛው ዘመን በ2002 ዓ.ም. ነው:: ዕለቱን ዘርቶ ዕለቱን የሚያጭድ ገበሬ የለም:: እኛም ፍሬው ለምን ቶሎ አልደረሰም? ብለን ተስፋ መቍረጥ አይገባንም:: ገበሬ የስድስትና የሦስት ወር ዘሩን ዘርቶ እርሱን በመጠበቅ ቁጭ አይልም:: በወር የሚደርስ ጎመን ይተክላል:: በገበሬ ቤት መዳረሻ ይዘራል:: በዕቅዳችንና በግባችን መካከል ያለውን ሰፊ ጊዜ በሌላ ተግባር መሙላት ይገባናል:: አንዳንድ ፍሬ በሃያ ዓመት



www.ethiopinorthodox.org

የሚደርስ ቢሆንም ከዚያ በኋላ ግን የማያቋርጥ በረከትን ያመጣል:: ይልቁንም ተግተን እያገለገልን ፍሬ የሚዘገይባቸው ጊዜአቶች አሉ:: ጸሎታችን ሰዎቹን ሁሉ ነክቶ ሲጨርስ ከዚያ በኋላ በአንድ ቀን ሺዎች ይማረካሉ:: በአገልግሎት ውስጥ ያለው የፀጥታ ጊዜ ምሥጢሩ ካልገባን ተስፋ ሊያስቆርጠን ይችላል:: በርግጥ ባለማወቅ ጊዜንና ጉልበትን የምንጨርስበት አገልግሎት አለ:: እያገለገልን ያለነው እግዚአብሔር ያሳየንን ማሳ መሆኑን በትክክል መለየት አለብን:: እግዚአብሔር ባሳየን አገልግሎት ተግተን መዝራት አለብን:: የገበሬ ድርሻ ዘሩን መዝራትና አረሙን መንቀል እንጂ ፍሬውን መወሰን አይደለም:: የእኛም ድርሻ ቃሉን መዝራት ነው፣ የተዘራውን ማብቀል፣ የተሞላውን ውሃ ወይን ማድረግ ግን የጌታ ድርሻ ነው:: ይልቁንም የአገልግሎት ዋጋ ያለው ምን ያህል በትጋት በመዝራታችን እንጂ በተቀበሉን ሰዎች መጠን አይደለም::

ከሌሎች ይልቅ የተፈተንን አይደለንም:: እንደውም የእግዚአብሔር ሞልቃቃ ልጆች ነን:: ዘር ቆርጣሚ ተብሎ እንደሚጠራ መሬት የእግዚአብሔርን ውለታ የበላን ሰዎች ነን:: ውለታችንን ደብቀን ጉድለታችንን የምናወራ ነን::: እግዚአብሔር በእኛ ላይ ያፈሰሰው ውለታ አላፈራም:: የዛሬ ጉድለታችን የትላንቱን ውለታ፣ የነገን ተስፋ ሸፍኖብናል:: ሙከራ ለማድረግ ደክሞኛል እንላለን:: መጋደልን ጠልተን ስለተጋደሉ ጽኑአን ግን መተረክ እንወዳለን:: አብርሃም ሊንከንን ያዘገየው ጥቁሮችን የሚጨቁነው ክፉ መንፈስ ነበር:: ያየውን አይቶ ቢያዘገየውም አብርሃም ሊንከን ግን ሙከራዎቹን አላቋረጠም:: እኛም ተስፋ የምንቆርጠው በሥጋችን ብቻ ሳይሆን በሰይጣንም ውጊያ ነው:: ሰይጣን ደግሞ ያየውን አይቶ እንጂ እንዲሁ ጉልበቱን አይጨርስምና ውጊያ ሲበዛ ልንነቃ ይገባናል:: የአብርሃም ሊንከን የትዕግሥቱ ምሥጢር መጽሐፍ ቅዱስ ነበር:: በአንድ ወቅት ይህ አብርሃም ሊንከን እንዲህ ብሏል:- «መጽሐፍ ቅዱስን በማንበቤ ብዙ አትርፌአለሁ:: እስቲ አንተም በመንፈስና በእምነት ተሞልተህ አንብበው፤ ያለ ጥርጥር በሕይወትህ ዘመን ሁሉ የተሻለ ሰው ሆነህ ትኖራለህ:: እንደ ተከበርክም ታልፋለህ::»

ዛሬ በሥራችን ስንለግም፣ ጠዋት ተነሥተን ለመሄድ ስንታሽ ሥራ በማጣት ያለቀስንበትን ዘመን ማሰብ አለብን:: ደግሞም እኛ በታማኝነት ስንሠራና ሰዎችን ስናስተናግድ ሰዎች እግዚአብሔርን:- «የተባረከ ሰው ገጠመኝ ስሙ ይመስገን» ብለው በእኛ መልካምነት ያመልኩታል:: ሥራ ብናጣም ፈጽመን ተስፋ መቍረጥ አይገባንም:: በደጅ የምንሠራው ብናጣ ደካማ ወላጆቻችንን እናገልግል፤ እግዚአብሔር በረከት ያለውን እንጀራ ያዘጋጅልናል::



መልካሙን ሁሉ ያቀርብልናል:: ሥራ አጣሁ ብለን ክፉኛ ስንከፋ እንዲህ እናስብ:- «ሥራ ያማረኝ ጤና ቢኖረኝ ነው:: ጤና ባይኖረኝ ሥራ አያምረኝም ነበር:: ጤና ባጣ ቢያንስ ዛሬ የካርድ አምሳ ብር አወጣ ነበር:: ስለዚህ ዛሬ በቀን አምሳ ብር የሚከፈልበት የጤና ደሞዝተኛ ነኝ» ብለን ማመስገን አለብን::

የበሽታና የችግር ብዛት አይገድልም:: ሞት ጥሪ ነውና:: ስለዚህ ችግሬ በዛ አሁንስ በቃልኝ ብለን መፍራት የለብንም:: እግዚአብሔር በቃ ሳይል በቃ አንበል:: ላስፈራን ፍርሃቱ፣ ለሞትም ሞቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና እርሱን በትዕግሥት እንጠብቀው::

## ጸሎት

እውቀትህ ከእኔ ይልቅ የተደነቀች፣ ማስተዋልህ በዘመን ሁሉ የማይለካ፣ ለሚታገሡህ ቸር የሆንክ፣ ስድብን በክብር የምትለውጥ ጌታዬ አመሰግንሃለሁ:: በዚህ ፈራሽ በሆነው ድንኳን ኑሮዬ እቃትታለሁ:: በረታሁ ስል እናወጣለሁ:: ዕንባዬና ሳቄ ተራ እያጡ ይቀላቀሉብኛል:: ተደስቻለሁ ስል መልሼ ተስፋ ቢስ እሆናለሁ:: ሐኪሜ ሆይ መርምረኝ:: ጉድለትን ብታገኝ በችሎታህ አክመኝ:: የዘሩንህ ጨረር የሚናወጥ ልቤን ያጽናው፣ የአባትነትህ ፍቅር እንደ ገና ተስፋ ማድረግን ይስጠኝ:: ዓለሙን ያለ መሣሪያ ያነጽከው እኔንም ሠርተህ ጨርሰኝ:: ሰማይን ያለ ምሰሶ ያጸና ቃልህ የእኔንም ሕይወት ያቁም:: ምድርን በውሃ ላይ ያጸና ቃልህ በሚያረገርገው ዘመን ያጽናኝ:: ሥራዬን በደስታ እንድሠራ፣ አሁንም እንድሞክር እርዳኝ:: ምንም ብፈተን መኖርን ከሚጠላ ፈተና አድነኝ:: በማይበርደው ተስፋህ ለዘላለሙ አሜን!


www.ethiopinorthodox.org

## ምዕራፍ ሃያ ሁለት

## የሚመጣውን እንጠብቅ

ትዕግሥት ማለት አለመቆጣት ብቻ አይደለም ብለናል:: የትዕግሥት ጥልቅ ትርጉም ያልተሸበረ መንፈስ፣ የማይበርድ ተስፋ፣ ተጨማሪ ሙከራ ማድረግ እንደሆነ ባለፉት ምዕራፎች አይተናል:: ከትዕግሥት ጥልቅ ትርጉሞች ዋነኛው ትርጉም ደግሞ እግዚአብሐርን መጠበቅ ነው:: ትዕግሥት ማለት ዝምታ ወይም ማድፈጥ አይደለም:: ትዕግሥት ዕድልንና የጊዜ ችሮታን መጠበቅም አይደለም:: ትዕግሥት ስላቃተን ተስፋ ቆርጠን መቀመጥም አይደለም:: ትዕግሥት የሚመጣውን ለመቀበልም ሰውነትን በጭካኔ አዘጋጅቶ መጠበቅም አይደለም:: ትዕግሥት ከዚህ በላይ ምንም ቢሆን አይደንቀኝም የሚል የተሰላቸ መንፈስም አይደለም:: ትዕግሥት የቅድስና አካል ነውና ከእነዚህ ሁሉ ደካማ አመለካከቶች የተለየ ነው:: ትዕግሥት ስለሚመጣው ነገር እግዚአብሔርን በተስፋ መጠበቅ ነው:: ቀጥሮ የማይቀር እርሱ ብቻ ነውና:: በተስፋ መጠበቅ አንድ ነገር ሲሆን ለተስፋችን የተደገፍነው እግዚአብሔርን መሆኑን ማረጋገጥ ደግሞ ሌላው አንገብጋቢ ነገር ነው:: ማመን ቢያድንም የሚያድነው እምነት ግን የተደገፈው በሚያድነው አምላክ ላይ መሆን አለበት:: ሰዎች ዛፉንም ድንጋዩንም ከልባቸው ያምናሉ:: ከልብ ማመናቸው ብቻውን እምነታቸውን ልክና ዋስትና ሰጪ አያደርገውም::

በዘመናት ሁሉ የሰው ልጆችን የገዛቸው እመጣለሁ የሚለው መለኮታዊ ተስፋ ነው:: አዳም ከገነት ሲሰደድ መጥቶ ያድነኛል በሚል ተስፋ ተሰደደ (ዘፍ. 3:15):: አበው በምሳሌ፣ ነቢያት በትንቢት መምጣቱን ገለጡ:: የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ክርስቶስ በሥጋ መጣ:: ተመልሶ ከማረጉ በፊት እንደሚመጣ ተስፋ ሰጠ:: ባረገ ባመቱ ጀምሮ የጥንት ክርስቲያኖች ይመጣል እያሉ ይጠብቁት ነበር:: ላለፉት ሁለት ሺህ ዓመታትም የክርስቶስ ዳግም ምጽአት አልተረሳም:: ይልቁንም እኛ በመምጣቱ ዋዜማ ላይ ያለን አማንያን ነን:: በነቢያቱ እመጣለሁ ብሎ መጣ:: ለሐዋርያቱም ዳግም እመጣለሁ ብሎ ተስፋ ሰጥቷልና ይመጣል:: እርሱ ቀጥሮ አይቀርምና:: ለእኛ ግላዊ ችግር ብቻ ሳይሆን ለሰፊው ዓለም መፍትሔውም የክርስቶስ መምጣት ነው:: ከዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት በፊት በሥጋ ሲመጣ ሞትና ኵነኔ ማብቂያ እንዳገኘ፣ አሁንም ዳግም በልዕልና ሲመጣ መከራና ጭንቅ ምዕራፍ ያገኛል:: የክርስቶስ



መምጣት የአማንያን የተስፋ ፍጻሜ፣ የቤተ ክርስቲያንም ዕለታዊ መፈክር ነው::

በዓለም ላይ የጠበቁት ወዳጅ፣ የጠበቁት ቀንና ዕድል አይሆንም:: እግዚአብሐርን የሚጠብቁ ግን አያፍሩም:: ከእግዚአብሐር ውጭ የምንጠብቃቸው ነገሮች ብዙ ዘመን አንገት አስደፍተውናል፣ በከተማ አስመንነውናል፣ ጉዳቱን ለራሳችን ተቀብለን ለሚያውቁን ምን ብዬ እናገራለሁ? በማለት ተጨንቀናል:: አለመሆን የፍጡርነታችን መገለጫ ነው:: አለመሆን ድንቅ አይደለም:: የሚሆነው ሁሉ ከዚህ በፊት በብዙዎች የሆነ ነው:: አዲስ ነገር የለም (መክ. 1:9):: ከዚህ ሁሉ በላይ ከእግዚአብሐር ውጭ በሌሎች ነገሮች መታመን የድንቁርና ድንቁርና ነው:: ከእግዚአብሐር ውጭ በሰዎች፣ በሁኔታዎችና በዕድሎች ተስፋ አድርገን ብዙ ዘመን አፍረናል:: ሰዎች በራሳቸው ተስፈኞች ናቸው:: ተስፈኛውን ሰው ተስፋ ማድረግ ተላላነት ነው:: ሁኔታዎች በራሳቸው ቸርነት ሊያደርጉልን የማይችሉ ግዑዛን ናቸው:: ቀኖችም እግዚአብሐርን ተክተው ለእኛ የሚሠሩ አይደሉም:: ዕድል የምንለውም አምላክ አይደለምና መስጠትና መንሣት አይችልም:: ሰዎችን፣ ሁኔታዎችን፣ ዕድልንና ቀንን እያዘጋጀ ጉድለት የሚሞላ፣ ሀዘንን የሚሽር የሰማይ አምላክ እግዚአብሐር ብቻ ነው:: ስለ እኛ ግድ የሚለውንና የሚመጣውን ጌታ መጠበቅ ብቻ በድፍረት ያቆማል::

ከእግዚአብሐር ውጭ ሌላ ተስፋ ያበጁ ሁሉ ልባቸው ተሰብሯል፣ ፊታቸው ጠቍሯል፣ ትጥቃቸው ተፈትቷል፣ ፍካታቸው ጠውልጓል:: ከእግዚአብሐር ውጭ ወደ ተዘጋ መንገድ ጉዞ ጀምረን የተመለስን ነን:: ተስፋ ያደረግናቸው ሰዎች፣ የጠበቅናቸው አጋጣሚዎች ብዙ ዘመን አሸማቀውናል:: ዓለም የሁለት ውህድ መሆኑን ዘንግተን ይሆናልን እንጂ አይሆንምን መጠበቅ አልቻልንም:: በመጀመሪያ ተስፋ የማይሆኑ ነገሮችን ተስፋ አድርገን ሳትን፤ ቀጥለን ይሆናልን ብቻ ጠብቀን የምንኖርበትን ዓለም ባሕርይ ዘነጋን:: አዎ እግዚአብሐር ሲሰጠን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሐር ሲከለክለንም እንኳ ምክንያቱ ከምክንያት በላይ ነውና ያረካናል::

ዓይናችንን በጥፊ እንደ ተመታ የጨለመብን፣ አቋማችንን መሸከም አቅቶን የተንገዳገድን፣ ጆሮአችንን ማመን አቅቶን እውነት ነው ወይ? ብለን የጠየቅን፣ ጣፋጩ ምግብ እሬት የሆነብን፣ እንቅልፍ የተረሳን፣ ሁሉንም በጅምላ መጥፎ ነው ያልን፣ የተነሣንበትና የምንደርስበት ወደብ የጠፋን፣ አቅጣጫ ጠቋሚዋን



www.ethiopinorthodox.org

እንዳጣች መርከብ በመሐል ባሕር ላይ ግራ የተጋባን፣ ለዓመት ያሰብነው በዕለት ያለቀብን፣ ጥርጣሬና ፍርሃት አማካሪ የሆነብን፣ ሁሉን በበጎ ዓይን ማየት የቸገረን፣ ከሚመጣው አደጋ የቅድሚያ ፍርሃቱ የገደለን፣ በሙቀት የበረደን፣ በብርድ የተቃጠልን፣ ከተፈጥሮ የተገለልን፣ ቋንቋችን የተሰበረብን፣ መናገርን አጋር ያደረግን፣ ሳናስብ የምንናገር የተናገርነውንም የማናስብ፣ የማደርገው ሁሉ ትክክል ነው ያልን፣ በአፋችን እሳት በልባችን ፍም የያዝን፣ ብሶት የሚያስለቅሰን፣ አባብሉኝ የምንል፣ የወደድኩት ርቆኝ የጠላኹት ተጣበቀኝ የምንል፣ ደህና ያልነውን ከስረን መጥፎ ያልነውን ባዶ ላለመሆን የያዝን፣ ደግሞ ምን አሉ? እያልን የማንችለውን አሉታ ለመስማት የናፈቅን፣ በአደባባይ ራቁታችንን የቆምን ያህል የተሰማን፣ የሕይወት መለኪያ የወደቀብን፣ ከጠፋብኝ ወዳጅ ጋር እኔም ልጥፋ ያልን፣ እውነ ሕልም የሆነብን፣ ሐሰተኛ ሳቅ የገረፈን ... እኛ ነን:: አዎ ከእግዚአብሔር ውጭ የጠበቅናቸው ነገሮች ሁሉ አልሆን ያሉን ሰዎች ነን::

መጽሐፍ:- *«በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም»* (ሮሜ. 10:11) ይላል:: ደግሞም:- *«በለሱን የጠበቀ ፍሬዋን ይበላል፥ ጌታውንም የሚጠብቅ ይከብራል»* (ምሳ. 27:18) ይላል:: ከእግዚአብሔር ውጭ ጠብቀን ብናፍር ተገቢ ነው:: ውርደት ቢገጥመንም ውጤቱ ነው:: ቃሉ:- *«በሰው የሚታመን ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ ልቡም ከእግዚአብሔር የሚመለስ ሰው ርጉም ነው:: በምድረ በዳ እንዳለ ቍጥቋጦ ይሆናል:: መልካምም በመጣ ጊዜ አያይም፤ ሰውም በሌለበት፥ ጨው ባለበት ምድር በምድረ በዳ በደረቅ ስፍራ ይቀመጣል:: በእግዚአብሔር የታመነ እምነቱም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ብሩክ ነው:: በውኃ አጠገብ እንደ ተተከለ፥ በወንዝም ዳር ሥሩን እንደሚዘረጋ ሙቀትም ሲመጣ እንደማይፈራ ቅጠሉም እንደሚለመልም፥ በድርቅ ዓመትም እንደማይሠጋ ፍሬውንም እንደማያቋርጥ ዛፍ ይሆናል»* ይላል (ኤር. 17:5-8)::

በሁለት ዓይናችን ሁለት ነገር ማየት፣ በሁለት ጆሮአችን ሁለት ነገር አጥርተን መስማት አንችልም:: ሁለት ዓይን የተደረገልን አንድን ነገር በሁለት ማረጋገጫ እንድናይ እንጂ ሁለት ነገርን እንድንፈልግ አይደለም:: ሁለት ጆሮ የተተከለልን አንድን ድምፅ በሁለት ምስክር እንድናፀና እንጂ ሁለት ነገሮችን እንድንሰማ አይደለም:: የእምነት ዓይናችን እግዚአብሔርንና ሰውን ካየ፣ የእምነት ጆሮአችን እግዚአብሔርንና ሰውን ከሰማ አስቸጋሪ ነው:: እምነት ለእግዚአብሔር ብቻ ነው:: እምነት ከፍ ያለ ዋጋ





የምንቀበልበት በመሆኑ ያንን ዋጋ ያመናቸው ሰዎች ሊሰጡን አይችሉምና በመጨረሻ ማፈራችን አይቀርም::

ያልጠገብናቸው ወዳጆች፣ በደንብ ያላየናቸው አዲስ ጓደኞች ልባችንን ለከንቱ ትምክሕት አሳልፈው ይሰጡታል:: አዲስ ፍቅር ያስክራልና እግዚአብሔርን እንዳናይ ይጋርዱናል:: ዓይናችንን ከእርሱ ላይ እንድናነሣና የወደፊት ዋስትናችንን በእነርሱ ላይ እንድንመሠርት ያደርጉናል:: እነዚህ ትምክሕቶች ግን መደገፋችንን ካረጋገጡ በኋላ ዘወር ይላሉ:: ያን ጊዜ እንወድቃለን:: የገፋነውን እግዚአብሔርንና መልካም መካሪዎቻችንን በማሰብ መፀፀት እንጀምራለን:: ከእግዚአብሔር ውጭ ያለ ትምክሕት ሁሉ የነፋስ ጭራ፣ የጉም ስፍር፣ የአረፋ ኳስ መሆኑን እንረዳለን:: ከገንዘባችንም ሆነ ከፍቅራችን፣ ከጊዜያችንም ሆነ ከተስፋችን ሳንሆን በመቅረታችን ቍጭት ያንገበግበናል:: ከከዱን ትምክሕቶቻችን ይልቅ የእኛን እምነት እናወግዛለን:: ከሚጋልበው ተአምር መሳይ ነገር ሂደቱን በጠበቀው ተፈጥሮ እንማረካለን:: የምንታመንባቸውን ሰዎች እናስቀስፋቸዋለን:: ትምክሕታችን ለእኛም ሆነ ለእነርሱ አይበጅም:: «እርሱ ሳለ ምን እሆናለሁ?» ስንል እያለ ብዙ እንሆናለን፣ «እርሱ እያለ ማን ይነካኛል?» ያልንለት ሰው ራሱ ይነካናል:: ወድቀን ሲያየን እንደማያውቀን፣ እንደ መንገደኛም አልፎን ይሄዳል:: «ቆሞ ይቀብረኛል» ያልንለትን ቆመን እንቀብረዋለን:: «መውለድ እንደ እኛ ነው፣ አስተምሮ እውጭ አገር መላክ» ስንል ልጆቻችንን በመቅሰፍት ሰይፍ እናስቆርጣቸዋለን:: በትሕትናና በፈሪሃ እግዚአብሔር የያዙት እንጂ የተመኩበት ነገር አይሆንም::

በምድረ በዳ ላይ የበቀለ ቍጥቋጦ ዝናብና ጠልን እንደ ናፈቀ እንዲቀር፤ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ውጭ ተስፋ የሚያደርግ በምኞት እንዳበዱ ይኖራሉ:: የፈለጉትን ቢያገኙም ባለቤት ስለሌለው ደስታ አይሰጣቸውም:: የሰጠኝ እግዚአብሔር ነው ስንል እንደታሰበልንና እንደ ተወደድን ይሰማናል:: ምስጋና ስንሞላ ደስታና ኃይል ይበዛልናል:: ከንቱ ትምክሕት ድንጋዩን ወርቅ አስመስሎ ያሳየናል:: ለመቀበል ሰግደን ቀና ስንል ድንጋይ ይሆንብናል:: ችግራችንን ያቀላል ብለን የሮጥንበት ሌላ የችግር አካል የሆነበት፣ እንደ ድንጋይም የከበደን ወቅት ጥቂት አይደለም:: ትምክሕቱን ከእግዚአብሔር ውጭ የሚያደርግ በረከት ይርቀዋል፣ ከደግ ዘመንም አይደርስም:: ሕይወቱ ከሀዘንና ከእንጉርጉሮ መንፈስ፣ ኀሊናው ከማጣትና ከብቸኝነት ስሜት አይላቀቁም:: ለመበተን ይሰበስባል፣ ለማፍረስ ይክባል:: በፍጡር የሚታመን ርጉም ነው (ኤር. 17:5)::



www.ethiopinorthodox.org

እምነት ሁለት ዓይነት ገጽታ አለው:: እነዚህ ገጽታዎች የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች በመሆናቸው የሚለያዩ አይደሉም:: እነርሱም:- መስማማትና መተማመን ናቸው:: መስማማት መስማትን ይጠይቃል:: ስለዚህ ወንጌል ሲነገር ሰምቶ የተቀበለ አመነ ወይም ተስማማ ይባላል (ሮሜ 10:17):: መተማመን ደግሞ መፎከር፣ መደገፍ፣ ልብን መጣል ነው:: እርሱን አምኜ ምን ሆኜ? እርሱን ጠርቼ መች አፍሬ? እርሱን ለብሼ መች ተደፍሬ የሚል ትምክሕት ነው:: አንድ እህታችን አንድ አባትን በምሽት ስትሸኛቸው እቤታቸው ጋ አውርዳቸው ተጠራጥራ ቆመች:: «ምነው ልጄ አትሄጅም ወይ?» ብለው ቢጠይቋት:- «ቆይ ከኋላችን ያሉ ሰዎች እነማን ናቸው? ይለፉ ብዬ ነው፣ እርስዎን የሚያጠቁ እንዳይሆኑ» ብትላቸው እኚህ አባትም:- «በይ ሂጂ ክርስቶስን እንዴት ብትንቂው ነው?» በማለት ተቆጡ:: በእውነትም ይህ የመተማመን ንግግር ነው:: እኚህ አባት እርሱ እያለ ማን ይነካኛል? በሚል ጥላ ውስጥ አርፈዋል:: እንዲህ ያለ ትምክሕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል:: ቃሉ:- *«በእግዚአብሔር የታመነ እምነቱም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ቡሩክ ነው:: በውኃ አጠገብ እንደ ተተከለ፥ በወንዝም ዳር ሥሩን እንደሚዘረጋ ሙቀትም ሲመጣ እንደማይፈራ ቅጠሉም እንደሚለመልም፥ በድርቅ ዓመትም እንደማይሠጋ ፍሬውንም እንደማያቋርጥ ዛፍ ይሆናል»* (ኤር. 17:7-8) ይላልና::

ኑሮዬ ይበቃኛል ብለን እንድናርፍ የሚያደርገን እምነት ነው:: ደስታን የምንጎናፀፈው በእምነት አማካይነት ነው:: ነገሮችን የምንለካው ካመነው ጌታ ብርታት አንፃር ነው:: ስለዚህ የራሳችን ማንነት አያስፈራንም:: ከደህና የተወለደም ሆነ ከደህና የተጠጋ አማኒ ብቻ ነው:: እምነት በሁኔታዎች ላይ ያልተመሠረተ ሰላምን ያጎናጽፈናል:: አሁን ካለው የክፋት ኃይል በላይ የጽድቅን ኃይል እንድንጨብጥና እንዳንሠጋ ያደርገናል:: ዓመት ካመት በቀደመው ፍቅራችንና እርጋታችን እንድንኖር የሚያደርገን እምነት ነው:: እምነት በትኩሳት ዘመን ጥላ፣ በጥማት ዘመን መንፈሳዊ ውሃ ነው:: እምነት የማያስፈልገን ዘመን የለም:: የሩቁን በረከት የምናቀርብበት፣ የቅርቡን ጥፋት የምናርቅበት ኃይል እምነት ነው:: ሐሰተኛ ሳቅን አስወግዶ የልብ ደስታን፣ አስመሳይ ኑሮን አርቆ እውነተኛ አቋምን፣ ሽንገላን ገፍፎ ሐቀኛነትን የሚያጎናጽፈን እምነት ነው:: በረሀብ ዘመን የምንጠግበው፣ በጦርነት ቀጠና በሰላም የምናልፈው፣ ከተጠመደብን ወጥመድ የምንሾልከው በእምነት አማካይነት ነው:: ትልቁ እምነትም እግዚአብሔርን በትዕግሥት መጠበቅ ነው:: ማድረግ ስላቃተን መቀመጥ ይህ እምነትም ትዕግሥትም አይደለም:: ማድረግ በምንችልበትም ዘመን እግዚአብሔርን መጠበቅ እምነት ይባላል:: የበጎ ነገር ሁሉ ወጣኝና





ፈጻሚ እግዚአብሔር ብቻ ነውና እርሱን መጠበቅ የፍጥረት ሁሉ ናፍቆት ነው::

ማሽላውን የሚጠብቅ አረኛ ዋሽንቱንና ወንጭፉን ይዞ በማማው ላይ ይቀመጣል:: በደጅ ተቀምጦ እናቱን የሚጠብቀው ሕፃን በሄደችበት አቅጣጫ ዓይኑ ተተክሎ ይቀራል:: ዘርን የተቀበለች ሴት የመውለጃዋን ቀን በዝግጅት ትጠብቃለች:: ተስፋን የተቀበሉም እግዚአብሔርን ይጠብቃሉ:: አዎ የሚመጣውን ይጠብቃሉ:: «ተስፋህን ፈጽም ከመከራዬ ልረፍ፣ ተስፋህን ፈጽም የተሳለቁብኝ አምላክ እንዳለኝ ይወቁ፣ ተስፋህን ፈጽም የሚወዱኝ ደስታዬን ይዩ» እያልን መወትወታችን ተገቢ ነው:: እግዚአብሔር ግን አላረፈደም:: መጠበቅ አድካሚ ነው:: ሰው ቀጥረን ሲዘገይብን በየአምስት ደቂቃው ልዩነት ልባችን ይራወጣል:: ያን ሰው ብቻ ስለምንጠብቅ ደቂቃው በሄደ ቍጥር ብስጭት ይመጣብናል:: ያ ሰው ባይመጣ ብለን መጽሐፍ ይዘን ብንወጣ በሌላ ጊዜ የማናነበውን መጽሐፍ አጋምሰን የምንጠብቀውን ሰው እናገኘዋለን:: ቢቀርም ከእውቀት ጋር ስለተገናኘን መቅረቱ ቅር አያሰኘንም:: አዎ መጠበቅ ያደክማል:: እግዚአብሔርን የምንጠብቀው በእኛ ሰዓት ስለሆነ ሰዓቱ ያለፈ ሲመስለን እናዝናለን:: ለእርሱ ግን ሰዓት አያልፍበትም:: ጊዜን ተቀባይ ሳይሆን የጊዜ ባለቤት ነውና:: ምንም ሳንሠራ ጊዜ ያለፈ ይመስለናል:: አላወቅንም እንጂ እኛ ባንሠራ እግዚአብሔር ግን እየሠራን ነበር:: የሌለንን ስንጠብቅ ያለንን ከመጠቀም ጋር ቢሆን ጊዜው ረዘመ ባላልን ነበር:: ሕይወት አንድ ብቻ አይደለም:: የሕይወት ሙሉ ነገር የጎደለን ነገር ብቻ አይደለም:: የጎደለን ነገር የሕይወት አንድ ነገር ነው:: ሕይወት ግን ዘርፈ ብዙ ናት:: ስለዚህ ሁሉንም ነገር አጨልመን ማየት የለብንም:: ናፓልዮን እንኳ «በትዕግሥት መጠበቅ ለሚችል ሰው፣ ዓለም ሁሉ ወደ እርሱ ይጓዛል» ብሏል:: ሌላ ደራሲም:- «ጽናት ካለህ የደራጎንን መንጋጭላ ልትፈረክስ አንበሳን ከእግርህ ሥር ልታጋድም ተፈቅዶልሃል» ብሏል::

የእያንዳንዱ ቀን ፈተና ውስጣዊ ጉልበትን በሚጠይቅበት ዓለም ላይ ታጋሽ መሆን ትልቅ ጥበብ ነው:: በሕይወት ላይ በጉልበት፣ በንግግር ችሎታ የማይፈቱ ብዙ ቋጠሮዎች አሉ:: የሚበዛው ፈተና በትዕግሥት የሚፈታ ነው:: ዓመፀኞችን በሚያመጡብን ዓመፅ ስንታገሣቸው ተጸጽተው መፍትሔ ይዘው ይመጣሉ:: ትዕግሥት ጠላትን ወዳጅ የማድረግ አቅም አላት:: ብዙ ጊዜ በደረሰብን ፈተናና መከራ መጽናናትን እንጠይቃለን:: ነገር ግን በዚህ ችግር ብንጽናና ሌላ ያልጠበቅነው ችግር ደግሞ ይመጣል:: ትዕግሥትን ብንለምን ግን በሁሉ እንጸናለን:: ትዕግሥትን



www.ethiopinorthodox.org

የማይጠይቅ ምንም ዓይነት ሂደት የለም:: ልብስ እስኪደርቅ፣ ምግብ እስኪበስል፣ የትራፊክ መብራት እስኪለቀን እንኳ ትዕግሥት ያስፈልገናል:: አዎ የእያንዳንዱ ቀን ፈተና ውስጣዊ ጉልበትን ስለሚጠይቅ ታጋሽ መሆን አለብን::

የእግዚአብሔርን ጊዜ እንጠብቅ:: በእኛ ጊዜ የሚሆኑ ነገሮች ሁሉ መልካም አይደሉም:: የእኛ ነገር ዳቦ ያነሣን መስሎን ድንጋይ የምንዘግን፣ ዓሣ ያነሣን መስሎን እባብ የምንጨብጥ ነን:: በእግዚአብሔር ጊዜ የሚሆን መሠረት አለው:: ደስታውም እስከ ትውልድ የሚተርፍ ነው:: ጊዜ በራሱ አይሰጠንም፣ አይነሣንም:: ጊዜ ግን የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና በጊዜ ውስጥ እግዚአብሔር የሚያደርገውን እንጠብቅ:: የእግዚአብሔር ተስፋ በብዙ ሺህ ትውልድ የተፈተነ ነው:: እብለትና መታጠፍ የለበትም:: በእርግጥ የሚሆን ነው::

መጠበቅ መልካም ነው:: የመኖር አምሮታችንን ከሚጨምሩ ነገሮች አንዱ ያልተፈጸሙልን ነገሮች ገና መኖራቸው ነው:: ጉድለቶች ገና ልኑር፣ ይህ ተሟልቶ በዓይኔ ልይ እንድንል ያደርጉናል:: ሕይወትን ተጓዥ የሚያደርጋት ያልተፈጸመ ምኞት ነው:: በኑሮአችን ያለው ጉድለት የምንኖረው ገና በዓለም ወይም ባልተፈጸመ ተስፋ ላይ መሆኑን ያሳየናል:: ይህ ጉድለትም አደጋ ሳይሆን ተፈጥሮአዊ፣ መጥፎ ሳይሆን በጥበብ የተደረገ የኑሮ ምሥጢር ነው:: ሁሉም ነገር የተሟላላቸው ደስታቸው ሳይሟላ በነበረው ዘመን የነበራቸው የተስፋ ደስታ እንኳ አሁን የላቸውም:: ስለዚህ ጉድለታችን ተስፋ እንድናደርግ ይጎተጉተናልና መልካም ነው:: እኛ የማንችለው ነገር መኖሩ በሚችለው አምላክ እንድንደገፍ ያደርገናል:: እርሱ የሥጋችንና የነፍሳችን ፈጣሪ በመሆኑ ለሥጋችንም ሆነ ለነፍሳችን ጉድለት ትልቅ መልስ ነው:: ከእኛ መልስ፣ ከፍጡራንም መልስ አምላካዊው መልስ ልብን ያሳርፋል (ሮሜ. 11:4):: ስለዚህ እርሱን መጠበቅ አለብን:: ዘላለማዊውን ጥያቄ ይመልሳል እያልን በጊዜያዊው ጥያቄ ልንጠራጠረው አይገባም:: በሰው እርምጃ እርሱን ለመቅደምም አቋራጭ መንገድ መጠቀም የለብንም:: ስለዚህ እርሱን እንጠብቅ::

ስላልቻልን ያላደረግነው ነገር ከጽድቅም ከኃጢአትም ይቆጠራል:: ድሆችን ለመርዳት ሙሉ ርኅራኄ ኖሮን ፍጹም ሳንችል ብንቀር እንዳደረግን ይቆጠራል:: ክፉን ለማድረግ አስበን አቅም አጥሮን ባንፈጽመው እንዳደረግነው ይቆጠራል:: ማድረግ እየቻልን በጸሎት ማሳሰብ «ያለኝ የሚመስለኝ ጉልበቴ ያንተ ነውና ፈቃድ ስጠኝ» ማለት በመሆኑ ደስታን ያመጣል:: ማድረግ ስላልቻልን ዝም



www.ethiopinorthodox.org



ማለት ወይም ተበሳጭቶ መቀመጥ ደስታን ያርቃል:: እግዚአብሔርን የምንጠብቀው ምንም ማድረግ ስለማንችል ከሆነ የመፈጸሙን ደስታ ሳናገኝ እንቀራለን:: ተስፋ ቆርጠን ከመቀመጥ የእግዚአብሔርን ጊዜ መጠበቅ ጉዳዩ ሲሆን የመሆንን ደስታ ያጎናጽፈናል::

የብዙ ሰዎች ጭንቀት ጊዜው አለፈ የሚል ነው:: ጌታችን ግን ጊዜ የማያልፍበት፣ ሞትም የማይገድበው አምላክ ነው:: የአልዓዛርን ታሪክ ደግመን መመልከት ያስፈልገናል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይወደው የነበረው አልዓዛር መታመሙን በሰማ ጊዜ ሊፈውሰው አልሄደም:: ከሞት በማስነሣት የበለጠ ሊያሳየው ዘገየ እንጂ (ዮሐ. 11:6):: እርሱ የበለጠ ሊሠራ ይዘገያል:: ታሞ ቢፈውሰው «የሕሙማን ጤና» ተብሎ ይመሰገናል:: እርሱ ግን «የሞት መድኃኒት» ተብሎ ለመመስገን ዘገየ:: አልዓዛር ሞቶ በተቀበረ በአራተኛው ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደረሰ (ዮሐ. 11:17):: እንደ ሰው አቆጣጠር ጊዜው አልፏል:: ታሞ ቢደርስ መልካም ነበር፣ አሁን ግን አብቅቷል በሚባልበት ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጣ:: ሞት ለሥጋ ለባሽ ፍጻሜ ነው፣ ለእግዚአብሔር ግን የትልቅ ተግባሩ ጅማሬ ነው:: የዘላለም ሕይወት ምዕራፍ እንኳ በሙላት የሚጀምረው ከሞት ቀን አንሥቶ ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሽተኛን የሚፈውስበትና ሙታንን የሚያስነሣበት ኃይሉ ያው ኃይሉ ነው::

በአይሁድ ባሕል አንድ ሰው ሲሞት ነፍሱ ለሦስት ቀን ያህል በዛፍ ላይ ቆይታ ሠለስቱ ከተለቀሰ በኋላ ወዳጆችዋን ተሰናብታ ትሄዳለች ይባላል:: ከሠለስቱ በኋላ ወዳጆች ሁሉ:- «እንግዲህ ይበቃል፣ እርሱ ከዚህ በኋላ ገንዘብ አይሆንም፣ ያሉትን ይባርክ» እያሉ ሁሉም ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ:: ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው በሰው ፍጹም «አይቻልም» በተባለ በአራተኛው ቀን ነው:: እነዚያ የሰው አጽናኞች ሲበተኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻውን ሊያጽናና መጣ:: ግርግሩ እያለ ለእርሱ ጊዜ መስጠት ይቸግረናልና አጀቡ ሲበተን ኢየሱስ ክርስቶስ ይመጣል:: እነዚያ አጽናኞች «እንግዲህ ሞቷል!» ብለው ሞትን እያጸኑ ያጽናኑ ነበር:: ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሞተውን ጠርቶ ሕይወትን በማግኘን አጽናናቸው::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ ያየችው ማርታ:- *«ጌታ ሆይ፥ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር»* (ዮሐ. 11፥21) አለች:: እንደ እርሷ እምነት ኢየሱስ ክርስቶስ ባለበት ሞት የለም:: ዮሐንስ በመጨረሻው ዘመን የሚሆኑትን ጭንቆች ባየ ጊዜ የዚህ ሁሉ ክፋትና ጭንቅ ማብቂያው የክርስቶስ መምጣት መሆኑን

አምኖ:- *«አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና»* አለ (ራእይ 22:20)። እርሱ ሲመጣ ብቻ ሞትና ጭንገፉ፣ መከራና ፍርድ አልባነት ድንበር ያገኛል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ:- *«ወንድምሽ ይነሣል»* (ዮሐ. 11:23) አላት። ሁለት ዓለም ዓይቶ እንደሚመለስ፣ ያለቀሱለትን ወዳጆቹን ቀና ብሎ እንደሚያይ፣ በቁሙ ክፉ ያላቸው ሰዎች የእርሱ መሞት እንዲህ እንደሚሰብራቸው ያያል አላት። የምንጠላው ሰው ሲሞት እንሰበራለን፣ ክፋቱን ዳግም ላለማንሣት ዝም እንላለን፣ መረታቱን እያሰብን ለራሳችን እናዝናለን፣ በቂመኛ ነታችን ራሳችንን እንታዘባለን። ለካ የምንጠላላውና የምንጨካከነው ዘላለም የምንኖር እየመሰለን ነው! የሞታችን ቀን ቀና ብለን ማየት ብንችል እነዚያ ይጠሉናል የምንላቸው ወዳጆቻችን መሆናቸውን በተገነዘብን ነበር።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ:- *«ወንድምሽ ይነሣል»* ሲላት እርሷ ግን:- *«በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ እንዲነሣ አውቃለሁ አለችው»* (ዮሐ. 11:24)። የመጨረሻውም ቀን የሚያስነሣው የኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን ነው። ያ ሥልጣን ዛሬም ይሠራል። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ:- *«ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል»* (ዮሐ. 11:25) አላት። ለእርሱ የጊዜ ገደብ የለበትምና አልዓዛርን ከሙታን መንደር ወደ ወጣበት የሕያዋን ማኅበር መለሰው። ለእርሱ የጊዜ መለኪያ አይበጅለትም። አዎ ለእርሱ ጊዜ አያልፍበትም። ከሞት በኋላ አራት ቀን ቆይቶም ያድናል።

የሚሹትን ነገር በምንም መንገድ ማግኘት አለብኝ ብለው ጉዞ የጀመሩ ብዙዎች ናቸው። የሰው መንገድ አድካሚና ሩቅ ነው። እንዳሰብነው ልንጀምር እንችላለን፣ ውጤቱን ግን ልንቆጣጠር በማንችልበት ዓለም ላይ የእኛ መንገድ አስፈሪ ነው። በራሳችን ለምናበላሸው ነገር ዋስትና የለንም። እግዚአብሔር ግን የሚሰጠን ነገር ቢበላሽ እንኳ ዋስትና ዳግም ህልውና አለው። አብርሃም ይስሐቅን በጎሊናው ከሠዋው በኋላ ትንሣኤ በሚመስል ተአምር አግኝቶታልና (ዘፍ. 22:9-14)። የራሳችን መንገድ ረዝሞብን ብዙ ያለቀስን ሰዎች ነን። «ላም እሳት ወለደች እንዳትልሰው ፈጃት፣ እንዳትተወው ቆጫት» እንዲሉ ለመያዝም ለመተውም አጣብቂኝ የሆነ ፈተና በአቋራጭ መንገዳችን መጥቶብናል። የምንሻውን ባቋራጭ ልናገኘው ብንችል እንኳ እርካታ ግን የለውም። በአቋራጭ ገንዘብ የፈለጉ አግኝተዋል። ኑሮአቸው ግን የስጋት ነው። ትዳርን የፈለጉ በአቋራጭ አግኝተዋል። እግዚአብሔርን ከማያምን ሰው ጋር መቆራኘት ግን ምን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍል እያዩት ነው። ሰው በትእዛዛቱ በነጻ ካልተማረ እየከፈለ ከዕንባ ጋር ይማረዋል። በጠረጴዛ



www.ethiopinorthodox.org



ላይ የሚቀመጡ የፕላስቲክ ፍራፍሬዎች ከእውነተኛው ይልቅ ያምራሉ። በሩቅ አስጎምጅተው ሲቀርቧቸው የማይበሉ ናቸው። በእውነት ልብን ያደርቃሉ። የዓለም ተስፋ፣ የአቋራጭ ስኬቶች የፕላስቲክ ፍራፍሬዎች ናቸው። ገበታ ቢሞሉም አያጠግቡም። እነርሱን ለማግኘት ግን ስንት አደረግን፣ ስንት ሆንን። ውጤቱ ግን እርካታ ማጣት ሆነ። ዓለም ከምትሰጠን እግዚአብሔር ቢከለክለን ይሻላል። ለራሳችን ደግ ሆነን በአቋራጭ ከምናተርፈው እግዚአብሔር በጊዜው የሚሰጠን የመንፈስ እርካታ አለው። አሊያ ደርሰንበት እንደገና ለመመኘት፣ ትዳርን ይዘን ትዳር ለመፈለግ፣ ሀብትን ይዘን ሀብትን ለመፈለግ ከወደድን የአቋራጭ መንገድ አለልን። በአቋራጭ የምናገኘው ነገር እኛን ብቻ ሳይሆን የእኛ የሆኑትንም እንዳስተከዘ ይኖራል። በእውነት እግዚአብሔርን እንጠብቅ! የትዕግሥት ጥልቅና ዋናው ትርጉም እግዚአብሔርን መጠበቅ ነውና።

## <u>እናስተውል</u>

እግዚአብሔር ፍጥረታትን በሦስት ዓይነት መንገድ እንደ ፈጠረ እናያለን። በዝምታ፣ በቃልና በተግባር። የዘፍጥረት መጽሐፍ በቃል ከተፈጠሩት ፍጥረታት አንሥቶ ይዘግባል። እግዚአብሔር ግን በዝምታ ነፋስና እሳትን፣ መላእክትንና መንግሥተ ሰማያትን ፈጥሯል። በዝምታ የፈጠራቸው ፍጥረታት ኃያላን ፍጥረታት ናቸው። ከዚህ የምንረዳው እግዚአብሔር ዝም ሲልም እየሠራ እንደሆነ ዳግመኛም በዝምታም መሥራት እንደሚችል ሲሆን ከዚህ በላቀ የምንረዳው እግዚአብሔር በዝምታው ኃያል ሥራ እንደሚሠራ ነው።

ጩኸታችን መልስ ያጣ ሲመስለን ለምን ተፈጠርኩኝ? እንላለን። የመፈጠራችንን ዓላማ የሚነግረን ሰብአዊ ፍልስፍና እንፈልጋለን። የመፈጠራችን ዓላማ ግን ያለው የፈጠረን አምላክ ጋ ነው። እርሱን በትሕትና ብንጠይቀው ይመልስልናል። አንድ ሰው:- «ዓላማን በመፈለግ ዓላማ አይገኝም። እግዚአብሔር በእኔ ላይ ያለው ዓላማ ምንድነው? ስንል ግን ዓላማችንን እናገኘዋለን» ብሏል። አንድ ቄስ በአንድ እናት የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ያስተላለፉት ምክር የመፈጠርን ዋጋ ያሳያል:- «ካልተወለድን በቀር ይህችን ዓለም ማየት በፍጹም አንችልም። ስለዚህ ተወለድን። ካልሞትንም በቀር የወዲያኛዋን ዓለም ማየት አንችልምና ስለዚህ እንሞታለን። ሞታችን ዓለም ማያ ነው። እኛ ሞት እንለዋለን። ጌታችን ግን ይህን ቀን ልደት ይለዋል» ብለዋል።

የተፈጠርነው በዚህ ዓለም የተሳካ ኑሮ ለመኖር ብቻ አይደለም:: የተፈጠርንበት ዋነኛ ዓላማ የዘላለም ሕይወትን ለመውረስ ነው:: የዚህ ዓለም ኑሮ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል:: የሰማዩ ሕይወት ግን የተረጋገጠ ተስፋ ነው:: የዚህ ዓለም መከራውም ተድላውም ኃላፊ ነው:: የማያልፈው ግን የወዲያኛው ዓለም ነውና መፈጠራችንን እንውደደው::

ጥበቃችንን ከሚያዝሉ ነገሮች አንዱና የመጀመሪያው አስተያየት ማብዛታችን ነው:: ይህ የሆነው በዚህና በዚያ ምክንያት ነው የሚል አስተያየት እናበዛለን:: ትንታኔ ማብዛት ግን የመጠበቅን ጉልበት ይጨርሳል:: ምክንያታዊ መሆንና ለችግራችን አንድ ተከሳሽ ማግኘት እንፈልጋለን:: ይህም የሕይወት አንዱ ክፍል ነው ብለን ማረፍ አይሆንልንም:: ይህ ነገር የመጠበቅ ጉልበታችንን ያዝለዋል:: ሕጻን ልጅ ከወላጆቹ ጋር የሚሄደው ዝርዝር መረጃ ተቀብሎ አይደለም:: ወላጆቹ ባዩት ተረጋግቶ ይጓዛል:: በዚህ እምነቱ የተጎዳ ሕጻን እንዳለ በዓለም ላይ አልሰማንም:: እግዚአብሔርም ስለ ሁሉም ነገር ዝርዝር መረጃ አይሰጠንም:: እርሱ ወዳየልን ግብ እንድንጓዝ ግን ይጠራናል:: የእስራኤልን ልጆች ስለ ባሕሩ መንገድ አልነገራቸውም:: ቢነግራቸው ኖሮ ወደ ሙሴ እየቀረቡ:- «ሙሴ እስቲ መንገዱን ያቅናልህ እኔ አስም ስለሚያስቸግረኝ የባሕር መንገድ አይስማማኝም» ይሉት ነበር:: ሌሎችም:- «ሙሴ ይቅርታ አድርግልኝ፣ እኔ ተራራ መውጣት እንጂ ባሕር ማየት በተፈጥሮዬ አልወድም ያዞረኛል:: እናንተንም ከማስቸግር ሰላም ያግባችሁ እንደደረሳችሁ ደብዳቤ ላኩልን» ይሉ ነበር:: እግዚአብሔር ግን የተስፋውን ፍጻሜ ነገራቸው እንጂ ዝርዝር መረጃ አልሰጣቸውም:: ለምን? ስንል ስለማይጠቅማቸው ነው::

መጠበቅን ከሚያዝሉ ነገሮች ሁለተኛው የእኛን ኑሮ ከሌሎች ኑሮ ጋር ማነጻጸር አንዱ ተጠቃሽ ነው:: «እኔ ከእነርሱ ይልቅ መንፈሳዊ ሕይወቴ ደካማ ነው ወይ? እኔ ከእነርሱ ይልቅ በድያለሁ ወይ?» የሚል ንጽጽር ውስጥ መግባት የመጠበቅን ጉልበት ይጨርሳል:: ይህ አስተሳሰብ ፍቅር የተሞላ አስተሳሰብ ሳይሆን ቅንዓት ያለበት አስተሳሰብ ነው:: የምንፈልገውን ነገር መፈለግ ያለብን በሰው እጅ ላይ ስላየነው ሳይሆን ስለሚያስፈልገን ብቻ መሆን አለብት:: ይህ በሰዎች ላይ ያለንን መልካም አመለካከት ይጠብቅልናል:: አዎ እግዚአብሔርን ብቻ እንጠብቅ!





## ጸሎት

ሞቴን ሽረህ ሕይወትን የሰጠኸኝ፣ የውርደት ሸክሜን አራግፈህ የክብር ካባን ያጎናጸፍከኝ፣ የትካዜ ማቄን ቀድደህ ደስታን ያስታጠቅከኝ ቸር አባት እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ:: ችግሬን ሁልጊዜ ከማውራቴ የተነሣ የቃላቱ ረድፍ እንኳ አይዛነፍም:: መጽሐፍ እንደሚያነብ ችግሬን እተርካለሁ:: ችግሬን ባገነው ይበልጥ ከበደኝ:: ችግሬን ትቼ አንተን እንዳይ እባክህ እርዳኝ:: የእኔ ችግር ካንተ እጅ ሳይሆን ለጣትህም አይመጥነውም:: በታላቅነትህ ፊት ጉዳዬ ትንሽ ነው:: ተራራ የሆነብኝ ነገር በሰናፍጭ ቅንጣት እምነት እንደሚወገድ ነግረኸኛል:: እባክህ እንዳምንህ እርዳኝ:: በሰዎች አለማመን ስተች እውላለሁ:: የእኔን አለማመን ግን በሕግ እንደ ተፈቀደ እቆጥረዋለሁ:: እባክህን ራሴንም ሰዎችንም ሳይሆን አንተን እንዳይ እርዳኝ:: አፌን ምስጋና ሙላ:: እንደ ተደረገልኝ መጠን እንድኖር እርዳኝ:: በትዕግሥት አንተን መጠበቅ መልካም ነውና የመጠበቅ ጉልበትን አድለኝ:: በፈሰሰው ደምህ በአማኑኤል ስምህ አሜን!



www.ethiopinorthodox.org

# ማጠቃለያ

የእግዚአብሔር ትዕግሥት ለወደቁ ሰዎች የተዘረጋ እጅ፣ ከእግዚአብሔር ቤት ለወጡ ሰዎች የተከፈተ በር፣ ለጠፉ ሰዎች የመዳን ዕድል እንደሆነ በታሪክም በዘመንም አይተናል:: እኛም የትዕግሥቱ ፍሬዎች ሆነን ይኸው ቆመናል:: እግዚአብሔር ጸሎታችንን እስኪመልስ መታገሥ ተገቢ ነው:: ምክንያቱም የእኛ ያልሆነውን ነገር ስንጠይቅ መታገሥ ብቻ ሳይሆን ብንከለከልም ለመደሰት ዝግጁ መሆን አለብን:: እግዚአብሔር ግን እኛን የታገሠን በበደላችንንና በኃጢአታችን በመሆኑ ትዕግሥቱ ብርቱ ነው:: የእግዚአብሔር ትዕግሥት የአእምሮ ሕጻናትን በጥበብ፣ ደካሞችን በብርታት፣ ዓመፀኞችን በጽድቅ ያሳድጋል:: ሳኦልን ጳውሎስ ያደረገ የእግዚአብሔር ትዕግሥት ነው::

እርሱ በትዕግሥቱ ይችለናል:: ተስፋ ያደርገናል፣ አይቸኩልም፣ በጊዜውም ያደርግልናል:: እኛም ባሕርይውን ልንካፈል ተጠርተናል ደግሞም ድነናል:: ስለዚህ ሰዎችን በበደላቸው ይቅር የምንል፣ በፍላጎታቸው ሳንሰለች የምንሰጥ ቻይ መሆን ይገባናል:: እኛ እንድንችል የምንጠየቀው ትንሽ በደልን፣ ጥቂት ሰዎችን ነው:: እግዚአብሔር ግን የዓለሙን ዓመል ሁሉ ችሎ ስድስት ቢሊየን ሕዝብን እንደ አንድ ሰው የሚመግብ ጌታ ነው::

አንድ ቀን የምትሞት ጫጩት እንኳ መሞቷ ለባለቤቷ ይቆጫል:: ሕያው ነፍስ የሆነው ሰውማ መጥፋቱ ለፈጠረው ጌታ እንዴት አያሳዝንም? እናት ዘጠኝ ወልዳ ለማን ታዳላለች? መልከ መልካሙም መልከ ጥፉውም፣ ንጹሑም ኃጥኡም ከእርሷ የወጡ የእርሷ ልጆች አይደሉምን? እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ መውደዱ ሰውን ለወዳጅነት በመፍጠሩ ነው:: እርሱ ለማንም አያዳላም፣ ይጥፋ ብሎም አይጨክንም:: እኛ ሳንቲም ቢጠፋ ይቆጨናል፣ ሰው ግን መጥፋቱ አይቆጨንም::

እግዚአብሔር ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለምኞቱም እያዘነ በትዕግሥት ይጠብቀናል:: ያየልንን እስክናይ፣ ያሰበልንን ራእይ እስክናደርግ ይጠብቀናል:: እርሱ ከመቃብር ይልቅ ከባቴ አበሳ (በደልን ሸፋኝ) ነው:: እርሱ የተማጸኑትን አውጥቶ ለጠላት አይሰጥም:: ለእርሱ የነገርነውን ምሥጢር የትም አናገኘውም:: እርሱ እንዳየ ሰው ቢያየን፣ እርሱ እንደሰማ ሰው ቢሰማን አንድ ቀን እንኳ ለመኖር የማይፈቀድልን ሰዎች በሆንን ነበር:: ድካማችን





ሳይገርመው ዛሬም ለንስሐ የሚጋብዘን፣ መልካምነታችንን የሚናፍቅ ግሩም አባታችን ነው::

የእግዚአብሔር ይቅርታ ብዙ ነው:: እርሱ የእንደገና አምላክ ነው (ዮሐ. 21:1):: ስንጠፋ ይፈልገናል:: ካለንበት ድረስ መጥቶ ይቀሰቅሰናል:: የሚቹን ሞት የማይፈቅድ እርሱ ብቻ ነው (ሕዝ. 18:32):: የሚፈልገን የሚጎድልበት ኖሮ፣ ኃጢአትን መከልከሉ እንዳንገዳው ብሎ፣ መታገሡ ግድ የለሽ ሆኖ አይደለም:: እግዚአብሔር እንድንመለስ ጊዜ ይሰጠናል:: የእርሱ ጊዜ የመመለስ ዕድላችን ነው::

ከፊት ለፊታችን ያለው ወዳጃችን እጁን በዘረጋልን ቍጥር እርምጃችን ይጨምራል:: ፈጥነን ከእቅፉ ለመግባት እንጣደፋለን:: ምክንያቱም የወዳጅ እጅ ሲዘረጋ ይከብዳልና:: ታላቁ ወዳጃችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እጆቹ በምስማር ተቸንክረው ተዘርግተዋልና ወደ እቅፉ ፈጥነን ልንገባ ይገባናል:: እጁን የዘረጋው በደጃፋችን ቆሞ የሚያንኳኳው የሚጣራው ጌታ ሊከብደን ይገባል (ራእ. 3:20):: በሚገፉ የወዳጆቻችን ክንዶች እያለቀስን ወደሚሰበስብ ክንድ አለመግባታችን ያስወቅሰናል:: ስለዚህ በእምነትና በንስሐ ወደ ሕይወት እቅፍ መግባት አለብን::

ከኢዮብ ባልንጀሮች አንዱ ነዕማታዊው ሶፋር:- *«የጥበቡን ምሥጢር ቢገልጥልህ! ማስተዋሉ ብዙ ነውና:: እግዚአብሔር ለበደልህ ከሚገባው አሳንሶ እንደሚያስከፍልህ እወቅ»* (ኢዮ. 11:6) ብሏል:: እግዚአብሔር በደላችንን ባነሰ ዋጋ፣ መልካምነታችንን በበዛ ዋጋ የሚከፍል ነው:: እርሱ ለሰናፍጭ ቅንጣት እምነታችን ትልቅ ዋጋ የሚሰጥ፣ ለተራራው ኃጢአታችን ትንሽ ዋጋ የሚከፍል ነው::

እግዚአብሔር በበደላችን ብቻ ሳይሆን በፍላጎታችንም ችሎናል:: የሰው ይቅርታ ከሚችለው በላይ በድለነዋል:: በደላችንን ይገልጥልናል እንጂ አጋልጦን አያውቅም:: ከእርሱ የተቀበልነውን ስጦታም ከፍጡር ተቀብለን ቢሆን ኖሮ ሰቀቀኑ በገደለን ነበር:: የእርሱ ስጦታ ግን ሊከፍሉት የማያሳስብ ከራስ ይልቅ የራስ ሆኖ የሚሰማ ነው:: እኛስ ይቅርታ እየለመንን ይቅር ለማለት፣ እየተቀበልን ለመስጠት ተቸግረን ይሆን? የመቻል ባሕርይውን እኛም ማሳየት አለብን:: ዘመኑን ሳይሆን ክርስቶስን መምሰል አለብን::

ደጁን ከፍቶ ፍጥረቱን የሚጠብቅ አምላክ ስላለን እንደነቃለን:: እርሱ በማንም ተስፋ አይቆርጥም:: ከአባት ይልቅ አሳቢ፣ ከእናት ይልቅ ቅርብ ነው:: ስለዚህ የሚወደንን ልንወደው፣



www.ethiopinorthodox.org

የሚፈልገንን ልንፈልገው ይገባል:: ሲወዱት የማይወድ ግዑዝ ብቻ ነው:: ሕይወት ያለው ሁሉ ምላሽ ይሰጣል:: ውሻ እንኳ ቀድሞ ይወዳል፣ ሲወዱትም ምላሽ ይሰጣል:: እኛ ሰው ነንና የሚወደንን አምላክ ልንወደው ይገባናል:: ስንከተላት የምትሸሸንን ጥላ ዓለም ከመከተል የሚፈልገንን መፈለግ ትልቅ ጥበብ ነው::

በሕይወታችን ላይ እርሱ ካልሞላው በቀር የዓለም ሀብትና እውቀት የማይሞላው የተፈጥሮ ክፍተት አለብን:: እግዚአብሔርን መፈለጋችን የልምምዳችን ውጤት ሳይሆን የተፈጥሮ ግዴታ ነው:: ሰው ያለ እግዚአብሔር መኖር የማይችል ደካማ፣ መርካት የማይችል ጎዶሎ ነው:: በራሳችንም ሆነ በሌሎች ተስፋ መቍረጥ የለብንም:: የእግዚአብሔር ተስፋ የመነሣት ኃይላችን ነውና::

እግዚአብሔር አይቸኵልም ትዕግሥተኛ ነው:: ሕልውናውን የካዱትን ሳይቀር ይታገሣል:: እርሱን መካድ ራስን መካድ፣ እርሱን ማጣት ሕይወትን ማጣት ነው:: ከእግዚአብሔር ጋር ጀምረው ከራሳቸው ጋር የጨረሱ እነዚያ አዋቂ ነን ባዮች እንዴት ያሳዝናሉ? የፈጠራቸውን ሳያውቁ እንዴት አዋቂ ነን ይላሉ? የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ከሆነ የጥበብን ሀሁ፣ የጥበብን አልፋ ሳይቆጥሩ እንዴት ሊቃውንት ነን ይላሉ? ይህ ውብ ፍጥረት በማን ተበጀ? በአጋጣሚ እንዴት ሊገኝ ይችላል? ደግሞስ ክረምትና በጋውን ሌሊትና ቀኑን በትጋት የሚያፈራርቀው ማን ነው? እንኳን ፈጣሪውን ፍጥረቱን መርምረው ማወቅ ያልቻሉ እግዚአብሔርን እንዴት ይክዳሉ? እባካችሁ ተመለሱ! እናንተ ብትክዱትም እርሱ ግን አልካዳችሁምና ንስሐ ግቡ! ለእርሱ አልገዛም ብላችሁ ኃጢአትና ሱስ ደግሞም ጭካኔ ገዛችሁ:: እንደ ሰው ተፈጥራችሁ እንደ ሰው አልኖራችሁም:: ተመለሱና መልካችሁን እርሱ ያስተካክልላችሁ!

እግዚአብሔር ባለመቸኰሉ ፍጥረት ረግቷል:: እኛም ዕድላችንን መታገሥ፣ ሰዎች በኃይል ሳይሆን በፍቅር እንዲማረኩ መሻት ይኖርብናል:: የፍቅር ምርኮኛ አይደክምምና:: የፍቅር ምርኮኛ ነጻ አውጭ አይፈልግምና:: የቍጣ ምርኮኛ ግን ቍጣው ሲበርድ ይሄዳል::

አንድ ወዳጄ:- «መንግሥተ ሰማያት የእግዚአብሔርን ትዕግሥት ታሳየናለች:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ዘላለም መኖር የፈለገው እንደ እኛ ካለ ለእርሱ ከማይታዘዝና በየደቂቃው ቸል እያለ ከሚያስቸግረው ሰው ጋር ነው» ብሏል:: እኛ ብንሆን በምድር ያቆሰለንን ለዘላለም በሰማይ አብሮን እንዲኖር አንጠራውም::





በርግጥም መንግሥተ ሰማያት የትዕግሥቱ መገለጫ ናት! በእውነት ይህ ፍቅር እንዲያሸንፈን እንፍቀድ!

እግዚአብሔር በጊዜው ይሠራል:: የእኛ ሩጫ እሱን አይቀድምምና ፍላጎታችንን በኃጢአት መንገድ ለማግኘት መፈለግ የለብንም:: ምክንያቱም በኃጢአት ሰላምን ማትረፍ አይቻልም:: የእኛ አቋራጭ መንገድ የዘመናት ጦርነትና ሁከትን ይወልዳል:: የሰው የትዕግሥት መጨረሻው ለእግዚአብሔር የሥራ መጀመሪያው ነውና መበርታት ይገባናል:: በእያንዳንዱ ቀንና በሁሉም ስፍራ ስንኖር ትዕግሥት ያስፈልገናልና ታጋሽ መሆን ይገባናል:: ወደ ትዕግሥት ጥልቅ ትርጉም መድረስ ያስፈልገናል:: ለዚህም ይረዳን ዘንድ ወደ ትዕግሥት አምላክ እንጸልይ:-

አቤቱ ጌታዬ ሆይ! የመኖሬ ምሥጢር ትዕግሥትህ ነውና አመሰግንሃለሁ:: አምላኬ ሆይ ትዕግሥት በማጣት የፈጠርኳቸው ስህተቶቼ ከፊቴ ቆመው አፍጥጠውብኛል:: የገዛ ጥፋቴን መመልከት ደክሞኛልና ትዕግሥተኛ አድርገኝ:: በሁሉ ተስፋ ማድረግንም ስጠኝ:: በጉልበትና በኃይል የምኖር መስሎኝ ብዙ ከተንዝኩ በኋላ ትጥቄን አራግፌ ወደ አንተ መጥቻለሁና ጌታ ሆይ እውነተኛውን ትዕግሥት ስጠኝ:: አንተ ከእኔ ጋር፣ እኔም ከአንተ ጋር እንዳለሁ እስኪሰማኝ ድረስ አሳርፈኝ:: ጌታ ሆይ የሰው ፍቅር ኵሬ፣ ያንተ ፍቅር ምንጭ ነው:: ፍቅር ፈላጊ ነኝና ከኵሬ ስቀዳ ያለቀብኝ ልጅህን ከማያልቀው የፍቅር ምንጭህ አጠጣኝ:: በሰው ዘንድ አፍ አለኝ፣ በአንተ ፊት ግን አፍ የሌለኝ በደለኛ ነኝ፤ ምሕረት ገንዘብህ ነውና ማረኝ:: በመንግሥተ ሰማያትም ገና አብሬህ እንድኖር ጠርተኸኛልና ይህን ትዕግሥትህን ለዘላለም አመሰግናለሁ:: በአንድ ልጅህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ላንተ ይገባሃል:: ከእርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን!

✠✠✠✠✠



www.ethiopinorthodox.org